# ማርያም እና

# ተአምረ ማርያም




## የኢየሱስ እናት ማርያም እና የትውፊቷ ማርያም

ዘላለም መንግሥቱ



# ማርያም እና ተአምረ ማርያም

የኢየሱስ እናት ማርያም እና የትውፊቷ ማርያም

ከዘላለም መንግሥቱ

# ማርያም እና ተአምረ ማርያም

የኢየሱስ እናት ማርያም እና የትውፊቷ ማርያም

ዘላለም መንግሥቱ (መጀመሪያ በሦስት መጣጥፎች © 2012 ፪ሺህ፬ ዓመተ ምሕረት፤ ዳግመኛ © 2022 ፪ሺህ፲፬ ዓመተ ምሕረ።)

ይህን መጽሐፍ ባለቤትነቱን ሳይወስዱና ለሽያጭ ሳያውሉ ጸሐፊውን በማሳወቅ ማባዛትም ማሰራጨትም ይፈቀዳል።

በተለይ ካልተጠቀሰ በቀር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. (1962) የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

* * * * *

# Mary and *The Miracle of Mary*

Mary the Mother of Jesus and the Book *Te'amre Maryam (The Miracle of Mary)*

Zelalem Mengistu (© 2012 and 2022)

This work can be reproduced and disseminated by only notifying the author, without claiming ownership, and so long as it is not for profit.

All Scripture quotations are from the 1962 edition of the Amharic Bible published by the Bible Society of Ethiopia.

የሽፋን ዲዛይን፥ ዘመን ግራፊክስ።

መድረከ ዕዝራ
ለጌታ ቃል እና ለቃሉ ጌታ ታማኝ በመሆን
ezra forum
being true to the Word of God and the God of the Word

ይህች መጽሐፍ

ተጨማሪ ድጋፍ የማይሻውን የቃሉን ብቻ እውነት ለማካፈል ለሚተጉ ሁሉ

የተበረከተች ናት።

ማውጫ

መግቢያ - ገጽ 5

## ማርያም

እውን ጅሐድ ታወጀ? - ገጽ 10
ነገረ ማርያም በመደዴው ምእመን ዘንድ - ገጽ 13
ማርያም እግዝእት ናትን? - ገጽ 23
ወላዲተ አምላክስ ናት? ወላዲተ አምላክ ምን ማለት ነው? - ገጽ 26
ቤዛዊተ ኵሉስ ናት? - ገጽ 28
እመ ብርሃንስ ናት? - ገጽ 29
እውን ማርያም ዐርጋለች? - ገጽ 30
ቃሉን የአለማወቅና እንዳይታወቅ የማድረግ ጉዳት - ገጽ 31
የማርያም እይታ በተርታው ምእመን ዘንድ - ገጽ 40
ማርያም ታማልዳለችን? - ገጽ 42
ለዘላለም ድንግል ናትን? የኢየሱስ ወንድሞች ጉዳይስ? - ገጽ 47
ማርያም ስለ ራሷ የሰጠችው ምስክርነትስ? - ገጽ 64

## ተአምረ ማርያም

ተአምረ ማርያም ምንድር ነው? አሳታሚና ባለቤቱስ? - ገጽ 67
የመጽሐፉ ምንጭ ወይም ደራሲ ማን ነው? - ገጽ 69
የጸሐፊው ወይም ጸሓፊዎቹ ባህርያት - ገጽ 71
የመጽሐፉ ባህርያት / ይዘት - ገጽ 79
መደምደሚያ - ገጽ 106
ዋቢ መጻሕፍት - ገጽ 107

# መግቢያ

ይህ ጽሑፍ በሦስት ክፍሎች ተሰናድቶ በመጀመሪያ የተሰራጨው በኛ አቆጣጠር በ2004 ዓመተ ምሕረት ነው። መነሻ የሆነው ከመጋቢ ዳዊት ሞላልኝ ስብከት ላይ ተቀነጫጭበው ለተወሰዱ አሳቦች የተሰጠ ምላሽን ተከትሎ፥ 'ፕሮቴስታንታዊ ጅሐድ' ተሰኝቶ የተዘጋጀውና የተሠራጨው ቪድዮ ነው።

ከዚያ በኋላ በነገረ ማርያም ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች እየተነሡ የመለስኩባቸው ጊዜያት አያሌ ናቸው። ብዙዎቹን ወደዚህ ጽሑፍ ልጣፍ በማመልከት እንዲያነብቡ አመላክቻለሁ። እዚህ ግን ጠቅላላውን አሳብ በአንድ መጽሐፍ መልክ የማቀርበው መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ነገረ ማርያም እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኘውንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጻረረውን ተአምረ ማርያም የተባለ መጽሐፍም አያይዘን እንድናየው ነው።

ስለ ማርያም የተጻፉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ ብዙ ሃይማኖታውያን መጻሕፍት፥ ገድላት፥ መልካት፥ ድርሳናት ይገኛሉ። በአገራችን በብዛት የተደረሱት በ15ኛው መቶና ከዚያ በኋላ ባሉት ዘመናት ነው። እንደ ፋና ወጊ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መጻፍ ብቻ ሳይሆን በግዴታ ለማርያምና ለመስቀል፥ ለስዕልም እንዲሰገድ በአዋጅ አስደንግጎ ነበር። ይህን ያልተቀበሉ በክፉ ቅጣት እየተቀጡ የመቀጣጫም፥ የጽናትም ምሳሌ ሆነው አልፈዋል።

ነገረ ማርያም በአገራችን ትናንትም ዛሬም ጉልህ ስፍራ የያዘ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ቃሉ ምን ይላል ብሎ መመርመር የክርስቲያኖች ተቀዳሚ ኃላፊነት ነው። እኛ ወንጌላውያን አማኞች ቃሉ ያላለውን ስለማንሰብክና ያለውንም ስለማናስቀር፥ ስለ ኢየሱስ እናት ማርያም ተጨማሪ፥ ተደማሪና ተደራቢ ነገሮችን ስለማንል ከእውነቱ ያስቀረን መስሎ በአንዳንዶች ይታሰባል። ያ ግን ስሕተት ነው። ቃሉ ምን ይላል? ቃሉ ስለ ኢየሱስ እናት ስለ ማርያም ምን ይላል? ያለውን አናስቀርም፤ ያላለውም አንጨምርም። ቃሉ ስለ ኢየሱስ እናት ስለ ማርያም ያላለውን አስገድደን ስለ እርሷ እንደተናገረ አድርገን አናስጮኸውም፤ በስሕተት አንፈታውም፤ አንተረጉመውም። በዐውዱ በማጥናት እውን ይህ ስለ እርሷ የተነገረ ነው? ወይስ ስለሌላ ብለን እንመረምራለን።

ወንጌላውያን አማኞች ማርያምን እንደሚያጣጥሉ የሰበኩ አንድ ቄስ፥ "እነዚህ መጤ የፈረንጅ ሃይማኖት ሰባኪዎች እናቱን ጥለው ልጁን ይሰብካሉ። ይህ ማለት ከታሸገ የምግብ ቆርቆሮ ውስጥ ምግቡን በልቶ ቆርቆሮውን ወዲያ መጣል ነው እኮ!" እንዳሉ አንድ የሰማቸው ጓደኛዬ አጫውቶኝ ነበር። የቄሱ ምሳሌ በመጀመሪያ ደካማ ብቻ

ሳይሆን ትክክለኛ ያልሆነ ምሳሌ ነው። የመለኮትና ሰብነት ግንኙነት ከቆርቆሮና ሥጋ የሚነጻጸር አይደለም። ማርያምና ኢየሱስ ቆርቆሮና ሥጋ አይደሉም። ሁለተኛም፥ እንዲያው ሆኑ ቢባልስ፥ ከቆርቆሮው ሥጋውን የበላ ሰው ቆርቆሮውንም መቆርጠም አለበት የሚባል ግዳጅ ውስጥ ቢገባ ስሕተት አይሆንም? ወይም ሥጋውን የበላሁበት ቆርቆሮ ነውና ብሎ ለቆርቆሮው ማማ ሠርቶ ሊያጥንለት ወይም ሊሰግድለት ተገቢው ነው? አይደለም። እዚህ ላይ ነው ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን።

የዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ከላይ የጠቀስኩት የሁለት ሰዎች ስብከትና ምላሽ ቢሆንም፥ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የኢየሱስ እናት ማርያም በቃሉ ውስጥ የተጠቀሰችባቸውን ቦታዎች በዐውዳቸው እናያቸዋለን። በቃሉ ውስጥ የማይገኙ ነገሮች የተጻፉባቸው ትውፊታውያን መጻሕፍት ብዙ ናቸው፤ ሁሉንም ለመመልከት ጊዜና ጉልበት ይጠይቃል። አንዱንና በተለይ በአገራችን በስፋት የሚታወቀውን፥ ተአምረ ማርያም የተባለውን በተለይ እንመለከታለን። ሦስቱ መጣጥፎች በመጀመሪያ ከተጻፈው ይዘታቸው ሳይለወጥ እንደገና ሳነብባቸው በመጠኑ የጨመርኳቸውና የለወጥኳቸው ቃላት አሉባቸው።

መልካም ንባብ።

ዘላለም መንግሥቱ © (፳፻፲፬ ዓመተ ምሕረት - 2022)



ክፍል አንድ

# መንደርደሪያ

ማርያም እግዝእት ናትን? ያለ ኃጢአት ተጸንሳለች? ማርያም ልጆች ነበሩአት ወይስ አልነበሩአትም? ወላዲተ አምላክ ምን ማለት ነው? ማርያም ታማልዳለችን? ቃሉ የሚለው መነገር የለበትም? መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው የወጣ ነገር እንዴት መነገርና መሰበክ አለበት? የሕዝቅኤል የተዘጋው በር ማርያም ናትን? የያዕቆብ መሰላልና ሐመረ ኖኅ ማርያም ናትን? ቤዛዊተ ኩሉ ዓለምስ ናትን? በእውን ቤዛ ናት? ወደ ሰማያት ዐርጋለች? ወደ ሰማየ ሰማያት ፈልሳለች?

ተአምረ ማርያም ምንድር ነው? መቼ ተጻፈ? ማን ጻፈው? ከየት ተገኘ? መቼ ተተረጎመ? ተአምረ ማርያም ምንድር ነው? ማን ጻፈው? የት ተጻፈ? መቼ ተጻፈ? ለምን ተጻፈ? የደራሲዎቹ ማንነት በውል ይታወቃል? ወደ ግዕዝ መቼና በማን ተተረጎመ? ውጪያዊ ምስክሮች አሉት? ውስጣዊ ማስረጃዎችስ ምን ያመለክታሉ? እርግጥ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞአል ወይስ ቀድሞውኑ የተደረሰው በግዕዝ ነው? ይህ መጽሐፍ እርስ በርሱ ይጋጫል? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርስ ከቶውኑ ይስማማል? ካልተስማማ እንደምን ሊያደርጉት ይገባል? ለመሆኑ ክርስቲያኖች ሥልጣን ያለው ቃል አላቸውን? ሌሎች መጻሕፍትንም ሆነ ትምህርቶችን መለካትና መፈተሽ ያለባቸው እንዴት ነው? ከዚህ ሥልጣን ካለው ቃል ጋር የሚጋጩ መጽሐፎች ምን ማድረግ ይገባቸዋል?



እነዚህ ከላይ የተጻፉት ጥያቄዎች በዚህ ሥራ ውስጥ ከሚፈተሹት መካከል ጥቂቱ ናቸው። ለዚህ ጽሑፍ መነሻው አንዲት ትንሽ የዩቲዩብ ቪዲዮ ቁራጭ እንድመለከት ተልካልኝ ያየሁት ነው። መጋቢ ዳዊት ሞላልኝ በአንድ ሁለት ስብከቶች ላይ ከሰበካቸው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነክ ቃላት ላይ የተሰጠ ምላሽ ነበረ። ግን እንዳልኩት ስብከቱም ምላሹም ቁራጭ ብቻ ነበረ።

ቀጥሎም ሌላ ወንድም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመ/ር ምህረተአብ አሰፋ አማካይነት ተዘጋጅቶና ተቀናብሮ የተሰራጨ ምላሽ ላከልኝ። በዚህኛው ምላሹ ሙሉና የተቀነባበረ ሲሆን የመጋቢ ዳዊት ስብከት አሁንም ምላሽ ሊሰጥበት ተፈልጎ የተወሰደው ቅንጣቢ ብቻ ነው። ይህን የምጽፈው በምላሹ ቪድዮ ላይ ጥቂት መጻፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼ ነው።

ይህ ጽሑፍ የተጻፈው በመላው የቪድዮ ምላሹ ሳይሆን በሁለት ነጥቦች ላይ ብቻ ይሆናል። አንደኛው ርእሱ ነው። ርእሱ፥ ‘ፕሮቴስታንታዊ ጅሐድ’ ተሰኝቶአል። ሙሉውን የዚህ መጣጥፍ መነሻ የሆነውን የመ/ር ምህረተአብን የዲቪዲ ስርጭት ለማየት ምንጩ http://www.youtube.com/watch?v=Y47C_SCkjIA ነው።[1]

አንደኛው ነጥብ ርእሱ ሲሆን ሁለተኛው ይኸው ሰባኪ በተለይ አንዱና ዋናው ነጥቡ ስለሆነው ስለ ማርያም በሰፊው ከሰበከው ከ2ኛው ዲቪዲ የተወሰደ አሳብ ላይ ሆኖ ስብከቱን ከስነ አፈታት አንጻር መመልከት ነው። በተመሳሳይ ርእስ የተዘጋጀው ሁለተኛ ዲቪዲም መ/ር ምህረተአብ በነገረ ማርያም ላይ የሰበከው ሲሆን በመረጃው መረብ በhttp://www.youtube.com/watch?v=GPBzIS5Le_A&feature=related ይገኛል።[2]

የቪድዮ መልእክቱን ከተመለከትኩ በኋላ መልእክቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ለማየትና ለመገምገም ፈለግሁ። አዚህ ላደርግ የሞከርኩት ይህን ነው። ግን በዚህ ላበቃ አልፈልግም በኦርቶዶክሳዊ ነገረ ማርያም (Mariology) ዋነኛ አገራዊ ምንጭ ተደርጎ የሚታየው ተአምረ ማርያምን በተመለከተም ጥቂት መባል ያለበት መስሎ ተሰምቶኛልና በመጨረሻው ይህንን መጽሐፍም እዳስሳለሁ። አሁን አሁን ነገረ ማርያሙ ወደ አምልኮተ ማርያም (Mariolatry) የተለወጠ ሆኖአል። ይህንን ከሊቃውንቱ ይልቅ ከመካከለኛው ወይም መደዴው ምዕመን ጋር ስለ ማርያም

[1] ይህን ጽሑፍ በመጽሐፍ መልክ እንደገና ሳሰናዳ ቪድዮው ከምንጩ ላይ የለም፤ ተወግዶአል።
[2] ይህም ቪድዮ አሁን በስፍራው የለም። ቪድዮዎቹ የሚነሡትና የሚወገዱት ችግር ስላለባቸው ነው።

በመነጋገር መረዳት ይቻላል። ተርታው ምእመን የሚናገረው መረዳቱ የአማካዩ አስተምህሮ ይዘት አመልካች ተደርጎ መወሰድ ይችላል።

## ከውን ጅሃድ ታወጀ?

ርእሱ፥ *ፕሮቴስታንታዊ ጅሃድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ሲፋፋም* የተባለ በተመሳሳይ ርእስ ሌላ መጽሐፍም ተጽፎ ተሰራጭቶአል።[3] በርእሱ ላይ እንግሊዝኛውም (ፕሮቴስታንታዊ) ዐረብኛውም (ጅሃድ) አልቀረም። ጅሃድ የሚለው ቃልም በግርድፉ ተተርጉሞ የከተት ሠራዊት ዘመቻ ተደርጎም ቀርቦአል። የመጽሐፉ ርእስ እንደ መ/ር ምህረተአብ ለአንድ የወንጌላዊ እምነት ሰባኪ የተሰጠ ምላሽ ሳይሆን በጠቅላላው በወንጌላውያን አማኞች አመለካከት ላይ የቀረበ ርችት ነው። ስሕተቱ እዚህ ላይ ነው።

የንግግርና የጽሑፍ ወይም የኅሊና ነፃነት በሚፈቀድበት ኅብረተ ሰብ ወይም መንግሥት ውስጥ ማንም ሰው ምንም ቢናገር በቤተ ክርስቲያን ወይም በአንድ ሃይማኖት ላይ ጅሃድ ታወጀ ማለት ስሕተትም፥ ሐሰትም፥ ነውርም፥ ወንጀልም፥ ኃጢአትም ነው። መጋቢ ዳዊት ሞላልኝ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍ ቅዱስን ቢያስተምር ተልእኮው፥ ጥሪው፥ ኃላፊነቱ ነው። የካ ሚካኤል ወይም ዲማ ጊዮርጊስ ቅጽር ውስጥ አንድ ዲያቆን ወይም ቄስ ወይም ባህታዊ፥ 'እነዚህ ብሮቴስታንትዎች የጌታን እናት ትተው ልጇን ይሰብካሉና የእግዝእትነ ጠላቶች ናቸው፤ የእርሷ ጠላቶች የኛ ጠላቶች ናቸው' ብሎ ሰበከ እንበልና፥ ይህን ስላለ ኦርቶዶክሳዊ ጅሃድ ታወጀብን ብንል አልተሳሳትንም? ተሳስተናል። ነጠላ ስም ጠርተን 'ዲያቆን እገሌ፥ ወይም መምህር እገሌ በስብከቱ በዚህ ርእስ ላይ እንዲህና እንዲህ አለ፤ ይህ አባባል ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር ሲፈተሽ . . .' ከማለት ያለፈ ውርጅብኝ የተገባ አይደለም።

የመጋቢ ዳዊትን ስብከት በመጀመሪያው መጣጥፍ ጽሑፍ ዝግጅት ወቅት አላየሁትም ነበር። በኋላ ግን አግኝቼ በሙሉው አደመጥኩት። ስብከቱ በዘዳ. 30፥11 ላይ የተመሰረተ ሆኖ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለሚፈልጓት ከባድ ያለመሆኗን በማውሳት በጣም ግልጽ የሆነውን ወንጌል ሌሎች አደፍራሽ ነገሮች የሸፈኑትና የጋረዱት መሆኑን ነው በስብከቱ የገለጠው። አንዱ መጋረጃና መሸፈኛ ደግሞ በዚህ የተወሳው የነገረ ማርያም ጉዳይ ነው። ለአንድ የወንጌል አማኝ ሰባኪ ደግሞ ይህን መስበክ ኃላፊነቱ ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ነው። ኢየሱስን ማሳየት ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ እንዳይታይ

[3] በእሱባለው በለጠ የተጻፈው *የገሃነም ደጆች ፕሮቴስታንታዊ ጅሀድ በኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶነት ላይ ሲፋፋም* የሚል መጽሐፍም በርእስ ተጋሪ መጽሐፍ ነው።

የሚጋርዱ መጋረጃዎችንም ማሳወቅ ኃላፊነቱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እንቀበላለን የሚሉ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጭ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ትምህርት ከሆነው ከክርስቶስ ወደ ሌላ የሚያመለክቱ ከሆኑ ለመተቸት እና ለማስተማር የሚገባውን ያህል አርጎአል።

ማንም ሰባኪ የራሱ ስልት እንዳለው መጋቢ ዳዊትም የራሱ ቁመናና መልክ፥ የማስተማር ስልት እና አቀራረብ አለው። አቀራረቡ ምናልባት አወዛጋቢ ሊሆን ይችላል። ወይም ግልጽ ሆኖ በወንጌላት የተጻፈውን ሆን ብለው ስውር ለሚያደርጉ ወይም ቀላልና ሊረዱት የሚቻል ሆኖ በቃሉ የተጻፈውን ውስብስብና ከባድ የሚያደርጉ ሰዎችን የሚያናድድና የሚያበሳጭ ወይም ተገዳዳሪ ሊሆን ይችላል። ይህ የቅርጽ እንጂ የይዘት ጉዳይ አይደለም። ይዘቱ ትምህርቱ እውነት ነው ወይስ አይደለም? ነው።

ከተወሰዱት ቁራጮች (ክሊፖች) የተረዳሁት ሌላ ነገር ደግሞ አንድ ሰዓት ሙሉ ከተሰበከው ስብከት ያን የሚያህል በሁለት ዲቪዲ የተቀናበረ ምላሽ የተሰጠበት ክፍል የተወሰደው ተጠራቅሞና ተደምሮ ከ3 ደቂቃ የማይበልጥ ብቻ መሆኑ ነው። ከአንድ ሰዓት ስብከት 3 ደቂቃ ማለት 4% ያህል ብቻ ማለት ነው። ያም አላዋቂዎችንና ጠቅላላውን ስብከት ያልሰሙትን በቁጣና በጥላቻ እንዲያስነሣ ሆኖ መቀናበሩን ነው። ጅሃድ የተሰኘበት ምክንያትም ይህ ይሆናል። ዳራው ያልተገለጠ የጥቂት ሰከንዶች ቃል ቀንጭቦ ማቅረብ በስነ ጽሑፍ ባህል ከወንጀል የማይተናነስ ተላላፊነት ነው። እነዚያን ቁራጮች የሰሙት ጠቅላላውን ለመስማት መፈለጋቸው መቼም የማይቀር ነውና ያንን ያደረጉ ቀን ወይም የልቡና ዐይናቸው የተገለጠ ቀን ቢያንስ እነ መ/ር ምሕረተአብን እና የዲቪዲውን አዘጋጅና አሳታሚዎች መታዘባቸው አይቀርም።

ከዚሁ ዲቪዲ ቅንጣቢውን ብቻ ነውና ብዙም መተቸት አልችልም። በቀጣዩ ጽሑፍ ፈልጌ ካየሁ በኋላ የምናገረው ይኖረኛል። ካየሁት ቅንጣቢ በመነሣት ግን የመጋቢ ዳዊት አቀራረቡ የራሱ ስልት ቢሆንም ስለተነሱት ነጥቦች የነጠሩ የቃሉን ጥቅሶች በግልጥ፥ በተሻለና በጨዋ ቋንቋ፥ ማስረጃዎችን በግልጽና ምንጮችን በመጥቀስ ማቅረብ ይችል ነበር እላለሁ። በሙሉው ስላላየሁት፥ 'አላቀረበም ወይም በደፈናው ሳያቀርብ ቀረ' ማለትም አልችልም። ይሁን እንጂ የስሕተቶች አስረጂያችን አባባል፥ ወይም የስሕተቶች ማረጋገጫችንና መልስ መቅጃችን የኢንተርኔት ካፌ፥ ወይም እውቅ ሰባኪ፥ ወይም ሌላ መሆን የለበትም።

በመ/ር ምህረተአብ የተወሰደው የቪድዮው ክፍል ግን ቅንጣቢ ብቻ ሆኖ ለማናደድና በጥላቻ ለማነሣሳት እየተቆረጠ የተለጠፈ ነው። እንደተነገረው በሕግ ዳኝነት ፊት መቆም አንድ ነገር ነው፤ ግን ሰፊውን አርቶዶክሳዊ ምእመናን፥ 'ጅሃድ ታወጀባችሁ'

በማለት ለምላሽ ማነሣሳት የራቀ ግብ ያለው ይመስላል። ይህን ያልኩት ምላሹ የታቀደው መልስ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ስነ ልቡናዊ የጥላቻና የብቀላ ቅስቀሳ ለመጫር ስለሚመስል ነው።[4]

ነባራዊውን እውነት መናገርና ከቃሉ አንጻር ስሕተትን መግለጥ ግን ወንጀልና የጦርነት ክተት አዋጅ ወይም የዲቪዲ ዝግጅቱ እንዳለው ጅሐድ አይደለም። ሙስሊሞች ነቢያችን ተዋረደ፥ መልኩ በወረቀት ላይ ተሳለ፥ መጽሐፋችን ላይ ተጻፈበት፥ ስለ ዒሳ (በእነርሱ መረዳት ኢየሱስ) አዳኝነት በጆሮአችን ተነገረን፥ ወዘተ፥ ብለው የክርስቲያኖችን አፍ ለመዝጋት ብቻ ሳይሆን ነፍስ ለማጥፋት በየቦታው እንዳደረጉት ያለ ዘመቻ ማወጅና ማዝመት ውጤቱ ክፉ ነው። ጅሃድ ከዚህ የለሰለሰ ትርጉም ሊሰጠው ቢሞከርም እንደምናውቀውና እንደምናየው ለሃይማኖት ቀንቶ ሥጋን መግደል ነው። የፍጻሜው ትርጉሙ ይኸው ነው። በእውነቱ የትኛውም ሃይማኖት በታሪክ ውስጥም ሆነ በዘመናችን ነፍስን በማጥፋትና በማስጠፋት የሚደሰትና የሚኮራ ከሆነ፥ የሚያደፋፍርና የሚያበረታታም ከሆነ ያ ሃይማኖት ሃይማኖት ሳይሆን ፖለቲካ ነው። ያውም ጥሬና ያልበሰለ፥ አስቀያሚና ገዳይ ፖለቲካ ነው።

አንድ ወንጌላዊ ሰባኪ ያመነበትን ነገር መስበኩን ጅሃድ ካሉት በወንጌላውያን አማኞች ላይ የደረሱትን አካላዊና ቁሳዊውንም የጨመረ ስነ ልቡናዊና መንፈሳዊ ስደትን፥ አካላዊ ጉዳትንና የንብረት ውድመትን ምን ብለው ሊጠሩት ነው? በጨዋነት መነጋገርና መከራከር ብቻ ሳይሆን በጨዋነት መነታረክም እንኳ እኮ ይቻላል። መ/ር ምህረተአብ የዳዊትን ስብከት ጅሐድ ብሎ ከሰየመው በቀጣዩ ጅሃድ ብሎ በሰየመው ነገር ላይ የጅሐድ ምላሽ ጦር ቢያስከትትስ? አስከትቶም ሰባኪውን ወይም ማኅበረ ምእመናኑን ወይም ሰፊውን ወንጌላውያን አማኞች ለማሳደድ ቢጋበዝስ? የስብከቱ ቅላጼ ለዚያ የሚያነሣሳ ምታ ነጋሪትና ቀረርቶም ይመስላል። ቅንብሩና አሰያየሙ ይህን ለማድረግ የማይመለስ ወይም ወደዚያ አቅጣጫ የሚያዘግም ያስመስለዋል። ቃል ተነግሮብናል፤ ስብከት ተሰብኮብናል እና ሰይፍ መዝዘን እንነሣ ማለቱ ነው? በዲቪዲው መግቢያ የተጠቀሰው ቁጣ መቀስቀስና ሕዝብ ማነሣሳት አዝማሚያው ምንድርነው? የቪዲዮ ዝግጅቱ እንደተናገረው ከላይም እንደጠቀስኩት ጉዳዩን ወደ ሕግ አቅርቦ፥ 'እንዲህ ሰበከ' ብሎ መክሰስ ወይም መጠየቅ አንድ ነገር ነው። ሕግ እስካስኬደው ድረስ መሄድ ይችላል። ጅሃድ አወጀብን ብሎ መክሰስ ግን ይቻል ይሆን? ስለ እርሱና ስለ ርእሱ ስሕተት ይህን ካልኩ ላብቃና ወደ አንዱ የመ/ር ምህረተአብ ስብከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ላምራ።

---

[4] መ/ር ምህረተአብ ይህ አስተሳሰቡ የኖረበትና ያልተላቀቀው አባዜ ነው። ያንን ከሰበከና ቀርጾ ካሰራጨ ከ10 ዓመታት በኋላም፥ ይህን ጽሑፍ እንደገና ለማቅረብ በማሰናዳበት ጊዜም አንድ፥ ወንጌላዊ እምነትን የወከለ የመሰለው ሰው ስለ መስቀል አደባባይ የተናገረውን ቃል በቃል በመውሰድ ሰዎችን ለጦርነት እስከ ማነሣሳት ደርሶ ነበረ።

## ነገረ - ማርያም በመደደው ምክመን ዘንድ

ሁለተኛው ነጥብ በዚሁ የመጋቢ ዳዊትን ስብከት ጅሃድ ባሰኘው ሰባኪ በመ/ር ምህረተአብ የተሰበከው ክፍል ስለ ጌታችን እናት ስለ ማርያም የተነገረው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መደገፊያ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎና ተጠናቅቆ ካበቃ ከመቶና ከሺህ ዓመታት በኋላ የተደረሱና የፈሉ መልክአ እገሌ፥ ድርሳነ እገሌ፥ ተአምረ እገሌ፥ ውዳሴ እገሌ ወዘተ፥ የተባሉ ድርሰቶች መሆንም የለባቸውም። ለነገሩ መጽሐፍ ቅዱስን በድርሳኖች ለመደገፍ መሞከር ምሰሶን በሰንበሌጥ እንደመደገፍ ነው። መለኮታዊ ምንጭነት ያለውና በክርስትና ትምህርትና አኗኗር ላይ ከምንም ሕግ በላይ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በመሆኑ መተኮር ያለበት ይህ ቃል ነው። በዚህ መጣጥፍም የምሞግተው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማርያም ይህን ይላል ወይስ አይልም? ደግሞም የሚለው ምንድር ነው? በማለት ነው።

የአማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ከቁጥር የሚገባ አይደለም። ደግሞም ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የሚያውቀው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ቢጋጭም ቢጣላም ከዚያ ውጪ ያለውን ነው። ልጅ ሳለሁ ስለ ማርያም የማውቀው ነገር መልእክተን ካስተማሩኝ የኔታ፥ የክርስትና አባቴ ከሆኑት መሪጌታ፥ እንዲሁም ከእናቴ የሰማሁት ነው። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሚበረታታ ልማድ አይደለም። በኔ የልጅነት ዕድሜ ጨርሶውኑም በአማርኛ ሲሰበክ ሰምቼ አላውቅም። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ስጀምር ስለ ማርያም እሰማ የነበረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ ብቻ ሳይሆን ፈጽሞ የሚጣላና የሚጋጭ ነገር ሆኖ አገኘሁት። እንግዲህ ይህ የአማካዩ ምእመን ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎቹና ሊቃውንቱም ትምህርት ሆኖ ሲገኝ ግጭቱን እንዴት ሊያስታርቁ እንደሚሞክሩ ማየት ራሱ ትንግርት ነው። ባለ ሥልጣኑ መጽሐፍ ተለይቶ አልተቀመጠም፤ ወይም ሁሉም መጽሐፍ እኩል ሥልጣን እንዳለው ሆኖ ስለቀረበ ቃሉና ትውፊቱ መታረቅ አይችሉም።

ይህን ጽሑፍ በመጀመሪያ በጻፍኩበት ዓመት የፈረንጆች ገና ዕለት በአንድ ቤት ለራት ታድመን ነበር። ከእራት በፊት ቃል እንዳካፍል ተጠይቄ ነበርና ገላ. 4፥4ን አካፈልኩ። ቃሉ፥ *ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤* የሚል ነው። ከእራት በኋላ በጭውውት ጊዜ አንድ ሰው፥ “ቅድም ያካፈልከው ቃል ጥሩ ነው፣ ግን ለምን ሴት አልካት” አለኝ። ማርያምን ማለቱ ነው። “ወንድ ስላልሆነች ነዋ!” ብዬ ልመልስ ቃጥቶኝ ነበር። አሳቡ ገብቶኛል። ሊጠይቅ የፈለገው፥ ‘ለምን እመቤታችን ቅድስት

ድንግል ማርያም አላልከም? ሴት ስትል እኮ እርሷን ማዋረድህ ነው፤ ማቃለልህ ነው' ለማለት ነው። ከሌላ ወንድም ጋር ተረዳድተን ቃሉ ሴት እንደሚልና ሊል የፈለገበትን ዓላማም አስረዳን። ሰውየው አሁንም፥ 'ቃሉ እንደዚያ አይልም።' ብሎ ተከራከረ። እንደሚል ስንነግረው፥ 'ቃሉ እንደዚያ ካለ ቃሉ ራሱ ተሳስቷል፤ ተርጓሚዎች አሳስተው ጽፈውት ነው።' አለን። አሁንም አለመሆኑን አስረዳነው።

እርሱ ራሱ አነበዋለሁ ባለው የግዕዝ አዲስ ኪዳንም ሆነ በሌሎች ትርጉሞችና ቋንቋዎችም ቃሉ ያው መሆኑን ነገርነው። ይህን አስረድተን እንዲያውም ጌታ ኢየሱስ ራሱ አገልግሎቱን በጀመረና ውኃውን ወደ ወይን በለወጠ ጊዜ፥ እንዲሁም ሁሉን ጨርሶ በመስቀል ላይ ሳለ እናቱን ማርያምን፥ "አንቺ ሴት . . ." እንዳላት (ከዮሐ. 2 እና 19 በመጥቀስ) ነገርኩት። ይህ ደግሞ ማሳነስ ወይም ማቃለል ሳይሆን የተለመደ አባባልም፥ የግንኙነትን ድንበር የሚገድብም አገላለጽም ነው አልኩት። ይህንን ስል፥ "ኢየሱስ ይህንን ብሎ ከሆነ [ማርያምን አንቺ ሴት ብሎ ከሆነ] እርሱ ራሱም፥ ልክ አይደለም፥ እናቱን እንዴት፥ 'አንቺ ሴት' ይላል? ይህን ብሎ ከሆነ እርሱም ተሳስቷል" አለን። ለማርያም የሚሰጠው የተሳሳተ ምልከታ ቅዱስ ቃሉን እና ሥጋ የሆነውን ቃል፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ራሱንም እንኳ ተሳስቶአል ከማለት የማያግድ ነው። ይህ ይገርማል! ያሳዝናልም! ይህ የአማካዩ ምእመን አምነትና እውቀት ነው።

ይህ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ከቶም አንብቦ አያውቅምና ኢየሱስ ያለውንና ያላለውን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን ራሱን የሚያውቀውም በስማ በለው ነው። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ያለምንም መጠራጠር መቀበል ይገባዋል። ሌሎች መጻሕፍትንና ድርሰቶችን ከሚያነብበው በላይም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይጠበቅበታል። መጻሕፍትን ወይም ድርሳናትን፥ ገድላትን ወይም መልካ መልኮችን ከተጻፉባቸው ታሪካዊ መቸት አንጻር ማየትና መተቸትም መበረታታት አለበት። መጽሐፉ እውነት ከሆነ ፍተሻው ይበልጥ ይገልጠዋል፤ ውሸትም ከሆነ በዚያው ልክ ይገልጠዋል። ውሸት ካልሆነ በቀር ትችትን ወይም ሕያሴን የሚፈራ መጽሐፍ የለም።

በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ማርያም የተሰጣት ስፍራ ለመረዳት የሚከብድ መለኮታዊ ወይም የመለኮት አከል ሥልጣን ነው። ልክ በስዕሎቻቸው ሁሉ ትንሽ ኢየሱስና ትልቅ ማርያም እንደምትታየው ሁሉ ለማርያምና ለኢየሱስ የሚሰጡት ስፍራም በዚያ ልክ የተመጠነ ይመስላል። በአማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ምናብ ውስጥ የተሳለው ኢየሱስ እናቱ ማርያም የምትጠይቀውን ወይም የምትነግረውን ሁሉ ተቻኩሎ የሚፈጽም፥ አንዱንም እንቢ የማይል ታዛዥ ልጅ ምስል ነው። በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት የኖርን ሁሉ ይህን እናውቃለን። ለአንዳንዶች ልክ እንደ ስዕሉ ሁሉ፥ ኢየሱስ አሁንም ምሪትና ድጋፍ፥ ጥበቃና ክብካቤ የሚያሻው ሕጻን ይመስላቸዋል።

ወንጌላውያን አማኞች ማርያምን እንደሚያጣጥሉ የሰበኩ አንድ ቄስ፥ “እነዚህ መጤ የፈረንጅ ሃይማኖት ሰባኪዎች እናቱን ጥለው ልጁን ይሰብካሉ። ይህ ማለት ከታሸገ የምግብ ቆርቆሮ ውስጥ ምግቡን በልቶ ቆርቆሮውን ወዲያ መጣል ነው እኮ!” እንዳሉ አንድ የሰማቸው ጓደኛዬ አጫውቶኝ ነበር። የቄሱ ምሳሌ በመጀመሪያ ደካማ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ያልሆነ ምሳሌ ነው። የመለኮትና ሰብነት ግንኙነት ከቆርቆሮና ሥጋ የሚነጻጸር አይደለም። ማርያምና ኢየሱስ ቆርቆሮና ሥጋ አይደሉም። ሁለተኛም፥ እንዲያው ሆኑ ቢባልስ፥ ከቆርቆሮው ሥጋውን የበላ ሰው ቆርቆሮውንም መቆርጠም አለበት የሚባል ግዳጅ ውስጥ ቢገባ ስሕተት አይሆንም? ወይም ሥጋውን የበላሁበት ቆርቆሮ ነውና ብሎ ለቆርቆሮው ማማ ሠርቶ ሊያጥንለት ወይም ሊሰግድለት ተገቢው ነው? አይደለም። እዚህ ላይ ነው ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን።

ስለ ኢየሱስ እናት ማርያም ከኦርቶዶክሶች ጋር መነጋገር የሚያጣላ ተደርጎ ስለሚገመትና ስለሚነገር ብዙዎች አያነሱትም። ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን የሚቀበሉ ሁሉ የተጻፈውን ቃሉን በአክብሮት ሊቀበሉ ግድ ነውና የሚያጣላ ወይም የሚያስቀይም ወይም ሌላ ተብሎ ዝም አይባልም። ቃሉ የሚናገረውን በአክብሮት እንቀበላለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፈውን እንደተጻፈ ያህል ተደርጎና ተቆጥሮ ሰዎች ያለ ጥያቄ እንዲቀበሉት ወይም የተጻፈውን እንዳልተጻፈ ሁሉ እንዲዘልሉት ወይም በዐውደ ወጥ አፈታት እየተፈታ ያላለውን እንዲል እንዲደረግ የተገባ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ በተናገረባቸው ቦታዎችና ጉዳዮች ሁሉ የተናገረውን እንደምናከብር ሁሉ ዝም ባለባቸው ቦታዎችና ጉዳዮችም ዝምታውን ማክበር አለብን እንጂ ያንን ዝምታ በራሳችንና ሰዎች በፈጠሩት ምናባዊ ትረካ መሙላት የለብንም። ቃሉ የማይናገረውንና ምንም ያላለበትን ወይም ዝም ያለበትን ዝምታውንም እናከብራለን እንጂ በራሳችን ምናባዊ አመለካከት ክፍተት የመሰለንን ቦታ ሁሉ አንጠቀትቅም። ለምሳሌ፥ ወንጌላት በአራት የተለያዩ ሰዎች የተጻፉ የጌታ ታሪኮች ናቸው። ከአራቱም ውስጥ በሁለቱ ወይም በሦስቱ ወይም በአራቱም ውስጥ የተደጋገሙ ጉልህ ታሪኮች አሉ። አንዳንዶቹ ታሪኮች ደግሞ በአንዱ ብቻ የተጻፉ ናቸው። ሆኖም ተጽፈዋል። ጨርሶውኑ ያልተጻፉም ታሪኮችም አሉ። ጌታ በአሥራ ሁለት ዓመቱ በመቅደስ ከተገኘበት በቀር አገልግሎት እስኪጀምር ያለው የሠላሳ ዓመታቱ ታሪኩ ፈጽሞ አልተጻፈም። አልተጻፈም ማለት ታሪክ አልነበረም ማለት ነው? አይደለም። አልተጻፈም እንጂ ታሪክ አለ ብለን ታዲያ ይህን ‘ጎዶሎ’ (ጎዶሎ አይደለም እንጂ) ለመሙላት ታሪክ መበጀትና መፈጠር አለበት? አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ከመወለዱ በፊት የሆነውን ታሪክ ከማርያም የሰሙት ወንጌላቱን የጻፉልን ጸሐፊዎች አይጽፉልንም ነበር? ሊጽፉልን ይችሉ ነበር። ግን አልተጻፈልንም። ለምን? ይህ ለመዳናችን

አስፈላጊያችን አይደለም? ደግሞም እንዲጽፉ የመራቸው መንፈስ ቅዱስ ይህ እንዲገባ አላደረገም። ቃሉ ዝም ሲል ዝምታውም የመናገሩን ያህል አክብሮት ይገባዋል።

ስለ ማርያም የተጻፈልንም እንዲሁ ልናውቀው የተገባንን ያህል ነው። ሌላ ማወቅ ያለብን ወይም የሚያስፈልገን፥ ለትምህርትና ለተግሳጽ፥ ልብን ለማቅናት በጽድቅ ላለው ምክር የሚጠቅመን ቢሆን ኖሮ በተጻፈልን ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የፈለግነውን የመጠን ቁጥር ጽፈንበት ወደ ገንዘብ የምንለውጠው ባዶ ቼክ አይደለም። ምንም ነገር ባልተጻፈበት ሰነድ ሰዎች ያሻቸውንና የፈጠሩትን ጽፈው ሊዶሉ አይገባም።

ስለ ማርያም የተጻፉ የኋላ ዘመናት ታሪኮች የእግዚአብሔር መንፈስ ያልመራቸው የሰዎች ፈጠራዎች እና ተረቶች መሆናቸውን የምናውቀው ከተገለጠውና ከተጻፈው ቃሉ ጋር የተጋጩ ሲሆኑ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ካልመራቸው ደግሞ ሌላኛው መንፈስ እየመራቸው ነው ማለት ነው። ወይም ቢያንስ፥ ከአእምሮአቸው የፈለቀውን፥ ልባቸው የወለደውን ፈጠራ እየጻፉልን ነው ማለት ነው። ድርሳናት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ከማቅረብ ይልቅ ከክርስቶስ የሚያርቁ ሲሆኑ፥ ክርስቶስን ኃይለኛ ዳኛ፥ ጨካኝ ጌታ አድርገ ስሎ ድርሳኑ የተጻፈለትን ሰው ወይም ሴት ርኅሩኅ፥ አዛኝ፥ ይቅርታን ከየትም ገብተው የሚያመጡ ሲደረግ ይህ በኃጢአተኛ ሰውና የኃጢአት መድኃኒት በሆነው አዳኝ መካከል ጣልቃ መግባትና አዳኙን ጌታ መሸፈን ነው።

ተአምረ ማርያም፥ እና ውዳሴ ማርያም፥ መልክአ ማርያም፥ (መልክአ ማርያም ስለ ማርያም መልክ እያንዳንዱ የሰውነቷ ክፍል እየተጠራ ሰላምታ ይገባሻል እየተባለ የሚጸለይና በየቀኑ የሚነበብ መጽሐፍ ነው።) እና እነዚህን የመሰሉ ሌሎችም መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉት ትረካዎችና ልብ ወለዶች ከወንጌሉ እውነት ጋር የሚጋጩ ብቻ ሳይሆኑ አምልኮን ከእግዚአብሔር የሚቀንሱና ለሌላ የሚያሳልፉ፥ እምነትንም በአንዱ አዳኝ ላይ ከማድረግ የሚያስጥሉ ናቸው። መዳን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ፈጽሞ የቀረበ ነውና የሚያምን ሁሉ በነጻ የሚቀበለው ነው። ለኛ ነጻ ነው ማለት ግን የተከፈለ ዋጋ አልነበረም ማለት አይደለም። ጸጋው ነው መዳንን ነጻ ያደረገው። በጸጋው እንዲያው አምነን ከመዳን የሚያጎድለን ማናቸውም ነገር ከኛ እጅግ መራቅ አለበት።

ስለ ማርያም የአማላጅነት መብትና ሥልጣን በኢኦተቤ/ክ የእምነት ሰነድ ውስጥ የተጻፈው ብዙና በብዙ ቦታዎች ነው የተጻፈው፤ አንዱና በብዙ ሊቃውንት የተጻፈውና በሊቃነ ጳጳሳቱ የጸደቀው አንዱ እንዲህ የሚል ነው፤

> ቤተክርስቲያናችን ስለ እመቤታችን አማላጅነትና ቃል ኪዳን የምታስተምረው በቅዱስ መጽሐፍ በተጻፈው ቃልና ፍጹም በሆነ ሐዋርያዊ ትውፊት ነው ። እመቤታችን የእናትነት ክብርና የአማላጅነት ቃል ኪዳን ከልጅዋ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብላለች ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ልጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገው በእመቤታችን አማላጅነት ነው ። (ዮሐ. 2፡1 5) ። ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ «እነሆ ልጅሽ» (ዮሐንስ 19፡26) ብሎ ቤተክርስቲያንን ለርሷ «እነሆእት እናትህ» ብሎ እርሷን ለቤተክርስቲያን አደራ ሰጥቷል ። እመ አምላክ ፡ ወላዲተ አምላክ መሆኗን አምነው «ሰአሊ ለነ ቅድስት» ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያሉ ስሟን የሚጠሩትን ሁሉ እንደሚምርላት የማይለወጥ ቃል ኪዳን ተቀብላለች ።

(ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ ገጽ 52።)

ይህ በ18 የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት የተዘጋጀና በሊቀ ጳጳሳቱ የጸደቀ የእምነት አቋም ነው። ‘ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያሉ ስሟን የሚጠሩትን ሁሉ እንደሚምርላት የማይለወጥ ቃል ኪዳን ተቀብላለች።’ የሚለው ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የወጣና ከአዳኙ ወደ አማላጅ፥ ከፈጣሪ ወደ ፍጡር፥ ከጸጋ ወደ ሥራ የሚያመለክትና የሚመራ አስተምህሮ ነው። ሰዎችን የመዳናችን ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ወደ ሌላ ወደ ማናቸውም ነገር የሚያመለክትና የሚመራ ማናቸውም ትምህርት ከሰይጣን ነው። አትጠራጠሩ ከሰይጣን ነው። መዳንን ፍለጋ ከክርስቶስ ወደ ሌላ የሚያመለክት ማናቸውም ትምህርት ከአጋንንት ነው። ሃይማኖታዊ ካባ ሊለብስ ይችላል፤ የሚጥምና ለጆሮ ደስ የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል፤ ዋጋ የማይጠይቅና ቅልል፥ ቅልብጭ፡ያለ ሊሆን ይችላል፤ ግን ክርስቶስን የሚጋርድ ማናቸውም ትምህርት ከጥልቁ የሆነ ትምህርት ነው።

ሊቃውንቱ በጻፉት ሰነድ ውስጥ ኋላ በመጨረሻው፥ በተአምረ ማርያም ትንተና ክፍል እንደምናየውም፥ ትንሣኤዋና ዕርገቷና ፍልሰቷም በቤተ ክርስቲያኒቱ የእምነት አንቀጽ በግልጽ ተቀርጾ የተቀመጠ ነው። ማርያም ከሙታን ተነሥታለች፥ ከሙታን መነሣት ብቻ ሳይሆን ዐርጋለች፤ ማረግ ብቻ አይደለም ፈልሳለችም፤ ፍልሰታ ለማርያም እየተባለ እንዲከበር በሃይማኖቱ ተከታዮች ላይ የተጫነው ይህ ቀንበር በቃሉ ውስጥ፡ የማይገኝ የሐሰትና የፈጠራ ትምህርት ነው። የተጻፈው እንዲህ ይላል፤

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲተላለፍ በመጣው ትውፊት በተገለጠው መሠረት በ64 ዓመት ዕድሜዋ በጥር 21 ቀን ዐርፋለች ። መላእክት ሥጋዋን አሳርገው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖሩት ። በዚያው ዓመት ሥጋዋ እስከ ነሐሴ 14 ቀን በገነት

ከቆየ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን መላእክት አምጥተው ለሐዋርያት ሰጡአቸውና በጌቴሴማኒ ቀበሩአት ፡ በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ ፡ በክብር ወደ ሰማይ ዐርጋለች ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት ፡ ትንሣኤና ዕርገት ይህን ታምናለች። ታሳምናለች ። በየዓመቱም ነሐሴ 16 ቀን የፍልሰትዋን መታሰቢያ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ታከብራለች (ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን) ።

(ምንጭ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ ገጽ 52-53።)

ወደ ፊት እንደምንመለከተው እንዲህ ያለው ትምህርት በቃሉ ውስጥ የሌለ፥ በቃሉ ውስጥ ከቶም የማይገኝ፥ የተፈጠረ አሳች ትምህርት ነው። አሳችነቱም ድነትን ከድነቱ ምንጭ እንዳይቀዱ ሰዎችን በማገዱ ነው።

ማርያምን በተመለከተ የተፈጠሩና በታሪክ ውስጥ እያደጉ የመጡ ብዙ ትምህርቶች አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው የኢየሱስ እናት ማርያም ታሪኳ በጣም ውብ ታሪክ ነው። ለጌታችን ሥጋ መልበስ የእግዚአብሔር መሳሪያ ሆናለች። መልአኩ ገብርኤል ተልኮ ከተናገራትና ኢየሱስን ከመጸነሷ ጀምሮ (እውነተኛው ታሪኳ እዚያ ነው የሚጀምረው) እስከ መስቀሉና ከዕርገቱ፥ በኋላም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብራ መገኘቷ በግልጽ ተጽፎ ይገኛል።

በካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከመወለዷ በፊት ያለው ታሪኳ፥ ያለ ኃጢአት ከመጸነሷ ጀምሮ ወደ ሰማይ እስከማረጓና መፍለሷና የአሁን የአማላጅነትና የቤዛነት ሥራዋ በሰፊው ይተረካል። ይህ በ2ጴጥ. 1፥16 እንደተጻፈው ያለ በብልሃት የተፈጠረ ተረት ነው። በ2ጢሞ 4፥4 እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ የተባለውም እንደዚህ ያለው አሳች ትምህርት ነው።

'ማንም ምንም ነገር ስለ እምነቱ ቢያስተምር የራሱ ጉዳይ ነው፤ ለምን ስለ እነርሱ ትምህርት መናገርና መጻፍ አስፈለገህ?' ሊሰኝ ይቻላል። ላያስፈልግ ይችላል፤ ግን መጽሐፉ ሲቀረደድና ያላለውን እንዲል ሲደረግ ዝም ማለት ለአንዳንዶች ምቹ ሊሆን የሚችለውን ያህል ለሁሉም ምቹ ይሆናል ማለት አይደለም። ከኛም መካከል ወደ አምልኮተ ማርያም የሚንሸራተቱና የሚያንሸራትቱ ሲከሰቱ ሌሎቹን አላዋቂ ወይም ያልተማሩና ያላደጉ አማኞች ሊያስቱ ስለሚችሉኡ እውነቱ መነገሩ ተገቢ ነው።

በኦርቶዶክሳዊ ወካቶሊካዊ አስተምህሮ ስለማርያም ከተፈጠሩት ተረቶች ዋናዎቹን በመጠኑ በዝርዝር ብንመለከታቸውም አንኳሮቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ያለ ኃጢአት መጽጸነሷ። (ጸ ጠበቅ የሚደረገው ፊደል ነው) ይህ ጽንሰት ኢየሱስን ያለ ኃጢአት መጸነሷ ሳይሆን እርሷ ራሷ፥ ማርያም ያለ አዳም ኃጢአት ወይም የውርስ ኃጢአት ወይም ያለ ጥንተ አብሶ ተረግዛ መወለዷ ነው። ልክ ኢየሱስ በተወለደበት መልኩ ነው የተወለደችው ሊሰኝ ነው።

ይህ እርሷን ብቻ ሳይሆን ወላጆቿንም ከአዳም ዘር ውጪ ያደርጋቸዋል። ይህ በቃሉ ውስጥ የሌለና የተፈጠረ ትምህርት ኢየሱስን ከአዳም ዘር የውርስ ኃጢአት ነጻ አድርጎ ለማቅረብ በወላጆቿ ላይ የተፈጸመው መለኮታዊ ተአምር መሆኑ ነው። ልብ ማለት ያለብን፥ ይህ እጅግ ትልቅና ግዙፍ አስተምህሮ ሆኖ እያለ በቃሉ ውስጥ፡ፈጽሞ ያልተገኘ እጅግ ዘግይቶ የተፈጠረ መሆኑን ነው።

ማርያም ያለ ኃጢአት መጸነስና መወለድ ከቻለች ኢየሱስ እንዴት ያለ ኃጢአት ሊወለድ አይችልም? ይህ ኢየሱስን ከውርስ ኃጢአት የጸዳ አድርጎ ለማቅረብ የተደረገ ሙከራ ብቻ ሳይሆን በአቋራጭ ለማርያም ልዩ ፍጡርነትን ለማቀዳጀት የተደረሰ ፈጠራ ነው። በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ይህ ትምህርት የተደነገገው እንደ ኤሮጳውያን ቆጠራ በ1854 ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መቼ መጣ ይህ ድንጋጌ? ቢባል የኖረ መሆኑ ብቻ ይነገራል እንጂ በዚህ ጊዜ ተብሎ የተሰነደ ሰነድ በቀላሉ አይገኝም።

ኃጢአት የሌለበት ሰው ምንም አዳኝ እንደማያስፈልገው የታወቀ ነው። አዳኝ የማያስፈልጋት ቢሆን ኖሮ ማርያም በሉቃ. 1፥47 እንደተጻፈው በመድኃኒቷ ሐሴት ስለምን አደረገች? *ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤* ብላለችና።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተጻፈው በኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ውስጥ ከማርያም ጋር አራት ሴቶች ተጠቅሰዋል። በመጀመሪያዎቹ 6 ጥቅሶች ስማቸው የተጻፈልን እነዚህን ሴቶችና ታሪካቸውን ስንመረምር የሚያስመሰግንና የሚያስወድስ ታሪክ ያላቸው ሴቶች ከቶም አይደሉም። ትዕማር ማለት ይሁዳ ከልጁ ሚስት መንታ ልጆች የወለደባት ናት። ራኬብ የተባለችው ሴት በብዙ ትርጉሞች ረዓብ ተሰኝታለች፤ ረዓብን ከሆነች የኢያሪኮዋ ጋለሞታ መሆኗ ነውና ከጠፉት አሞራውያን ወገን ናት። ሩትም አይሁዳዊት አይደለችም፤ ሞዓባዊት ናት፤ በሐረጉ ውስጥ ግን ገባች። ቤርሳቤህ እንዲያውም የዳዊት ሚስት ሳትሆን የኦርዮ ሚስት ነው የተባለችው፤ ታሪኩ መጥፎ ነው። የነዚህ አሳፋሪ ሴቶች ታሪክ ከንጉሡ ኢየሱስ ታሪክ ውስጥ ተቀርፈው

አልወጡም። እነዚህ ሴቶች ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ በገሃድ የታወቁ ኃጢአተኛም አሕዛብም ሴቶች ናቸው።

ማርያም ልዩ ፍጡር ኖራ ቢሆን ከነዚህ ለማነጻጸር እንኳ የማን ልጅ መሆኗ አይጻፍም ነበር። የትውልድ ሐረግ የወንድ ብቻ ሳይሆን እናቶችም የሚጻፉበት መሆኑ ከብሉይ ኪዳን ነገሥታት ይታያል። በተአምረ ማርያምና በሌሎቹም መልካ መልኮች የተጻፉት የማርያም መወለድ ከኢየሱስ ያልተናነሰ ትንግርት ነውና ይህ በእውነት ብዙ መቶዎችና ሺህዎች ዓመታት ቆይቶ መጻፍ ነበረበት? እውነት ኖሮ ቢሆን ከወንጌሉም በፊት መጽጻፍ አልነበረበትም? ወይም ከወንጌሉ ጋርና በወንጌሉ ውስጥ መጽጻፍ አልነበረበትም?

<u>2. ዘላለማዊ ድንግልና።</u> ኢየሱስ ከድንግል መወለዱ በግልጽ ተጽፎአል፤ ማቴ. 1 እና ሉቃ. 1። ዮሴፍም ማርያምን የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ እንዳላወቃትም በግልጽ ተጽፎአል። ስለዚህ የጌታ ሥጋ መልበስ ልደት ፍጹም ልዩ ነው። ሥጋ በመልበሱም ፍጹሙ አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖአል። ታዲያ ማርያም ጌታን ከወለደች በኋላ ሌላ ከወለደች ወይም ብትወልድ የጌታ ማንነት ይለወጣል? ማንነቱ እንዳይለወጥ ነው ማርያም ለዘላለም ድንግል የተሰኘችው? ወይስ የእርሷ ማንነት ላይ ዘብ መደረጉ ነው? ጉዳዩ ግልጽ ነው።

ጌታ ከድንግል ሥጋን ነሥቶአልና ከዚያ በኋላ ማርያም ብትወልድም ባትወልድም የእርሱ ማንነት አይለወጥም። የእርሷ ግን አሁን እንደተሰጣት ያለውን ክብር አይሆንም። ለማግነን ሲባል በነበራት ላይ ሌላ ሰው ሠራሽ ክብር ይጨመራል እንጂ አይቀነስም። ስለዚህ ለእርሷ የተለየ ስፍራ ለመስጠት ነው ከመውለዷ በፊት ድንግል፥ ስትወልድ ድንግል፥ ከወለደችም በኋላ ድንግል ሆና የነበረችና የኖረች የተደረገው።

ማርያም ኢየሱስን ከመውለዷ በፊት ብቻ ሳይሆን ጊዜ ወሊድም ድንግል መደረጓ የኢየሱስን መወለድ ለማርያም ሲባል፥ ፍጹም የሆነ አካሏ ከስቃይ ነጻ እንዲሆን ሲባል ጭንቅ የሌለበት ሆኖአል። ይህ ለመረዳትም ለማስረዳትም የሚከብድ ብቻ ሳይሆን ማርያምን ከሴቶች የተለየች የሚያደርግ ትምህርት ነው። መልአኩ ገብርኤል ለማርያም የተናገራት፥ 'አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ።' ነው እንጂ ከሴቶች የተለየሽ ነሽ አላለም፤ ሉቃ. 1፥28። ኤልሳቤጥም ተመሳሳይ ቃል መናገሯ በሉቃ. 1፥42 ተጽፎአል። ከሴቶች መካከል መባረክ እና ከሴቶች የተለዩ መሆን የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ጊዜ ወሊድ ድንግል መሆን የሴትነትን ወግና የማርያምን ሴትነት ብቻ ሳይሆን የኢየሱስን ሰውነትም የሚያጠያይቅ የሚያደርግ ትምህርት ነው።

ማርያም ስትወልድም ድንግል ከሆነች እርሷ ከምጥ ጭንቅ ትድን ዘንድ ኢየሱስ እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ሌላ ፍጡር ሆኖ ነው የተወለደው ማለት ነው። አዲስ ክርስቲያን ሳለሁ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ካስተማሩኝ አንዱ ቀድሞ ቄስ የነበሩ መምህር ይህን ኢየሱስ ሲወለድ እርሷ ድንግል ሆና እንድትቀር እርሱ ልክ እንደ ቅቤ ለስላሳ ሆኖ ከውስጧ እንደወጣ ቀድሞ ያስተምሩ እንደነበሩ አስተምረውን ነበር። ይህ ሰውነቱን አይጋፋም? ማንም በሥጋ የሚወለድ ሕፃን እንደ ቅቤ ቅልጥ፥ ፍስስ ብሎ ከማኅጸን አይወጣም። በዘፍ. 3፥16 *ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤* የተባለው ለሴቶች ሁሉ ነው። ማርያምም ከሴቶች መካከል ትባረክ እንጂ ከሴቶች ያልተለየች ሴት ናት። ምጥና ጭንቀት ለኃጢአተኞች ሴቶች እንደሆነ ለማስረዳት ሲባል እና ይህንን ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ ለመቃወም ነው ማርያም የሔዋን ወይም የአዳም ኃጢአት የሌለባትና ይህ ምጥና ጭንቀት እንዳይነካት የተፈጠረው። በቃሉ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ማርያም ከሴቶች የተለየች አልተባለችም።

<u>3. ወደ መንግሥተ ሰማያት ማረጓ።</u> በካቶሊክ አስተምህሮ የምድር ኑሮዋ ዘመን ሲፈጸም ሳትሞት እንደ ሔኖክ ወደ ሰማይ ማረጓ ነው የተጻፈው። ሞታ ሳይሆን ሳትሞት። በኦርቶዶክስ ደግሞ ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፍ ውስጥም እንደተጻፈው፥ ተአምረ ማርያምንም ስንመለከት እንደምናየው፥ በ64 ዓመቷ ሞታ ተቀብራ በ3ኛው ቀን ተነሥታ ማረጓ ተጽፎአል። የቱ ትክክል ሊሆን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋ. 1፥14 ከጌታ ወንድሞች ጋር ስለ ማርያም ከተናገረ በኋላ ስለ እርሷ ምንም የተናገረው ነገር የለም። ቃሉ የሚለው፥ *እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።* ነው። ያ ስፍራ ማርያም ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰችበት ነው። ታዲያ ስለማርያም ዕርገት መጻፍ ያስፈለገው ማንን የተለየ ለማድረግ ነው? በግልጽ እንደተጻፈልን የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው፤ ስለዚህ ማርያም ያለ ኃጢአት በመሆኗ መሞት የለባትምና ለምን አለመሞቷ አይጻፍ? ካቶሊኮቹ ይህን ለማስተካከል ይሆናል አለመሞቷን የጻፉት። ይህን ትምህርት ደንግገው ያቆሙትም በጎርጎራውያን አቆጣጠር በ1950 ነው። መቶ ዓመት እንኳ ያልደፈነው አዲስ አስተምህሮ ነው። በኦርቶዶክስም ሞቷ ከተጻፈ አይቀር ከሙታን ተነሥታ ማረግ ኖረባት። ያውም ቀኑንም እንኳ አልለወጡትም፤ በ3ኛ ቀን!

<u>4. አማላጅነቷ።</u> ያለ ኃጢአት የተጸነሰችው፥ ለዘላለሙ ድንግል የሆነችው፥ ወደ ሰማይ ያረገችው ማርያም ሥራዋ በዚያ ብቻ ማብቃት የለበትም። ይህኛው የአማላጅነት

ትምህርት ደግሞ አሁንም አማላጅ ሆና የፈለገችው፥ የለመነችው፥ የጠየቀችው ሁሉ እየተፈጸመላት የምትኖር የመሆኗ ትምህርት ነው። የመንግሥተ ሰማይ ደጅ ተሰኝታ በእርሷ በኩል ካልሆነ ማንም ወደ እግዚአብሔር የማይደርስ ተደርጎ ተስተምሯል። ኢየሱስ ዳኛና ፈራጅ እርሷ ደግሞ አዛኝ፥ መሐሪና ርኅሩኅ ተደርጋ ተስላለች። ይህንን የአማላጅነት ስሕተት ወደ ፊትም እናነሣዋለን።

5. <u>ቤዛዊተ ኵሉ።</u> አማላጅ ብቻ ሳትሆን እንዲያውም ቤዛ ናት፤ የዳንነው በእርሷ ደም መሆኑም ተጽፎአል። በመስቀል ላይ የፈሰሰው የጌታ ደም የእናቱ ደም ነውና ያዳነን የማርያም ደም መሆኑ በግልጽ ተነግሮአል። የማርያም ደም አዳኝ ቢሆንማ ክርስቶስ ቀድሞውኑ መምጣትም ባላስፈለገም ነበር። አዳኝ ደም እያለ ሌላ ለምን አስፈለገ? ቤዛ ማለት ለኃጢአት ፈንታ ሆኖ የሚሞት ማለት ነው።

ጌታ ቤዛ መሆኑ በማያሻማ ቋንቋ ነው የተጻፈልን፤ ማቴ. 20፥28 *እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።* ይላል። የምንጸድቀው በሌላ በማንም ሳይሆን በክርስቶስ ቤዛነት በኩል መሆኑ ተጽፎልናል፤ *በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።* ሮሜ 3፥24። 1ጢሞ. 2፥6 *ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤* ይላል። የኃጢአት ስርየት ያገኘነው በቤዛነቱ ነው፤ *እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።* ቆላ. 1፥13-14። ማርያም ቤዛ አይደለችም። ቤዛ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። ማርያምን ቤዛ ወይም የሁሉ ቤዛ ማድረግ ክርስቶስን መጋረድ ነው። የሰይጣን ተቀዳሚ ተግባር ሰዎች ክርስቶስን እንዳያዩ፥ እንዳያውቁ፥ እንዳይቀበሉ፥ እንዳይድኑ ማድረግ ነው። ይህንን የቤዛነት ነጥብ ዝቅ ብሎ ለብቻ አነሣዋለሁ።

6. <u>መገለጧ።</u> ይህ በካቶሊክኛ አካሄድ ከሄድን ሌላ ተጨማሪ ሆኖ መጠቀስ የሚችል ነጥብ ነው። ያም የማርያም በታሪክ ውስጥ፥ በዘመናት ውስጥና ዛሬም በራእይም፥ በአካልም እየተገለጠች ለሰዎች መታየቷ ነው። በተለያዩ አህጉራት ይህ በመከሰቱ ካቶሊኮች በተገለጠችባቸው ቦታዎች ገዳማት በመገደምና ሕንጻዎች በማነጽ መታሰቢያዋን እያበዙና እያባዙት ነው። የተገለጠችባቸው ቦታና ጊዜዎች አሁን ከሺህ አልፈዋል። የሚያሳፍረው ተገልጣ ተናገረች የሚባለው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ቢቃረንም እንኳ ያለ ምንም ጥያቄና ጥርጥር እንዲያው እንዲቀበሉት መደረጉ ነው።

በኦርቶዶክስ፥ በተአምረ ማርያም ከተጻፉት ሌላ በአካል ተገለጠች የተባለባቸው ሕዝባዊ ታሪኮች ከቁጥርም አይገቡም። በ1990ዎቹ አጋማሽ አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ግቢ ታየች እየተባለ የተወራና የተሠራ ነገር ነበረ። በቅርቡ ደግሞ ‘ማርያም ተገለጠች’ ሳይሆን ‘ማርያም ነኝ’ የምትል ሴትም ተነስታ ሽብርና ግርግር መፈጠሩ የታወቀ ነው።

እነዚህ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና ትምህርት ጋር ይጋጩ ወይም ይስማሙ ግድ ሳይኖር ነው በድፍኑ ቃሉን የማይመረምርና የማይጠይቅ ሕዝብ አፍንጫው ተይዞ የሚጋተው። ጥቂት ጥያቄዎች ቢጠየቁ ተገቢ ነው። እነዚህን ጽሑፎች ማን ጻፋቸው? ለምን ጻፋቸው? መቼ ተጻፉ? ቀድሞ ከተጻፉ ትምህርቶች በምን ይስማማሉ በምንስ ይለያሉ? ከመጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ትምህርት ጋርስ ይስማማሉ? ወይስ ይጋጫሉ? በተለይ የመጨረሻው ጥያቄ አንገብጋቢ ነው። ሰውን ወደ አምላክነት ስፍራ ከፍ አድርጎ የሚሰቅል፥ የአምላክ የእግዚአብሔርን ሥልጣን ከፍሎና ገምሶ የሚወስድና የሚቀንስ፥ ቀንሶም ለሌላ ለፍጡር የሚሰጥ፥ ከእውነት ቃል ጋር የሚጋጭ ማናቸውም ድርሳን፥ ገድል፥ ተዓምርና መልክ ምንጩ ሰይጣን እንጂ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

## ከውን ማርያም እግዝእት ናት?

እርግጥ ነው ማርያም የጌታችን እናት ናት፤ ጸጋ የሞላባት ናት፤ ከሴቶች መካከል የተባረከች ናት፤ የማኅጸንዋ ፍሬ የተባረከ ብጽዕት ናት። ግን እመቤት (እግዝእት) ናት? አይደለችም። እግዝእት ማለት አንስታዊ የጌታ ወይም የእግዚአብሔር ማዕረግ ነው። በጾታ ሴት የሆነች ጌታ ማለት ነው። ከጌታ በቀር ደግሞ ጌታ የለም። ይህ ስግደትንና አምልኮን ከጌታ በቀር ለሌላ ለመስጠት የሚደረግ ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ እርምጃ ከዐሠርቱ ትእዛዛት በቀጥታ ሁለተኛውን ትእዛዝ የሚጥስ ነው። ምስልም መሥራት ስግደትም ማቅረብና ማምለክ ይህ እንጂ ሌላ ከቶም አይደለም። ኋላ በታሪካችንም የምናየው ሕጋዊ ወይም ሃይማኖታዊ የተደረገው ለስዕል መስገድ ለጣዖት መስገድ ነው።

ስለ ማርያም የተጻፉት ድርሳናትና ገድላት በካቶሊካውያንም ሆነ በኦርቶዶክሳውያን የተጻፉባቸውንና የተደረሱባቸውን ዘመናት ብንመረምር ከታሪኩ ዘመን በእጅጉ የራቁና የኋላ ምዕት ዓመታት ድርሳናት ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ፥ ስለማርያም ዕርገት የተጻፉ ድርሳናት ከ6ኛው መቶ በፊት አልነበሩም። በካቶሊካውያን ዘንድ በ13ኛው መቶ ከፊል ተቀባይነት እየተቀዳጀ መጥቶ ርእሱ ክርክር ሲደረግበት ኖሮ

በካቶሊካዊ ሃይማኖት ዶግማ የሆነው ቀደም ሲል በጠቀስኩት ዓመት በ1950 ነው። የማርያም ያለኃጢአት መጸነስ በክርክር ኖሮ በ1854 ነው ይፋ ዶግማ የሆነው።

በኛ አገር የገነነ አምልኮተ ማርያም የደራው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ይመስላል። ካቶሊካዊ ግንኙነትም ተጀምሮ ነበርና ይህ ግንኙነት አጉልቶት ይሆን? ምናልባት ሊሆንም ይችላል። በዘመኑ ሊጎበኝ በመጣው ፈረንሳዊ ሰው እና በአባ ጊዮርጊስ መካከል ንግግር ተደርጎ ነበረ። ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ወደ ቫቲካን ተላከ። የሮማ ቤተ ክርስቲያን ቸል ብትለውም ግንኙነቱ ኋላ ከ90 ያህል ዓመታት በኋላ ለፖርቱጋሎች መጠራትና መምጣት ምክንያት ሆኖ ነበር። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ራሱ የማርያም አምልኮን በአዋጅ ሕጋዊ ያደረገ፥ ለመስቀልና ለስዕል የማይሰግዱ በጽኑዕ እንዲቀጡም የደነገገ ንጉሥ ነው። ተአምረ ማርያም የተተረጎመውም በዚህ በእርሱ ዘመን መሆኑ ይገመታል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና ተደንግጎ ሲያበቃና ወንጌላቱ አራቱ ብቻ መሆናቸው ሲረጋገጥ ታሪኩ ግልጽ ነው። የወንጌላቱ ዓላማም በግልጽ ይነበባል፤ ይህም ወደ ነፍሳችን እረኛና ጠባቂ፥ ወደ ዓለም መድኃኒት ወደ ክርስቶስ የሚያመለክት ነው። የታሪክ ማዕከልና እንብርት ወደሆነው በመስቀሉ ላይ ወደተፈጸመው ድንቅ የእርቅ ሥራ የሚያመለክት ነው። ይህ ክብርም፥ ምስጋናም፥ አምልኮም፥ ስግደትም፥ ውዳሴም ለሌላ ለማንም ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔር ብቻ መሆን እንዳለበት ያሳየናል።

ለእግዚአብሔር ብቻ ካልሆነ በቀር ለአምላክ የሚሰጥ ማናቸውም ነገር ለሌላ ፍጡር መሰጠት የለበትም። ማርያም የጌታችን እናትም እንኳ ብትሆን የአምላክን ክብር ቆርሰን ልናቀርብላት አልታዘዝንም። ጌታ አላዘዘንም፤ ሐዋርያቱም አላስተማሩንም። በዘመናችን እንደሚታየው የመሰለ የገነነ አፍቅሮተ ማርያምና አምልኮተ ማርያም አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ፥ ጌታ እናቱ ወደ እርሱ እንዳመለከተችው እርሱም ወደ እርሷ ምነው አላመለከተም? ሐዋርያትስ ከሰፊና ጥልቅ ትምህርታቸው ምነው ይህን አላስገቡም? የለም፤ ይህ ደሓራዊ ትምህርት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በቀጥታም በርቀትም የማይገኝ ኋላ የተፈጠረ የስሕተት ትምህርት ነው። ከአንዱና ብቻውን ከሆነው አምላክ በቀር ለሌላ ስግደትና አምልኮን፥ ውዳሴና ምስጋናን መስጠት ጣዖትን ማምለክ ነው። ኢሳ. 42፥8 እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም ይላል። እግዚአብሔር ክብሩንም ምስጋናውን ከማንም ጋር አይጋራም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ እናት ማርያም የሚናገረውና የማርያም አምላኪዎች የሚናገሩትና የሚያስተምሩትና የጻፉት ሁሉ በወንጌላት ውስጥ ከተጻፈችው ማርያም የተለየ ነውና ሌላ ማርያም እንጂ ያቺ ማርያም የኢየሱስ እናት ማርያም ናት ማለት

አይቻልም። 'የማርያም አምላኪዎች' ስል ለማርያም ከሚቀርበው ለአምላክ ብቻ ከሚሰጠው ያላነሰ ውዳሴና ጸሎትም ስለሚቀርብላት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያትና ታሪኳን የምናነብበው ማርያም ጨዋና ስፍራዋን በትክክል ያወቀች ሴት ናት። በካቶሊክ እና በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የምናያት ማርያም እርሷ የምትፈልገው ሁሉ የሚደረግላትና ሌሎችም እርሷን የሚጠይቁት ሁሉ ምንም ይሁን በእግዚአብሔር ያለ ምንም ጥያቄ የሚፈጸምላት እመቤት ናት። መድኃኒትና መዳንም አያስፈልጋትም፤ በሉቃ. 1፥47 *ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤* የተባለውም ያለ አግባብ የገባ ነው ብለው የሚያስቡ አይጠፉም። ምክንያቱም ከጥንተ አብሶም፥ ከጎልዮ ኃጢአትም፥ ከግብር ኃጢአትም ሁሉ ነጻ ናትና መድኃኒት ለምን ያስፈልጋታል? ከኃጢአት ነፃ ሆና የተጸነሰች ከሆነች አዳኝ አያሻትም።

ወላጆቿም ሆኑ የዘር ሐረጓ በጠቅላላው ከአዳማዊነት የጸዳ የተለየ ሐረግ ካልሆነ ከዚህ እንዴት ነጻ ልትሆን እንደቻለች ድንቅ ነው። እርሷ በወንጌላት ውስጥ የምናያት ማርያም ግን፥ *ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤* እንዳለች የጌታ አክባሪ፤ መንፈሷ በመድኃኒቷ በአዳኟ ሐሴት ያደረገች፥ አዳኝና መድኃኒት እንዳስፈለጋት የተረዳችና የተናገረች ናት። ኃጢአተኛ ሰው ሆኖ አዳኝ የማያስፈልገው ከቶ ማን ነው? ማርያም ስለ ራሷ እንዲህ ከመሰከረች እርሷን እንስማ ወይስ ስለ እርሷ የሚናገሩት ሌሎች የሚሉትን እንስማ? ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው ይሏል ይህ ነው። ስለ አንድ ሰው እና ያንን ሰው ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የሚያውቅ ያ ሰው ራሱ ነው። ሌላው ሁሉ የሚያውቀው እውቀት ከዚያ ሰው ያነሰና ያ ሰው ከገለጠው የተከፈለ ብቻ ነው። ለዚህ ነው፥ 'ማርያምን ወይስ ስለ እርሷ ከብዙ መቶዎች ዓመታት በኋላ የጻፉ ሰዎችን እንስማ?' ያልኩት።

እግዝእት ከላይ እንዳልኩት እመቤት ማለት ነው። እመቤትም የጌታ እኩያ ነው። ጌታን ጌታችን እንደምንል ሌላ ሰውን ጌታችን ብንል ስሕተት እንደሚሆን እርሱን ጌታ በምንልበት መልክ ሌላ ሴትን እመቤታችን ብንልም ያው ነው። እግዝእ ማለት በአንስታይ ጌታ የማለት አቻ ነው። ሰውን ጌታው ወይም እመቤት ማለት በአንዳንድ ቋንቋዎችና ባህሎች የተለመደ ነው። ነገር ግን ጌታ ወይም ጌታው ማለት እና ጌታዬ ማለት የተለያዩ ናቸው። እመቤት ማለትና እመቤቴ ማለትም የተለያዩ ናቸው። እመቤቴ ወይም ጌታዬ ስል ያንን ሰው ወይም ያቺን ሴት በላዬ ላይ ባለ ሙሉ ሥልጣን አድርጌ መቀበሌ ነው።

በ2ኛ ዮሐንስ የተጠቀሰችውን ሴት እመቤት ብሎ ዮሐንስ ጠርቶአልና ማርያም ስለምን እመቤት መባል አይገባትም የሚል ጥያቄ ቀርቦልኝ ነበር። ያቺን የ2ኛ ዮሐንስ ሴት ማርያም ናት የሚሉም አሉ። አለመሆኗን ዐውዱና በውስጡ ያለው ይዘት

ስለሚያሳይ እዚያ ውስጥ አልገባም። ዐውዱና ይዘቱ ስል ለምሳሌ፥ ይህች ሴት ልጆች ያሏት መሆኗ የተጻፈ ሲሆን፥ ማርያም ናት የሚሉ ይህ ደግሞ ይቆረቁራቸውና ይጥሉታል። ነጥቡ ግን፥ ይህች ሴት እመቤት ወይም የተመረጠች እመቤት ተባለች እንጂ ዮሐንስ፥ 'እመቤቴ' አላላትም። ልዩነቱ ግልጽ ነው።

## ወላዲተ ክርስቶስ ናት? ወላዲተ አምላክ ምን ማለት ነው?

በኦርቶዶክሳዊ እና ካቶሊካዊ ሃይማኖት ማርያም ወላዲተ አምላክ ናት። ስያሜው ግዙፍ ነው። ቃሉ ወይም ስያሜው የተጀመረው በ4ኛው መቶ ምዕት ዓመት ስለ ክርስቶስ ማንነት በተፈጠረው ክርክር ወቅት ነው። በኒቅያው ጉባኤ ክርክር ሆኖበት የክርስቶስ መለኮትነት በተረጋገጠበት ጉባኤ ማርያምም የመለኮት ተሸካሚ ወይም ቴኦቶኮስ፥ (በግሪክ Θεοτόκος) መሆኗ ተብሎ በ431 የኤፌሶን ጉባኤ ተቀባይነት ያገኘ ስያሜ ነው።ቀጥተኛ የቃሉ ትርጉም የመለኮት ተሸካሚ ማለት ነው። ስያሜው ግን በማርያም ማንነት ሳይሆን የዚያ ዘመን አከራካሪ ጉዳይ በነበረው በክርስቶስ ማንነት፥ ማለትም፥ አምላክ እና ሰው ብሎ የመለየቱ ክርክር ላይ ያተኮረ ነው። ንጥር ትኩረቱ ከማርያም የተወለደው ኢየሱስ እርሱ አምላክ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጉዳይ ነው። እመ አምላክ ለሚለው በግሪኩ Μήτηρ Θεοῦ በካቶሊክ በላቲኑ ደግሞ Mater Dei ይሰኛል። በድንግል ማርያም ማኅጸን ያደረው ሥጋን የነሳው ጌታ፥ ሰው የሆነው፥ ጌታ ሆኖ ጌታ የነበረውና ሆኖ የኖረው ነው።

ኤልሳቤጥ ማርያምን፥ 'የጌታዬ እናት' ማለቷ እውነት ነው። *የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?* ሉቃ. ፩፥43። በማርያም ውስጥ የነበረው ኢየሱ እርሱ ጌታ ነው። ይህንን የኤልሳቤጥን ሰላምታና የመልአኩ ገብርኤልንም ሰላምታ በማያያዝ አንድ መጽሐፍ ሰዎች ይህን የመልአኩ ገብርኤልንና የኤልሳቤጥን ሰላምታ በመጥቀስ፥ ምስጋና እና ውዳሴን ለማርያም ማቅረብ የተገባ ስለመሆኑ የኤልሳቤጥን ሰላምታ፥ 'ምንኛ አስደናቂ <u>ውዳሴ</u> ነው?' ሲል የገብርኤልን ሰላምታም፥ 'ምስጋና' በማለት፥ "እመቤታችን የተመሰገነችው <u>በሰዎች</u> ብቻ ሳይሆን <u>በመላእክትም</u> ነው" ይላል።[5] ነገሩ ውዳሴና ምስጋና ሳይሆን ሰላምታ መሆኑን መገንዘብ አይከብድም።

የዚህ ከላይ የተጠቀሰው አሳብ መጽሐፍ ጸሐፊ አቀራረብም ከዲቪዲው የተለየ አይደለም፤ ትኩረቱ በአንድ እውቅ የወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን ሰባኪ ስብከት ላይ ያነጣጠረ ሆኖ ወንጌላውያን አማኞችን የፈረንጅ ፍርፋሪ ለቃቃሚ ይላቸዋል። ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች የሕይወትን እንጀራ የበሉ ናቸው እንጂ የፈረንጅም የአበሻም

---

[5] ስውሩ አደጋ፥ ገጽ ፻-101።

ቅራሪና ፍርፋሪ ለማኝ እንዳይደሉ ድፍን ካልሆነ በቀር በአሜሪካ የሚኖረው ስውሩ አደጋ የተባለው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ልቡናም ያውቀዋል። አገር ቤት ተቸግረን ፍርፋሪ የበላን ቢመስለው እጎኑ ያሉት ጎረቤቶቹስ? ቢያንስ ያንን ማወቅ ነበረበት።

ወደ ሰላምታው ስንመጣ፥ ማርያም ለገብርኤል ምላሽ ስትሰጥ፥ "ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው?" አለች እንጂ፥ "ይህ እንዴት ያለ ውዳሴና ምስጋና ነው!" አላለችም። ደግሞም፥ 'በሰዎችና በመላእክት' የሚለውን አጋኖ እናስተውል። ገብርኤል አንድ መልአክ፥ ኤልሳቤጥም አንዲት ሴት ናቸው። ደግሞም ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ፥ ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞልቶባት የተናገሩት ሰላምታ ነው። ይህ የቀረበ የአንድ ጊዜ ሰላምታ ማርያም በሕይወት ሳለችም ከሞተች በኋላም አልቀጠለም፤ መቀጠልም የለበትም፤ ሊቀጥልም አይችልም፤ በአካል የለችምና። ሳለች እንኳ በሉቃ. 11፥27-28 አንዲት ሴት፥ *የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው።* ስትል ጌታ፥ 'እውነትሽን ነው፤ ልክ ነሽ።" አላላትም። ያላት፥ *ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው።* ነው።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሰላምታዎች ውስጥ ማጤን ያለብን ሰላምታዎቹ የታሪክ ጽሑፍ አካል መሆናቸውን ነው። በታሪክ ጽሑፋት ውስጥ የተነገሩት ነገሮች ሁሉ እንደዚያ ቃል በቃል በተጻፈበት መልክ የምንደግማቸው ድርጊቶች አይደሉም። ትእዛዛት ሆነው አልተሰጡም። ይህ ድርጊት ወይም ሰላምታ ወይም ውዳሴ ለማርያም ሲቀርብ ከዚያ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቶም አልታየም፤ አልተሰማም።

በሉቃ. 1፥48 *የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤* ብላለችና፥ ተብሎም ተጽፎአልና፥ ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ማለታቸው ግን ይቀጥላል። ይህ ደግሞ ምስጋናና ውዳሴ ወደ እርሷ ማቅረብ ሳይሆን የሆነችውን ኹነት መናገር ነው። በወንጌል የተጻፈ ለማርያም የቀረበ ሌላ ሰላምታም ሆነ ምስጋናና ውዳሴ የለም።

ወደ ነጥቤ ስለመስ፥ ወላዲተ አምላክ ሲባል እርግጥም ስያሜው ግዙፍ ነው። ማርያም ኢየሱስ መለኮት እያለ *ሥጋን* የነሳባት እናቱ ናት እንጂ የመለኮትነቱ ወላጅ አይደለችም። መለኮት አይወለድም። እመ አምላክ ወይም ወላዲተ አምላክ ሲባል እንደሚታወቀው ማንም ልጅ ከእናቱ በፊት ሊኖር አይችልምና፥ የእናቱም ኋላኛና ተከታይ ነውና፥ መገኘቱ ደሐራዊ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ አምላክ ነውና ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም። ይህ ማለት፥ ማርያም እግዚአብሔርን አልወለደችም እና ኢየሱስ አምላክ አይደለም ማለት ግን አይደለም። ማርያም ከመለኮት ቀዳሚነት እንደሌለባት ሁሉም የሚቀበለው ቢሆንም፥ ሹመቱ ለማያስተውለው ሰው መለኮታዊ ክብርንና ውዳሴን ለማርያም የሚያቀዳጅ ነው። ማርያም ያደረገችው ወይም የሆነችው ነገር ከዘላለም የነበረው ቃል፥ እርሱም

*እግዚአብሔር ወልድ፥ ሥጋን እንዲነሳ፥ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ እንዲያድር ራሷን ያዘጋጀችና መመረጧንም የተቀበለች ሴት ሆና መገኘቷ ነው።*

## ቤዛዊተ ኩሉ ዓለምስ ናት?

ለዚህ ምላሻዊ ሥራ መነሻ የሆነኝ ቀደም ሲል የጠቀስኩት የመምህር ምሕረተአብ ዲቪዲ መግቢያ፥ "የመዳናችን ምክንያት፥ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገርንባት መሰላል፥ የአዲስ ኪዳን ኪሩብ" ይላታል። በዲቪዲው፥ ዓለምን ያዳነች የተቤዠች ሆና ቀርባለች። መድኃኒት ናት፤ ነቢያትንና ጻድቃንን የምትዋጅ እመ ብርሃን፥ ቤዛዊተ ዓለም መሆኗ ተነግሮአል። ቤዛ ማለት የነፍስ ዋጋ ለነፍስ የሚከፈል ዎጆ ነው። ቤዛ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለኃጢአት ፈንታ ወይም ምትክ ሆኖ የሚሞት ማለት ነው።

ስለ ቤዛነት የአዲስ ኪዳን ትምህርት ግልጽ ነው፤ ቤዛችን አንድ ብቻ፥ እርሱም በመስቀል ላይ የሞተልን ክርስቶስ ነው። ሌላ ቤዛ መኖሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈምና በኋላ ከተፈጠረ ይህ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ስሕተት መሆኑ ግልጽ ነው። ታዲያ ይህን ስሕተት መምህራኑ ስለምን ያስተምራሉ? ደሟን አፍስሳ የሰውን ልጅ እንዳዳነች የሚሰበክ የጌታ ደም የእርሷ ንጹህ ደም በመሆኑ ነው ይሉናል። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ከቶም ይህንን አያስተምርም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ቤዛ የጌታ ቤዛነት ነው። ጌታ ቤዛ መሆኑ በማያሻማ ቋንቋ ነው የተጻፈልን። ጥቂት ጥቅሶችን እንመልከት።

ማቴ. 20፥28 *እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።* ይላል።

የምንጸድቀው በሌላ በማንም ሳይሆን በክርስቶስ ቤዛነት በኩል መሆኑ ተጽፎልናል፤ *በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።* ሮሜ 3፥24።

1ጢሞ. 2፥6 *ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤* ይላል። የኃጢአት ስርየት ያገኘነው በቤዛነቱ ነው፤

*እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።* ቆላ. 1፥13-14።

*በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት፤* ኤፌ. 1፥7

*ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤* 1ጢሞ. 2፥6

*የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም፤* ዕብ. 9፥12

*መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፤* ሐዋ. 4፥12።

እነዚህ ጥቂት ግን ዋና የቤዛነት ምንነትን ገላጭ ጥቅሶች ናቸው። የማርያም ሞት የሚያድነንማ ቢሆን ክርስቶስ መሞትም አያስፈልገውም እኮ ነበር። ይቅርና መሞት፥ ቀድሞውኑ መወለድም አያስፈልገውም ነበር። ማርያም ከኃጢአት ንጹሕ ሆና ከተወለደች እርሷ መሞትና በደሟ መንጻት አይቻለንም ነበር? ማርያም ቤዛ አይደለችም። የሁሉ ቤዛም፥ የአንድ ሰው ቤዛም አይደለችም። ቤዛ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። ማርያምን ቤዛ ወይም የሁሉ ቤዛ (ቤዛዊተ ኵሉ) ማድረግ ክርስቶስን መጋረድ ነው። ይህ ደግሞ የሰይጣን ተቀዳሚ ተግባር ነው። ሰይጣን ሰዎች ክርስቶስን እንዳያዩ፥ እንዳያውቁ፥ እንዳይቀበሉ፥ እንዳይድኑ ማድረግ ግቡ ነው።

## እመብርሃንስ ናት?

ይህም አሳብ እመ አምላክ የሚለው ጋር ተቀራራቢ ነው። ጌታ የዓለም ብርሃን መሆኑን ተናግሮአልና (ዮሐ. 8፥12 እና 9፥5) የእርሱ እናት መሆኗን ገላጭ ይመስላል። ግን እግዚአብሔር የብርሃናት አባት እንደተባለ እርሷም የብርሃን እናት ስትባል ከማን ጋር እየተስተያየችና እየተካከለች መሆኗን እናስተውል። *በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።* ያዕ. 1፥17። እግዚአብሔር የብርሃናት አባት ከሆነና ማርያም የብርሃን እናት ከተባለች እኩያነቱ ምን እየተደረገ ነው?

ማርያም ሌላው ሁሉ ማዕረግ ባይሰጣትና የጌታችን እናት ወይም የኢየሱስ እናት ብቻ ብትባል ምንም የሚጎድልባት ነገር የለም። ፈጽሞ የለም። ወ/ሮ የሺመቤትን እንደ ምሳሌ እንውሰድ። ወ/ሮ የሺመቤት የተሰማ ወይም የአሸብር እናት ሊሆኑም ይችላሉ። የራስ ተፈሪ ወይም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እናትም ወይዘሮ የሺመቤት ናቸው። እኚህ ሴት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ እናት ቢባሉ ወይም በኖሩበትና ተፈሪ መኮንንን በወለዱበት የኤጀርሳ ጎሮ ቋንቋ ሃ'ራ ታፋሪ ቢባሉ በሰውነታቸው፥ በቁመናቸው፥ በማንነታቸው ላይ የሚፈጥረው ምንም ለውጥ የለውም።

ይህ አጠራር የስያሜ ጉዳይ ብቻ ነው ሊባል ይቻላል። ጉዳዩ ግን ልክ እንደ ስዕሎቹ ከዚያም ያለፈ ሊሆንም ይችላል። የማርያምንና የኢየሱስን የተለመዱትን ስዕሎች አይተናል? የማርያም ስዕል በኦርቶዶክስም በካቶሊክም ሁሌም ሙሉ፥ ቆንጆ፥ ጠንካራ፥ ትልቅ፥ ወዘተ፥ ሆኖ ከኢየሱስ ጋር አብረው ባሉባቸው ስዕሎች ሁሉ ደግሞ ኢየሱስ ደካማ፥ ትንሽ፥ ሕጻን ወይም ከእርሷ ያነሰ ሆነው ይሳላሉ። ብዙዎቹ የማርያም ተከታዮች ኢየሱስ ዛሬም ሕጻንና በጉያዋ ያለ መስሎ ይሳልባቸዋል። ታሪኩን የማያውቁት አሁንም በእቅፍ ያለ ልጅ ብቻ ይመስላቸዋል። ስያሜም እይታንም ሊያዛባ ይችላል።

## ከሙን ማርያም ዐርጋለች?

ከላይ በአጭር እንደቃኘነው በካቶሊክ አስተምህሮ በ1950 የተቀነነው ቀኖና እንደሚነግረን የምድር ኑሮዋ ዘመን ሲፈጸም ሳትሞት እንደ ሔኖክ ወደ ሰማይ ማረጓ ነው የተጻፈው። ስታርግ ደግሞ ሲያልን አራቁታ ነው የሄደችው። በኦርቶዶክስ ደግሞ በ64 ዓመቷ ሞታ ተቀብራ በ3ኛው ቀን ተነሥታ ማረጓ ተጽፎአል። በኦርቶዶክስ ይህን የሚመለከተው ተአምር በተአምረ ማርያም የተጻፈው (ተአምር 3 እና ተአምር 6) እርስ በርስ ይቃረናል። ተአምር 3 አይሁድ ሐዋርያቱ ሊቀብሩአት ሲወስዱአት ሬሳዋን ሊያቃጥሉ ሲደርሱባቸው ትተዋት መሸሻቸውንና ገብርኤል ከዮሐንስ ጋር ሥጋዋን ከሕይወት ዛፍ በታች አኑረው ነፍሷ ማረጓ ተጽፎአል። የሕይወት ዛፍ በምድር ይሁን ከምድር ውጭ አልተነገረም። በተአምር 6 ደግሞ አልሸሹም፤ አልጣሏትም፤ አልቅሰው፥ እጅ ነስተው በጌቴሴማኔ ቀበሩአት እንጂ ይላል። የቱ ይሆን ትክክል? ይህ ከሺህ 500 ዓመታት ያህል በኋላ የተደረሰ ድርሰት ነውና የቱም ትክክል አይደለም። መጽሐፉ (ተአምረ ማርያም) ልብ ወለድ መሆኑ በግልጽ ይታያል፤ የልብ ወለድ መጽሐፍ መለኪያዎችንም ያሟላል። ይህንን በሌላ ክፍል በስፋት እናየዋለን።

ሰዎች ልብ ወለድ ጽሑፎችን እንደ እውነት የሚቀበሉበት ዘመን ላይ እንገኛለን። በ1990ዎቹ የዳን ብራውን The DaVinci Code መጽሐፍ በወጣ ጊዜ የፈጠራ ጽሑፎችን ማንበብ ስለምወድድ አንድ የመጻሕፍት መሸጫ ሱቅ ሳለሁ አንሥቼ በችኮላ ቃኘሁት። ኢየሱስን ገጸ ባህርይ ያደረገ ልብ ወለድ መሆኑ ስላልሳበኝ ተውኩት። ከ10 ዓመታት በኋላ ሰዎች ወድደውት፥ መውደድ ብቻ አይደለም ግርር ብለው ከኋላው ሄደውለት፥ ትልቅ ሲኒማ ሆኖ ተሠርቶ፥ እንደ እውነት ተደርጎ ተቀብለውት፥ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ደብቃ ያኖረችው ምስጢር አፈትልኮ እንደወጣ፥ ኢየሱስ ሚስት እንደነበረችው፥ ልጆች እንደነበሩት፥ ዝርያዎቹ አሁንም በአውሮጳ መኖራቸው እውነት መሆኑ ሲነገርና ያነበቡትና ያዩት በደም ፍላት

ሲከራከሩ ታዝቤ መጽሐፉን አነበብኩት። ሳነብበውም አሁንም ያው ልብ ወለድ ነው። ግን እውነትን ለማወቅ ያልወደዱ ሰዎች፥ እውነትን የተቀሙ ሰዎች ሐሰትን እውነት ብለው ይቀበላሉና እንደዚያ የተቀበሉት መጽሐፍ ነው።

ተአምረ ማርያም ዕርገቷን (በተአምር 7) ከእጸ ሕይወት ስር አሰነሥቶ እንዳሳረገው ስለሚናገር አሁንም ግጭት አለበት። የተነሣችው ከጌቴሴማኔ ካልሆነ የተቀበረችው ጌቴሴማኔ አይደለምና ይህም ውስብስብ ሊፈቱት ያስፈልጋል። በእውነቱ ይህ የሚፈታ ልቃቂት ሳይሆን ሊቀበሉት ሳይሆን ሊጠየፉት የተገባ መድኃኒታችንን፥ ቤዛችንን፥ ጌታችንን ለመሸፈን የተፈጠረ እኩይ ሥራ ነው። ለማርያም የሚሰጣትን የቆየውንም ዘመናዊውንም አድናቆተ ማርያም ወደ አምልኮተ ማርያም የቀየረ ሥራ ነው። በተአምር ተጸንሳ፥ በተአምራት የተንቆጠቆጠ ኑሮ ኖራ፥ በቤዛነት ሞታ፥ በክብር ካረገች ከጌታ ክርስቶስ ምን አነሰች? ይህ ለማርያም የተሰጠ ስፍራ ከአክብሮት ያለፈ አክብሮት በመሆኑ የጣዖት አምልኮ ነው። የእግዚአብሔር ክብር ከእርሱ ተቀንሶ ለማንም ሊሰጥ የተገባ አይደለም።

ከክርስቶስ በቀር በትንሣኤ አካል በክብር ያረገ ማንም የለም። ማርያም እንዲህ በመሰለ ክብርና በትንሣኤ አካል ዐርጋ ኖሮ ቢሆን አዲስ ኪዳን እንደምን አልጻፈውም? ይህ እኮ በዓይነቱም በክብሩም ከክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት ጋር አንድ ዓይነት ነውና ሳይጽፉት ሊቀር ወይም ሊረሱት፥ ሊዘነጉት የተገባ አይደለም። ግን አልተጻፈም። ለምን? አዲስ ኪዳን ወይም ወንጌሉ ስለ ኢየሱስ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን እንዲህ ያለው ነገር ባለመፈጸሙም ነው።

## ቃሉን የአለማወቅ እና እንደይታወቅ የማድረግ ጉዳት

አማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለው ትውውቅ በጣም ትንሽ ወይም ምንም ነው። ይህ እውነት ነው። እኔ ከሕጻንነቴ እስከ ወጣትነቴ በኢኦተቤክ ሳድግ፥ ሳስቀድስ፥ ስቆርብ፥ ስጾም፥ ሳከፍል፥ ወዘተ፥ መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ሲነገር ሰምቼ አላውቅም ነበር። የነፍስ አባታችን ወይም የክርስትና አባቴ የሆኑት መሪጌታ ሲመጡ መጽሐፍ ቅዱስ አንብበውልንም አያውቁም፤ ይዘውም መጥተው አይመጡም። አሁን ሳስበው መጽሐፍ ያላቸውም አይመስለኝም። አባቴና የአባቴ ጓደኞች ሲያነብቡ ወይም ሲነጋገሩ እሰማ የነበረው ስለ ፍካሬ ኢየሱስ፥ ውዳሴ ማርያም እና ዘሰኔ ጎልጎታ ነው። ኋላ ካደግሁ በኋላ ፍካሬ ኢየሱስን ሳነብበው ጥቂት ከራእያዊ መጻሕፍት የተወሰዱና በውስጡ የተበተኑ ጥቂት ጥቅሶች አሉበት። በአብዛኛው ምእመናን እጅ የሚገኙት እንዲህ ያሉት በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የታተሙ መጻሕፍት ናቸው። እነዚህን መጻሕፍት ብንመረምር አንባቢዎቹ

በሚገናቸው ቋንቋ የተጻፉትም ጥቂት ናቸው። በሚገባቸው በቋንቋቸው የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውና ያንን የሚያነብቡ ዛሬም እጅግ ጥቂት ናቸው።

ከዚህ በፊት በሴሚነሪ ስማር ሳለሁ ለአንድ ጥናት ዝግጅት በናሙና እየተወሰዱ ከተጠየቁ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ያገኘሁት አኀዝ የሚከተለውን ይመስላል። ቁጥሩን በትክክል ባላስታውስም 3/4ኛ እና 1/4ኛ ልዩነት ነበረው። ከ3/4ኛ በላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሌላቸው ናቸው። ከእነዚህ ከፊሉ ሌሎች ድርሳናት እና መልክአዎችን የሚያነብቡ ሲሆኑ ከፊሉ ምንም የማያነብቡና ቅዳሴና ንባብ (በማያውቁት በግዕዝ ቋንቋም ቢሆን) ብቻ የሚሰሙ ናቸው። ከቀሩት ሩብ ያህል ውስጥ ደግሞ ገሚሱ መጽሐፍ ቅዱስ ኖሮአቸው ግን የማያነብቡ ወይም አንብበው የማያውቁ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ቅዠት እንዲያርቅላቸው ተንተርሰው የሚተኙም ይገኙበታል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብቡ ወይም በሚገባቸው ቋንቋ የሚሰሙ እጅግ በጣም ጥቂት ሆነው አግኝቼአለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስን ሰዎች በቋንቋቸው እንዲያነብቡ በማበረታታት ፈንታ ቤተ ክህነት ስታዳፍን ኖራለች። ምናልባት ሰዎች በሚገባቸው፥ በሚያውቁት ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነብቡ ቢበረታቱ እውነቱን ከተረቱ ለይተው እንዲያውቁ ስለሚረዳቸው ያ እንዳይሆን የተደረገ አሠራር ሊሆን ይችላል። ወይም ቃሉን ማንበብ፥ መፍታትና ማስተማር የጥቂት የተወሰኑ ሊቃውንት ብቻ ተግባርና ኃላፊነት ሆኖ ስለሚታይም ስለሆነ ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያውም ለተርታው አማኝ በሚናገሩበት ቋንቋ እንዳይታተም ቀዳሚ ተፋላሚ ቤተ ክርስቲያን ሆና የኖረችባቸው ዘመናትም አሉ። ይህንን ለመረዳት የእንግሊዝኛውንና የአማርኛውን መጽሐፍ ቅዱስ ጅማሬ ታሪክ በትንሹ ለማሳየት ልሞክር።

ይህ ጉዳይ ከመጽሐፉ አሳብ የወጣና ከነገረ ማርያም ጋር ምንም ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው ቢሆንም የተሳሳቱና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ትምህርቶችን በገፍ እንድንቀበል የሚያደርጉን ቅዱስ ቃሉ ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የተፋታን ሆነን ስንገኝ ነው። ቃሉ ሰዎች በሚረዱበት ቋንቋ እንዳይኖር ሲደረግ መንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እንዲቆዩ ተደርገዋል፤ ለጨለማም ተዳርገዋል ወይም አልፈው ተሰጥተዋል ማለት ነው። በቋንቋችን ለምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ አድናቆት እንዲኖረን የተገባ ስለሆነ ነው ይህንን ንዑስ ክፍል የማካፍለው።

በአውሮጳ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እንግሊዝኛና ወደ ጀርመን ቋንቋዎች እንዳይታተም ቀዳሚዎቹ ከልካዮችና ተከላካዮች ካህናትና ቀሳውስት ነበሩ። በዚያው ሕዝቡ በማይገባውና ሊረድዳው በማይችለው በላቲን ቋንቋ ብቻ እንዲነበብ ግዴታ ሆኖ ለብዙ መቶ ዓመታት ቆይቶአል። በአገራችንም ከዚህ ያልተለየ ነበር። የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይተረጎምና በእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት

በ1810ዎቹና 1820ዎቹ የታተመውም ገብቶ እንዳይሰራጭ ግንባር ቀደም ተፋላሚ ቤተ ክህነት መሆኗ ራሱን የቻለ ታሪክ ነው።

በአገራችን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ አገሮችም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሕዝባዊ ቋንቋ እንዲተረጎም የጣሩት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይልቅ ተርታ ክርስቲያኖችና የወንጌል መልእክተኞች መሆናቸው እውነት ነው። ማድረግ የነበረባት ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ኋላ ነገሩ ተለውጦ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ተመሥርቶ አብያተ ክርስቲያናት ተሳታፊ በመሆን በተለያዩ የሕዝብ ቋንቋዎች ቃሉ መትተርጎሙ እውነት ነው። በቀዳሚ ታሪካችን ግን እንዲህ አልነበረም። የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በሕዝብ ቋንቋ ከቶም እንዳይኖር ብቻ ሳይሆን ሲኖርም እንዲጠፋ፥ ካልሆነም እንዳይሰራጭ እንቅፋት የሚሆኑት የነባሯ ቤተ ክርስቲያን ካህናት መሆናቸው ያስደነግጣል። በአገራችን የመጀመሪያው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በውጪ ተተርጉሞ ከታተመም በኋላ ወደ አገር እንዳይገባና እንዳይሰራጭ ቤተ ክህነት እንቅፋት መሆኗ ወደ ጎን መተው የሌለበትና ትምህርት ልንቀስምበት የተገባ ታሪክ ነው። ይህ በአገራችንም በሌሎች አገሮችም፥ በተለይም በአውሮጳ በመካከለኛው ዘመን የታየ እውነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጠባቂ መሆን የተገባቸው የመጽሐፉ ጠላቶች ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲፈልቁ መቼም ያሳዝናል።

ወደ እንግሊዝኛው የመጀመሪያ ትርጉም ታሪክ ስንሄድ፥ እጅግ ልቀው የሚታወቁት ሁለት ቀዳሚ ትርጉሞች የዊክሊፍ እና የሚልያም ቲንዴል ትርጉሞች ናቸው። ሦስተኛውና ኋላ በ1611 የተተረጎመው ይፋ የእንግሊዝኛ ትርጉም (ኪንግ ጄምስ ቨርዥን የሚባለው) 80% ያህሉ የወሰደው ከዊልያም ቲንዴል ትርጉም ነው። ቀድሞ ጥቂት ቁርጥራጭ ምንባባት በእንግሊዝኛ የእጅ ጽሑፋት ቢኖሩም ቀዳሚውን የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሕዝቡ ቋንቋ የተረጎመው ጆን ዊክሊፍ ነው። ከዊክሊፍ ቀጥሎ የተረጎመው ደግሞ የዊልያም ቲንዴል ትርጉም ነው። ቲንዴል ይህን ማድረጉ፥ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ሰፊው ሕዝብ በሚጠቀምበት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መተርጎሙ ወንጀል ሆኖበት በቤተ ክርስቲያን ተወግዞ በ1536 በእሣት ተቃጥሎ ነበር የተገደለው። ቲንዴል በሚቃጠልበት እንጨት ተጠፍሮ ታንቆና በእሳት ተቃጥሎ በሚሞትበት ጊዜ ድምጹን ከፍ አድርጎ በጩኸት የጸለየው ቃል፥ "እግዚአብሔር ሆይ፥ የእንግሊዝን ንጉሥ ዐይኖች ክፈት" ብሎ ነበር። ጸሎቱ ተሰምቶ ነበር። መቶ ዓመት ሳይሞላ 'ኪንግ ጄምስ ቨርዥን' የሚባለውን ትርጉም የእንግሊዝ ንጉሥ ራሱ አስተባብሮ አስተረጎመ።

አስተርጓሚው ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ንጉሥ ጄምስ ነበር! ቀድሞ ሰባ ሊቃናት የተባለውን የብሉይ ኪዳን የግሪክ ትርጉም ያስተረጎመው የግብጹ ንጉሥ የነበረው ግሪካዊው በጥሊሞስ ፍላደልፍ ነበር። አይሁድ ለሕዝቡ ቃሉ እንዲደርስ ብለው

የተረጎሙት ሳይሆን አሕዛብ የሆነ በእስራኤል አምላክም ያላመነ ንጉሥ! እዚህ አገራችን በኛም ታሪክ ቃሉ ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ያደረጉት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩ። ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን የአገር ንጉሥ! ይደንቃል።

ጆን ዊክሊፍ ቄስ ያይደለ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፥ ሰባኪና ተርጓሚ ነበረ። ሎላርድ ተብለው ከተጠሩ ጋር አብረው ሆነው ክህነትን የሚቃወምና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ የሚያተኩር ስብከት ይሰብኩ ነበር። በዘመኑ ካህናት መንፈሳውያን የቃሉ ሰባኪዎች ሳይሆኑ ዓለማውያንና በምድራዊ ብልጽግና የሰከሩ ከበርቴዎች ነበሩ። የሎላርዶች ስብከት የቃሉ ሰባኪ አገልጋዮች ከምድራዊ ብልጽግና የተለዩ ይሁኑ፥ የሰማያዊው መንግሥት አዋጅ ነጋሪዎች ይሁኑ የሚልም ነበር። ሎላርድ ማለት የስድብ ስም ሆኖ ያልተማረ፥ ቢማርም በእንግሊዝኛ ብቻ የተማረ፥ ላቲንን የማያውቅ ማለት ነው። ይህ ስብከታቸው እና 'ቃሉ በሕዝብ ቋንቋ መተርጎም አለበት' የሚለውን በዘመኑ ይናኝ የነበረ አሳብ ይደግፉና ያሰራጩም ስለነበር በሮማዋ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደ ከሐዲ ተቆጥረው ተሰደዱ።

የፕሮቴስታንት ንቅናቄ ጥንስስ ይህ የዊክሊፍ እና የሎላርዶች ንቅናቄ መሆኑን ታሪክ ጸሐፍት ይናገራሉ። አራቱን ወንጌላትና ምናልባት ጠቅላላውን አዲስ ኪዳን የተረጎመው ራሱ ዊክሊፍ እንደሆነ ሲታመን እርሱ ይህን ሲሠራ ሳለ ረዳቶቹ ሎላርዶች ደግሞ ብሉይ ኪዳንን እንደተረጎሙ ይገመታል። መጽሐፍ ቅዱስን የተረዳ ሰው በመሆኑ በክህነት፥ በጵጵስናና በምኩስና ዙሪያ ያሉትን ስሕተቶች አውግዞ ያስተምር ነበርና በዘመኑ ሁሉ ጥቃት ሲሰነዘርበት ኖረ። ይህ ሰው ዊክሊፍ በ1384 መጨረሻ ሞተ። ሥራው ግን አልሞተም። ትርጉሞቹ ከመሞቱ ሁለት ዓመታት ቀደም ብለው ጀምሮ እስከ 1395 ድረስ እየተጻፉ ይወጡ ነበር። ያኔ ማተሚያ ገና ስላልታወቀ በእጅ ጽሑፍ ነበር ይጻፉ የነበሩት። ይህ የትርጉም ሥራ ወንጀልና ኃጢአት ሆኖበት እርሱን ብቻ ሳይሆን ሥራዎቹን ሁሉ ለማውገዝ ሲባል አጥንቱ ከተቀበረበት ተቆፍሮ ወጥቶ በዘመኑ ከሐዲዎች ተብለው የተፈረጁ እንደሚደረጉት እንዲቃጠል በሜይ ወር 1415 ተወሰነና አጽሙ ከተቀበረበት ከ30 ዓመታት በኋላ ወጥቶ እንዲጋይ ተደረገ። በዚያውም የዊክሊፍን ሥራ ያሰራጭ የነበረ ጃን ሃስ ክህነቱ ተገፍፎ እርሱም እንዲቃጠል ተፈረደበት። ይህን በግንባር ቀድማ ያደረገችውና ያስደረገችው ቤተ ክህነት ናት፤ አስፈጻሚዎቹም ካህናት ናቸው።

ይህ ዊክሊፍ አጥንቱ ከመቃብር ወጥቶ የተቃጠለው ከፕሮቴስታንት ንቅናቄ መቶ ዓመታት በፊት ሲሆን በዚያው የእርሱ አጥንት በተቃጠለበት ጊዜ በአገራችን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት እንመለስ የሚሉ ደቂቀ እስጢፋ የተባሉት ሰዎችም የተነሱበትና የከፋ ቅጣትን የተቀበሉበት ዘመንም ነበር። አንዱ መሠረታዊ ልዩነት ግን በአውሮጳ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ምድራዊውን መንግሥት የተቆጣጠረችበት ጊዜ

ሲሆን በዚያን ጊዜ በአገራችን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥትና በንጉሥ (በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ) መዳፍ ውስጥ የገባችበት ጊዜ መሆኑ ነው። እዚያ ቤተ ክርስቲያን መንግሥትን፥ እዚህ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን የተቆጣጠሩበት ዘመን ነበረ። ቤተ ክርስቲያን ቃሉ ለሕዝብ ጆሮ እንግዳ ሆኖ እንዲቀር ያደረገችውን ያህል ንጉሡም ይህንኑ አብዝቶ አደረገ እንጂ የተሻለ አልሠራም። በአገራችን ታሪክ አንዳንድ ንጉሦች መንፈሳዊነት ሲያይልባቸው፥ አንዳንዶች ቃሉ በእውነት ለሕዝብ በሕዝብ ቋንቋ መድረስ እንዳለበት ገብቶአቸው ይህ እንዲሆን ሲጥሩ፥ ሌሎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ራሷን የመግዣ መሣሪያ በማድረግ ጨለማ እንዲጠነክር መብራትን ሲያጠፉ ኖረዋል።

ወደ አማርኛው ትርጉም ስንመጣ፥ ጥቂት ቁርጥራጭ ምንባቦች በ16ኛው መቶ በሮም አገር መትተርጎማቸው ቢታወቅም የመጀመሪያው ሙሉ የአማርኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ እትም የ1879ኙ ነው። ዛሬ በብዙዎች እጅ የሚገኘው የ፲፱፻፶፩ ዓመተ ምሕረቱ ትርጉም ሁለተኛው የአማርኛ ትርጉም ነው። የዚህኛው አስጀማሪ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ዐሼ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ተፈሪ በነበሩበት ጊዜ ነበር። ሥራው በጣሊያን ጊዜ ተቋርጦ፥ እንደገና ቀጥሎ ያስጨረሱትም ራሳቸው ናቸው። ይህ ለነባሯ ቤተ ክርስቲያን አንገት የሚያስደፋ ታሪክ ነው።

እንዲያውም ማስተርጎምና ማሳተም የተገባት ቤተ ክህነት ወደ አማርኛ የተተረጎመው የመጀመሪያው የአባ ሮሜ ወይም አቡ ሩሚ ትርጉም የተባለው የ1879 ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሶች እትም ወደ አንባቢ እጅ እንዳይደርሱ ከአቡንና ከእጨጌ እስከ ካህናት ድረስ ቤተ ክህነት ተጻራሪ ሆና መቆየቷን የመጀመሪያውን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ያሳተመው የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዘገባዎች ያመለክታሉ። እነዚህ ዓመታዊ ዘገባዎች የታሪክ ብልጽግናን የተጎናጸፉ ዘገባዎች ናቸው። እዚህ ጥቂት ላውሳ።

በ20ኛው የChurch Missionary Society for Africa ጉባኤ ዘገባ የመጀመሪያውን የአቡ ሩሚን (አባ ሮሜ) የአማርኛ ቅጅና ግዢ በተመለከተ ስለ ሚስተር ጆዌት ሁኔታ ካተተ በኋላ (ዊልያም ጆዌት ከ9500 ገጾች በላይ የሆነውን ሙሉ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከአስተርጓሚው በ1250 ፓውንድ ግዢውን ያከናወነው ሰው ነው) እንዲህ ይላል፤

> ". . . ካለፈው ዘገባ እንደሚስተዋለው የግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ በአበሻ ቀሳውስት ላይ ትልቅ የለውጥ ኃይል ምናልባት መፍጠር ቢችልም በአገሪቱ ቋንቋ ማዘጋጀትና ማሰራጨት በሕዝቡ ላይ ብርሃን እንደሚፈነጥቅ መታወቅ አለበት። እንደሚታየው አማርኛና ትግርኛ የሚባሉ ሁለት ትልልቅ ቋንቋዎች አሉ። ሚስተር ጆዌት በአባይ ጉዞው ቋንቋውን የሚያውቀውን ሚስተር ፒርስን ማግኘቱ ይህን ሰው በትርጉሙ ተሳታፊ አድርጎታል። የማርቆስ ወንጌል ቀድሞውኑ በአማርኛና በትግርኛ ተተርጉሞአል።

ከዚህ በፊት የተነገረለት የአማርኛ ትርጉም በካይሮ በሚገኘው የፈረንሳይ ቆንስል ገጾች ወደ ኤሮጵ ቢላኩም ወዳልተላከላቸው ሰዎች እጅ በስሕተት ገብቷል። ሥራው አሰሊንን 10 ዓመታት ወጥሮት ቆይቷል። እየተሠራ ያለው በአሰሊን ስር ሆኖ በ[ኢትዮጵያዊ]ዜጋ ነው። በትርጉሙ የዕብራይስጡ ጽሑፍ ከሰብትዋጅንት ዐረብኛ እና ሶርያ ትርጓሜዎች ጋር እና ማብራሪያዎች ጨምረው እየተጠቀሙ ነው። . . . ይህ ትርጉም አሁን ተጠናቅቆአል። ቋንቋው አማርኛ ሲሆን በጎንደር ካለው የመንግሥት ቋንቋ አንድ ሆኖ በአበሻ ፊደል የተጻፈ ነው። . . . የብሪታንያና የውጪ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የማልታ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን ሚስተር ጆዌትን ወኪል አድርጎ ግዢውን እንዲፈጽም በጠየቀው መሠረት ሚስተር ጆዌት የትርጉሙን ጽሑፍ ሊገዛና ለሕትመት ሊያመጣ ወደ ግብጽ ሊሄድ ይዘጋጃል"[6]

አባ ሮሜ በአውሮጳ የሚታወቁት Abu Rumi Habessinus ተሰኝተው ነው። አበሻው አቡ ሩሚ ማለት ነው። የአማርኛ ትርጉም ሥራውን የጀመሩት አስቀድመው አቅደውና አልመው ሳይሆን ከካይሮው የፈረንሳይ ቆንስል 'አጋጣሚ' አገናኝቶአቸው ነው። አቡ ሩሚ አባይን ወንዝ ምንጭ ፍለጋን ያካሄደው የጄምስ ብሩስ አገር አመልካች [እና አማርኛ አስተማሪ] ነበሩ። የጉዞ ፍቅር ያደረባቸው ከዚህ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። ግብጽን፥ ሶርያን፥ ኢየሩሳሌምን ሕንድን ተጉዘው አይተዋል።

በካይሮ አቋርጠው ሲያልፉ ድንገት በጠና ታመሙ። አቡ ሩሚ በዚህን ጊዜ የ45 ወይም የ50 ዓመት ዕድሜ ሰው ናቸው። ይኸኔ ነው አሰሊን የተባለው ፈረንሳዊ ቆንስላ ያገኛቸውና ወስዶ ያስታመማቸው። በዚህ ዘመን (1800ዎቹ መጀመሪያ) የአውሮጳ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዓይነተኛ ባህርይ ወንጌልን በዓለም ማዳረስና ቃሉን በሰሚዎች ቋንቋ መተርጎም ነበር። አሰሊንም የዚህ ተጋሪ የነበረ ሰውና የቃሉ አጥኚ ነበረ። እያስታመማቸውና እያገገሙ ሳሉ አሰሊን ያስተዋለው የሰውየውን የቋንቋ ሊቅነት ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን ለመመለስ ብዙ ተጥሮ አለመሳካቱና አሁን ደግሞ ይህ ዕድል በድንገት የመገኘቱን ሁኔታ በተመለከተ አሰሊን እንዲህ ይገልጠዋል፤ "ይህንን ምስኪን ሽማግሌ ባገኘሁ ጊዜ የተደነቅሁትን መደነቅ ተመልከቱ፤ ይህ ሰው የአገሩ ስነ ጽሑፍ ሊቅ ነው፤ ደግሞም እስከ እስያ ሩቅ ድረስ ዘልቆ የሄደ ተጓዥና የ[ጄምስ] ብሩስ እና የሰር ዊልያም ጆንስ አስተማሪም ነው።"[7] ይህን ያነበብኩበት መጽሐፍ ስለ አቡ ሩሚና ስለ ትርጉም ሥራው እንዲህ ይላል፥

---

[6] Proceedings of the Church Mission Society for Africa and the East, Twentieth Year (1819-1820), pp, 111-113.

[7] Bagster, Samuel, p. 49. ይህ የሳሙኤል ባግስተር መጽሐፍ በ1848 የታተመና በዚያን ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች የተመለሱባቸው ታሪኮች ጥርቅም ነው። ከአማርኛው ጋር የትግረና የትግሪኛ ትርጉሞች ታሪክም አብሮ ተጽፎአል።

> አቡ ሩሚ ከራሱ ቋንቋ በተጨማሪ የግሪክ፥ የዐረብ እና የፋርስ ቋንቋን በማወቁ ለዚህ ትርጉም በጣሙን ብቁ የሆነ ሰው ነው። በቋንቋው መተርጎሙን በአሰሊን መሪነት ወዲያው ተያያዘው። ለአስር ዓመታት በሳምንት ሁለት ቀን ከምንም ሌላ ተግባር ተነጥለው ትርጉሙ የተሠራበትን የዐረብኛውን መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ ጀመሩ። ዐረብኛው ግልጽ ያልሆነባቸውን ቃላት አሰሊን ከምንጩ ቋንቋ፥ ከሶርያ ትርጉም፥ ከሰብትዋጅንት እና ከተላያዩ መዛግብተ ቃላት ይፈታ ነበር። ደግሞም አቡ ሩሚ የሚጠቀምበት የግእዝ ቋንቋ ራሱ ጥሩ መክፈቻ ነበረ። በሥራው የመጀመሪያ ዓመታት አሰሊን በዚህ ሽማግሌ ጓደኛው ትእግሥት በጣም ይደነቅ ነበር። በኋላ ግን እየተረጎሙ ወደ ጳውሎስ መልእክቶች ሲደርሱ የአቡ ሩሚ ፍላጎት መቀዝቀዝ ጀመረ። ይህም የሆነው የሥራው ከባድነት ስላስፈራው ነው። ወደ ኢየሩሳሌምም መሄድ ተመኘ። ይህ ሥራ [ሊያልቅ ተገባድዶ ግን] በጅምር እንዳይቀር ብዙ ጊዜ በወሰደ ልመናና መስዋዕት አሳመነውና ሥራው ቀጠለ። ይህ ሥራ እንደተጠናቀቀ የሆነውን ከዚህ ጋር አያይዞ መናገር አላስፈላጊ አይመስለኝም። ይህ ምስኪን ሰው የትርጉም ሥራው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የተወደደ ምኞቱን ሊፈጽም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ። እንደደረሰ ግን በወረርሽኙ ምክንያት ሞተ።[8]

አቡ ሩሚ ሥራቸውን በወግ አጠናቀቁና በኢየሩሳሌም በ1819 ሞቱ። ከላይ እንዳልኩትም የእንግሊዝ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሥራውን ከአሰሊን ገዝቶ የራሱ በማድረግ እንዲታተምና እንዲሰራጭ ሌላ ጥረት አድርጎአል። በ1820 ግዢው ተፈጽሞ በ1821 ወደ እንግሊዝ ከመጣ በኋላ አማርኛን በሚያውቁት የአገሩ ሰዎች ታይቶ በአድናቆት ጸደቀ። ትርጉሙን የፈተሸው ዶ/ር ሳሙኤል ሊ በ1822 ለመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴው ስለዚህ ሥራ ሲጽፍ፥ "ሥራው በልዩ ችሎታና በጥንቃቄ እንደተሠራ ይታያል፤ በብዙ የምሥራቅ ቋንቋዎች እንደሚታየው ያለ ለአንድ ቃል ብዙ ቃላትን በመጠቀም የመራቀቅ ሊቅነትን ማሳየት በተርጓሚው አልታየም፤ ነገር ግን የተመጠነ፥ ቀላል እና ጤናማ ነው።[9] እንደ ናሙና ሆኖ በስፍራው የተቀመጠው ዮሐ. 1፥1-14 እውነትም ይህ ትርጉም 'የተመጠነ፥ ቀላል እና ጤናማ' (precise, easy and natural) እንደሆነ ያሳያል።

የአማርኛ (የግእዝ) ፊደላት ተቀርጸው በ1824 ዶ/ር ሊ፥ ሚስተር ጆዌት እና በጊዜው ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበሩ ጋር እየሠራ የነበረው የምሥራቃውያን ጥናቶች ሊቅ ሚስተር ቶማስ ፔል ፐላት ፈትሸውት ወንጌላት ታተሙ። በ1829 ደግሞ አዲስ ኪዳን፥ በ1840 ብሉይ ኪዳን ታተሙ። በ1842 ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ ታተመ። ከዚህ ሙሉ እትም ቀጥሎ የታተመው እስከ ቅርብ ጊዜ እየተሰራጨ የዘለቀው የ1879 እትም የሚባለው ነው።

---

[8] እላይ የተጠቀሰው።

[9] እላይ የተጠቀሰው።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ሚስዮናውያን ወንጌልን ለማሮጥ ይለፉና የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስን ለማሰራጨት ይተጉ በነበረ ጊዜ ካህናትና ሊቃውንት ይህንን ጥረት ይጋፉ እንደነበር በዘመኑ የተጻፈ የመጽሔቶች መድብል እንዲህ ይገልጣል። ሳሙኤል ጎባት በኢየሩሳሌም በቅስና ሲያገለግል ሳለ ከኢትዮጵያ የሄደው ሚስተር ፍላድ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበሩት ሚስዮናውያን ሁኔታ ሳሙኤል ጠይቆት ሲመልስለት ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ሳይደብቅ ከነገረው በኋላ ደስ የሚያሰኘውንም እርምጃ ሲያካፍለው እንዲህ ይላል፤

> ከኢየሩሳሌሙ የአንግሊካኑ ቄስ ከዶ/ር ሳሙኤል ጎባት ዘንድ ጥቂት ሰዎች በመቶ የሚቆጠሩ ለአበሾች የሚታደሉ መጽሐፍ ቅዱሶች ይዘው እንደመጡ ንጉሡ በሰማ ጊዜ ወዲያውኑ የደንብራ [ደንቢያ?] እና ጭልጋ አገረ ገዦችን ከንብረታቸው ሁሉ ጋር ይዘዋቸው እንዲመጡ አዘዘ። ከንጉሡ፥ ከአቡኑ እና ከብዙ ቀሳውስት ጋር ከተነጋገርኩት እንደተገነዘብኩት አቡኑ፥ እጨጌው (የመነኮሳቱ አለቃ) እና ካህናቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይሰራጭ ይፈልጋሉ። ለብዙዎቹ እንዲያውም የእግዚአብሔር ቃል ሕዝብ በሚረዳው ቋንቋ መተርጎሙ የሚያስገርም ነገር ነው የሆነባቸው። ስለዚህ [ትርጉም] ብዙዎች በንቀት ቃል እየተናገሩ የቤተ ክህነቱን ግእዝ የሚባለውን የኢትዮጵኛ ቋንቋ እያከበሩ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ከብዙ መቶ ካህናት ቋንቋውን [ግእዝን] የሚያውቁ አምስት እንኳ ማግኘት ይቸግራል። አቡኑ አንድ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ በስጦታ ለመቀበል እንቢ ብሏል። ንጉሡ ግን የተለየ ነው። ምንም እንኳ በሙያው ወታደር ቢሆንም ከቀሳውስቱ ይልቅ ብሩህ ሰው ነው። መጽሐፍ ቅዱሶችንና [አዲስ] ኪዳኖችን ገጸ በረከት አድርገን አቀረብንለት። ከነዚህ መካከል አራት የግእዝ ዝቅጅዎችም ነበሩበት። ንጉሡ እነዚህን [አራቱን] ወደ ጎን ወረወረና፥ 'ማንም ሊረዳቸው የማይችላቸውን እነዚህን መጻሕፍት ለምን አመጣችሁ? ምን ይጠቅማሉ? የአማርኛዎቹ በጣም ይሻላሉ፤ ሁሉ ሊረዳቸው ይችላልና' አለ።[10]

ይህ ጽሑፍ በመቀጠል መጽሐፍ ቅዱስ በመሪዎች፥ በምእመናን፥ በፈላሾች እና በካህናቱም ላይ ስለፈጠረው ተጋቦት እያብራራ የሁለትና የሦስት ቀን የእግር መንገድ ተጉዘው መጽሐፍ ቅዱስ ለመለመንን ስለሚመጡ ሰዎችም ይናገራል። ስለፈጠረው ለውጥም እንዲህ ይላል፥

> . . . ቀድሞ ይጠየፉት የነበሩት ካህናት አሁን አማርኛውን ካነበቡት በኋላ ከግእዙ ይልቅ ይህንን ወደውታል። ንጉሡም የየዕለቱን መዝሙረ ዳዊት እና የጸሎት ምንባቡን የሚያነብበው በአማርኛ ሆኗል። ስለዚህ፥ 'የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በአበሻ አገር ማሰራጨት ድካም ነው፤ ተነባቢ አይደለም፤ ካህናቱ አይፈልጉትም' አትበሉ። ምናልባት ለጊዜው ውጤታማ አይሆን ይሆናል። በጊዜው ግን ቃሉ በኢሳ. 55፥10-11 እንደተጻፈው የተላከበትን ዓላማ ይፈጽማል። . . . የንጉሡ ንስሐ አባት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ተሐድሶ

[10] The Church of England Magazine, Vol. 45 July-December 1858. pp. 316-318.

ለማድረግ ይመኛል። በየማክሰኞውና በየእሑዱ ከብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ለሕዝቡ በሚገባው ቋንቋ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲነበብ አስቦአል። ጸሎቱም እንኳ በአማርኛ እንዲደረግ ምኞት አለው። መልካም አሳቡ ይፈጸም ዘንድና የኢትዮጵያ ጨለማ በብርሃን እንዲተካ ሐሰተኛ መድኅኖቻቸውና ጣዖቶቻቸውም በራሳቸው ቋንቋ በሚያነብቡት በእውነተኛው ብርሃን መጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት እንዲወገዱ እግዚአብሔር ንጉሡን በመንፈሱ ይቀባው። እውነተኛው የወንጌል መልእክተኛ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው። ለአበሾች መጽሐፍ ቅዱሶችን ማቅረብ ብዙ የወንጌል መልእክተኞች ከመላክ የተሻለ ሥራ ይሠራል። ነፍሳትን እናጭዳለንና የእግዚአብሔርን ቃል እንዝራ።[11]

መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ስለሚፈጥረው ዘላለማዊ ለውጥ ከአውሮጳውያን ሰዎችም፥ ከላይ በዐፄ ኃይለ ሥላሴም ጥረት እንደተመለከትነው ከካህናቱ ይልቅ ነገሥታቱ ሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱስን በገዛ ቋንቋው እንዲያውቅ መጣራቸው አስመስጋኝ ጥረት ነው። ጥረቱ ከሌላው አቅጣጫ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወንጌል ከሰዎች ሕይወት አልፎ የአገሪቱንም መልክ በለወጠ ነበር። የአቡ ሩሚ የአማርኛ ትርጉም ትልቅ ለውጥ በአገሪቱ ክርስትና ላይ መፍጠሩ የታወቀ ነው። ጠቅላላውን ውጤትና ፍሬ የሚያውቀው የቃሉ ባለቤት የሆነው ጌታ ብቻ ሲሆን ከተተረኩልን አንዱ ቃሉን በማጥናትና በቅድስና ለመኖር በመጣር የነበሩ ጥቂት መነኮሳት በሐማሴን በጸዓዘጋ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ተደብቆ የኖረውን የአቡ ሩሚን የ1940 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም ባገኙ ጊዜ መንፈሳዊ ጥማታቸው እንደጨመረና ለነፍሳቸው ጥያቄም መልስ ማግኘታቸው ነው። ይህ መቃቃት በኋላ ለኤርትራ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን፥ ኋላም የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ የተጀመረችበት ጅማሬ ነው።

የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስን ጅማሬ የጻፈው ጉስታቭ አሬን ስለዚህ አጀማመር ታሪክ ሲጽፍ፥ እንዲህ ብሎአል፤ "ይህ በጸዓዘጋ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግድግዳ ሸንቁር በ1860ዎቹ መጀመሪያ የተገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ማንም መኖሩን ሳያውቅ ለብዙ ዓመታት በዚያ ኖሮ ይሆናል። ምናልባት ክራፕፍ ወይም ሙሌይሰን በግንቦት ወይም ሰኔ 1843 የChurch Missionary Society ከአገር ውስጥ ከመውጣቱ በፊት ካሰራጩት አንዱ ሳይሆንም አይቀርም። ምክንያቱም ፍላድ ለደጃዝማች ኃይሉ በግዛቱ እንዲያሰራጭ አራት የበቅሎ ጭነት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ከላከበት ከ1866 መጨረሻ በፊት በሐማሴን ምንም የ[አማርኛ] መጽሐፍ ቅዱስ እትም ኖሮ አያውቅም።"[12]

[11] እላይ እንደተጠቀሰው፤ ገጽ 318።

[12] Aren, Gustav, p. 184-5.

ከላይ የጻፍኩት ከነገረ ማርያም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው የመጽሐፍ ቅዱስ በሕዝባዊ ቋንቋ የመተርጎም አስፈላጊነት ነው። ቀጥተኛ ግንኙነት አይኑረው እንጂ ግንኙነት ግን አለው። ሰዎች ቃሉን ባወቁት መጠን ቃሉ ያልሆነውንም ያውቃሉ። ስለ ማርያም የተጻፈውን ካወቁ ያልተጻፈውንና የተፈጠረውንም ያውቃሉ። ሰዎች በቃሉ ውስጥ ባልተጻፉት ተረታ ተረቶች በቀላሉ የሚጠለፉት መጽሐፍ ቅዱስን ባለማወቅ ነው። ለምሳሌ፥ በ15ኛው መቶ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ስለ ማርያም፥ ስለ መስቀልና ስለ ስዕል ስግደት የተጻፉ መጻሕፍት እንደ እንጉዳይ እየበቀሉ በነበሩበት ጊዜ ቃሉን ያወቁ ሰዎች በእምነትና ለእምነት ዋጋ ሲከፍሉ ያላወቁት ግን በጨለማ ነበር ሲዳከሩ ኖረው ያለፉት። ተርታው አማኝ ቃሉን ካላወቀ ቃሉን በሚተኩ በገድላ ገድሎች፥ መልካ መልኮች፥ ድርሳናትና ተአምራት መጽሐፎች፥ ማንበብ የማያውቁትም ስዕላ ስዕሎችን በአየትና በመሳለም ከእውነት ርቀው ይኖራሉ። ቃሉን ማወቅና ማሳወቅ ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው።

ቃሉን አለማወቅ በመጽሐፉ መጨረሻ ክፍል እንደምንመለከተው ለልብ ወለዶች፥ ለተረቶችና ከዚያም ለወረዱ ጽሑፋት ይዳርገናል። ሁሉ እውነት ይመስለናል። እውነትን የምንፈትንበትና የምንፈትሽበት መጽሐፍ መኖሩን ስናውቅ ግን ሌላውንና ሌሎቹን መጻሕፍት ሁሉ ወደ መፈተሻው እናመጣቸዋለን። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያውቁ ቃሉን ወደ ቋንቋቸው ለመተርጎም የጣሩት ሰዎች ይህንን ሰው ፈጠር ስሕተት ለመቋቋም ቤተ ክርስቲያን አቅም ያጣችበት ምክንያት መሆኑን ስላወቁም ጭምር ነው።

ከእውነተኛው አዳኝ ወደ ሌላው ሊጎትቱ የሚወድዱ አሳቾች ሁሉ ሰዎች እውነተኛውን ቃል እንዲያውቅና እንዲያነብብ አይፈልጉም። በጨለማ እየዳከረ እንዲኖር ይሻሉ። ይህ በቀጥታ የሰይጣን እጅ ያለበት ቢሆንም፥ ከዚያ በመለስ የሰዎች አለማወቅ፥ ወይም አውቆ ለጥቅም መደለል አለበት። ጥቅሙ፥ ሥጋዊ፥ ምድራዊ፥ እንደ ዝና፥ ሥልጣን፥ ገንዘብ እና የመሳሰሉ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ እውነተኛ አማኝ ማድረግ ያለብን ማንንም መጽሐፍ መፈተሻ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ እንዳለን ማወቅና መጽሐፉንም የሌሎቹ ሁሉ መለኪያና መፈተሻ አድርጎ መጠቀምን ማወቅና መለማመድ ነው።

## የማርያም ክይታ በተርታው ምእመን ዘንድ

የተለያዩ የማርያም ስዕሎች የሚባሉትን ስዕሎች ስመለከት ይህን ከታች ያለውን አገኘሁ። በአሜሪካ በሎስ አንጀለስ የምትገኝ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ድረ ገጽ የመግቢያው ገጽ ዋና ስዕል ነው።



ይህ ለዐይን ከተለመዱት ስዕለ ማርያሞች አንዱ ነው። ይህ እርቶዶክሳዊ የማርያም አሳሳል ከተለምዶው የስዕል ሕግ ያፈነገጠ ነው። እርስዋን ለማጉላትና ለማግነን ሲባል ሌላው ሁሉ ይመነምናል። ለምሳሌ ይህ ስዕል በስነ ስዕል እይታ ወይም ከስነ ጥበብ ሒስ አንጻር ከታየ ማርያም ወይ ከነጎልያድም የምትበልጥ እጅግ ግዙፍ ናት ወይም ቀሳውስቱ ድንክዬዎች ናቸው። ከጀርባዋ ቢሆኑ ኖሮ በመካከል ያለው ስፍራ ርቀት አሳንሶአቸዋል ሊባል ይችላል። ይህ እንዳይባል ደግሞ ከበስተ ፊት በኩል ነው ያሉት። በስዕሉ የምትታየው "ማርያም" ቀሳውስቱ ወዳሉበት መጥታ ብትቆም ቀሳውስቱ ከጉልበቷ ትንሽ ከፍ ቢሉ ነው እንጂ ከዚያ አይረዝሙም።

እዚህ የተንጸባረቀው ልዩ የሆነ የማጉላት ሂደት በስዕሉ ብቻ ሳይሆን በነገረ ማርያም አስተምህሮም ላይም የሚታየው ነው። ካቶሊካዊና እርቶዶክሳዊ ነገረ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቶም የማይገኙ ትምህርቶች ተጭነውበት የገዘፈና የከበደ ነው። ማርያም ከፍጥረቷ ውጪና በላይ የሆነ ስብእናና እግዚእና ተጎናጽፋ ትገኛለች።

ከስዕሉ ጎን የጻፍሁት አሳሳሉ ከተለምዶው የስነ ስዕል ሕግ ያፈነገጠና እርስዋን ለማግነንና ለማጉላት ሲባል ሌላው ሁሉ፥ መላእክቱም ሰዎቹም ሁሉ የመነመኑ መሆናቸውን የሚናገር ነው። ይህ ስዕል በስዕል ሐያሲ ዓይን ቢታይ ማርያም ከጎልያድም የምትበልጥ ግዙፍ ናት ወይም ቀሳውስቱ እጅግ ሲበዛ ድንክዬዎች ናቸው። ቀሳውስቱ ከጀርባ ቢሆኑ ኖሮ የስፍራ ርቀት (በperspective አሳሳል) አሳንሶአቸዋል ሊባል ይቻላል። በስዕሉ የምትታየው 'ማርያም' ወደ ቀሳውስቱ መጥታ ብትቆም ቀሳውስቱ ከጉልበቷ ጥቂት ቢረዝሙ ነው።

ይህ ማጉላት በስዕሉ ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክሳዊና ካቶሊካዊ ነገረ ማርያምም የሚንጸባረቅ ነው። ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ ማዕረጎች፥ ሹመቶችና ሥልጣኖች ተጭነውባት እግዚእና የተጎናጸፈች ተደርጋ ነው የተቀረጸችው። በሰፊው ወይም በተርታው ሃይማኖተኛ ዘንድ ማርያም ልዕለ ተፈጥሮን የተጎናጸፈች የሰማይም የምድርም ንግሥት ናት። በንድፈ አሳብም ባይሆን በተግባር ግን በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል የገባች ጣዖት ሆናለች። በዮሐ. 14፥6 ጌታ ኢየሱስም፦ *እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።* አለ። የነገረ ማርያም ቀንደኛ አስተምህሮ ደግሞ በማርያም በቀር ወደ ወልድ የሚደርስ የለም የሚል ነው።

ማርያም ክርስቶስን እስክትሸፍን ድረስ በመካከል ገብታለች። *የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።* (ዕብ 12፥1-2) የተባልነውን ይህን የእምነታችንን ራስና ፈጻሚ እንዳንመለከት የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ሳይሆን የስሕተት አስተማሪዎች የሆኑቱ

ምክንያት አደረጉአት። በመስቀል ታግሦ በአብ ቀኝ የተቀመጠው እርሱ ሆኖ ሳለ ማርያምም ባለ ዙፋን ብቻ ሳይሆን ሥልጣን የመማለድ ችሎታ ተቀዳጅታ በዙፋን ተቀመጠች። ሐሰትን ያስተማሩትን የሐሰት አስተማሪዎች ማለት መናፍቅነት ተሰኘ። ስለ ማርያም እውነቱን ብቻ መናገር ጸረ-ማርያም አሰኘ። ስለ ማርያም በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የመሰለ ቃል መናገርም መናፍቅ የሚያሰኝ ሆነ።

ወንጌላዊ እምነት እስኪታይ ድረስ ብልጭ ብሎ በነበረበት ቀደም ሲል በጠቀስኩት በነ አባ እስጢፋኖስና ደቀ እስጢፋኖስ ወይም በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ቃሉን ያወቁት ሊያርሙ የተነሡት እንዱ ይህ ስሕተት ነበረ። የማርያም አምልኮ በአጭር እብጠት አብጦ የፈነዳው በዚያን ጊዜ ነው። ወንጌላዊ እምነት ተቆናጥጦ ስር መስደድ በጀመረበት በ20ኛው መቶ መጀመሪያ እና መስፋት በጀመረበት በ20ኛው መቶ አጋማሽ የወንጌላውያን አማኞች ስም ጸረ-ማርያም ነበረ። መጤ ሃይማኖትም ተባለ። ያልመጣ፥ በአገር ውስጥ የበቀለ ወይም የተፈጠረ የክርስትና ሃይማኖት ያለ ይመስል።

ጆሴፍ ጌበልስ የተባለ የጀርመን ናዚ ፓርቲ (የሂትለር) የፕሮፓጋንዳ ድርጅት ኃላፊ የነበረ ሰው፥ If you tell a lie big enough and keep repeating it, people will eventually come to believe it. ብሎ ነበር። አንድ እስኪደመጥ ድረስ ትልቅ የሆነ ውሸት ተናግረህ፥ ደግመህ ደጋግመህ ብትናገረው የኋላ ኋላ ሰዎች እንደ እውነት ይቀበሉታል፤ ያምኑታል። ማለት ነው። ውሸት ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር ሲነገር እውነት ቢመስልም እውነት ግን አይሆንም። ውሸትን ደጋግመው የሰሙ የዋሆች ውሸቱን እውነት አድርገው ቢቀበሉት ግን አያስገርምም። ይህ በታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ታይቶአል። እውን ጸረ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ማርያም የተጻፈውን የሚያስተምር እና በኋላ የተፈጠረውን የማያስተምር ነው ወይስ ያልተጻፈውን ፈጥሮና የተፈጠረውን አብዝቶ ከተጻፈው ጋር ቀይጦ የሚያስተምር? ለዚህ ጥያቄ ተገቢ መልስ መስጠት የጸረ ማርያምን ማንነት መግለጥ ነው።

የኢኦተቤክ የምታስተምራት ማርያም ክርስቶስን የምትሸፍን ብቻ ሳትሆን ማንም ወደ እርሱ ያለ እርሷ ሊመጣ እንዳይችል አማላጅ ወይም መካከለኛ የተደረገች ናት። ይህ አሳብ ካለፈው በትንሹ ካነሣነው ነጥቦች ወደ አንዱ ይመራናል። እውን ማርያም ታማልዳለችን? ወደሚለው።

## ማርያም ታማልዳለችን?

አንድ ኦርቶዶክሳዊ መጽሐፍ፥ "በአማላጅነቷ ለሚያምን በቃል ኪዳኗም ለሚማፀን ፍጥረት ሁሉ ለኃጢአት መደምሰሻ፥ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ ድልድይ ሆና

የተፈጠረች በልዩ የተመረጠች ፍጥረት ናት" ይላል።[13] ኃጢአት የሚደመሰስበት የክርስቶስ ደም ሳይሆን አማላጅነቷ፥ መንግሥተ ሰማያት የሚወረሰውም በኪዳኗ ሆነ።

ማማለድ ወይም መማለድ ማለት ስለ ሌላው ሆኖ፥ የሌላውን ጉዳይ ይዞ መፍትሔ፥ ብያኔ፥ ለማግኘት የሚደረግ ተተኪ መሆን ነው። ምልጃ የጸሎት ዓይነት ሆኖ ስለሌላው መጸለይ ነው። ማንም ሰው ስለ ሌላ ሰው ቢጸልይ ይህ ምልጃ ይባላል። በአዲስ ኪዳን ምልጃ የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ቋንቋ በሦስት የተለያዩ ቃላት ተገልጦአል። እነዚህም፥ δεήσει፥ ἐντεύξεις፥ እና ἱκετηρίας ናቸው፤ (ፊል. 4፥6፤ 1ጢሞ. 2፥1-2፤ እና ዕብ. 5፥7።

መካከለኛ የሚለውን ቃል ከታች ለብቻ እንመለከተዋለን። እነዚህ ምልጃን የሚገልጡ ቃላት በተገለጡባቸው ቦታዎች የሞተ ሰው በሕይወት ላሉ የሚጸልየው ሳይሆን ሕያዋን ስለ ሌሎች ሕያዋን ሰዎች ያቀረቡት ልመና ነው። የኢየሱስ እናት በገሊላ ቃና ሠርግ ዕለት ለጌታ የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት፥ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው ባለችው ጊዜ የሆነውን ምልጃ ልንለው እንችላለን። የኢየሱስን ማንነቱንና እርሱ ሊያደርግ የሚችለውን አውቃ ችግሩን ወደ እርሱ አቅርባለችና ይህ መማለድ ነው። ይህ ስለሌሎች ልመናን ማቅረብ ነው። የቃና ዘገሊላውን ጥያቄ ልመና ከማለት ማሳሰብ ልንለው ይቻላል። ሆኖም አሳቡ የጎደለ ነገርን ማሳየት ነው፤ ጉድለት እንዲሞላ ጥያቄን ማቅረብ ነው። ስለዚህም ከምልጃ ሊመደብ ይችላል። በሕይወት ሳለች ስለ ሌላው ያቀረበችው ልመና ነው። ከሞት በኋላ ግን ልታማልድ አትችልም። ከሞት በኋላ ስለ ሌሎች ሕያዋን ልመና ወይም ምልጃ ያቀረቡ ሰዎች ትምህርት በቃሉ ውስጥ አይገኝም።

ከሞት በስቲያ ስለ ሌሎች የሚያማልድ አንድ ብቻ አለ። *ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል* የተባለለት አንድ ብቻ ነው፤ ዕብ. 7፥25። እርሱም ክርስቶስ ነው። ከሞት ተነሥቶአልና! ከክርስቶስ ሌላ በትንሣኤ አካል የተነሣ ሰው አልኖረም። ሁላችንም ግን ለፍርድ ወይም ለሽልማት በትንሣኤ ቀን እንነሣለን።

ማርያም ከሙታን እንደተነሣች የሚነገረው ኋላ የተፈጠረተ ተረት ነው። በካቶሊክ አስተምህሮ የምድር ኑሮዋ ዘመን ሲፈጸም ሳትሞት እንደ ሔኖክ ወደ ሰማይ ማረጓ ነው የተጻፈው። ይህን ትምህርት ደንግገው ያቆሙትም የዛሬ 60 ዓመት ገደማ በ1950 ነው። ይህ በቀኖናቸው ከዚያ በፊት ያልኖረ ታሪክ ነው። መቶ ዓመት እንኳ ያልደፈነው አዲስ አስተምህሮ ነው። በኢኦተቤክ ደግሞ በ64 ዓመቷ ሞታ ተቀብራ በ3ኛው ቀን ተነሥታ ማረጓ ተጽፎአል። በኦርቶዶክስም መሞቷ ሳይካድ ሞቷ ከተጻፈ አይቀር ከሙታን ተነሥታ ማረግ ኖረባት። ያውም በ3ኛ ቀን!

ተአምረ ማርያምን በመሰሉ መጻሕፍት እንደተጻፈው የማርያም ሕይወቷ በአጭሩ 3 ዓመት በወላጆቿ ቤት፥ 12 ዓመት በቤተ መቅደስ ኖረች። ዮሴፍ እጮኛ ወይም ባል

---

[13] ፍሬ ሕይወት፤ ገጽ 194።

ሳይሆን ጠባቂና ሞግዚት የሆነ ሽማግሌ ሰው ነው፤ በእርሱ ዘንድ የቆየችውም 9 ወር ብቻ ነው። ኢየሱስን በ12 ዓመቷ ከወለደች በኋላ በ64 ዓመቷ እስከሞተች ድረስ ከኢየሱስ እና ከዮሐንስ ጋር ኖራ ሞተች። ሐዋርያት ሊቀብሯት ሬሳዋን ተሸከመው ሲሄዱ አይሁድ ደግሞ ሬሳዋን ሊያቃጥሉ (ሬሳ ማቃጠል የአይሁድ ልማድ አይደለም) አሳድደው ሲደርሱባቸው ሬሳዋን ጥለውት ሄዱ። ሬሳዋንና ዮሐንስን አንድ መልአክ ነጥቆ ወደ ገነት ወሰዳቸው። በ15ኛው ቀን ሬሳዋን አግኝተው ቀበሯት፤ ከዚያም በተቀበረች በ3ኛው ቀን ከሙታን ተነሥታ ወደ ሰማይ ዐረገች። ስታርግ ሐዋርያው ቶማስ ከሐገረ ስብከቱ ወደ ኢየሩሳሌም በደመና ተጭኖ እየበረረ ሲመጣ በደመና ተገናኙና ማረጓንም ኋላ ያበሰራቸው እርሱ ሆነ።

እውን እነዚህ ታሪኮች መቼ ተጻፉ ብለን ብንጠይቅ ከ4ኛው እስከ አስራ አምስተኛው ምዕት ዓመት እና ከዚያም በኋላ በየጊዜው እየተጨመረባቸውና እየተስፋፉ የተደረሱ የፈጠራ መጻሕፍት ናቸው። ዋና ግባቸውም አምልኮን ከእግዚአብሔር መቀነስና ፍጡርን ማስመለክ ነው። ይህ ደግሞ በተራው የነፍሳችን ቤዛ ከሆነውና በእርሱ ካልሆነ በቀር ወደ አብ ሊደርስ ማንም ከማይችልበት ጌታ ሰዎችን ማራቅና በእርሱና በሰዎች መካከል እነርሱ እንደሚሉት መሰላል ሳይሆን ግድግዳ መፍጠር ነው። እንደሚታወቀው በሁለት ነጥቦች መካከል ያለው አጭሩ መስመር ቀጥተኛው መስመር ነው። ሌላ ነጥብ በየትኛውም አቅጣጫ፥ በመካከልም ይሁን በጎን ከተፈጠረ መስመሩ ይርቃል እንጂ አይቀርብም። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛ ሰው የሆነው ክርስቶስ ብቻ ነው።

መካከለኛ ወደሚለው ቃል እንምጣ። በወንጌላትም ሆነ በአዲስ ኪዳን በጠቅላላው የማርያምንም ሆነ የሌሎችን ፍጡራን፥ የመላእክትም ሆኑ የማናቸውንም ሰዎች መካከለኛነት አናገኝም። መካከለኛ የምንለውን ቃል በተለምዶ አማላጅ ልንለው እንችላለን። በሁለት መካከል የሚገባ ወይም ራሱን የሚያቀርብ አስታራቂ ማለት ነው። መካከለኛ (μεσίτου፥ μεσίτῃ፥ μεσίτης) የሚለው የአዲስ ኪዳን ቃል 6ጊዜ የተጻፈ ሲሆን ቃሉን በዐውዱ ለማየት ገላ. 3፥19-20፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ዕብ. 8፥6፤ 9፥15፤ 12፥24ን ከዙሪያው ጥቅሶች ጋር ማጥናት ተገቢ ነው። መካከለኛ፥ በሁለት መካከል የሚሆን፥ አስታራቂ፥ አማላጅ ማለት ሆኖ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ቃሉን በስፍራው ስናየው ስለማንም ሳይሆን ስለ ክርስቶስ የሚናገር ነው። መካከለኛው እርሱ ብቻ ነው። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛ አንድ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ነው።

ኃጢአተኛ ሰው ደግሞ ወደ ክርስቶስ በቀጥታ መምጣት ይችላል። የጌታ ጥሪ፥ *እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ* ነው፤ ማቴ. 11፥ 28። ወደ እርሱ በቀጥታ መቅረብ እንችላለን። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ

መካከለኛ እንዳለ ተጽፎ በሰውና በመካከለኛው መካከል ደግሞ ሌላ ተለጣፊ መካከለኛ ቢያስፈልግ ኖሮ ይህ በእውን አይጻፍልንም ነበረን? ይህ በእኛና በመካከለኛው መካከል ሌላ አማላጅ መፍጠር በቃሉ ውስጥ የማናገኘው የስሕተት ትምህርት ነው።

የአዲሱ ኪዳን ዓላማ የሰዎች መዳን በመሆኑ፥ የሰዎች መድህን የሆነው ኢየሱስ ተነግሮ፥ ተሰብኮ፥ ተጽፎ፥ ሲያበቃ ይህኛው የአማላጅ አስፈላጊነት ከብዙ መቶዎች ዓመታት በኋላ ሊገለጥ ተብሎ ተመዝዞ ተደብቆ ቢቀር የጌታ የመምጣቱ፥ ሥጋ የመልበሱ፥ በመስቀል ላይ ኃጢአታችንን በሥጋው ተሸክሞ፥ የነጻንበትን ደሙን አፍስሶ፥ ተፈጸመ ብሎ የማዳኑን ገድል መፈጸሙና መሞቱ ያላለቀ ታሪክ ሊሆን ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ክርስቶስ ሰውን ሊያድን ወደ ምድር መጥቶ፥ የክርስቶስ የመጨረሻው ሥራ ተጠናቅቆ አልቆ፥ በእርሱና በኃጢአተኞች መካከል ትልቅ ገደል ገና ይኖርና ይህኛው ገደል በማርያም ብቻ እንደሚገጠም ተወስኖ፥ ነገር ግን ድልድይዋም ማርያም መሆኗ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ተገለጠ እንደማለት ነው።

ይህ የማርያም ተጨማሪ መካከለኛነት እውነት ቢሆን ኖሮ በአዲስ ኪዳን ገጾች በተጻፈ ነበረ። በግልጽ የተጻፈው ግን ከጌታ በቀር እርሷም ሆነች ሌላ መካከለኛ አማላጅ ከቶም አለመኖሩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ፥ 'የለም' ባለው ላይ ለምን፥ 'አለ' ይባላል። ምስክሩና ዳኛው በእጃችን ያለው ቃሉ ነው። ኦርቶዶክሶች ሌላ መጽሐፍ አምጥተው፥ ወይም ካቶሊኮች በጳጳስ የተቀነነ ነው ብለው፥ 'ይኸው እዚህኛው ገድል ወይም ድርሳን ወይም መልክ ላይ እንዲህ ተጽፎአልና ታማልዳለች' ቢሉ እንኳ አዲስ ኪዳን የምንለው የ27 መጻሕፍት ስብስብ ይህን አይልምና ተቃርኖ ሊፈጠር ነው። ከተፈጠረ ደግሞ ከሁለት ተቃራኒ ነገሮች አንዱ ነው ትክክል እንጂ ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም። የኋለኛው ትክክል ከሆነ የፊተኛው ሊሻር ያስፈልገዋል። የፊተኛው የማይሻር ከሆነ ደግሞ ከዚያ በኋላ የሚመጣው ተቃራኒ ትምህርት ሁሉ ስሕተት መሆኑን ማወቅ አለብን።

የክርስቶስ መካከለኛነት በሌላ የሚተካ ወይም የሚለወጥ አይደለም። ወደ መካከለኛው ለመቅረብ ደግሞ ሌላ መካከለኛ አያስፈልግም። ከሆነ በዚህኛው በአዲሱ መካከለኛና በእኛ መካከል ሌላ መካከለኛ ሊያስፈልግ እንደገና ይችል ይሆናል። ሰንሰለቱ እየተቀጠለበት፥ መስመሩም እየረዘመ፥ በእኛና ልንቀርብበት በተፈለገው መካከል ያለው ርቀት እየበዛ ሊሄድ ነው። ይህ ዋስትና የሌለው እርግጠኛ የማንሆንበት የመቅረቢያ መንገድ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው በኩል መርቆ የከፈተልን መንገድ ግን ቀጥተኛና ያለማንም ወደ እርሱ የምንቀርብበትና የምንገባበት ነው።

ምልጃ ለሌሎች የሚደረግ ጸሎት ወይም ልመና ሆኖ ይህ በእርግጥ በብዙ ቦታዎች ተጽፎአል። የሚያደርጉትም ሕያዋን ሰዎች እንጂ ሙታን አይደሉም። ከላይ እንደተመለከትነው ማርያም በሕይወት ሳለች ይህን ልመና አንድ ጊዜ አድርጋ ነበር። በዮሐ. 2 ስለ ወይን ጠጅ ማለቅ ለጌታ በነገረች ጊዜ። እንዲያም ሆኖ እንኳ የሚላቸውን እንዲያደርጉ ነገረች። ዛሬም ማርያምን የሚወዱና ሊሰሙ የሚፈልጉ ይህን ትእዛዝ ቢያደምጡ ምንኛ ድንቅ ነበር! ያኔ እርሱ የሚላቸውን እንዲያደርጉ እንደተናገረችው፥ ዛሬም ብትጠየቅ ያለምንም ጥርጥር፥ እርሱን ስሙት፥ እርሱ የሚላችሁን አድርጉ ነው የምትለው። በአዲሱም በአሮጌውም ኪዳን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው መካከለኛው አንድ ክርስቶስ ብቻ ነው። በአሮጌው ኪዳን ዘመናት ወደ ፊት የሚሆነውን ተስፋ አድርጎ በመጠበቅ፤ ከመስቀሉ ወዲህ ደግሞ የተፈጸመውን የማዳኑን ተውላጣዊ ሞት በመቀበል ብቻ ነው መዳንን የምንቀበለው። ዛሬ የኢየሱስ እናት ማርያም እንደገና መምጣት ብትችልና ብትመጣ ያኔ ካለችው የተለየ ነገር እንደማትናገር እርግጥ ነው። እርሷ የመዳን መንገድ መሆኗ ያኔ አልተጻፈምና ዛሬም ያንን አትልም።

ጌታ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ ወይም ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ ወይም ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም ያለው በቀጥታ ወደ እርሱ እንድንመጣ መጋበዙ እንጂ በሌላ በኩል እንድንሄድ አይደለም። እንግዲህ በሰውና በጌታ መካከል የሚገባ ምንም እና ማንም የለም። ከኖረ፥ ወደ እርሱ እንዳንሄድ፥ ወደ እርሱ እንዳንደርስ የሚያግድ አጋጅና ግድግዳ እንጂ አቅራቢና አጋፋሪ አይደለም። በተከፈተ በር ላይ መቆም እኮ በሩን መዝጋት ነው! ስለዚህ ወደ ክርስቶስ የምንቀርብበት መንገድ ክፍት ነው፤ መንገዱም እርሱ ነው፤ ዮሐ. 14፥6። ማርያም አማላጅ አይደለችም። እግዚአብሔር በክርስቶስ ወደ እርሱ የምንገባበትን በር አዘጋጅቶልናል። በሩም ክርስቶስ ራሱ ነው፤ ዮሐ. 10፥1-9። በበሩ ላይ ማንም አይቁም!

ጸሎትና ልመና፥ ውዳሴና ምስጋና ደግሞ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ከእግዚአብሔር በቀር ለማንም እንዲቀርብ አልተነገረም። ሲደረግም በስሕተትና በአምልኮተ ጣዖት ካልሆነ በቀር አይታይም። ሌላን እንደ ጌታ (እግዚእ ወይም እግዝእት) አድርጎ ይህን መፈጸም በቀጥታ ከቃሉ ጋር የተጻረረ ነገር ማድረግ ነው። ይህ ከዐሥርቱ ትእዛዛትም ሁለተኛውን መጣስ ነው። ጸሎት የአምላክ ብቻ ነውና ከእግዚአብሔር በቀር ለማንም መቅረብ ከቶም የለበትም። ማርያምን የሚያመልኩ ሰዎች ማርያምን እንደሚያመልኩ ሲነገራቸው እያመለኩ መሆናቸውን አይቀበሉም። ጸሎት ለአምላክ ብቻ የሚቀርብ ከሆነ፥ ጸሎትን ከአምላክ ሌላ ለሆነ ማቅረብ ያንን ጸሎትን የሚያቀርቡለትን ማምለክ እኮ ነው።

## ጽዮንስ ማርያም ናትን? ማርያምስ ንግሥት ናትን?

ስለዚህ ጉዳይ ከዐውዳቸው ተገንጥለው የሚጠቀሱት ሦስት ጥቅሶች የሚገኙባቸው ምዕራፎች መዝ. 45 እና 87፤ እና ኢሳ. 60 ናቸው። እንመልከታቸው።

ጽዮን ዛሬ ለሴት ልጆች የሚወጣ የተወደደ ስም ነው እንጂ የሰው ስም አይደለም። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ የቦታ ስሞች ለሰዎች መጠሪያነት ውለዋል። ኢየሩሳሌም፥ ዮርዳኖስ፥ ገሊላ፥ ቤተ ልሄም፥ ቢታንያ፥ ወዘተ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽዮን የስፍራ ስም ነው። ጽዮን በመጀመሪያ የተጠቀሰችው ዳዊት ኢያቡሳውያንን ተዋግቶ በያዛት ጊዜ ነው፤ 2ሳሙ. 5፥7። ኋላም የዳዊት ከተማ ተብላ ተጠራች። ጽዮን ማለት ከስፍራው ምንነት በስተቀር ትርጉሙ ምንም የሚስብ ነገርም የለውም፤ ምድረ በዳ፥ ደረቅ ስፍራ እንደማለት ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሰባክያንና ጸሐፍያን ጽዮንና ማርያም ሞክሼዎች እየሆኑ ይጠቀሳሉ። ጅማሮው ክብረ ነገሥት ነው። ከዚያ በፊት የተጻፈ ነገር መኖሩን አላውቅም። በክብረ ነገሥት ግን ታቦቱ ጽዮን እየተባለ በሴት ተጠርቷል። በብሉይ ኪዳን ታቦት በእንስት ፆታ አልተጠቀሰም። ታቦቱ እንጂ ታቦቲቱ ተብሎ አይታወቅም። ለምሳሌ፥ *ታቦቱን ወደ ማደሪያው አገባ፥* (ዘጸ. 40፥21)፤ *ሙሴም ታቦቱ በተጓዘ ጊዜ፦ አቤቱ፥ ተነሣ፥ ጠላቶችህም ይበተኑ፥ የሚጠሉህም ከፊትህ ይሸሹ ይል ነበር።* (ዘኍ. 10፥35)፤ *ዳዊትም ታቦቱ ዐርፎ ከተቀመጠ በኋላ በእግዚአብሔር ቤት ያቆማቸው የመዘምራን አለቆች እነዚህ ናቸው።* (1ዜና 6፥31)፤ ወዘተ። ይህ ማለት ፆታ አለው ማለት አይደለም፤ ግን በግሥ ወንዴና ሴቴ ወይም እንስትና ተባት እየተደረጉ የሚጠሩበት የግሥ አጣጣል አለ። ታቦት በእንስት አልተጠራም።

በክብረ ነገሥት በሰሎሞን ዘመን የሳባ ንግሥት (ክብረ ነገሥት የኢትዮጵያ ንግሥት ያሰኛታል) ሰሎሞንን ልትጎበኝ ሄዳ ስትመለስ አርግዛ መሆኑ፥ መጥታ እንደወለደችና ልጁ አባቱን ሊጎበኝ ከሄደበት ሲመለስ ታቦቱን ሰርቆ ይዞ መምጣቱ ተጽፎአል። ነገሩ ስርቆት እንዳይመስል ግን በረቀቀ ጥበብ ነው የተተረከው። የኢትዮጵያን የቃል ኪዳኑ ታቦት ማደሪያነቷንም ከዚህ ክብር ጋር ያቆራኛታል። በክብረ ነገሥት ታቦትም ማርያምም ጽዮን እየተባሉ ተጠቅሰዋል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሹመት፥ 'ንቡረ እድ' የሚባለው ሹመት ታቦቱ አለ የሚባልባት የአክሱም ጽዮን ወይም የአክሱም ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ማዕረግ ነው።

ታቦት እና ጽዮን በአንድ ላይ የተጠቀሱ ከሆነ አንዱ ሌላው አለመሆኑን ይህም ይመሰክራል። በ1ነገ. 8፥1 *ሰሎሞንም <u>የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን ያወጡ ዘንድ</u> የእስራኤልን ሽማግሌዎችና የነገድ አለቆችን ሁሉ፥*

*የእስራኤልን ልጆች የአባቶቻቸውን ቤቶች መሳፍንት፥ ንጉሡ ሰሎሞን ወዳለበት ወደ ኢየሩሳሌም ሰበሰባቸው።* ታቦቱን ከጽዮን ወይም ጽዮን ከተባለችው የዳዊት ከተማ ያመጡ ዘንድ ነው የተባለው።

በብሉይ ኪዳን ጽዮንም እንደ ስፍራ ታቦቱም እንደ ታቦት ተጠቅሰዋል እንጂ አንዴም ሁለቱም ሞክሼ ሆነው አልተጠቀሱም። ካልተጠቀሱ እኛ ከቃሉ በልጠን ሁለቱን ሞክሼ ልናደርግ ፈቃድ ከወዴት አገኘን?

'ጽዮን ግዑዝ ከተማ ከሆነች ለምንድነው እናታችን የሚሏት?' ተብሎም ጥያቄ ቀርቦልኛል። ጥሩ ጥያቄ ነው። መልሱ፥ 'በከተማዋ ስለተወለዱ ነዋ!' የሚል ነው። ከተማ ትወልዳለች? አነጋገሩ ምሳሌያዊ ቢሆንም አዎን ትወልዳለች፤ እስኪ ይህንን ጥቅስ እንመልከት፤ *ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል? በውኑ አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ሕዝብ ይወለዳልን? ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና።* ኢሳ. 66፥8። ከተማን በሴት ወይም እንስት ጾታ መጻፍ በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ አጻጻፍ ነው።

ኢሳይያስ ስለ ከተማዋ ነው በኃላፊ ጊዜ እየተናገረ ያለው እንጂ በትንቢት ስለማርያም ብዙ ልጆች መውለድ እየተናገረ አይደለም። ማርያም አምጣ ልጆች መውለዷን ከተስማሙ፥ ልጅ ሳይሆን ልጆች የሚለውንም ሊቀበሉ ግድ ነው። ግን ከአንዷም ጥቅስ መውለዷን እንጂ ብዙ መሆናቸውን አይቀበሉም። ከተማ እናታችን ልትባል ግን እንደምትችል እና በምሳሌያዊ ቋንቋ እንደምትወልድ መገንዘብ የተገባ ነው።

ጽዮን የሚለውን ቃል እንደ ቦታ ሳይሆን በማርያም እንለውጥና እንደ ማርያም እንውሰድ ከተባለም ጽዮን ወደ 150 የሚጠጋ ጊዜ ተጽፏልና እንውሰደውና እንይ ብንል ማርያም ተራራም፥ ከተማም፥ ኮረብታም፥ አምባም ትሆናለች። እንዲህ ያለው አተረጓጎም ደግሞ መሳትና ማሳት አለበት።

*ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።* መዝ. 87፥5 የሚለው ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የጽዮንን ማርያምነት ለመግለጥ የሚያወሱት ጥቅስ ነው። መዝ. 87 ሰባት ቁጥሮች ብቻ ያሉት አጭር ምዕራፍ ወይም መዝሙር ነውና ብንመለከተው ስለከተማ እንጂ ስለ ማርያም እንደማይናገር ግልጽ ነው። ደግሞም አንድ ጥቅስ ነጥሎና ቦጭቆ ሳይሆን በስፍራው ሲያነብቡት ነው ስለምን እንደሚናገር የምናውቀው።

*መዝሙረ ዳዊት* 87

*የቆሬ ልጆች የምስጋና መዝሙር።*

1፥ *መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፤*

2፥ ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፥ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል።

3፥ የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል።

4፥ የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ፤ እነሆ፥ ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያም ሕዝብ፥ እነዚህ በዚያ ተወለዱ።

5፥ ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።

6፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ፥ በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል።

7፥ በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል።

ያሰመርኩባቸውን ቃላትና ሐረጎች ብናያቸው ይህ፥ 'እናታችን ጽዮን' ወይም 'ጽዮን እምነ' የሚለው ስለ ማርያም አለመሆኑ ብዙም ጥናት አይጠይቅም። ቁጥር 1 ስለ መሠረት ይናገራል። ቁጥር 2 ስለ ደጆች። ቁጥር 3 በግልጽ የእግዚአብሔር ከተማ ይላል። ቁጥር 5፥ *ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።* ሲል መመሥረት ለሰው አለመሆኑ ግልጽ ሆኖ ይታያል። ሰው አይመሠረትምና። ቁጥር 6 በውስጧ ስለተወለዱት ይናገራል። ይህ በከተማዋ ውስጥ የተወለዱትን እንጂ በሴት ውስጥ የተወለዱትን አይደለም። ሴት ትወልዳለች እንጂ በሴት ውስጥ የሚወለድ ነገር የለም። ቁጥር 7 በአንቺ የሚኖሩ ይላል። በከተማ እንጂ በሴት ውስጥ የሚኖሩ የሉም። እንግዲህ ዕውድ የሚባል የአፈታት ደንብን ጥለን ጽዮን ማለት ማርያም ናት ካልን ማርያም ማለት ከተማ ናት ልንል ነው።

ሌላው ስለ ማርያም ጽዮንነት በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ክፍል ኢሳ. 60፥14 ነው። ጥቅሱ የሚለው፥ *የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፥ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፤ የእግዚአብሔርም ከተማ፥ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።* ነው። አሁንም አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ሂደት ዐውድ የሚባል ነገር አለና ጥቅስ በመንጠቆ መንጥቆ ሳይሆን በስፍራው ነው መታየት ያለበት። አሁንም ጠቅላላው ኢሳ. 60 ሲታይ ክፍሉ ስለ ከተማዋ ጽዮን ወይም መቅደሱ ስላለባት ከተማ ስለ ኢየሩሳሌም እንጂ ስለ ማርያም ምንም የሚናገረው ቀርቶ የሚጠቁመውን ነገር የለም። ለምሳሌ፥ ቁጥር 11፥ *በሮችሽም ሁልጊዜ ይከፈታሉ፤ ሰዎች የአሕዛብን ብልጥግና የተማረኩትንም ነገሥታቶቻቸውን ወደ አንቺ ያመጡ ዘንድ ሌሊትና ቀን አይዘጉም።* ይላል። ይህንን በማርያም መንዝረን ብንተረጉም ምንም ትርጉም አይሰጥም።

እንደ ቦታም እንኳ ብንወስድ እግዚአብሔር በጽዮን ያድራል (ኢዩ. 3፥21) ሲባል እግዚአብሔር በቦታ የተወሰነነቱን አመልካች አይደለም፤ ስለ ሕዝቡ መናገሩ እንጂ። እርሱ በቦታ የሚያድር አምላክ አይደለም። ጥንት የማደሪያው ድንኳን የሚባል ነበረ። ያም የመገኘቱ ምልክት የሆነው ታቦቱ የሚያድርበት እንጂ እርሱ የሚያድርበት

አልነበረም። ድንኳኑም ከተሠራበት ከምድረበዳው ጀምሮ በየቦታው ተተክሎ ነበር። ኋላ መቅደስ ሲሠራ የማደሪያው ድንኳን ቀረ። ኋላ ደግሞ መቅደሱ ራሱም ፈርሶ በውስጡ የነበሩት ንዋየ ቅድሳት ተመዝብረው ተወሰዱ።

በአዲስ ኪዳን ጽዮን የሚለው ቃል ሰባት ጊዜ ተጠቅሶአል። ከሰባቱ ውስጥ አምስቱ (ማቴ. 21፥4-5፤ ዮሐ. 12፥14-15፤ ሮሜ. 9፥32-33፤ 11፥26፤ 1ጴጥ. 2፥6) ከብሉይ ኪዳን ቀጥታ የተጠቀሱ ናቸው። ማርያምን አመልካች አይደሉም። ሁለቱ፥ ዕብ. 12፥22 እና ራእ. 14፥1 ደግሞ መጪዋን ከተማ የሚያመለክቱ ናቸው። ልክ እንደቀደመችው ኢየሩሳሌም መጪዋ የቅዱሳን መኖሪያም ኢየሩሳሌም እና ጽዮን ተብለዋል። ስለዚህ ጽዮን ማርያም አይደለችም። ማርያምም ጽዮን አይደለችም።

'ንግሥቲቱ በቀኝህ ቆማለች' የሚለው ሌላው ጥቅስ ነው። መዝ. 45፥9 ላይ፥ *የንጉሦች ሴት ልጆች ለክብርህ ናቸው፤ በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።* ተብሎ በተጻፈው የሚገኘውን ንግሥቲቱ ማርያም እንደሆነች የሚያስተምሩ አሉ።

መዝ. 45ን የአይሁድ ሊቃውንትም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንትም የመሢሑ ትንቢታዊ መዝሙር እንደሆነ ይተረጉማሉ። ቁጥር 6 እና 7 ላይ ያለው ቃል በዕብ. 1፥ 8-9 *ስለ ልጁ ግን፦ አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ ይላል።* ተብሎ በአዲስ ኪዳን ተጠቅሶአልና መሢሐዊ ሊባልም ይቻላል።

ሌሎች ደግሞ ይህ የአይሁድ የሠርግ ምሳሌነት ያለው ወይም በሠርግ የሚዘመር መዝሙር ወይም የንጉሥ ሠርግ መዝሙር ነው ይላሉ። ይመስላልም። ንጉሥ የሚለው ቃል በመዝሙሩ ውስጥ ሰባት ጊዜያት ተጽፎአል። ንጉሥ በክብሩ፥ በኃይሉ፥ በሞገሡ የሚታይበት መዝሙር ነው። ንግሥቲቱም እናቱ ሳትሆን ሚስቱ ናት። ንግሥቲቱ የተሰኘው ቃል שֵׁגָל (ሼጋል) ከንግሥትነት ይልቅ ሚስትነትን አመልካች ቃል ነው። ሌላ ንግሥት የሚባል ከንጉሥ ጋር የሚቀራረብ ቃል በዕብራይስጥ አለ፤ מַלְכָּה (ማልካህ) ይባላል። ሁለቱም የንጉሥ ሚስቶችን ገላጮች ናቸው። እናትንም ሊገልጡ ቢችሉም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የንጉሥ እናቶች እቴጌ እየተሰኙ በግልጽ በእናትነት ተጽፈዋል።

ይህንን መዝሙር መሢሐዊ ካደረግነውም የክርስቶስ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ናትና እርሷን አመልካች ነው፤ እንጂ ማርያምን በምንም መልኩ አያመለክትም። ይህ መዝሙር ስለ ማርያም የተነገረ ትንቢት አይደለም። መዝሙር እንጂ ትንቢትም

አይደለም። ትንቢታዊ ወይም ወደፊታዊ ሳይሆን ኃላፋዊ ነው። ከነዚህ ዐውድ ከለቀቁ አፈታቶች የምንረዳው ጥቅሶች ማርያምን እንዲያመለክቱ ብለው ማርያማውያን የማይቦጭቁት እና የማይቆለምሙት ጥቅስ አለመኖሩን ነው። እናጢን፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፎች ተቀባዮች፥ ተደራሾች አሏቸው። ያንን ማወቅ ከተሳሳተ አፈታት ይጠብቀናል። የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ዐውድን የተከተለ ነው። ዐውደ ወጥ መሆን ምንም ነገርን ያልሆነውን ሌላ ነገር ነው ብለው እንዲተረጉሙ ቀዳዳ ብቻ ሳይሆን በርም ይበረግዳል። የሳቱ ሰባኪዎች ያስታሉ።

## ከዘላለም ድንግል ናትን? የኢየሱስ ወንድሞች ጉዳይስ?

በመጀመሪያው ክፍል የጠቀስኩት መ/ር ምህረተአብ አሰፋ በሁለተኛው ዲቪዲው ስለ ማርያም ልዕልና በሰፊው ሲያትት ቃሉን እንደፈለገ፥ ዐውዱን እየተወ፥ ዋናውን አሳብ እየዘለለ ሲሰብክ መመልከት ለቃሉ ተማሪዎች እጅግ ይደንቃል። አንዱ ነጥብ ስለ ኢየሱስ ወንድሞች ወይም የማርያም ልጆች ስለተጻፈው የተናገረው ነው። በኦርቶዶክሳዊና ካቶሊካዊም ሃይማኖት ማርያም ኢየሱስን ከወለደችም በኋላ ድንግል ሆና የኖረች ናት። ከመውለዷ በፊት ብቻ ሳይሆን ስትወልድም፥ ከወሊድ በኋላም ድንግል ሆና ኖራለች። ቅድመ ወሊድ፥ ጊዜ ወሊድ፥ ድኅረ ወሊድ ድንግል ተሰኝታለች። ስትወልድ አወላለዷ በተአምር ስለነበረ ኢየሱስ የማርያምን የማኅጸን አፍ ሳይነካ ነው የወጣው! እንዲህ ከሆነ ደግሞ ኢየሱስ ሲወለድ መጠኑ ምን ያህል እንደነበረ መገመት እንኳ አዳጋች ነው። ዮሴፍ ከላይ እንደተጠቀሰው አረጋዊ ሊሞት የቀረበ ጠባቂ ሽማግሌ እንጂ እጮኛ አይደለም በማለት በስፋት አተተ።

*የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።* ማቴ. 1፥18። ወንጌሉ ማርያምና ዮሴፍ እጮኛሞች መሆናቸውን ነው የሚናገረው። *እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ።* ማቴ 1፥19። ዮሴፍ አረጋዊ ጠባቂ ከሆነና እንዲጠብቃትና እንዲያገለግላት ከተሰጠችው በስውር ሊተዋት ማሰብ የለበትም። የለም በስውር የተዋትም ሽማግሌው ዮሴፍ በድንግልና እንድትኖር እየጠበቃት እንጂ ስላረገዘች መተው አለበት ሊሰኝም ይቻላል። እንደዚያ አድርገን እንኳ እንውሰድ ቢባል፥ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶችስ?

*እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።* ማቴ. 1፥20-21። ለመውሰድ አትፍራ ማለት

የራስ ለማድረግ መውሰድ ነው። παραλαβεῖν ከራስ ጎን ለማድረግ መቀበል ነው። ቁጥር 24 ላይ ያለው ወሰደ የሚል ቃልም ተመሳሳይ ነው። አረጋዊው ጠባቂ ቀድሞውኑ እንዲጠብቅ ከተሰጠው፥ ለመውሰድ አትፍራ የሚባልበት ምክንያት የለም።

*ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።* ማቴ. 1፥21። በአይሁድ ባህል ስምን እናቶችም ማውጣት ቢችሉም የአባት ኃላፊነት ነው። ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ ተብሎ ለዮሴፍ ሲነገር ሚናውንም መግለጡ ነው። ኢየሱስ የዮሴፍ ልጅ አለመሆኑ ምንምም የሚያከራክር ስላልሆነ እዚህ ላይ መናገር አስፈላጊ አይደለም። ሰያሚውም በእውነቱ ዮሴፍ ሳይሆን አስቀድሞ ለአዳኙ የወጣለት የተገብሮ ስሙ ነው።

*በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።* ማቴ. 1፥22-23። ይህ ትንቢት አስቀድሞ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረ ትንቢት ነው። ትንቢቱ በድርብ ተፈጻሚነት ማርያምንና ኢየሱስንም አመለከተ እንጂ በስፍራው በዐውዱ ስናየው በጊዜው በቀጥታ ለአካዝ የተነገረ ቃል ነው። ኢሳ. 7ን በመላው ስናነብብ ይህንን ሳንቸገር መረዳት እንችላለን። ለይሁዳ ንጉሥ ለአካዝ የሚወለድ ልጅ አለ፤ ያ ልጅ ገና ክፉና ደጉን መለየት ሳይችል ሁለቱ ነገሥታት (ሶርያና እስራኤል) እንደሚሰበሩ የተነገረ ትንቢት ነው። አካዝ የነገሠው ከ735-715 (አንዳንድ ሊቃውንት ከ743-727 ያደርጉታል) ነው። እስራኤል ወይም የሰሜኑ መንግሥት የተሰበረውና ወደ አሦር የተጋዘው በ722 ዓ. ዓ. ነው። ይህ የሆነው በቀጥታ በአካዝ ዘመን ወይም ከአካዝ ዘመን መጨረሻ ወይም በልጁ በሕዝቅያስ ዘመን ነው። እንደተባለው ግን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሁለቱም መንግሥታት ፈረሱ። ትንቢቱም ያኔ ተፈጸመ። የአካዝን ታሪክ በ2ነገ. 16 እና 17 እናገኘዋለን።

አንዳንድ ትንቢቶች ድርብ ወይም ድርብርብ ፍጻሜ ያላቸው ናቸው። ይህ ትንቢት በማቴዎስ እንዲህ መጠቀሱ ድርብ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑንም አመልካች ነው። ማቴዎስ ያንን ጥቅስ መጥቀሱና መጻፉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተደረገ ሥራ ነው። ኢሳይያስ በጊዜው የተናገረውም ስለዚህኛው እያሰበ ባይሆንም እዚያ ያናገረው መንፈስ ቅዱስ፥ እዚህም ወንጌሉን ያስጻፈው መንፈስ ቅዱስ ድርብ ፍጻሜነቱን ያውቅ ነበርና ነው። እዚያ አማኑኤል የተባለ ልጅ መወለዱ በእርግጥ አልተጻፈም። ሆኖም በኢሳ. 8፥8 *እየጐረፈም ወደ ይሁዳ ይገባል፤ እያጥለቀለቀም ያልፋል፥ እስከ አንገትም ይደርሳል፤ አማኑኤል ሆይ፥ የክንፉ መዘርጋት የአገርህን ስፋት ትሞላለች።* ተብሎ ስለተጻፈ የወራሪውን ኃይል በዘመኑ እየጎረፉ መምጣት መግለጡ ይመስላል። እዚህ

ተደራቢው ፍጻሜ ላይ ግን የተወለደው ሕጻን በእርግጥም ስሙ ኢየሱስ ቢባልም እርሱ ግን አማኑኤል ነው። እንደ ቃሉ ትርጉም ከሰዎች ጋር የሆነ እግዚአብሔር ነው።

*የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው።* ማቴ. 1፥25። ዮሴፍ እንደወሰዳት፥ የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ እንዳላወቃት በማያሻማ ቋንቋ ነው የጻፈው። ቃሉን እንደ ቃሉ መውሰድ አለብን እንጂ ኋላ በተፈጠሩ ተረቶች መለወጥ ተገቢ ነው? አይደለም። የበኵር ልጅዋን እስኪታውቅ ድረስ ማለት ጊዜን አመልካች ነው። እስከ ማለት እስከ እስከተባለው ጊዜ ድረስ የተገደበ ነገርን አመልካች ነው። እስከ ከተባለው ጊዜ በኋላስ? ያ እስከ የተባለው ነገር ይወገዳል ማለት ነው። *እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤* ማወቅ በአእምሮ ማወቅ ቢሆንም በተጨማሪ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልዋጭ ወይም ጨዋ ቃል ነው። ይህ በብዙ ቦታዎች የተጻፈ ቃል ነው፤ ለምሳሌ፥ ዘፍ. 4፥1፥17 እና 25፤ 19፥8፤ 1ሳሙ. 1፥19። ዮሴፍ በአንዳንድ ኦርቶዶክሳውያን ስዕሎች ውስጥም እንደምናየው ያለ እጅግ ያረጀ አረጋዊ ሽማግሌ ሳይሆን ሚስት ያጨ ወጣት ሰው ነው። ይህ፥ *እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤* ማለት ከወለደች በኋላ አውቋታል ማለት ነው።

የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉት በእውን የማርያም ልጆች የሆኑ ወንድሞቹ ካልሆኑ እነማን ናቸው? ማርያም ድንግል ሆና ለዘላለም እንደምትኖር የሚያስተምሩ ሰዎችን ብንጠይቅ ወንድሞቹ የተባሉት ደቀ መዛሙርቱ፥ ወይም ሐዋርያቱ ወይም ዘመዶቹና ሌላም እንደሆኑ ይነግሩናል። በካቶሊክ ትውፊት እነዚህ ወንድሞች የአጎትና አክስት ልጆች ሲሆኑ በኦርቶዶክስ ደግሞ የዮሴፍ የቀድሞ ልጆች ናቸው። በካቶሊኮች ዘንድ እንደሚጠቀሰው ላለው የቅርብ ዝምድና (የአጎትና አክስት ልጅ ወይም የእኅትና ወንድም ልጅ በአዲስ ኪዳን ἀνεψιὸς (አኔፕሲዮስ) የሚል ቃል አለ። ይህ ቃል እያለ ἀδελφός (አዴልፎስ ወንድም) እና ἀδελφή (አዴልፌ እኅት) የሚል ቃል መጠቀማቸው የማንነት ገላጭ ነው።

እርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ወንድሞች የሚለውን ቃል በሰፊው የሥጋ ላልሆኑ ሥጋዊ ዝምድናዎች እና ለመንፈሳዊ ወንድሞችም ይገለገልበታል። ለምሳሌ፥ ዘጸ. 2፥11፤ አሞ. 1፥9፤ ሐዋ. 1፥15፤ 3፥22፤ 17፥14፤ 18፥18፤ 1ቆሮ. 16፥12፤ ወዘተ። እነዚህ በነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች የሥጋ ወንድሞች አይደሉም ግን ወንድሞች ተሰኝተዋል። በወንጌላት ውስጥ የምናገኘው የኢየሱስ ወንድሞች አገላለጥ ከእነዚህ የተለዩ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል። ግን የኛዎቹና የዘመናችን ሰዎች ዘመዶቹ እንደሆኑ የሚነግሩንን እነዚያ ያኔና እዚያ የነበሩት፥ ማንነታቸውን የሚያውቋቸው ሰዎች ዘመዶቹ መሆናቸው ጠፋቸውና ነው፥ 'ወንድሞቹና እኅቶቹ' ብለው በስም እየጠቀሱ፥

ወላጆቻቸውንም በስም እየጠቀሱ የተናገሩት? አይደለም፤ ያውቋቸዋል። እኛ ከምንገምተው ይልቅ እነርሱ የተናገሩትና የተናገሩትም የተጻፈልን ይበልጣል።

ቀደም ሲል፥ ስለ ማርያም ማርያም ራሷ የምትናገረው እውነት ሌላው ስለ እርሷ ከሚናገረው ይበልጥ ተአማኒ እንደሚሆን እና መሆንም እንዳለበት ተመልክተን ነበር። እዚህም ወንድሞቹ ስለተባሉቱ እኛ የመሰለንን እና የምንገምተውን ከምንናገር ያዩአቸውና የሰሙአቸው፥ አብረዋቸው የኖሩና በስም ያወቁአቸው የሚሉትን መቀበል አይቀልለንም? ማን ይናገር? የነበረ ማለት እኮ ይህ ነው። በግምት፥ እንዲያው በነሲብ፥ ወይም ከሙቶዎች ዓመታት በኋላ ዮሴፍ ቀድሞ ሚስት ሳትኖረው አትቀርም፤ ወይም እንዳለችው አድርገን እንጻፍ ተብሎ መቼ በእርግጥ እንደተፈጠረ እንኳ ማስረጃ የማይቀርብለትን አፈ ታሪክ ትምህርት አድርጎ ማስተማር ስሕተት ነው። በተለይም ትምህርቱ ከደኅንነት ጋር የሚቃረን ሲሆን የሐሰት ትምህርት ነው።

ስለ ማርያም ዘላለማዊ ድንግልናዋ (ዘላለማዊ ድንግልና ሲሉ ከመውለዷ በፊት ስትወልድ እና ከወለደች በኋላ ነው) በጣሙን ተደጋግመው ከሚጠቀሱት ጥቅሶች ሁለቱን እንመልከት። እነዚህ ጥቅሶች በዐውዳቸው ሲታዩ ስለ ማርያም እንደማይናገሩ በጣም ግልጽ ነው። እነዚህን ሁለት ጥቅሶች መመልከት አስፈላጊነቱ ሌሎቹንም በተመሳሳይ መልክ እንድንመለከት በማለት ነው።

*የመጀመሪያው* ጥቅስ መኃ. 4፥12 ያለው፥ *እኅቴ ሙሽራ የተቈለፈ ገነት፥ የተዘጋ ምንጭ የታተመም ፈሳሽ ናት።* የሚል ቃል ነው። ጥቅስ ከዐውዱ ተገንጥሎ መውጣት የለበትም። መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፥ ሰሎሞን ከጻፋቸው ከሺህ የሚበልጡ መዝሙሮች አንዱ ነው። የፍቅርን ምንነት ለመግለጥ አካላዊ ውበትንና ወሲባዊ ቋንቋን በሰፊው ስለሚጠቀም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ እንኳ መወሰዱ ከብሉይ ኪዳን ቀኖና ጀምሮ የሚከብዳቸው በታሪክ ውስጥ አልጠፉም። ክብደቱን ለማቅለልም መጽሐፉን መንፈሳዊ ብቻ በማድረግ የእግዚአብሔርና የእስራኤል ፍቅር ወይም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር መገለጫ አድርገው በስዕላዊነት ወይም ተምሳሌታዊ አተረጓጎም ዘይቤ የሚያስተምሩ አያሌ ናቸው። እነሆ፥ አዚህ ደግሞ ማርያም ሆና ቀርባለች።

መዝሙሩ ግን የሰሎሞንና የሱላማጢስ ፍቅር የተገለጠበት ቅኔ ነው እንጂ ስለ ማርያም ከቶም የሚናገር አለመሆኑን እንይ። በመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ደንብ አንድ ምንባብ ግልጽ ከሆነና ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ሌላ ስሜት ልንፈልግለት አይገባም። ምሳሌ ካልሆነና ምሳሌ መሆኑ ገሃድ ካለሆነም ምሳሌ አድርገንና ግልጹን አወሳስበን ምስጢር አድርገን የምስጢሩን መፍትሔ ልንፈልግለት የተገባ አይደለም። ምክንያቱም፥ ቀድሞውኑም ምስጢር አልነበረማ! ቀድሞውኑም ምሳሌ አይደለማ!

በሰሎሞን ዘመን ከተጻፈ፥ ይህ መጽሐፍ ከክርስቶስ ልደትና ከወንጌሉ ታሪክ 900 ዓመታት በላይ ቀድሞ የተጻፈ ነው። መኃልዩ የሆነና እየሆነ ያለ ነገርን እየገለጠ እንጂ የተጻፈው እንደ ትንቢት አለመሆኑ ግልጽ ነው። ይህች ገነት ተቆልፋ፥ ተዘግታ፥ ታትማ የቀረች አለመሆኗን ደግሞ መኃልዩን ስናነብብ እንረዳለን። ራሷም ወዳጇን፥ በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 16፥ *የሰሜን ነፋስ ሆይ፥ ተነሥ፥ የደቡብም ነፋስ ና በገነቴ ላይ ንፈስ፥ ሽቱውም ይፍሰስ ውዴ ወደ ገነቱ ይግባ፥ መልካሙንም ፍሬ ይብላ* ብላ የለም? በ6፥2 ደግሞ፥ *ውዴ በገነቱ መንጋውን ያሰማራ ዘንድ አበባውንም ይሰበስብ ዘንድ ወደ ሽቱ መደብ ወደ ገነቱ ወረደ* የሚል እናነብባለን።

ወዳጇ ወደ ገነቱ እኮ ገብቷል። ይህ ወሲባዊና ሩካቤያዊ ቋንቋ ነው። የተቆለፈ ገነት ለሁሉ የተከፈቱ ያለመሆን ምሳሌ እንጂ ለአንዱ የታሸጉ መሆን አይደለም። ይህች ሴት በውዷ ፍቅር ስትነደፍ ትታያለች፤ ወዳጇን ቀምሳዋለችና ጣፋጭ እንደሆነ ትመሰክራለች። ይህ ወዳጇ ወዳጇ ብቻ ሳይሆን ባልንጀራዋም ነው (5፥16)። ሴቲቱ ወይም ሱላማጢስ ማርያም ከሆነች ይህ ወዳጅና ባልንጀራ ማን ነው? እግዚአብሔር ሊሰኝ ይሆን? ይህ ማርያምን ያለ ቅጥ ከፍ ማድረግ ነው ወይስ እግዚአብሔርን ያለ ልክ ዝቅ ማድረግ ነው?

ይህች ወዳጇ 'ውዴ' እያለ የሚጠራት ሴት ማርያም ከሆነች እርሷ 'ወዳጄ' እያለች የምትጠራው ሰው ማን ሊሆን ነው? ሌላ ማንም እንዳይሆን ደግሞ ሰሎሞን ተብሎ በግልጽ ተጽፎአል። ሰሎሞን በመጽሐፉ ውስጥ በስም ሰባት ጊዜ ተጠቅሶአል፤ 1፥1 እና 5፤ 3፥7፥ 9 እና 11፤ 8፥11 ሁለት ጊዜ። ሰሎሞን ለተባለው ስም ሌላ ትርጉም እንፈልግለት ብንል ደግሞ የማንወጣው የተሳሳተ የአፈታት ረግረግ ውስጥ እንገባለን። ይህ አንደኛው ጥቅስ ነው።

ሁለተኛው የምንመለከተው ጥቅስ ማርያም በትንቢተ ሕዝቅኤል የተጻፈው የተዘጋው በር መሆኗ ነው። ቃሉ በሕዝ. 44፥2 የተጻፈው ነው። እንዲህ ይላል፥ *እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።* ይህ ሕዝቅኤል በራእዩ ያየው ቤተ መቅደስ ነው።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጥቅስ ነቅሎ ወይም ፈንቅሎ በማውጣት ግዙፍ አስተምህሮ መገንባት አይቻልም። ውዳሴ ማርያም በተባለ የውዳሴና ጸሎት መጽሐፍ ጸሎተ ረቡዕ ቁ. 7-8 ይኸው ክፍለ ምንባብ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ "ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ እርሷ መሰከረ ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጃ ምሥራቅ አየሁ አለ። ከኃያላን ጌታ በቀር ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የለም። ቅድስት ሆይ ለምኚልን። ኖኅትም ደጅም መድኃኒታችንን የወለደች ድንግል ናት፤ እርሱን ከወለደች በኋላ

እንደቀድሞው በድንግልና ኖራለችና።”[14] ለማግነን ነው ‘ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ’ የተሰኘው እንጂ በሕዝቅኤል ውስጥ ድንቅና ታላቅ ቁልፍ የሚል ሐረግ የለም። ያው የሌለ ትምህርት ሲፈጠር በማግነን ነው የሚጀመረው።

ከመውለዷ በፊት ድንግል፥ ስትወልድ ድንግል፥ ከወሊድ በኋላም ድንግል መሆኗን ቃሉ በግልጽ ያረጋግጣል የሚለው የመ/ር ምህረተአብ አሰፋ ማስረጃ ኢሳ. 7፥14 ነው። ይህ ግልጽ ቃል ነው ድንግል መጸነሷንና ጌታ ያለ ወንድ ፈቃድ መወለዱን እንጂ ከዚያ በኋላ ማርያም ለዘላለም ድንግል መሆኗን አይናገርም። ከወለደች በኋላ ድንግል መሆኗን ደግሞ መምህሩ የጠቀሰው ሕዝ. 44፥1-2ን ነው። ይህን ሲጠቅስ፥ “አዎ ከወለደች በኋላ ድንግል ነች የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አለ . . . በር የተባለው የድንግል ማርያም ድንግልና ነው፤ ማሕጸን ነው፤ አፈ ማሕጸኗ ዐውደ ማሕጸኗ ነው፤ ለዘላለም ተዘግቶ ይኖራል፤ አማናዊት መቅደስ እሷ ነች” ብሎአል፤ (ሁለተኛው ዲቪዲ)። ከዚያም ወንጌላውያን አማኞችን ለመዝለፍ፥ “. . . ኢየሱስን እንወደዋለን የሚሉ ከሆነ ለምንድርነው የተቀመጠበትን ዙፋን ማክበር ያቃታቸው?” የሚል ጥያቄ አቅርቦአል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን ስለንጉሡ ክብር ሲባል እስካሁን ሰው እንዳልተቀመጠበትና በካቴድራል እንደሚገኝ ምሳሌ ሰጥቶ ማርያም መከበር እንዳለባት ገለጠ።

ምሳሌውንና ንጽጽሩን ብንመለከት አስቂኝም ነው። የኃይለ ሥላሴ ዙፋንም በዚህ ስሌት ከቀጠለና ከኖረ ሳይመለክ ይቀራል? የቁሳቁስ አምልኮ እኮ እንዲህ ነው የሚጀምረው። ቀደም ሲል እንደተጠቀስኩት፥ ‘ማርያምን ወዲያ ጥለው ልጇን የሚወዱ የቆርቆሮ ምግብ በልተው ቆርቆሮውን የሚጥሉት’ እንዳሉት መነኩሴ መሳይ ምሳሌ ነው። ማርያም ግዑዝ መቀመጫ አይደለችም። ግዑዝ መቀመጫ ብቻ ሳይሆን እንደ ምሳሌም በማድረግ፥ መርከብም፥ መሰላልም፥ ሙዳይም፥ ሳንዱቅም ያደርጓታል። መምህሩ እንደዚያ አስቦ ከሆነ ደግሞ ንጉሥና ዙፋን አይነጻጸሩም። ዙፋኑ የተሠራው ከእንጨት ወይም ከብረት ወይ ከዕንቁና ከወርቅም እንኳ ቢሆን ንጉሥ ንጉሥ፥ ዙፋን ደግሞ ዙፋንና መቀመጫ ነው። ይህ ደካማ ምሳሌ ነው። ዙፋን ንጉሥ ስለተቀመጠበት መከበርና ለዙፋን መሰገድ ካለበት ይህ ግልጽ አምልኮተ ጣዖት ነው።

ወደ ጥቅሱ ስንመለስ፥ ይህ በር እውን የማርያም ድንግልና ነውን? ይህም ድምዳሜ ከዐውዱ የወጣ ጥቅስ መሆኑን ከዚያው ከሕዝቅኤል ምዕራፍ 44 ሳንወጣ እንረዳለን። ለምሳሌ፥ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ፥ *አለቃው ግን እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ይቀመጥበታል በበሩ ደጀ ሰላም መንገድ ይገባል በዚያም መንገድ ይወጣል*

[14] ውዳሴ ማርያም የዕለተ ረቡዕ ንባብ፥ ቁጥር 7-8።

ተብሎአል። አለቃው ማን ነው? ለምንስ ይቀመጥበታል? ደግሞ የሰሜኑ በር አለ ወደ መቅደሱም የሚገቡ አሉ። መቅደሱም የሚገቡበትና የሚወጡበት ነው። እውን ይህ የምሥራቁ በር የማርያም ድንግልና ከሆነ የሰሜኑ በርስ? ምኗ ነው? ጠቅላላው መቅደስ ደግሞስ? የምሥራቁ በር አፏ ማኅጸኗ ነው ከተባለ መቅደሱ ማኅጸኗ መሆን አለበት። ማኅጸን ደግሞ አንድ ብቻ በር እንዳለው የታወቀ ሲሆን ሌሎች እንዴትና በምን በኩል ገቡ? ሌሎቹ በሮችስ ምን ሊባሉ ነው?

ሕዝቅኤል በራእዩ ያየው መቅደስ ደግሞ ከቶውኑ የማይገባበት ታሽጎ የሚኖር ነው ወይስ የሚገባበት? ይህ መቅደስ ማርያም፥ የምሥራቁም በር ድንግልናዋ ነው? ይህ ራእይ አንደኛ ራእይ መሆኑን አንዘንጋ። ሁለተኛ ማንም የማይገባበት መቅደስ የለምና ይህ የተዘጋ መቅደስ አለመሆኑንም እናስተውል። ራሱም ሕዝቅኤልም እኮ ገብቶበታል። በአካል ይሁን በራእይ ግን ገብቶበታል። ወደ መቅደሱም አገባኝ፥ ይላል፤ ሕዝ. 41፥1። ይህ ሌላ መቅደስ ያለመሆኑ ግልጽ ነው። መቅደሱን የሚለካውና ለሕዝቅኤል የሚናገረው "ሰውዬው" የተባለውም ገብቶበታል። በሩ የድንግልናዋ በር ከሆነ መቅደሱ እርሷ መሆኗ ነው፤ ሌሎቹ እንዴት አድርገውሳ ወደ እርሷ ገቡ?

ሕዝቅኤል ያገለገለው የሰሎሞን መቅደስ በፈረሰበትና ሕዝቡ ተማርከው በተጋዙበት ዘመን በመሆኑ እግዚአብሔር ከዚያ የተሻለ፥ የበለጠ፥ የገነነ፥ የከበረ የሚመለክበት መንገድ እንዳለ እያሳየው እንጂ ስለ ማርያም እየነገረው አልነበረም። ማርያም ሌሎች ልጆች ወለደች ማለት ማርያምን የሚያረክስ እንደሆነ የሚታሰብ ስለሆነ ርብርቡ ማርያም ርኩስ እንዳትሰኝ ነው። እንጂ መውለዷ ኢየሱስን አያረክሰውም። ወንድ ያለማወቋ ድንግል መሆኗ ነው። ያለ ዘር መወለዱም ኃጢአት አልባ መሆኑን ይገልጣልና እርሱ ከተወለደ በኋላ ሌሎች ልጆችን ብትወልድ ኢየሱስ በሰውነቱ የሚጨመርበት ወይም ከመለኮቱ የሚቀነስበት ነገር የለም። ልጅ መውለድ ደግሞ እንዴት ነው ማርያምን የሚያረክሳት? ይህ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ፈቃድና ትእዛዝ አይደለም ወይ?

መ/ር ምሕረተአብ ሉቃ. 2፥7 ከተጻፈው በመነሣት 'የበኩር ልጇን ወለደች ይላልና ተከታይ አላት ይላሉ።' በማለት ማርያም ልጆች እንደነበሩአት የሚናገሩትን ወንጌላውያን አማኞች ያወግዛል። እርግጥ በኩር ማለት ማኅጸንን የሚከፍት ሁሉ ነው። ተከታይ ኖረም አልኖረም የመጀመሪያ ልጅ በኩር ነው። በኩር ማለት ቀዳሚ፥ ትልቅ ማለት ነው። ለእንስሳም፥ ለእህልና ለአትክልትም ይባላል። በተለምዶው አገባብ ግን በኩር ተከታይ አለው፤ ማኅጸን የከፈተ ብቻ ሳይሆን ተከታይ ወንድሞችና እኅቶች ያሉትም በኩር መባሉ መነቀፍ የለበትም።

በዚሁ ልክ ደግሞ መስተዋል ያለበት መምህር ምሕረተአብ የበኩር ልጇን ወለደች ማለትን 'ተቀዳሚም ተከታይም የሌለውን አንድ ልጇን ወለደች ማለት ነው።' ብሎ

ደፍኖ እንደዘጋው ቃሉ ያንን የሚያስብል ፈቃድ የሚሰጥ አለመሆኑንም ነው። በኵር ተከታይ ባይኖርም በኵር የሆነውን ያህል ተከታይ ሲኖርም በኵር መባሉ እውን ነው። ወንጌሉን የጻፉልን ጸሐፊዎች፥ 'ተቀዳሚና ተከታይ ያልኖረውን አንድያ ልጇን ወለደች።' ብለው ምነው አልጻፉልን? በጻፉልን ስፍራ ስለ ማርያም እና ስለ ዮሴፍ የተባለው በሉቃ. 2፥7፥ *የበኵር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው፤* እና በማቴ. 1፥25 *የበኵር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው* ነው። የመጀመሪያው ጥቅስ ትኵረት የበኵር ልጇ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ከበኵርነቱ ይልቅ እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ ማርያምን ያለማወቁ ነው። 'እስከ' ለቦታ ድንበርን፥ ለጊዜም ገደብን ያመለክታል።

መ/ር ምሕረተአብ 'እስከ' የሚለው ቃል በኦርቶዶክስ ትምህርት በሁለት እንደሚፈታ ካብራራ በኋላ አንዱ እስከ ተወሰነ እስከተገለጠ ወይም በስፍራው እስከተነገረው ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው እስከ ዘላለሙ ድረስ ነው በማለት ዮሴፍ ማርያምን ያላወቀበትን በሁለተኛው ይመድበዋል። አፈታቱ ጥሩ ይመስላል። እርግጥም እስከ ለእስከ ጊዜ፥ ለእስከ ወዲያኛውም ይሆናል። ግን እስከ መቼ መሆኑን ገላጩ ሁሌም አብሮ ይኖራል። አሁንም ዐውዱ ነው ገላጩ። በዚህ ክፍል 'እስከ' የሚለው አጣማሪ ከጊዜና ከሁኔታ ጋር የተቆራኘ ቢሆንም እርሱ ግን የኖኅ ቁራ የጥፋት ውኃ እስኪጎድል እንዳልተመለሰው 'እስከ' (ውኃው ከጎደለ በኋላም እንዳልተመለሰ ማለት ነው) እንደዚያ ነው። ወይም ሜልኮል ዳዊትን ስለናቀችው እስክትሞት ድረስ አልወለደችም ከሚለው በመነሣት "ታዲያ ከሞተች በኋላ ወለደች ነው?" በማለት በስላቅ መልክ ይህም ከዚያ አንድ መሆኑን ሊያብራራ ሞክሮአል።

በነዚህ ቦታዎች ያለው 'እስከ' እና በጠቅላላውም 'እስከ' የሚለው መስተጻምር በጠቅላላው ዋና አገባቡ በሁኔታዎች የተደገፈና ከዚያ በኋላ የሚለወጥ ግንኙነትን ለመግለጥ ሳይሆን በጊዜው ውስጥ የሆነውን የተፈጸመ ነገር ለመግለጥ ነው። ቁራው አልተመለሰም፤ ለምን? አንደኛ፥ ለምን እንዳልተመለሰ አልተጻፈምና አናውቅም። ሁለተኛ፥ ውኃው ከጎደለ በኋላ ወይም መጉደል ከጀመረ በኋላ መመለስ ለምን አስፈለገው? ሜልኮልስ? ከሞተች በኋላ ወለደች? አልወለደችም። ለምን? ይህ የተፈጥሮ ሕግ አይደለማ? ነገር ግን 40 ዓመት እስኪደፍናት አልወለደችም ብሎ ቢያቆም ኖሮ፥ ከዚያ በኋላ አልወለደችም ብለን መደምደም የአፈታት ደንብ ነው? አይደለም።

'እስከ' ከሚለው ቃል ቀጥሎ ጊዜውን ወይም ቦታውን የሚገድብ ነገር ከኖረ ያ 'እስከ' እስከዚያ ድረስ ብቻ ነው ማለት ነው። መ/ር ምሕረተአብ የገለጠው መዝ. 123፥2 'እስኪምረን' ወይም በማቴ. 28 ጌታ 'እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ' ያሉት

'እስከ' ከ'እስከ' በኋላ ያለውን በግምታዊ ንጽጽር አስገብተን በንድፈ አሳብ የምንናገርበት ሳይሆን እስከዚያ የሚደረገውን መናገሩ አለመሆኑን መረዳት ለምን ይሳነናል? መምህሩ ይህን ደካማ የቃል ጨዋታ ከሚያቀርብና እስከ የጊዜና የዘላለም ብሎ ግልጹን በድፍን ከሚዘጋው 'እስከ'ን በጊዜ መስፈሪያነትም ምነው ያላየው? ለምሳሌ ስለቁራው የተጻፈው 'እስከ' እና እዚያው በዘፍ. 8፥10 እና 12 የተጻፈው 'እስከ' ልዩነታቸው ምንድርነው? 'እስከ' እስከተገለጠበት ጊዜ ያለውን መግለጡ እንጂ በንድፈ አሳብ ከዚያ ስላለፈው አለመናገሩ መሆኑን ማሰብ አያቅትም።

መምህሩ ማርያም አለመውለዷን ሲያጸና፥ 'አዳም ሔዋንን ሕልቃና ሐናን ባወቀበት ሥጋዊ ግንኙነት እስከመጨረሻው እስከ ዘላለም አላወቃትም።' በማለት 'እስከ' የሚለውን እስከመጨረሻው ብሎ ይደመድማል። በደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት እስከ የሚለው ቃል ዐቢይም ደቂቅም አገባብ መሆኑን በመተንተን ቀሪነቱን ሳይለቅ ፍጻሜ በሌለው ነገርም፥ መገሥገሻና መድረሻ ያለውም መሆኑንም ይገልጣል። የወሰዳቸው ምሳሌዎችም የደስታ ተክለ ወልድ ይመስላሉ። እስከ. . . (ለዘላቂ) እና እስኪ. . . (ለወንድ) ወይም እስክ. . . (ለሴት) ደግሞ መድረሻ ያለው መሆኑ ተጽፎአል። የማርያም አለመውለድ እስከምትወልድ ተብሎ ነው የተጠቀሰው።[15]

ይህ አጠቃቀስ ዐውድን አለመከተል ብቻ ሳይሆን አመክንዮንም ያልተከተለ አፈታት መሆኑን ለማየት ከባድ አይደለም። እንደ ምሳሌ በመዝገበ ቃላቱም በመምህር ምሕረተአብም የተጠቀሰው ኖኅ የሰደደው ቊራ የጥፋት ውኃ እስከ ጎደለ ድረስ ወዲያ ወዲህ እየበረረ መቆየቱ ነው። ጉዳዩ የእስከ እና የእስኪ ወይም እስክ ባይሆንም ጉዳዩን ከሁለት ወይ ከሦስት አቅጣጫ እንየው።

አንደኛ፥ ይህ እስከ ሳይሆን እስኪ ነው፤ *ቁራንም ሰደደው፤ እርሱም ወጣ፤ ውኃው ከምድር ላይ <u>እስኪደርቅ</u> ድረስ ወዲያና ወዲህ ይበር ነበር።* ዘፍ. 8፥7። የ1879ኙም የ1954ቱም ትርጉሞች እዲሁ ይተረጉሙታል። እስከሚደርቅ አይደለም። የማርያምም እንዲሁ እስከ አይደለም። እስክ ነው። እስክትወልድ ነው የተሰኘው። *የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው።* ማቴ. 1፥25። እስከምትወልድ አይደለም።

ሁለተኛ እንዲህ ያለው አፈታት ድኩም ነው። እስከ የሚለው ሁሉ ቀጣይ ነው ካልን፥ እዚያው ዘፍ. 8፥10 *ከዚያም በኋላ ደግሞ እስከ ሰባት ቀን ቆየ፤ ርግብንም እንደ ገና ከመርከብ ሰደደ።* የሚለው እስከ ስላለ እስከ ሰባት ቀን ሳይሆን እስከወዲያኛው ነው ልንል ነው? አይደለም።

[15] ደስታ ተክለ ወልድ፤ ገጽ 142።

ሦስተኛ፥ በተጻፈበት ቋንቋ ይህ እውነት እንዲህ ያለ ልዩነት ፈጥሮ የሚያራቅቅ ቃል ነው ወይ? ብለን ብንጠይቅ አይደለም። አይደለም። ἕως (ሄኦስ) የሚለው ቃል እስከ ነው። እስከ መድረሻ አለው፤ ዳርቻ አለው። ቃሉ የተጠቀሰባቸውን ቦታዎች ሁሉ ስንመረምር የምናገኘው እውነት ይህ ነው። ቃሉ 'እስከ' ካለ በኋላ መጨረሻ ሳይሆን የጊዜ ገደብ ማድረጉ ወይም፥ 'እስክትወልድ' ማለቱ እኛ 'እስከ መጨረሻ፥ እስከ ዘላለም' የሚል ቅጥያ እንድንጨምርበት ሙብት ወይም ሥልጣን ይሰጠናል? አይሰጠንም። በቃሉ ላይ ልንጨምርም፥ ከቃሉ ልንቀንስም፥ ቃሉን ልንለውጥም አንችልም። ይህ የመዛግብተ ቃላት ትርጉሙ ካስኬንና ከሄድንበት ነው።

ወንድሞቹስ? መ/ር ምሕረተአብ 'ወንድሞቹ' የሚለው ቃል ፕሮቴስታንቶች የማርያምን ሌሎች ልጆች መውለድ የሚገልጡባቸው ጥቅሶች መሆናቸውን በማስረዳት ጥቂት ዋና ዋና ጥቅሶችን (ማቴ. 12፥46፤ ማቴ. 13፥53-58፤ ሐዋ. 1፥14፤ ገላ. 1፥18-19) ካነበበ በኋላ ወንድሞች የሚለውን ቃል በአራት ተርጉሞ፥ የቅርብ ዘመድ፥ የአገር ልጅ፥ የቤተ ሰብ የአንድ አባት እናት ልጆች፥ የሃይማኖት ጓደኞች እንደሚባሉ ገልጦ፥ "ታዲያ የጌታ ወንድሞች የተባሉት ከነዚህ አራቱ የትኞቹ ናቸው? ቢባል የቅርብ ዘመዶቹ የተባሉት ናቸው። . . . እነዚህ አረጋዊው ዮሴፍ ቀድሞ ከሚች ሚስቱ የወለዳቸው ልጆቹ ናቸው . . . ከጌታ ጋር አብረው ያደጉ በመሆናቸው የጌታ ወንድሞች ተባሉ።" በማለት ይደመድማል። በካቶሊኮች ነገረ ማርያም የቅርብ ዘመዶች፥ የአክስትና አጎት ልጆች ናቸው ነው የሚባሉት። አዲስ ኪዳን የተጻፈበት የጽርዕ ቋንቋ እንዲህ ላለው ዝምድና ቀደም ሲል ἀνεψιὸς (አኔፕሲዮስ) ἀδελφός (አዴልፎስ) እና ἀδελφή (አዴልፌ) የሚለውን ቃል ስጠቅስ እንዳልኩት ራሱን የቻለ ቃል አለው።

መጽሐፍ ቅዱስ ወንድሞች የሚለውን ቃል በሰፊው የሥጋ ላልሆኑ መንፈሳዊ ወንድሞችም ይገለገልበታል። ይህ እውነት ነው። እንዲያውም፥ መምህር ምሕረተአብ ካቀረባቸው አራት መደቦችም ይበልጣል። እስከ 12 የተለያዩ መደቦች ይደርሳሉ፤ ለምሳሌ፥ በግብር የሚመሳሰሉ ወንድም ተሰኝተዋል (ምሳ. 18፥9)፤ የሰው ዘር ሁሉ (ማቴ. 7፥3-5)፤ ጌታም ተከታዮቹን ወንድሞቼ ብሎአል (ዮሐ. 20፥17፤ ዕብ. 2፥13)። ሌሎችም አሉ፤ ይህ ግን ዋናው ነጥብ አይደለም። ዋናው ነጥብ መምህሩ ከነዚህ ብዙ መደቦች አንዱን ብቻ ለይቶ መምረጡና የኢየሱስ ወንድሞች እና እኅቶች የተባሉትን የማርያም እንጀራ ልጆች ማድረጉ ነው። ይህንን ለማድረግ ያስቻለው ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ደግሞ የለም። የለም መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ሌሎች መጻሕፍት ይህንን ይደግፋሉ ያስተምራሉ ካልን ደግሞ ወደ ሥልጣን ጥያቄ ልንሄድ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እና እኩል ሥልጣን ያለው ሌላ መጽሐፍ ወይም መጻሕፍት አሉ ወይ? ይህንን ትምህርት በእውን ያገኘነው ሥልጣን ካላቸው መጻሕፍት ካልሆነ፥ እነዚያ

መጻሕፍት የአዋልድ መጻሕፍት ናቸው? ወይስ ከነዚያም በኋላ የተደረሱ ድርሳናት፥ ተአምራትና መልካ መልኮች ናቸው?

እንዲህ የመሰለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የራቀና አዲስ ትምህርት ሲቀርብ፥ ዮሴፍ አረጋዊ፥ ቀድሞ ያገባና 7 ልጆች ያሉት፥ ማርያምም የ7 ልጆች እንጀራ እናት መሆኗ የተጻፈበት ጠንካራና መጽሐፍ ቅዱስን መገዳደር የሚችል፥ ተረት ያይደለ፥ መቼ፥ በማን፥ ለምን፥ እንዴት እንደተጻፈ፥ ሊፈትሹት ፈቃደኛ የሚሆን ምንጭ መቅረብ ነበረበት፤ አልቀረበም። እንዲያው አድማጩ ወይም ተመልካቹ ሁሉ ዮሴፍ አረጋዊ መሆኑንና ቀድሞ የነበራት ሚስቱ የሞተችበት የነበረ ሰው መሆኑን በደፈናው እንደሚያውቅና እንደሚቀበል በመረዳት ብቻ ዲቪዲው ታትሞ ለሽያጭና ስርጭት ውሎአል። ይህንን ዲቪዲ የሚመለከቱ ይህንን ታሪክ ጨርሶ የማያውቁ መኖራቸው ከግምት ገብቶ መሠረቱ ከምንጩ፥ ምንጩም ከወዴት መሆኑ መቅረብ ነበረበት። አልቀረበም። ፕሮቴስታንታዊ ጅሐድ ተብሎም አይደል ጉዳዩ የቀረበው? ከሆነ እኮ ለተቃዋሚዎቹ አፋቸውን መዝጋት የሚችል ማስረጃና መረጃ መቅረብ ነበረበት። አልቀረበም።

‘ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል።’ የሚለውን ያላወቁ ሰዎች እጮኛን በትክክል እንዳልተረዱ በማብራራት ማርያም የዮሴፍ እጮኛ የተባለችው ለጋብቻ ነው የሚሉትን ወይም የሚለውን ቃል ነቅፎአል። ‘ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል።’ የሚለው ምሳሌ፥ አባባል ነው እንጂ ቃለ እግዚአብሔር አይደለም። እንዲህ ያለ ትርጓሜ ደግሞ የስሕተት ትርጓሜ ስለሆነ ንባብ የገደለውን ይብሱኑ ይቀብራል እንጂ አያድንም። መምህሩ ማርያም እጮኛ የተባለችባቸው ምክንያቶች እንዲህ በማለት ያብራራል፤

1. መቆጠር እንድትችል የትውልድ ሐረግ ውስጥ እንድትገባ፤ [ሌሎች ሴቶች ሐረጉ ውስጥ የገቡት ለመቆጠር ነው? አይደለም።]

2. የአዳምና የሔዋን ልጅ ለመባል የዮሴፍ እጮኛ ተባለች፤

[ባትባልስ የማን ልጅ ኖራለች? ማንስ ፍጡር የአዳምና የሔዋን ዘር አይደለምን? ለዚህ እጮኛ መሆን አስፈላጊ ነው? ያልታጨች ያላገባች የአዳምና የሔዋን ልጅ አይደለችም ማለት ነው? ደግሞስ የአዳምና ሔዋን ልጅ ከሆነች አዳማዊ ፍዳና አብሶ ወይም ጥንተ አብሶ አለባት ወይስ የለባትም? ለዚህ የቀረበው አንዳንዶች ማርያምን የሥላሴ አራተኛ ወይም መለኮታዊ ፍጡር አድርገው ስለሚያስቡ ነው ብሎአል። ማን ነው ማርያምን አራተኛ የሥላሴ አካል ናት ያለ? ለነገሩ ሥላሴና አራት አብረው ይሄዳሉ?]

3. ሳታገባ ጸንሳ ብትገኝ በሙሴ ሕግ መሠረት ስለምትወገር፤

[ከሆነስ እንዳትወገር አረጋዊ ሰውን ማግባቷ ከእርሱ ማርገዟን በማሳየት ወይም በማስገመት እንዳትወገር መሆኑ ነው?]

4. በሚያስፈልጋት ሁሉ የአምላክን እናት እንዲንከባከብ እንዲያገለግል እንዲጠብቅ ብቻ አረጋዊ ዮሴፍ ታጨ።

[ስለዚህ በዚህ ዝርዝር መሠረት የታጨው ወይም እጮኛው ዮሴፍ ነው እንጂ ማርያም አይደለችም ማለት ይቻላል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ አይሁዳዊ ባህል እና የዚያን ዘመኑ ሥርዓት ወደ ጎንም መተው የለበትም። የምትታጨው ሴት ናት። የምትታጨውም ለወንድ ነው። ሆኖም ወንድም ሴትም እጮኛ ይባላሉ፤ ማቴ. 1፥16-24፤ ሉቃ. 2፥4-5።]

ከዚያ በኋላ እጮኛ የሚለው ቃል አልተጠቀሰም (ሕጻኑንና እናቱን ይላል) ለምን? ማርያም ከዚያ በኋላ እጮኛ ልትባል አትችልማ! የትኛዋም ሚስት ሚስት ሆና እጮኛ እየተባለች የምትጠራ የለችም። ትኩረቱ ደግሞ በኢየሱስ ላይ ሆኖ እናቱንና ሕጻኑን ሳይሆን ሕጻኑንና እናቱን ይላል። ይህም ምንም ችግር የለበትም። ሚስትህንና ስላላለ ሚስቱ አይደለችም ለማለት ከሆነ አንድ ማስረጃ ባልተባለው ዝምታ ሳይሆን ባለው ወይም በተባለው እውነታ ነው መፈተን ያለበት። ያላለውማ ቁጥር ስፍር የለውም። ለዚህ አይደል ያላለውን አለ እያሉ ሐሰት የሚፈለፈለው? ሔዋን የአዳም አክስቱ ተብላ አልተጻፈችምና አክስቱ አይደለችም ወይም ማርያምን የዮሴፍ እኅት አላለምና እኅቱ እንዳልሆነች አያችሁ? ብሎ በባዶ ሜዳ መከራከር እንደ ማለት ነው።

በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ በማቴ. 1፥16 እንዲሁም ቁጥር 19-20 ዮሴፍን እጮኛ የሚለው ቃል በጽርዕ ባል (ὁ ἀνὴρ- አኔር)፥ ማርያምን እጮኛህን (τὴν γυναῖκά- ቴን ጉናይካ) የሚለውም ጉኔ የሚለው ቃል ሚስት ሆኖ ሚስትህን የሚል ቃል መሆኑን እንወቅ። በሌሎች ቦታዎች ሚስት የሚለው ቃልና ይህ እዚህ እጮኛ የሚለው ቃል ተመሳሳይ ናቸው። ለምሳሌ፥ ከወንጌሉም ሳንወጣ በሉቃ. 8፥3 ዮሐና የኩዛ ሚስት መሆኗ ተጽፎአል፤ እዚህ ሚስት የተባለው እዚያ እጮኛ የተሰኘው ይኸው ቃል ነው። ተመሳሳይ ቃል ነው። ወይም ሉቃ. 17፥32 'የሎጥን ሚስት አስቡአት' የሚለው ቃሉ አሁንም ይኸው ነው። የሎጥ ሚስት እጮኛው እንዳልነበረች ልጆችም እንደነበሩአቸው እናውቃለን።

ይህ ማለት በማርያም የልዑል ኃይል በጸለላትና በማኅጸኗ ኢየሱስ በኖረ ጊዜ ዮሴፍ እና ማርያም ተጫጭተዋል እንጂ ተጋብተዋል ማለት አይደለም። በአይሁድ ባህል እጮኝነት እንደ ትዳር ያህል ክብደት የሚሰጠው መሆኑ እሙን ቢሆንም ጋብቻው ያልተፈጸመ በመሆኑ ቢለያዩ የፍቺዋን ጽሕፈት ሊሰጣት አይገደድም። ለዚህ ነው በስውር ሊተዋት ያሰበው።

በሉቃ. 2፥4-5 ያለው ከእጮኛው የሚለው ቃል ከላይ ካየነው የተለየ ነው። ይህ ቃል እጮኛም ሚስትም የሚሉት ቃላት አብረው የሚገኙበት ነው። ማርያም የታጨች ሚስት መሆኗን ለመግለጥ ሁለቱም ቃል እንዲህ ተጽፎአል፤ σὺν Μαριὰμ τῇ μεμνηστευμένῃ αὐτῷ γυναικί (ሱን ማሪያም ቴ ሜምኔስቴውሜኔ አውቶ ጉናይኪ)። ሁለቱም ቃላት በአንድ የማይገኙባቸው ጥንታውያን ጽሑፋት አሉ። በብዙዎቹ ጽሑፋት የሁለቱም ቃላት አብሮ መሆን የሚያሳየው ማርያም በዚያን ወቅት በጋብቻ ያልተጠናቀቀ እጮኛ መሆኗን ነው። የአማርኛዎቹ ትርጉሞች ከአባ ሮሜ ትርጉም እስከ መደበኛው ትርጉም ድረስ ሁሉም ሁሉንም እጮኛ ብለውታል። በሉቃ 2፥2-4 ያለው ቃሉ እጮኛ ብቻ ተብሎ ባይተረጎም ካጫት ሚስቱ ወይም ካገባት እጮኛው ጋር እንደማለት የመሰለ ቃል ነው። የሚጋጭ ቢመስልም ቃሉ ቃል በቃል ከተተረጎመ አሳቡ ይህ ነው። እጮኝነት የሚስት ያህል ክብርና ክብደት ያለው መሆኑ በአይሁድ ባህል የታወቀ፥ በሕጋቸውም የተጻፈ ነው፤ ዘዳ. 22። ድንግል ከተደረሰባት የደራሹ ሚስት ትሆናለች፤ ባሏ ሲደርስባት ደግሞ ድንግል ሌላ ወንድ የማታውቅ ድንግል እንድትሆን የሚጠበቅ ደንብ ነው። በሉቃ. 2 ካለው እጮኛ የሚል የግሪክ ቃል የምንረዳው ዮሴፍ አረጋዊ ጠባቂ መሆኑን ሳይሆን ሊያገባ ያጨ መሆኑን ነው። ለአረጋዊ አረጋዊ የሚል ቃል፥ ለጠባቂ ጠባቂ የሚል ቃል፥ ለባለ አደራም ባለ አደራ የሚባል ቃል ጠፍቶ እጮኛ መባሉ ስሕተት አይደለም። ቃሉ እጮኛ ካለ፥ ማንም ሰው፥ እኛም ጭምር፥ አረጋዊና የአደራ ጠባቂ ብለን ልንተረጉም ፈቃድ አልተሰጠንም።

የማርያም ከኢየሱስ ሌላ አለመውለድ በጥብቅ የተገመደ ትውፊት በመሆኑና ይህንን ትውፊት የሚገጥል ማናቸውም ቃል ደግሞ ትርክቱን ፈጽሞ የሚጥለው በመሆኑ ትውፊቱ ከተደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጨረሻው በትጋት የሚጠበቅ ሆኖአል። ማንም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ዓይኖቹ በትውፊቱ ሳይቀልሙ ወንጌልን ካነበበ በግልጽ የሚረዳው እውነት ኢየሱስ የሥጋ ወንድሞችና እኅቶች እንዳሉት ነው። ግልጹ ይህ ነው። ግልጽ የሆነውን መፍታት አያስፈልግም። ግልጽ ስለሆነ አይፈታም!

ወርቃማው የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ደንብ የሚባለው የሚነግረን የሚነበበው ክፍል ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ሌላ ስሜት አለመፈለግን ነው። አይደለም ከተባለ ግን ይህንን ግልጽ ሳለ ምስጢር የተደረገውን ለማብራራት ግልጹ ደፍርሶ እንደማይታይ መደረግ ይኖርበታል። እየሆነ ያለው ይህ ነው። ለማርያም ከሙብቷ የበለጠ ሥልጣን ሰጥተው አሁን ወደ ቀደመው ሰውነቷ መመለስ ነው የቸገራቸው። ይህ ማለት ቤት ለመሥራት ከጣራ ጀምሮ ወደ መሠረት እንደመውረድ ማለት ነው። ማንም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ጠንቅቆ እንደሚያውቀው ለሚያስተምረው ትምህርት መደምደሚያ አበጅቶ ደምድሞ የመደምደሚያውን ማዋቀሪያ ለመሥራት መዋተት ወይም መደምደሚያውን

የሚደግፉ ጥቅሶች ለመፈለግ መልፋትና ጥቅሶቹም እርሱ የፈለገውን እንዲሉ መታገል የለበትም። ብዙ የስሕተት አስተማሪዎች የሚያደርጉት ይህንን ነው። መጀመሪያ መድረሻቸውን መንጥረው ደልድለው ካዘጋጁና ከሠሩ በኋላ ትምህርቱ ሁሉ ወደዚያ እንዲያመራ ያደርጉታል። ለምሳሌ፥ ማርያም ለዘላለም ድንግል ናት የሚለው ትምህርት ከተፈጠረ በኋላ ትምህርቱን የሚደግፍ ወይም የሚያመላክት ጥቅስ መፈለግ ይጀመራል። ካልተገኘም ጥቅሱን እንደምንም አድርጎ ያንን እንዲል ማስገደድ ነው። ያላለውን እንዲል ሲያስገድዱትም ነው የምናየው።

በመጀመሪያ ማርያም ልጆች እንደሌሉአት የተጻፈ ነገር የለም። ከዚህ በታች የሚቀርቡት ጥቅሶች መ/ር ምህረተአብም የጠቀሳቸው ሲሆኑ ልዩነቱ ከድምዳሜ በመነሣት የሚተረጎሙ ሳይሆኑ ራሳቸው ስለራሳቸው እንዲናገሩ የተተዉ ናቸው። ከተበታተኑት ሰፊ ትርጓሜዎች አንዱ ትርጓሜ ብቻውን ተነጥሎ ካልተሰጠው በቀር ከዐውዱ እንደምንረዳው ወንድም ማለት የሥጋ ወንድም ነው። ችግሩ ቃሉ ግልጽ ሳይሆን መቅረቱ ሳይሆን ትውፊትና ተረት ቃሉን በላጭ ሆኖ መገኘቱ ነው። ለተረትና ትውፊት ሥልጣን ሰጥቶ ወደ ባለ ሥልጣኑ ቃል ሲመጡ ሥልጣኑን መግፈፍ አሳፋሪ መስሎ ስለታየ ዓይንን በጨው ታጥቦ ሁለቱንም እንደ ባለ ሥልጣን እያዩ መሳከር ነው።

ኢየሱስ ወንድሞችና እኅቶች እንዳሉት በግልጽ ተጽፎአል፤ ወንድሞቹና እኅቶቹ የተጻፉባቸው ዋና ክፍሎች ከታች ያሉት ናቸው፤

<u>ማቴ. 12፥ 46-50</u> *ገናም ለሕዝቡ ሲናገር፥ እነሆ፥ እናቱና ወንድሞቹ ሊነጋገሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር። አንዱም። እነሆ፥ እናትህና ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል አለው። እርሱ ግን ለነገረው መልሶ፡- እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው። እርሱ ግን ለነገረው መልሶ፡- እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው። በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና አለ።*

<u>ማር. 3፥ 30-35</u> *ርኵስ መንፈስ አለበት ይሉ ነበርና። እናቱና ወንድሞቹም መጡ በውጭም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት። ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበሩና። እነሆ፥ እናትህ ወንድሞችህም በውጭ ቆመው ይፈልጉሃል አሉት። መልሶም። እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? አላቸው። በዙሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩትም ተመለከተና። እነሆ እናቴ ወንድሞቼም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ ነው እኅቴም እናቴም አለ።*

<u>ሉቃ. 8፥ 19-21</u> *እናቱና ወንድሞቹም ወደ እርሱ መጡ፥ ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ሊያገኙት አልተቻላቸውም። እናትህና ወንድሞችህ ሊያዩህ ወድደው በውጭ ቆመዋል*

*ብለው ነገሩት። እርሱም መልሶ፦ እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት እነዚህ ናቸው አላቸው።*

<u>ማቴ. 13፥ 53-58</u> *ኢየሱስም እነዚህም ምሳሌዎች ከጨረሰ በኋላ ከዚያ ሄደ። ወደ ገዛ አገሩም መጥቶ እስኪገረሙ ድረስ በምኩራባቸው ያስተምራቸው ነበር፤ እንዲህም አሉ። ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው? ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም። ኢየሱስ ግን፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።*

<u>ማር. 6፥ 1-6</u> *ከዚያም ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት። ሰንበትም በሆነ ጊዜ በምኵራብ ያስተምር ጀመር፤ ብዙዎችም ሰምተው ተገረሙና። እነዚህን ነገሮች ይህ ከወዴት አገኛቸው? ለዚህ የተሰጠችው ጥበብ ምንድር ናት? በእጁም የሚደረጉ እንደነዚህ ያሉ ተአምራት ምንድር ናቸው? ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር። ኢየሱስም፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም። ስለ አለማመናቸውም ተደነቀ። በመንደሮችም እያስተማረ ይዞር ነበር።*

<u>ዮሐ. 2፥12</u> *ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፥ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ።*

<u>ዮሐ. 7፥ 3-10</u> *እንግዲህ ወንድሞቹ። ደቀ መዛሙርትህ ደግሞ የምታደርገውን ሥራ እንዲያዩ ከዚህ ተነሣና ወደ ይሁዳ ሂድ፤ ራሱ ሊገለጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ የለምና። እነዚህን ብታደርግ ራስህን ለዓለም ግለጥ አሉት። ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበትም ነበርና። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ ጊዜዬ ገና አልደረሰም፥ ጊዜያችሁ ግን ዘወትር የተመቸ ነው። ዓለም እናንተን ሊጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል። እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ፤ እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ ወደዚህ በዓል ገና አልወጣም። ይህንም አላቸውና በገሊላ ቀረ። ወንድሞቹ ግን ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ።*

ሐዋ. 1፥ 12-14 *በዚያን ጊዜ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ እርሱም ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል የራቀ ነው። በገቡም ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስም፥ ያዕቆብም፥ እንድርያስም፥ ፊልጶስም፥ ቶማስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፥ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም። እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።*

ገላ. 1፥19 *ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም።*

በዮሐ. 2፥12 *ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፥ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ።* በሚልበት ወንድሞቹ እና ደቀ መዛሙርቱ ጎን ለጎን የተቀመጡበት ጥቅስ ነውና አንዳንዶች ወንድሞቹን መንፈሳዊ ወንድሞች ብለው ወይም አድርገው እንደሚያቀርቡት መሆን አይችልም። ወንድሞቹ የተባሉት ደቀ መዛሙርቱ ናቸው ከተባለ እዚህ ሁለቱም በግልጽ ተለይተው ተጽፈዋልና። ወንድሞቹ ወንድሞቹ እንጂ መንፈሳዊ ወንድሞቹ አይደሉም። ደቀ መዛሙርቱም ደቀ መዛሙርቱ ናቸው።

በመ/ር ምህረተአብ ከቀረቡት ጥያቄዎች 'ማርያም ልጆች አሏት' ለሚሉ መቅረብ ያለባቸው ጥያቄዎች ተዘርዝረዋል።

ጥያቄ 1. ወንድ ስለማላውቅ ለምን አለች? በዘላለማዊ ድንጋሌ ለመኖር መወሰኗ ካልሆነ? የሚለው ነው። ከጥቅስ ተስፈንጥሮ ትምህርትን መጫን ካልሆነ በቀር፥ ጥቅሱ በስፍራው ሲታይ ማርያም ወደ ፊትም ወንድ ከቶውኑ ስለማላውቅ ወይም ላለማወቅ የወሰንኩ በመሆኔ ማለቷ ሳይሆን ወንድ ስለማላውቅ ማለቷ በዚያ ጊዜ የነበራትን የንጽሕና እና አካላዊ ድንግልና ሁኔታ መንገሯ ነው። በተጻፈበት ቋንቋም ሆነ፥ አማርኛንም ጨምሮ በየትኛውም ጤናማ ትርጉም የቃሉ ግስ ይህንን ጥቅስ `በድንግልና ለመኖር በመወሰኔ` ፈጽሞ አያሰኘውም።

ጥያቄ 2. ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ዮሐንስ እናቱን እንዲወስዳት ለምን ተነገረው ወንድሞች ቢኖሩ መጥተው ምነው እናታቸውን ያልተረከቡት? የሚል ነው። ወንድሞቹ በጌታ ላይ ምን ዓይነት አመለካከት እንደነበራቸው በግልጽ በወንጌላት ተጽፎአል። በመጀመሪያ ይፈልጉት ነበር፤ ኢየሱስ አበደ ብለው ከማርያም ጋር ሊፈልጉትም፥ ሊወስዱትም መጥተዋል (ማር. 3፤ ሉቃ. 8)። አበደ ካሉት ወዲያም አላመኑበትም ነበር (ዮሐ. 7፥5)። እነዚህ የማያምኑ ወንድሞች ናቸው። በእርግጥ ኋላ፥ ከትንሳኤው በኋላ፥ ከማርያም ጋርም አብረው ሆነው የጸሎት ትጉሃን ሆነዋል፤ *እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።* (ሐዋ. 1፥14)። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ባላመኑበት ዘመን ቢሞትና በዚያ

ባይገኙ ወይም ተገኝተውም ከሆነ በአጠገቡ ባይኖሩ ያስገርማል? አያስገርምም። ጌታ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ዮሐንስ በአጠገቡ ቆሞ ነበርና (ዮሐ. 19፥26) ለዮሐንስ አደራ መስጠቱ በማስደነቅ ፈንታ ወንድሞች የሉትምና ለዮሐንስ ሰጣት ያስብላል? አያስብልም። በስቅለቱ ታሪክ ብዙ ሰዎች በዚያ መኖራቸው የተጻፈ ሲሆን ወንድሞቹ መኖራቸው አልተጻፈም። ዮሐንስ ግን ኢየሱስ ከመስቀል ሆኖ ሲናገር በሚሰማበት ርቀት ላይ ነበረ።

<u>ጥያቄ 3.</u> ያዕቆብ ራሱን የጌታ ባሪያ አለ፤ ይሁዳም እንዲሁ ባሪያ አለ እንጂ ወንድም አላለም ስለዚህ ወንድሙ አይደለም፤ ቢሆን ኖሮ ወንድምነት አያሳፍርምና ተኩራርቶ የጌታ ወንድም ለምን አላለም? የሚል ነው። እውነት ነው ያዕቆብ የጌታ ባሪያ ብሎ ራሱን በመልእክቱ ገልጦአል። ይህ የሚያሳየው ወንድም ያለመሆኑን ነው ወይስ ባሪያ መሆኑን ነው? ይህ ጌታ ያኔ ያወቀው ሰው ብቻ የመሰለው ኢየሱስ አለመሆኑን፥ ፈጣሪውና ጌታው መሆኑን ያወቀ ሰው በሥጋ ዝምድናው መመካትን ለመለማመድ እውነት ይደፍራል? በሌላ ቦታ እኮ (ገላ. 1፥19) ያዕቆብ የጌታ ወንድም መሆኑ ተጠቅሶአል። እርሱ ግን ስለ ራሱ ያንን አላለም። አለማለቱ አለመሆኑ ሳይሆን ማንነቱን፥ የራሱንም የጌታውንም፥ ማወቁ ነው።

<u>ጥያቄ 4.</u> ማርያም ከአምላክ እናትነት ወደ ሰው (ሌላ ልጅ በመውለድ ማለት ነው) ወደ ሰው እናትነት የምትወርድ ይመስለናል? የሚል ነው። ይህ ኅሊናዊ ወስሜታዊ (subjective) ወይም የይመስለናል ጥያቄ ስለሆነ የሚመስለንም የማይመስለንም እንኖራለን። ወደ ተጨባጩ መሄድና ከተጨባጩ መንደርደር አለብን እንጂ በይመስለናልማ ስንት ተረት ሲነገረን ኖሮአል! መጽሐፍ ቅዱስና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች የመምሰልና አለመምሰል፥ የስሜታችን ያንን ነገር መቀበልና አለመቀበል ጉዳይ ሳይሆን የተጻፈውና የተላለፈልን እውነት ነው። መ/ር ምህረተአብ ለዚህ ያቀረበው ማብራሪያዎች እንደ ይመስለናል ሁሉ የመምሰል ምላሽ ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ አይደለም።

<u>ጥያቄ 5.</u> ማን የመለኮትን ዙፋን ይደፍራል? የሚል ነው። ማንም በማኅጸኗ ማደር እንደማይችል ማለት ነው። ለዚህም ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ይልቅ በመምህር ምሕረተአብ የተሰጠው ምላሽ መላእክት ወደ ማኅጸኗ ሲገቡና ሲወጡ፥ መቼ እንደገቡና እንደወጡ የማወቋ የሚያስደንቅ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ ነው። እዚሁ ራሱን በራሱ ሲቃረን አላስተዋለውም። ማኅጸኗ ዙፋኑ ከሆነ ወደ ማኅጸኗ መላእክትም ገብተዋል ማለት እኮ ነው። ዙፋን ማለት ንጉሥ የሚቀመጥበትና ተቀምጦ የሚከበርበት ነው። ማኅጸንና ዙፋንን ማገናኘትና ማቆራኘት ቅድም እንደተጠቀሰው የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን መልክ ነው።

<u>ጥያቄ 6.</u> ይህኛው ጥያቄ ሳይሆን ማሳረጊያ ሆኖ የቀረበው ነጥብ ነው። ማር. 6፥1-6 አይሁድ የኢየሱስን ወንድሞችና እኅቶች በመጥቀስ ማንነቱን በመግለጣቸው ይሰናከሉበት ነበር የሚለውን ሐረግ በመውሰድ። እነርሱ እንደዚያ በማለታቸው ተሰናከሉ፤ "እነርሱ ወንድም ነው ብለው በተሰናከሉበት አብደናል እንዴ ወንድም ነው ብለን የምንሰናከለው? . . . እኛ እንዳንሰናከል ወንድሞች ማለት የለብንም!" ብሎ ነበር የመለሰው እና የደመደመው። እውን አይሁድ የተሰናከሉት ኢየሱስን የነያዕቆብና ስምዖን ወንድም ነው ስላሉ ነው? ወይስ <u>የእነርሱ ወንድም ብቻ</u> ነው ብለው በመገመት ጌትነቱንና አምላክነቱን ባለመቀበላቸው? መልሱ ግልጽ ነው። እንደ መምህሩ አገላለጥ አይሁድ የተሰናከሉት ወንድሞች አሉት በማለታቸው ነው። ጌታ የእርሱ ወደሆኑት መጥቶ የገዛ ወገኖቹ አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ግን የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ተሰጣቸው፤ (ዮሐ. 1፥11-12) ነው የተባለው። እነዚህ ካልተቀበሉቱ ናቸው። ያልተቀበሉት ሁሉ የተሰናከሉት ናቸው።

## ማርያም ስለ ራሷ ምስክርነቷ

ሌላው ነጥብ፥ ማርያም ስለራሷ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተናገረችው ነገር፤ እርሷ ስለራሷ የሰጠችው ምስክርነት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምን አለች? ስለራሷ እራሷ የተናገረችውን ጥቂቱን እንይ።

ሉቃ. 1፥29 *እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች።* ይህ ለገብርኤል ሰላምታ የሰጠችው መልስ ነው። በቃል አልተናገረችውም አሰበች እንጂ። ሉቃስ በወንጌሉ መግቢያ እንደጻፈው በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትሎ ነው የጻፈውና ማርያምን ጠይቆ፥ ስለሆነው ነገር ሁሉ ተረድቶ ነው የጻፈው። ስለዚህ ነው ከሌሎቹ ወንጌላት ይልቅ ስለ መጀመሪያው ሁኔታ ይበልጡን በሉቃስ ተጽፎልን የምናገኘው። አሰበች ቢልም የገብርኤል ቃል ውዳሴ አይደለም፤ አምልኮም አይደለም። አንዳንዶች በስሕተት አጋንነው እንደሚናገሩትና እንደሚያስተምሩት ውዳሴ ሳይሆን ሰላምታ ማለቷን ልብ እንበል።

ሉቃ. 1፥38 *ማርያምም፥ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።* ይህ ለራሷ ያላትን ማንነት የሚያመለክት ነው። እነሆኝ የጌታ ባሪያ!

ሉቃ. 1፥46-55 *ማርያምም እንዲህ አለች። ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤* . . . በዚህ ክፍል ማርያም ጌታን አክባሪ መሆኗን፥ መድኃኒት እንዳስፈለጋት የተረዳች፥ በመድኃኒቷም ሐሴት ያደረገች፥ ራሷን ባሪያ ብላ የጠራች፥ ብፅዕት የሆነች ሆና እናያታለን።

በወንጌላት ውስጥ የምናያት የኢየሱስ እናት ማርያም እጅግ ጨዋ፥ ትሑት፥ ከማንነቷ አልፋ ያልሄደች፥ ከተሰጣት አሳልፋና አስበልጣ ምንም ያልተቀበለች፥ ሌሎች እንዲሰግዱላትና እንዲያጥኑላት፥ እንዲሳሏት፥ ምስሏን እንዲስሉና እንዲስሙላት፥ እንዲወድሷት፥ እንዲዘክሯት፥ አማልጂን እንዲሏት፥ እንዲሰፍሩላትና እንዲሠዉላት፥ ፈጽሞም፥ ከቶም፥ አንዴም እንኳ ያላመለከተችና ያልጠየቀች ሴት ናት።

ማርያምን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ የምናገኛት ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደ ደቀ መዝሙር አብራ በጸሎት ስትተጋ ነው። ሐዋ. 1፥14 *እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር* ይላል። እዚህ ሴቶችም ነበሩ፤ የኢየሱስ ወንድሞችም ነበሩ። ቀድሞ ያላመኑበት ወንድሞቹ አሁን ከትንሣኤው በኋላ አምነውበት ይታያሉ። ማርያምም ከእነርሱ ጋር አብራ ሆና በአንድ ልብ ለጸሎት ይተጉ ነበር ተባለ እንጂ ዛሬ በካቶሊክ እና ኦ.ኦተቤ/ክ እንደሚደረገው፥ 'እነዚህ ሁሉ ወደ እርሷ ይጸልዩ ነበር።' አልተባለም።

በዘመናት ውስጥ ማርያም አብራ ትጸልይ ነበር የተባለው ተገልብጦ ሰዎች ወደ እርሷ ሲጸልዩ ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ፈጽሞ ያፈነገጠ እንደሆነ መረዳት አለብን። ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ባህርያት አንዱ ጸሎትን መቀበሉ ወይም ሰዎች ወደ እርሱ መጸለያቸው ነው። መጽጸለይ ያለበት ወደ እርሱ ብቻ ነውና። በብሉይም በአዲስ ኪዳንም ቅዱሳን ወደ እግዚአብሔር ብቻ ጸልየዋል። ወደ እግዚአብሔር ብቻ መሆን ያለበትን ጸሎት ወደ ፍጡር ማቅረድ መለኮትን ማጋራት ነው። ያንን ፍጡርም ማመልኮት ነው። ማምለክም ነው።

# ተአምረ ማርያም ምንድርነው?




ባለፉት ገጾች ነገረ ማርያም በመደዴው ወይም አማካዩ ኦርቶዶክሳዊ ምዕመን ዘንድ ምን እንደሚመስል እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛት የኢየሱስ እናት ማርያም እንዴት በቃሉ ውስጥ እንደተገለጠች ተመልክተን ነበር። ማርያም እግዝእት ናትን? ወላዲተ አምላክ (ወይም የእግዚአብሔር እናት) ናትን? ቤዛዊተ ኩሉ እና እመ ብርሃን ናትን? ኪዳነ ምሕረት ናትን? በእውን አርጋለችን? ማርያም ታማልዳለችን? ለዘላለም ድንግል ናትን? የሚሉትን ጥያቄዎች ከቅዱስ ቃሉ አንጻር፥ ማለትም፥ ስለ ማርያም የተጻፉትንና ማርያምም ስለ ራሷ የተናገረቻቸውን ስፍራዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት መርምረን ነበር።

በቀጣዩ ክፍል ተአምረ ማርያም የተባለውን መጽሐፍ እንዳስሳለን። ይህ ዳሰሳ የመጽሐፉ ቅኝት ብቻ ሳይሆን መጽሐፉን ከደራሲው ወይም ደራሲዎቹ እስከ ይዘቱ ድረስ የማሔስ ጉዳይ ነው። በዚህ መጣጥፍ መጽሐፉን፥ ማለት ተአምረ ማርያምን የሚመለከቱ በርካታ ጥያቄዎችን አነሣለሁ። ከመንደርደሪያ ጥያቄዎች ጥቂቶቹ፥ ተአምረ ማርያም ምንድር ነው? ማን ጻፈው? የት ተጻፈ? መቼ ተጻፈ? ለምን ተጻፈ? የደራሲዎቹ ማንነት በውል ይታወቃል? ወደ ግዕዝ መቼና በማን ተተረጎመ? እርግጥ ወደ ግዕዝ ተተርጉሞአል ወይስ ቀድሞውኑ የተደረሰው በግዕዝ ነው? አሳታሚው ማን

ነው? ይህ መጽሐፍ ውጪያዊ ምስክሮች አሉት? ውስጣዊ ማስረጃዎችስ ምን ያመለክታሉ? ይህ መጽሐፍ እርስ በርሱ ይጋጫል? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርስ ከቶውኑ ይስማማል? ካልተስማማ እንደምን ሊያደርጉት ይገባል? ለመሆኑ ክርስቲያኖች ሥልጣን ያለው ቃል አላቸውን? ክርስቲያኖች ሌሎች መጻሕፍትንም ሆነ ትምህርቶችን መለካትና መፈተሽ ያለባቸው እንዴትና በምን መለኪያ ነው? ከዚህ ሥልጣን ካለው ቃል ጋር የሚጋጩ መጽሐፎችስ ምን መደረግ ይገባቸዋል? የሚሉትንና ሌሎችንም ያካትታሉ።

## ተአምረ ማርያም ምንድርነው?

ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ እንደ ስያሜው ሁሉ ማርያም እንዳደረገቻቸው የሚነገሩ የብዙ ተአምራት መድብል ነው። ከተአምራቱ በጣም ጥቂቱን ሕጻኑ ኢየሱስ ያደረጋቸው ሲሆኑ ብዙዎቹን ማርያምና የማርያም የተለያዩ ስዕሎች ናቸው ያደረጉት።

አንዳንዱ ምዕራፍ ምንም ተአምርነት የሌለበት፥ የተደረጉ ነገሮች የተዘገቡበት ዘገባ ቢሆኑም በእያንዳንዱና በሁሉም ምዕራፎች መግቢያ ወይም አናት ላይ ማርያም ያደረገቻቸው ተአምራት እንደሆኑ በቀይ ቀለም እየተጻፈ በአንቀጽ ተቀምጦአል። ተአምር ባልሆኑት ላይ በአናቱ ላይ የማርያም ተአምር መሆኑን መጻፉ የግድ መሆን ስላለበት የተደረገ ይመስላል። ለምሳሌ፥ ሁለተኛው ተአምር ወይም ምዕራፍ ማርያም ስለ መጸነሷና ስለ ልደቷ የተነገረ ሲሆን ያው የግዴታ ልማድ ሆኖ ክብርት እመቤታችን ያደረገችው ተአምር ተብሎ ተጽፎአል። ይህ ልማዳዊ ብቻ አጻጻፍ ካልሆነ በቀር እንደ ምዕራፍ 2 መግቢያ ማርያም ገና ከመጽጸነሷና ከመወለዷ በፊትም ተአምር ታደርግ ነበርና ከልደቷ በፊትም ቀዳሚ ኅልውና ነበራት ማለትም ሊሆን ነው። አጻጻፉ ይመስላል። ከሆነ ዘላለማዊት ናት ሊሰኝም ይመስላል።

## የመጽሐፉ አሳታሚና ባለቤትስ ማን ነው?

መጽሐፉን ያሳተሙ የተለያዩ አሳታሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እኔ ያነበብኩትን እትም ያተመው ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ሲሆን አሳታሚው አልተጻፈም። ከመግቢያው እንደሚነበበው ግን አሳታሚው ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ነው። ይህ መጽሐፍ በኢኦተቤክ ሰፊ ተቀባይነት ያለው የነገረ ማርያም ሰነድ መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም በማን ቡራኬ መታተሙ አልተጻፈም። በበርካታ የኢኦተቤክ መጽሐፎች እንደሚታየውም የሊቀ ጳጳስ ምስል እና መልእክትም የለበትም። ስለዚህም

አይቶ፥ መርምሮ አጽድቆ ለአንባቢ የተገባ ነው ብሎ ያሳለፈ ተጠያቂ አካል የለውም ማለት ነው።

በእውኑ የኢኦተቤክ ይህን መጽሐፍ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ አድርጋ ትቀበለዋለች? መቼም ከተቀበለችው በቂ የሆነ ታሪካዊ ምንጭ ያለው ሆኖ መገኘት አለበት? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርም መጋጨት የለበትም። ምክንያቱም ማንም ክርስቲያናዊ መጽሐፍ አስተምህሮአዊ ተደርጎ ከተወሰደ ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ እና መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መሆን አለበት። ታሪካዊ ከሆነ ደግሞ ታሪካዊ ብቻ ነውና ሥልጣን ያለው መጽሐፍ መሆን የለበትም። ደግሞም ከዋናው ክርስቲያናዊ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተያይቶ ሊቀበሉት ወይም ሊጥሉት የተፈቀደ መሆን የተገባው ነው። ይህ ማናቸውንም የአዋልድ መጻሕፍት የተመለከተ ነው። የኢኦተቤክ ይህን መጽሐፍ የኔ ብላ ትቀበለው ወይም አትቀበለው እንደሆነም ግልጽ አይደለም። በአንድ ድረ ገጽ ላይ በቅርብ ያነበብኩት ሁለቱ ሲኖዶሶች ከሚነጋገሩባቸው ነጥቦች አንዱ ይህ መጽሐፍ እንደሆነም ነው።[16]

መጽሐፉ አሁን በታተመበት ቅርጹ አማርኛው ከግዕዙ ጋር ጎን ለጎን በመሆን ተጽፎአል። አንዳንዱ የአማርኛ ቃላት ሆን ተብለው የተለሳለሱ ሲመስሉ አንዳንዱን አማርኛ ለመረዳት ደግሞ ራሱ ግዕዙ ለዘመናችን አማርኛ የቀረበ የሚመስልባቸው ቦታዎችም አሉ። አንዳንዱ ጥቅስ ከትርጉም ይልቅ ማብራሪያ የሚመስልባቸው ቦታዎችም ብዙ ናቸው። የተአምራቱ ቁጥራቸውም ከአንዱ እትም ወደ ሌላው ይለያያል ይባላል። እኔ ባነበብኩት የ፲ ፱ ፻ ፺ ፪ ዓመተ ምሕረት እትም መጽሐፍ ተአምራቱ ወይም ምዕራፎቹ 123 ናቸው። አንዳንድ ተአምራት ወይም ምዕራፎች በአንዱ የመጽሐፉ እትም ይገኙና በሌላው እትም የማይገኙ ከሆኑም መጠኑና ይዘቱ ከእትም እትም ይለያያል ማለት ነው።

በመምህር ባዩ ታደሰ መጽሐፍ[17] ውስጥ ከተቀነሱት ተአምራት አንዱን 'ተአምር 97' የተባለውን በመጥቀስ ከቀድሞዎቹ እትሞች በአንዱ (ለምሳሌ፥ ከ1924ቱ እትም) ተጽፎ ከኋለኞቹ እትሞች (ለምሳሌ፥ ከ1989ኙ እትም) እንደቀረ በማውሳት ይህ የሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በግልጽ በመጋጨቱ ምክንያት እንደሆነ ታትቶ ቀርቦአል። ለውጥ የሌለበት ለማስመሰል ግን 'በድጋሚ የታተመ' እየተባለ መቅረቡም ተወስቶአል።[18]

---

[16] ሲኖዶሶቹ ሁለት በነበሩበት ጊዜ ነው። http://www.abaselama.org/2011/11/blog-post.html

[17] በአባቶቻችን አፈርን  የተሰኘው ይህ መጽሐፍ ገድለ ተክለ ሃይማኖትንና ተአምረ ማርያምን የሚያሔስ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ በዚህ መስክ የሚያጠኑ ሰዎች መመልከት ካለባቸው ሥራዎች አንዱ መሆን አለበት።

[18] በአባቶቻቾችን አፈርን፥ ገጽ 109-113።

በሌላ አንድ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰ ተአምረ ማርያም ደግሞ ተአምራቱ አንድ መቶ አሥራ አንድ መሆናቸውን ይጠቅሳል።[19] ቁጥሩ ወጣ ገባ ነው። በአንድ ድረ ገጽ ስለ ተአምረ ማርያም በተጻፈ አጭር መልእክት ላይ ምላሽ ከሰጡት ሰዎች አንዱ ተአምር 19 ላይ ስለ መሐመድ የተጻፈ ነገር እንዳለበት ጠቅሶአል።[20] እኔ ባነበብኩት ምዕ. 19 ማርያም ሙታንን እያስነሳች ለሰዎች ስታሳይ ነው የተጻፈው እንጂ ይህ ስለሌለ በድረ ገጹ የተጻፈው ትክክል ከሆነ ምዕራፎቹ ተሸጋሽገው፥ ታጥፈው፥ ወይ ተሰርዘው ወይም ተጨምረው ይሆናል። ምናልባት አንዳንዱ እትም ምዕራፎቹ እየተመረጡና የሚያጠያይቁት እየተነቀሱ የታተመ ሊሆንም ይችላል፤ ግን ከላይ እንደተጠቀሰው 'በድጋሚ የታተመ' እየተባለ ከውስጡ እየተገመሰ ከቀረ ይህ ስነ ጽሑፋዊ እብለትና አንባቢን መደለል ነው።

## የመጽሐፉ ምንጭ / ደራሲው ማን ነው?

ተአምረ ማርያም በመጀመሪያ በግብጽ አገር ከመዓልቃ ከመንበረ ማርቆስ (እስክንድርያ ማለት ነው) የተገኘ በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈና በኋላ ወደ ግዕዝ ተተረጎመ የተባለ መጽሐፍ ነው። የጻፉት አባ አብርሃም፥ አባ ማርቆስና አባ ማቴዎስ የተባሉ [መነኮሳት] ሲሆኑ የጻፉትም ማርያም፥ አንዳንዴ ራሷ እየተገለጠች፥ ሌላ ጊዜ በሕልም፥ ሌላ ጊዜ በራእይ እየታየች እየተነጋገረቻቸው እንደሆነም በመቅድሙ ተጽፎአል። እነዚህ ሦስት መነኮሳት እነማን ስለመሆናቸው፥ መቼ ስለመኖራቸው፥ የት ስለመኖራቸው፥ የምን አገር ወይም የየትኛው ዐረብኛ ተናጋሪ አገር ሰዎች ስለመሆናቸው የሚናገርም ምንም ማብራሪያ በመጽሐፉ የለም። እነዚህ ጸሐፊዎች እነማን ናቸው ቢባል መታወቂያቸው ቢያንስ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኝ መሆን ነበረበት፤ ግን የለም። ስለዚህ ስለ ደራሲዎቹ የምናውቀው ከስማቸው በቀር ሌላ የለም።

በምዕ. 1 ደቅስዮስ የተባለ ሰው ታሪኳን ሲሰበስብ እንደተገለጠችለትና ስለጻፈላት እንዳመሰገነችውም ተጠቅሶአል። ይህ ደቅስዮስ ሰብሳቢም ጸሐፊም ተብሎአልና እንደ ሰብሳቢ ብቻ ሳይሆን ከነአባ አብርሃም ጋር እንደ ጸሐፊም የሚቆጠር ነው። በምዕ. 6 ደግሞ አንድ ሰው ሌላ መጽሐፍ፥ የፍልሰት መጽሐፍ እንዳገኘ ይናገራል። ቁ. 23 ላይ ይህን የጻፈ ዮሐንስ ነውም ይላል። ቁ. 18 ላይ እርሱ ራሱ የጻፈውን ነገረኝም ይላል። ስለዚህ ከነአባ አብርሃም በፊት የተጻፈ ያውም ዮሐንስ የተባለው ሐዋርያው ዮሐንስ ከሆነ፥ በሐዋርያው ዮሐንስ የተጻፈ የፍልሰት መጽሐፍም የነበረ ይመስላል። በምዕ. 7

[19] ለእውነት እንቁም፥ ገጽ 85።
[20] http://www.abaselama.org/2011/11/blog-post.html

ደግሞ ስንክሳርን በመጥቀስ ያንንም እንደ ምንጭ በመጥቀስ የማርያምን ዕርገት ይተርካል።

ስለ ደራሲዎቹ ከስማቸው ውጪ ከመጽሐፉ ውስጥ የምናገኘላቸው ነገር የለም። ስምና ማዕረግ ብቻ ‘አባ እገሌ’ ተብሎ ከመጠቀሱ በቀር ሌላ ያለመኖሩ ምንጩን ሆን ተብሎ የተድበሰበሰ ያደርገዋል። ‘አባ እገሌ’ ደግሞ የመነኩሴ ሁሉ መጠሪያ ነው። በማን ዘመን መንግሥት ወይም በማን ዘመነ ጵጵስና ነበሩ? የት ነበሩ? እነዚህ ሰዎች ሌላ ምን ጻፉ? ቢባል አጥጋቢ ቀርቶ የማያጠግብም ማስረጃ አይገኝም። ምናልባት ኖሮ ቢሆን ከዚያ በመንደርደር የዘመኑን ታሪካዊ ስነ መለኮት በመቃኘት ነባራዊ እውነታ መጨበጥ ይቻል ነበር፤ ወይም ሌላ የጻፏቸው ሥራዎች ቢኖሩ የሰዎቹን ስነ መለኮታዊ አቋም በንጽጽር መገምገም ይቻል ነበር። ግን እነዚህ ነገሮች የሉም።

የዐረብኛው የምንጭ ጽሑፍም መቼ እንደተጻፈ የሚያረጋግጥ ውጪያዊ ምስክር ወይም ውስጣዊ ማስረጃ አይገኝለትም። ከመጽሐፉ መግቢያ እንደሚገመተው የመጀመሪያውን የጻፉት በዐረብኛ ሳይሆን አይቀርም። እንደሚገመተው ያልኩት ግዕዙ ተተረጎመ የተባለው ከዐረብኛ መሆኑ እንጂ የምንጭ ቋንቋው ዐረብኛ ይሁን ወይም ራሱ ዐረብኛው ከሌላ ቋንቋ የተተረጎመ መሆኑን ስለማይናገር ነው። ከሆነ ዐረብኛ የግብጽ ቋንቋ የሆነውና ቅብጥ ወደ ኋላ ተገፍቶ ከመነጋገሪያ ቋንቋነት የተወገደው ከእስልምናና የዐረቦች ወረራና መስፋፋት በኋላ ስለሆነ ከ8ኛው ምዕት ዓመት በኋላ ይሆናል ማለት ነው። እንግዲህ በዐረብኛ መጻፋቸውና የተገኘው ከግብጽ መሆኑ የኢትዮጵያና የግብጽ አብያተ ክርስቲያናትን ቁርኝት ተንተርሶ አገሩን ግብጽ፥ ዘመኑንም ከእስልምና ወረራ በኋላ ጀምሮ እስከ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ባለው ጊዜ ነው ብሎ ሰፊ ግምት መቸር ይቻላል። በመቅድሙ የተነገረው ይህ የተተረጎመው መጽሐፍ የተገኘው ከመንበረ ማርቆስ መሆኑን ነው።

ትርጉሙስ? ተአምረ ማርያም ተተረጎመ የተባለበት ዘመኑም ተጽፎአል። ግን ዋናው ከተጻፈ ከስንት ዘመናት በኋላ ስለመተርጎሙ ግምትም እንኳ መገመት አይቻልም። ተርጓሚዎቹ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል የተባሉ ናቸው። አሁንም ከስማቸው ውጪ ስለሰዎቹ ከመጽሐፉ ውስጥ የምናገኘው ማንነታቸውን ገልጦ የሚያስረዳ ነገር የለም።

ዘመኑስ? ተረጎሙት የተባለበት ጊዜ “ቆስጠንጢኖስ የተባለ ንጉሣችን በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በነገሠም በ፯ ዓመት” ተብሎ ተጠቅሶአል። ቆስጠንጢኖስ ወይም ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሠው በኛ አቆጣጠር ከ፲፬፻፳፮-፲፬፻፷፩ ዓመተ ምሕረት ነው። የነገሠ 7ኛ ዓመቱ ፲ ፬ ፻ ፴ ፬ ዓ. ም. ነው ማለት ነው። በኋላ ላይ የምንጩን ድፍርስነት በተመለከተ አወዛጋቢና አጠያያቂ ነጥቦች አነሣለሁ። በአጭሩ ግን በመጽሐፉ ውስጥ ከተጻፈው የሚገኘው የተአምረ ማርያም ምንጭ፥ መነሻና የትርጉም ዘመን ይህ ነው።

## የጸሐፊው / የጸሐፊዎቹ ባህርያት

በአንዳንድ መጽሐፎች አንዳንዴ እውስጡ፥ አንዳንዴ በሽፋኑ ስለ ደራሲው የተጻፈ አጭር ወይም ረጅም ታሪክ ወይም ግለ ታሪክ ይገኛል። ከመጽሐፉም ከሌላ ስፍራም ካልተገኘ በመጽሐፉ ውስጥ ከተነገሩት ነገሮች በመነሣት አንባቢው የደራሲውን የተለያዩ የእምነትና ማኅበራዊ አቋሞች እንዲሁም ስነ ልቡናዊ ከባቢና ስፍራ ማወቅ ይችላል። በነጥቦች የተሠራ ስዕል እንደሚስል ልጅ፥ በመጀመሪያ ነጥቦች የነበሩት በኋላ ስዕል ሆነው ይታያሉ።

በተአምረ ማርያም ውስጥ ስለመጽሐፉ ደራሲዎችም ሆነ ተርጓሚዎች ማንነት፥ አገልግሎት፥ እምነት፥ ዘመን፥ ገጠመኝ፥ ቦታ፥ ቤተ ሰብ ወዘተ የተጻፈ ነገር ባይኖርም፥ ከመጽሐፉ በመነሣት ግን ተአምረ ማርያምን የጻፉት ደራሲዎች ወይም ደራሲ እምነቱ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳቱ፥ የታሪክ እውቀቱ፥ ከክርስቶስ ቁርኙቱ፥ ወዘተ፥ ምን እንዲመስል መገንዘብ ይቻላል። ጥቂቶቹ እነዚህ ናቸው።

<u>1. የተአምረ ማርያም ደራሲ እግዚአብሔርን የሚንቅ ሰው ነው።</u>

እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አድርጎ፥ *እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም* ብሏል፤ ኢሳ. 42፥8። በጠቅላላው ኢሳ. 40-45 ያሉት ምዕራፎች ዋና አሳብም እግዚአብሔር እርሱ ብቻውን አምላክ መሆኑ ነው። እርሱ ክብሩን ለሌላና ለተቀረጹ ምስሎች አሳልፎ አለመስጠት ብቻ ሳይሆን የተቀረጹ ምስሎች ፈጽሞም መደረግም የለባቸውም። ከ10ቱ ትእዛዛት 2ኛው ይህ ነው፤ *በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፥ አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም።* ዘጸ. 20፥4። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ግን በግልጽ ይህንን አምላካዊ ትእዛዝ በመተላለፍ የእግዚአብሔርን ክብር ለሌላ፥ ማለትም፥ በፈጣሪ ለተፈጠረች ለማርያም እና በሰዎች እጅ ለተሳሉ የማርያም ስዕሎች ሸንሽኖ አሳልፎ ይሰጣል።

በመጽሐፉ ውስጥ እግዚአብሔር የተገለጠበትን ክብር እና ማርያም የተገለጠችበትን ክብር ስናነጻጽር በጉልህ እግዚአብሔር የማርያም ፈቃድ ፈጻሚ ነው። ወሳኟ፥ አድራጊዋ፥ ቀጪዋ፥ ሸላሚዋ፥ ተበቃይዋ፥ ወደ ሲኦል አውራጇ፥ ከሲኦል ነጣቂዋ እርሷ ናት። አዳምና ሔዋን እና ሰው ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለእርሷ ክብር እንደተፈጠሩ ይናገራል መጽሐፉ።

በመጽሐፉ ውስጥ የሚታዩት የማርያም ስዕሎች እጅ ዘርግተው የመሥራትና የማድረግ፥ አፍ ከፍቶ ድምጽ አውጥቶ የመናገር፥ ብያኔ የመስጠት፥ ሲወጉት የመድማት፥ ተመልሰው ሲለጠፉ ጠባሳ ሆኖ የመቅረት ባህርይ ያላቸው ምስሎች ናቸው። ተአምራት ማድረግ የእግዚአብሔር ጸጋ ቢሆንም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ግን ተአምራት አድራጊው እግዚአብሔር ሳይሆን ማርያም እና ምስሎቿ ናቸው ተአምር አድራጊዎቹ። ከእግዚአብሔር ኃይል እና ከጌታ ከኢየሱስ ስምና ሥልጣን ውጪ ተአምር ከተደረገ የዚያ ተአምርና ምልክት ምንጭ እግዚአብሔር ሳይሆን ሰይጣን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ሰይጣን የጨለማው ዓለም ባለ ሥልጣን ነው፤ ሐዋ. 26፥17-18፤ 2ቆሮ. 2፥11፤ 11፥14፤ ራእ. 12፥9።

## 2. የተአምረ ማርያም ደራሲ መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቅ ሰው ነው።

በተአምረ ማርያም ውስጥ በጣም በጥቂት ቦታዎች አልፎ አልፎ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። እነዚህ የተጠቀሱ ጥቂት ጥቅሶች የተጠቀሱት ያለቦታቸው በመሆኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩና የሚጣሉ ናቸው። መጽሐፉ የተደመደመው ኢየሱስ 18 ዓመቱ ሆኖ በግሪክ አገር ሳለ ሲሆን በወንጌል ውስጥ ያደረጋቸው አንዳንድ ነገሮች ገና አገልግሎቱን ሳይጀምርም እንደተፈጸመ ሆነው ተጠቅሰዋል። የደራሲው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያለው ግንኙነት እነዚህን ጥቅሶች ለሚፈልጋቸው ዓላማ ለመውሰድ ብቻ ይመስላል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና መልእክት ሰው ንጹሕ ሆኖ ተፈጥሮ ሳለ ኃጢአተኛ መሆኑና እግዚአብሔር ይህን የወደቀ ሰው ለማዳን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ያደረገው የማዳን ሥራ ነው። ይህ ደግሞ በጣም ግልጽ ተደርጎ ተጽፎአል። በብሉይ ዘመን ከሲና ኪዳን በፊት በቃል በተነገረና በልቡና ሕግ፥ ከሕገ ልቡና ዘመን በኋላ ደግሞ ሕግ ተሰጥቶ ሰዎች የመዳንን መንገድ የሚሄዱበት ያንን ሕግ በመፈጸም ሆነ። ሕጉም ራሱ ሊመጣ ያለው ነገር ምሳሌና ጥላ ነው እንጂ በዘላቂነት ተጠብቆ የሚዳንበት አልነበረም፤ ዕብ. 10፥1። ያ ሁሉ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ጥላ ሆኖ የሚያመለክተው አካል ነበረ፤ ያም አካል በመስቀል ላይ የሞተው የክርስቶስ መሥዋዕትነት አካል ነው። ወንጌል በአንድ ጥቅስ ቢጠቀስ በዮሐ. 3፥16 የተጻፈው፥ *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና* የሚል ነው።

የተአምረ ማርያም ደራሲ የሸፈነው ትልቅ እውነት ይህ ንጥርና አንጡራው ወንጌል ነው። ተአምረ ማርያም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጻፈው የሰውን ልጆች ለማዳን እግዚአብሔር ያደረገውን እውነት የጋረደ መጽሐፍ ነው። በዮሐ. 14፥6 ጌታ፥ እኔ

*መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም* ያለውን የተጻረረ መጽሐፍ ነው። በሮሜ 10፥13፥ *የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና* የሚለው የምሥራች በሌላ ጫና ተተካ። መንገዱ ኢየሱስ ሳይሆን ማርያም፥ መጠራት ያለበትም የጌታ ሳይሆን የማርያም ስም ተደረገና ተለወጠ። ለዚህ ነው ይህ ደራሲ ደኅንነት የሚገኝበትን መንገድ ያልተገነዘበ፥ መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቅ ሰው ነው ያልሁት። ካወቀ ደግሞ ሳያውቅ የዘላበደ ሳይሆን አውቆ ያሳተ አሳች ነውና የባሰ አጥፊ ነው።

ቀደም ሲል በትንሹ ቢጠቀስም፥ ኋላ እንደምንመለከተው፥ ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት ዘመን ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን እንደልብ የማያገኙበትና የማያስተያዩበት ዘመን ነው። መንፈሳዊ በሚመስል ቋንቋ የተነገረውን ሁሉ እንደ እውነት ለመቀበል ሃይማኖታዊና ስነ ልቡናዊ ጫና የሚደረግባቸውም ስለሆነ እውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይጋጫል ወይስ አይጋጭም የሚለውን የሚጠይቅ አይኖርም። የተማሩት የሚባሉት አለማሳወቃቸው ግን የአዋቂ አጥፊ ያደርጋቸዋል።

ተራው ሕዝብ ሊገባው በሚችለው ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያገኝ በመርዳትና በማስተርጎም ፈንታ፥ ከ1800ዎቹ ጀምሮ ባለፉት 200 ዓመታት ሌሎች ጥረው የተረጎሙት እንኳ እንዳይደርስ ታላቅ ተጋድሎ ታደርግ የነበረችው ቤተ ክህነት መሆኗም አስተዛዛቢ ጉዳይ ነው። ይህ ራሱን የቻለ ሌላ ጉዳይ ቢሆንም እዚህ ያነሣሁት ከሕዝብ መጽሐፍ ቅዱስን አለማወቅና የተጻፈውን ሳያስተያዩ ከመቀበል ጋር መነሣት ስለተገባው ነው። እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ በኢኦተቤክ ስብከትና ትምህርት ለተራው ምእመናን በሚገባቸው ቋንቋ አይሰበክም ነበር። ተርታው ሕዝብ የግዕዝ ቋንቋን ከቶም አያውቅም። ያኔ ይህ ተአምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ በተጻፈበት ዘመንማ ሰው በተስኪያን ገብቶ ግድግዳ ላይ የተሳሉ ስዕሎችን ብቻ 'አንብቦ' ነበር የሚመለሰው እንጂ ሮሜ 10፥17 *እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው* የሚለውን አምኖ እንዲድን የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ አልተደረገም። የምእመናኑ አለማወቅ ብቻ ሳይሆን ያውቃሉ ተብለው ሊያሳውቁ የሚጠበቁትም ከቃሉ ጋር ጀርባና ጀርባ የሆነ እንደዚህ ያለ መጽሐፍ ሲያቀርቡ አሳዛኝ ታሪክ ነው። ምን ይደረግ! ቃሉን አያውቁትም። ቢያውቁት ኖሮ አይቃረኑትም ነበር።

### 3. የተአምረ ማርያም ደራሲ ክርስቲያንና የክርስቶስ ምስክር ያልሆነ ሰው ነው።

በተአምረ ማርያም ውስጥ ክርስቲያናዊ ባህርያት፥ ቃሉን ማንበብ፥ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ፥ ወንጌልን ላልዳኑት ማሳወቅ፥ ክርስቶስን መምሰል፥

የደቀ መዝሙርነት ኑሮ፥ የመንፈስ ፍሬ፥ ጠላትን መውደድ፥ የቅዱሳን በቅድስና መኖርና በእምነት መጽናት፥ ወዘተ፥ አይታዩበትም። ይልቁን፥ በቀል ይታይበታል። የማያምኑትንም፥ በወንጌል እውነት ተመርተው ሊኖሩ የሚወድዱትንም መበቀል ይታዩበታል። ክርስቲያን ክርስቲያን የተባለው የክርስቶስ ስለሆነ ነው። አዳኙ፥ መሪው፥ ጌታው ክርስቶስ ነው። በዚህ መጽሐፍ ግን ማርያም አዳኝ፥ ኮናኝ፥ አጽዳቂ፥ ወደ ሲዖል አውራጅ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት አስገቢ፥ እየተገለጠች መመሪያ የምትሰጥ ሆና ተገልጣለች። ይህ እርሷን ያለምንም ጥያቄ የሚከተል ሰው ክርስቲያን ነው መባል ያለበት ወይስ ‘ማርያን’?

ክርስቶስን የሚያውቅ ክርስቲያን ያለ ልክ ከፍ ያለውን ጌታ ስላወቀ በፊል. 2፥11 *መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው* እንደተባለ እርሱን የሚመሰክር ነው። ደግሞም ጌታ ከማረጉ በፊት በመጨረሻ የተናገረው ቃል፥ *ምስክሮቼ ትሆናላችሁ* የሚል ነው፤ ሐዋ. 1፥8። ክርስቲያን የክርስቶስ ምስክር ነው እንጂ የሌላ የማንም ምስክር አይደለም፤ ሊሆንም የተገባ አይደለም። እንዲህ ያለ መጽሐፍን የጻፉና ያስጻፉ፥ ከተጻፈ በኋላም የሚያሳትሙና የሚያሰራጩ ክፉኛ የሳቱት ክርስቲያን የማን ምስክር የመሆኑን እውነት ባለመረዳት ወይም ተረድተው ከሆነም ለማሳት ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ሳይሆን የሌላ ምስክር መሆን የሐሰት ምስክር ሆኖ መገኘት መሆኑን ባለመረዳት ወይም አውቆ ከሐሰት ጋር ለመቆም ነው።

ምስክር ያየውንና የሰማውን የሚናገር እንጂ ያዩና የሰሙት የጻፉትን የተነገረውን እውነት የሚሸፍን አይደለም። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ግን ጌታ ክርስቶስ ተለጣፊ ሆኖ ነው የሚታየው። ጌታ ከራሱ ጋር ሌላ ደባል የሚያቆምና የሚጋራ አምላክና አዳኝ አይደለም። በነዚህ ጥቂት ጥቅሶች ውስጥ “ብቻውን” የሚሉትን ቃላት እናጢን፤

*<u>ብቻውን</u> አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።* 1ጢሞ. 1፥17።

*ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና <u>ብቻውን</u> የሆነ ገዥ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ፥ ያሳያል።* 1ጢሞ. 6፥15።

*ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም <u>ብቻውን</u> ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ። . . . <u>ብቻውን</u> ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም ይሁን፤ አሜን።* ይሁ. 1፥4፥25።

ይህ ብቻውን የሚል ቃል (μόνος) የሚጋራው፥ የሚዳበለው፥ አብሮት የሆነ የሌለ መሆኑን ገላጭ ቃል ነው። ለደኅንነት ኢየሱስን ከማርያምም ሆነ ከሌላ ከማንም ማዳበል ፍትሕ ሳይሆን ክህደት ነው።

## 4. የተአምረ ማርያም ደራሲ ማርያምን መለኮታዊ ክብርን ለማቀዳጀት የጣረ ወይም እንዲያደርግ ያነሣሡት ሰው ነው።

ምናልባት መጽሐፉ ስለራሱ እንደሚናገረው ከግብጽ ተገኝቶና በዐረብኛ ተጽፎ ከሆነ ክርስቲያኖች ማርያምን እንደ አምላክ ያዩአታል የሚያሰኝ ዐረባዊ ጫና ሊኖርበትም ይችላል። ለምሣሌ፥ በኢስላም ግምታዊ አስተምህሮ መሠረት ክርስቲያኖች አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክን ሳይሆን ማርያምንና ኢየሱስን ከአላህ ጋር እኩል አድርገው እንደሚያመልኩ ይነገራል፥ ተጽፎአልም። 'የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ፥ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? በሚለው ጊዜ (አስታውስ) . . .'[21] በተአምረ ማርያም ደግሞ ማርያም ያላት ሥልጣንና የምታደርጋቸው ትንግርቶች መለኮት ብቻ እንጂ ማንም ፍጡር ሊያደርጋቸው የማይችላቸው ነገሮች ናቸውና እውነትም ከመለኮት ያልተናነሰ ኃይልና ችሎታ፥ ሞገስና ክብር፥ ሥልጣንና ስግደት ተጎናጽፋ ትገኛለች።

እርግጥ ነው ጌታን ያመኑና የሚከተሉ ተአምራትን እንደሚያደርጉ ተጽፎአልና በክርስትና ታሪክ ተአምራት አዲስ አይደሉም፤ መሆንም የለባቸውም። የዚህ የተአምረ ማርያም መጽሐፍ ማርያም ግን የተለየ ነው። የሞተን ማስነሣት አንድ ነገር ነው፤ ግን፥ ለምሳሌ፥ በምዕራፍ 18 እና 19 ውስጥ እንደሚነበበው በደብረ ምጥማቅ ተገልጣ በዚያ የነበሩ ዘመዶቻቸውን ብቻ ሳይሆን ጥንት የሞቱትን ሙታን፥ አዳምና ሔዋንም ሳይቀሩ እያስነሱ አምጥቶ ለተመልካች ማሳየት መለኮትን መጋራት አይባልም? ምክንያቱም ትንሣኤ የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ብቻ ሥራ ነው። ማርያም ይህንና ሌሎችንም ሁሉ የምታደርገው ደግሞ እንደ ጌታ ደቀ መዝሙር በሕይወት ሳለች ሳይሆን፥ ራሷም ከሞተች በኋላ እየተገለጠችና በአካል እየመጣች ነው።

በዚህ በተጠቀሰው ክፍል እንደታየው ያለ ከሞተ በኋላ ከሞት እየተነሣ፥ እየታየ፥ እየዳሰሰ፥ እያቀፈ፥ እየሳመ ገባሬ ተአምራት ሆኖ ከሰው ጋር የተባበረ ኖሮ አያውቅም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ፥ በትንሣኤ አካል ከሞት የተነሣ ጌታ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከዕርገቱ በኋላ እርሱ ራሱም የተገለጠው ለሁለት ሰዎች ብቻ ነው፤ ለጳውሎስና

[21] ቁርዓን፥ ምዕ. 5 (አል-ማኢዳህ) ቁጥር 116።

ለዮሐንስ። ሁለቱም ባዩት ጊዜ ምን እንደሆኑ ተጽፎልናል፤ ሐዋ. 9 እና ራእ. 1። በዚህ መጽሐፍ ውስጥግን ትንሣኤ ሙታን እንደ ቁርስና እንደ ምሳ ተራ ጉዳይ ነው።

በተአምረ ማርያም ጌታ ኢየሱስ በተጠቀሰባቸው ቦታዎች በ97.5% ያህሉ ልጇና ወዳጇ ነው። ፈጣሪዋ፥ አምላኳ፥ ጌታዋ ከመሆኑ ይልቅ ማለት ነው። ይህ ፈጽሞ አልተጠቀሰም ማለት ሳይሆን የተጠቀሰው 1-2% ብቻ ነው። በመጽሐፉ ሁለቱም የቀረቡት፥ ልክ እንደ ስዕሉ ሁሉ፥ እንደ እናትና ሕጻን ልጅ ነው። እናትና ሕጻን ልጅ ብቻ ሲታዩ ክብደትና ክብር የተገባት እናት እንደምትሆን ሆኖ ነው አቀራረቡ። ወደ መጽሐፉ መደምደሚያ አንድ ጊዜ የ5 ዓመት፥ አንዴ የ8፥ አንዴ የ12 ዓመት የተጠቀሰ ሲሆን መጽሐፉ ሲደመደም በመጨረሻው ምዕራፍ ኢየሱስ የ18 ዓመት ልጅና ገና አሁንም የተጠየቀውን አድራጊ ሆኖ ነው። ማርያም የግሪክን አገር መንብኘት መፈለጓን ነግራው እዚያ ወስዷት ታሪኩ እዚያ ይፈጸማል። ከነዚህ የመጨረሻ 4 ምዕራፎች በቀር በመጽሐፉ ውስጥ ኢየሱስ በእናቱ እቅፍ ያለ ሕጻን ነው። ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ እንኳ ሲታይ በሙሉ መለኮታዊ ክብርና ግርማው የሥላሴ አካልነቱ ሳይሆን እንደ ሕጻን ሆኖ ነው።

<u>5. የተአምረ ማርያም ደራሲ ወይም ይህን የመጽሐፉን ይዘት የተቀበሉትና ያስጻፉት ሰዎች በሰይጣን የተታለሉ ሰዎች ናቸው።</u>

በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች፥ 'ታይተዋል፤ ማርያምም ተገልጣ ተናግራቸዋለች፤ የተጻፈውም ነገር በትክክል የታያቸውና የተገለጠላቸው ነው' ተብሎ ቢወሰድ እንኳ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ሰዎችን እውነትና መንገድ ሕይወትም ከሆነው ከክርስቶስ የሚያርቅ ነገር ስላስተላለፉ በማርያም እየተመሰለ የተገለጠ ሰይጣን ያሳታቸው ሰዎች ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

በ2ቆሮ. 11፥14 ሰይጣን ራሱን የብርሃንን መልአክ እንዲመስል እንደሚለውጥ ተጽፎአል። ይህች ተገለጠች የተባለችው ማርያም ሐዋርያት የሰበኩትን እውነተኛ ወንጌል እንኳ ብትሰብክ ይህንም መቀበል ግዴታ አይሆንም፤ ምክንያቱም እውነተኛው ወንጌል ቀድሞውኑ ተሰብኮ፥ ተጽፎ ተላልፎአላ! በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚተላለፈው ትምህርት ደግሞ እውነት ሳይሆን ከእውነት ፈቀቅ የሚያደርግ ነው። ይህን በተመለከተ ጳውሎስ በገላ. 1፥8 *ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን* አለ። አዲስና ወንጌል የሚመስል ግን ያልሆነ ነገር የሚሰብክና ታይቶ የሚገልጥ የዚህ ውግዘት ተሸካሚ ነው። በተአምረ ማርያም የተሰበከውን ወንጌል ሳይሆን ከተሰበከው ወንጌል

የተለየ ነገር ነው የተጻፈው። ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ደራሲና ይህን መጽሐፍ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የሚካፈሉና የሚያካፍሉ ሁሉ የዚህ ውግዘት ተካፋዮች ናቸው።

6. የተአምረ ማርያም ደራሲ ደኅንነትን የማያውቅ ሰው ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ በተለይም በአዲስ ኪዳን በግልጽ ተጽፎልን የምናየው ደህንነት ወይም ድነት ውብ ነው! የእግዚአብሔር ድንቅ የሆነው አሠራሩ፥ ኃጢአተኛውን ሊያጸድቅ አንድያ ልጁን መላኩ፥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በፈንታችን በመስቀል መሞቱና እኛን ከዘላለም ሞትና ከኃጢአት ባርነት ነፃ ማውጣቱ፥ ይህ ድንቅና ክቡር የሆነ ግን ግልጥና ቀላል ሆኖ የቀረበው ሥራው አስገራሚ ነው። አቤት ደኅንነት ውበቱ! አቤት ደኅንነት ግልጽነቱና ቀላልነቱ! አቤት ውስብስብ ያለመሆኑ! አቤት እርግጠኝነቱ!

ደህንነት የሂደት ሳይሆን የቅጽበት ለውጥ ነው። ደኅንነት ይታወቃል፤ አንድ ኃጢአተኛ ሲድን መዳኑን ያውቀዋል። እንዲያውቅ የሚያደርጉት ዋና ዋና ምስክሮች አሉ።

1ኛው የማይዋሽ ቃሉ ነው፤ በዳንንባት ቅጽበት የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፤ ዮሐ. 1፥11-12፤ ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ ይህ ደግሞ የሚታወቅ ነው፤ 1ዮሐ. 5፥12-13።

2ኛ በዳንንባት ቅጽበት በውስጣችን መኖር የጀመረው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክርልናል፤ ሮሜ 8፥14-17።

3ኛው ምስክር የተለወጠ ሕይወታችን ነው። ቀድሞ የነበርነውን አይደለንም፤ ያልነበርነውን ደግሞ ሆነናል።

ሰው ሲድን አቤት እረፍት! አቤት እፎይታ፥ አቤት ሰላም! አቤት ነፃነት! በመስቀል ላይ ከተፈጸመው የጌታ ሥራ የተነሣ ደኅንነት በእምነት ብቻ ነውና በሥራ እግዚአብሔርን አስደስቶ መዳንንና ጽድቅን ለመቀዳጀት መፍጨርጨር የለም። ይህ ደኅንነት ደግሞ ይጠፋል ተብሎ በስጋትና በሰቀቀን ሳይሆን በታማኙ ታምኖ የሚኖሩት ኑሮ ነው። ክርስትና ይህ ቀላል የሆነ ክቡር መዳን ነው። መ/ር ምህረተአብ 'ፕሮቴስታንታዊ ጅሐድ' ብሎ ምላሽ በሰጠበት ስብከት ፓስተር ዳዊት፥ 'አታክብዱብን!' ያለው ይህንን ነው። መዳን ይህንን ያህል ቀላል ሆኖ ነው በአዲስ ኪዳን የቀረበው። ቀላል ነው ማለት ያልተወሳሰበ ነው ማለት ነው። ቀላል ነው ማለት ርካሽ ነው ማለት አይደለም። መዳን ክቡር ዋጋ የተከፈለበት ነውና ርካሽ አይደለም፤ ግን ነፃ ነው! እኛ ልንከፍለው ወይም ልንከፍልበት ስለማንችል ነፃ ነው፤ በጸጋ የሆነ ነጻ ስጦታ።

በተአምረ ማርያም ውስጥ ግን ይህንን ነፃ፥ ቀላል፥ ያልተወሳሰበ፥ የሚያሳርፍ ደኅንነት አናይም። የማናይበት ምክንያት ግልጽ ነው። አንድ ደራሲ የሚያሳየው ያየውን ነው። እነዚህ ሰዎች ይህንን በጸጋው ብቻ መዳንን አልቀመሱም። የተአምረ ማርያሟ ማርያም የመጽሐፍ ቅዱሷ ማርያም ከቶም አይደለችም። ይህች ማርያም የክርስቶስ ማዳን እንዳይታይ መጋረጃ ተደርጋለች። ስለዚህ ኢየሱስን እስከ መስቀሉ እንኳ ሳይሆን እስከ አገልግሎቱም ጅማሬ ሳያደርሱት በእናቱ ስር ያለ ታዛዥ ወጣት አድርገው በ18 ዓመቱ መጽሐፋቸውን ደመደሙ። ደኅንነት ያለው መስቀሉ ላይ ነዋ!

በመጽሐፉ ውስጥ የሚታዩት ሰዎችም መዳንን ያልተለማመዱ በነፍሳቸውም የተቅበዘበዙ ሰዎች ናቸው። በመጽሐፉ ጥላቻ፥ ቂምና በቀል፥ መግደል፥ ፍርሃት፥ የሥልጣን ጥም፥ ውሸት፥ ወዘተ፥ ይታዩበታል። በምዕ. 61 ማርያምም ውሸታም ተደርጋ ቀርባለች። በአንዲት ባልቴት ተመስላ ወደ አንድ ሹም ዘንድ ሄዳ የዋዳ አገር ሴት መሆኗን ነግራው ነበር። የተአምረ ማርያሟ ማርያም መዋሸትም ትችላለች። መቻል ብቻ ሳይሆን ትደሰትበታለች። ስለዚህ የተአምረ ማርያም መጽሐፍ ደራሲ ወይም ፈጣሪ ደራሲዎች የመዳንን ውበት የማያውቁ ሰዎች ናቸው።

7. የተአምረ ማርያም ደራሲ ያልተዋጣለት ልብ ወለድ ደራሲ ነው።

የተዋጣለት ቢሆን መጽሐፉ ልብ ወለድ መሆኑን ይገልጥ ነበር። ነገር ግን፥ መጽሐፉ እውነት ሳይሆን እውነት ተደርጎ ቀርቦአል። እውነት ያለመሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በቀጣዩ ንዑስ ርእስ ይቀርባሉ። በመጽሐፉ ውስጥ ከእውነት ጋር የተጠጋጋው ብቸኛ ታሪካዊ ክፍል በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ለማርያምና ለስዕል፥ ለመስቀልም ስግደት የተገባ አይደለም ብለው ስቃይ የደረሰባቸው ሰዎች (ደቀ እስጢፋኖስ) ጉዳይ የተጻፈበት ተአምር 24 (ወይም ምዕራፍ 24) ብቻ ነው። ለዚያውም ከተሰደዱቱ አንጻር ከተጻፈው ጋር ሲተያይ በውስጡ የተጠቀጠቁ ውሸቶችም አሉበት። በሌሎች ምዕራፎች የተጠቀሱ ታሪካዊ ሰዎችም እንኳ በታሪክ ማኅደር ሲፈተሹ በተአምረ ማርያም የሚታየው ማንነታቸው ከእውነተኛ ማንነታቸው ጋር አይገጥምም።

ተረቶችና የፈጠራ ሥራዎች የእውነት መልክ ሊይዙ የሚችሉባቸው ዘመናት ያኔ ብቻ አይደለም፤ ዛሬም ያው ነው። ለምሳሌ፥ የዳቪንቺ ኮድ የተባለው መጽሐፍ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ እውነትነት ተላብሶ፥ ፊልምም ሆኖ ለተመልካች ሲበቃ ያዩት አላዋቂ ሰዎች ታሪኩ እውነትና ቤተ ክርስቲያን እንዳይወጣ ደብቃ የያዘችው ምስጢር እንደሆነ ሽንጣቸውን ገትረው ተከራክረዋል። በሕይወት ያለው ደራሲ መጽሐፉ ልብ ወለድ መሆኑን እየመሰከረም እንኳ ልብ ወለዱን እውነት ነው ብሎ መከራከር ጅልነት

ሳይሆን እብደት ነው። ተአምረ ማርያምም ሆን ተብሎ ባለበት መልኩ ተጽፎ ካልሆነ ምናልባት በመጀመሪያ እንደ አጫጭር ተረቶች መድብል ተጽፎ ኋላ ማርያማዊ ቀለም የተቀባበት ይመስላል፤ ምናልባት ሊሆንም ይችላል። ግን እውነት ተደርጎ ነው የተወሰደው።

እነዚህ ሰባት ነጥቦች ልናጤናቸው የተገባቸው የደራሲው ወይም የደራሲዎቹ ባህርያት ናቸው። እንደ ደራሲው መጽሐፉ ራሱ ደግሞ ሲፈተሽ ይህ መጽሐፍ የራሱ ውስጣዊ ባህርያት አሉት። በቀጣዩ ክፍል ይህንንም እንዳስሳለን።

## የመጽሐፉ ባህርያት / ይዘት

ራሱን በየጊዜው ለማረምና ለማስተካከል ወይም ከዘመኑ ጋር ለመመሳሰል ከሚጥር በቀር በየትኛውም ሃይማኖትም ይሁን ፍልስፍና ዘንድ አንድ ዋና መሠረታዊ መጽሐፍ ይኖራል። ሌሎች ጥቃቅን መጻሕፍትም ደግሞ ይኖራሉ። ሁልጊዜ ጥቃቅኖቹ የዋናውን አሳብና ፈለግ እየተከተሉ ያንን ያጠነክሩታል፥ ያብራሩታል እንጂ አይቃረኑትም፤ አይጻረሩትም። ዋናው መጽሐፍ ስሕተት ያለበትና የሚስተካከል፥ ወይም በየጊዜው የሚሻሻል ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በጥቃቅኖቹ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት አሳቦች በሙሉ ወይም በከፊል ስሕተት የተገኘባቸው እንደሆነ፥ ወይም ከዋናው መጽሐፍ ጋር የተጋጩ ሆነው ቢገኙ ዋናው ትክክል ጥቃቅኖቹ እንደ ስሕተተኛ ይቆጠራሉ።

ወደ ክርስትና እምነት ስንመጣ ምንጩ መንፈስ ቅዱስ የሆነ አንድ ዋና፥ የማይለወጥ፥ ትክክለኛ፥ ሙሉ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ አለን። ይህ መጽሐፍ ማናቸውም ሌላ መጽሐፍ፥ ስብከት፥ እና ትምህርት ብቻ ሳይሆን አኗኗርም፥ ልምምዶችም፥ የሚፈተሹበት ነው። ይህ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ማንም ክርስቲያናዊ ካባ የደረበ መጽሐፍ ከካባው በታች ያለው ሰውነቱ በዚህ መጽሐፍ መርማሪነት መፈተሽ አለበት።

ተአምረ ማርያም ምንጩ ምንድርነው? ትውፊት ነው ወይስ አፈ ታሪክ? ወይስ ተረት? ለምን ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስ አልሆነም? ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጡ ጥቂት ምንባቦች መጽሐፉን ክርስትና እንዲሸት ተብለው ከዐውዳቸው ተፈንቅለው በውስጡ ተስገዋል። ይህን የሚያህሉ ግዙፍ የስሕተት ትምህርቶች ሲሰጡ በመጽሐፍ ቅዱስ መፈተሽ አያስፈልግም ነበር? ሌሎችም መፈተሻዎች አሉ።

መጽሐፉ እርስ በርሱ ይጋጫል ወይስ አይጋጭም? ከሌሎች መሰል መጽሐፎች ጋርስ ይስማማል ወይስ ይጣላል? በአፈጣጠሩስ ተዓማኒነትን የጨበጠ ነው? ከታሪክና

ከተረት ወደ የቱ ይቀርባል? ወደ የቱስ ያዘነብላል? ታሪካዊ ከሆነ ታሪኩ ከሌላ ምንጭ ጋር ሊስተያይ ይችላል? እነዚህ ጥቂት የመፈተሻ ጥያቄዎች ናቸው።

ተአምረ ማርያምን አንብቤ ከፈጸምኩ በኋላ በውስጡ ካገኘኋቸው ሕጸጾች መካከል ዋና ዋና የምላቸው እነዚህ ናቸው፤

የደፈረሰ ምንጭ፥
የተቃለለ ክርስቶስ፥
የተጋነነች ማርያም፥
የተፈናቀለ ታሪክ፥
የተምታታ ሲያልና መንግሥተ ሰማያት፥
የተጣረሰ ደኅንነትና የተቃወሰ ክርስትና፥
የተላቀቀ መልክዓ ምድር፥
የተዋረደ ጋብቻ፥
ያፈነገጠ ተፈጥሮ።

እነዚህን ነጥቦች በቀጣዮቹ ገጾች በነጥብ በነጥብ አወሳቸዋለሁ። እንዲህ የከፋፈልኩት መጽሐፉን በየምዕራፉ ከመሄድ ይልቅ በነጥብ መሄዱ የተሻለ ሆኖ ስላገኘሁት ነው። ከነጥቦቹ አንድ ሁለቱ በቀደሙት ገጾች የተነካኩ ናቸውና በነዚህ እጀምራለሁ። በየክፍሉ ውስጥ የተወሱት በአብዛኛው ናሙና ምሳሌዎች ናቸው እንጂ ሕጸጾቹ በሙሉ ቢዘረዘሩ በትክክል ራሱን መጽሐፉን የሚያህል ወይም የሚበልጥ ሌላ መጽሐፍ ይወጣዋል።

<u>1. የደፈረሰ ምንጭ።</u>

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የእትሙ አሳታሚው አይታወቅም። መታወቁ መልካም የሚሆነው ጥያቄንና አጠያያቂ ጉዳዮችን ለመነጋገር እንዲያስችል ነው። አሳታሚውን በተመለከተ መጽሐፉ ከእትም ወደ እትም የሚሸጋገረው ከገቢ ምንጭ ጋር በተያያዘ መልኩ ሊሆን ይችላል። የደፈረሰው ምንጭ ግን የመጀመሪያ ደራሲውን የሚመለከት ነው።

የደፈረሰ ሲባል የጠራ ነገር ተቃራኒ መሆኑን ለማሳየት ነው። በዝርዝር እንደምናየው መጽሐፉ ከግብጽ የመነጨ ለመምሰል ያልተሳካ ሙከራ ያደርጋል። በመምህር ባዩ ታደሰ የተጻፈ መጽሐፍ ምንጩን በተመለከተ፥ “በ1989 ዓ.ም. የታተመው ተአምረ ማርያም በዚህ ጊዜ ተጻፍሁ ብሎ በግልጽ ባይነግረንም በውስጡ ከያዛቸው ዘመኑንን ከሚያመላክቱ ታሪኮች ተነስተን ድምዳሜዎች ላይ መድረስ የሚያስችሉንን ፍንጮች ይዟል።” ብሎ ሦስት ትልልቅ ነጥቦችን፥ ማለትም፥ በዘመኑ በርካታ መጻሕፍት

መደረሳቸውን፥ የተተረጎመበትን የአባ ሚካኤልንና አባ ገብርኤልን ዘመነ ጵጵስና፥ በዘመኑ የተደረገውን የነ አባ እስጢፋኖስ ስደት ዘርዝሮ ይህንኑ አሳብ ሲደመድም እንዲህ ይላል፥ "መጽሐፉን ትኩረት ሰጥተን ስንፈትሸው ግን በ15ኛው ክፍለ ዘመን ጳጳሳቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ አከናወኑት የተባለውን ኢትዮጵያዊ ታሪክ በውስጡ ይዞ ስለሚገኝ ከግብጽ ነው የመጣው መባሉን ለማመንና ከዚያ ክፍለ ዘመን በፊት የተጻፈ ነው ለማለት የሚያስችለንን ድፍረት እንድናጣ ያደርገናል።"[22]

ዲያቆን ጽጌ ሥጦታው ባስተማራቸው ትምህርቶች ላይ በኢኦተቤክ ቅዱስ ሲኖዶስ የሊቃውንት ጉባኤ በተደረገበት ሃይማኖታዊ ምርመራ ወይም ክርክር አንዱን የክስ ጥያቄ፥ "ተአምረ ማርያም የተጻፈው አባ እስጢፋኖስን ለመቃወም ነው ብለሃል ተባልሁ" በማለት ያነሣና መጽሐፉ በእርግጥ የተሠራው እዚሁ አገር ውስጥ መሆኑን በዝርዝር መልሶአል። ይህንንና ሌሎችንም ተቀራራቢ ጥያቄዎችንም በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ አካትቶአል።[23]

ተአምረ ማርያም በውስጡ እንደተጻፈው በእርግጥ ከመንበረ ማርቆስ ከተገኘ ከዚያ ወዲህ ወይም ከዚያ በኋላ በመንበረ ማርቆስ ይህ መጽሐፍ መኖሩ የታወቀ ነው ይሆን? ወደ መንበረ ማርቆስ ከመግባቱ በፊትስ የት ነበር? ወይስ እዚያ ነው የመነጨው? የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ይህ መጽሐፍ ኖሮአት ያውቃል? ዋናው ቅጅስ በዚያ ይገኛል? ወይም ይህን መጽሐፍ ንብረቴ ነው ብላ ታውቃለች? በዐረብኛ የተጻፈ ከዚያ በፊት ብዙ መቶዎች ዓመታት ያስቆጠረ የምንጭ መጽሐፍስ አለ? እንዲያው በዐረብኛ ተጽፎ ከሆነ ተብሎ ከታሰበ ለማለት ነው እንጂ የምንጩ ጽሑፍ በግብጽ ስለመኖሩ የሚናገር ምንም አመላካች ነገር በመጽሐፉ ውስጥ የለም። ከግብጽ ውጪ ስለመኖሩም አመልካች ነገር የለም። ቀድሞ ከተጻፈ የኋላ ታሪክን እንደ ታሪክ የመጻፉ አስተዛዛቢነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

የምችለውን ያህል ውጪያዊ ምንጮችን ከመጻሕፍትም፥ ከመረጃ መረብም በመፈለግ ይህንን የአገራችንን ተአምረ ማርያም የሚመስል ወይም እንደ ምንጭ ሆኖ ሊጠሩት የሚቻል ቀራቢ ሰነድ ላገኝ አልቻልኩም። ተገልጠው በድረ ገጾች ከተሰደሩት የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የሰነድ ስብስቦች ውስጥም እንኳ ይህ ተአምር የለም። በዲያቆን ጽጌ መጽሐፍ ውስጥ ተአምረ ማርያም በግብጽ አለመኖሩን በተመለከተ ብዙ ዓመታት (10 እና 13 ዓመታት) በዚያ ተቀምጠው የመጡ መነኮሳት ይህን መሳይ ተአምር [ተአምረ ማርያም] በግብጽ ያለመኖሩን ማረጋገጣቸውን ዘግቦአል።[24] 'ምንጩ ጠፍቶ ቅጅው ብቻ ነው አሁን ያለው ወይም በዚህ ዘመን የቀረው' ካልተባለ ምንጩ ካለበት ተገኝቶ

[22] በአባቶቻችችን አፈርን፥ ገጽ 114-115።
[23] ይነጋል፥ ገጽ 55-59።
[24] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 57።

ቢፈተሽ ስለምንነቱ ከቅጅው ይልቅ እውነቱን የመግለፕ ጉልበት ይኖረዋል። ከሌለም፥ 'ዋናው እነ አባ አብርሃም የጻፉት ከገጸ ምድር ጠፍቶ አሁን የሚገኘው ይህ በእጃችን ያለው የኛ ቅጅ ብቻ ነው' ተብሎም መገለፕ አለበት።

በሌላ ገጽታው ግን ተአምረ ማርያም የተተረጎመ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የተሠራ አገር በቀል መጽሐፍ መሆኑን የሚገልጡ እጅግ በርካታ ማስረጃዎችን በውስጡ የታቀፈ ጽሑፍ ነው። ይህ ማለት የወዲያ ታሪኮች ከግብጽ ከመጡት የተሰሙ ወይም የተነገሩ ሊኖሩ መቻላቸው ሳይዘነጋ ነው። በግብጽ ውስጥ ያሉ ገዳማትና ግልጽና የታወቁ ያልሆኑ ቦታዎችም ጭምር ተጠቅሰዋል። ግብጽና ግብጻውያን ግን እየተደነቁ ሳይሆን እየተወገዙ የተነገረባቸው ታሪኮች ያይላሉ። በአንጻሩ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እየተመሰገኑ ተጽፈዋል። ግብጻዊ ምንጭ ግብጽን ሲያኮስስና ሲያዋርድ፥ ኢትዮጵያን ሲያገንንና ሲያሞግስ ይነበባል። ይህም ገራሚ ነው።

በግብጽ ውስጥ በዐረብኛ ቋንቋ ስለ ማርያም እየተጻፈ <u>የኢትዮጵያ ቦታዎች</u> እጅግ ተዘርዝረው ተጽፈዋል። እነ ሽሬ፥ ተከዜ፥ ዋሊ (ዋልድባ?)፥ ሸዋ፥ ደዋሮ፥ ሙገር፥ ወግዳ፥ መርሐ ቤቴ፥ ኢፋት፥ ትግራይ፥ የረር፥ አግዓዚ፥ ደብረ ብርሃን፥ ዳሞት፥ ጎጃም፥ አክሱም፥ መጠራ፥ ጣና፥ ሀዘሎ፥ ደብረ ወገግ፥ ዝቋላ፥ ወዘተ፥ ተጽፈዋል። <u>የኢትዮጵያ ሰዎች</u> እነ ሠረቀ ብርሃን፥ አስከናፍር፥ ዘሚካኤል፥ ዘርዑ፥ ያሬድ (የመዝሙርና ዜማው ያገራችን ሰው)፥ ዘርዓ ያዕቆብ፥ ዘርዓ ክርስቶስ፥ ዘርዓ ሐዋርያት፥ ወዘተ፥ ተጠቅሰዋል። <u>በኢትዮጵያ የሆነ ታሪካዊ ክስተት</u> ለማርያምና ለመስቀል መስገድ የተገባ አይደለም ያሉ የነ ደቀ እስጢፋኖስ ዝርዝር ታሪክ ሁሉ መጽሐፉ ከውጭ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያ እየዘገበ የነበረ ሳይሆን እውስጥ ሆኖ እየተናገረ ያለ መጽሐፍ መሆኑን ይፋ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ግዛቶች ስሞች እነ ማርያም የኖሩባቸውና ከሄሮድስ ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል ተሰኝቶ ነው። ይህም ራሱ ራሱን ማቆም እስከማይችል ድረስ የገዘፈ ፈጠራ ነው። እውነተኛው ታሪክ የተጻፈው በማቴ. 2፥13-23 ብቻ ሲሆን በትንቢት እንደተጻፈው የሄዱትና <u>የቆዩት በግብጽ፥ የተመለሱትም ከግብጽ</u> ነው። ተአምረ ማርያም ኢትዮጵያ ውስጥ በደብረ መጠራ ሳሉ የሄሮድስ ሞት ተነገራቸው የሚለው ከአዲስ ኪዳን ጋር ይጋጫልና ትልቅ ውሸት ነው። የተመለሱት ከግብጽ እንጂ ከኢትዮጵያ አለመሆኑ በግልጽ ተጽፎአል።

ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኖሮ ቢሆን ማቴዎስ ይህን ለምን አይነግረንም ነበር? ከሆነ ምንም አሳፋሪ ነገር የለበትም። ይህ የተሳገ ትረካ መጽሐፉ እዚሁ አገራችን ተቦክቶ የተጋገረበት አንድ አመላካች ነው። መመለሳቸውን በተመለከተ ማቴዎስ ከግብጽ ሲል ተአምረ ማርያም ከመጠራ (ኢትዮጵያ) ይለዋል። ማቴዎስ ለዮሴፍ ተነገረው ሲል ተአምረ ማርያም ለማርያም እንደተነገራት ያደርገዋል። ማቴዎስ መልአክ በሕልም

ነገረው ሲል ተአምረ ማርያም ገብርኤል ለዮሴፍ ነግሮት ለማርያም ያረጋገጠላት ደግሞ ልጇ ኢየሱስ ነው ይላል። ይህኛው እርስ በርሱም የተጋጨ ነው። እነዚህ ሁለት ምንጮች እንዲህ ከተጣሉ ማን ይደመጥ? ከተረት የሚያንሱ ነገሮች የታጨቁበት ተአምረ ማርያም ወይስ መጽሐፍ ቅዱስ?

እዚህ ተደርሶ ወደ ዐረብኛ ተተርጉሞ እንደገና ወደ ግዕዝ የተመለሰ የግብጽ ደርሶ መልስ ቲኬት ተቆርጦለት ሄዶ እንደመጣ የተደረገ ሥራ ካልሆነ፥ ወይም የጥንት ባላባቶች የአገልግል ምግብ ሲያምራቸው እቤት የተሠራ የአገልግል ምግብ አገልጋይ ተሸክማ በፀሐይ ስትዞር ውላ መልሳ ወደተሠራበት ቤት እንደምታመጣው ዓይነት ካልሆነ በቀር ተአምረ ማርያም የአገር ውስጥ ሥራ ነው። ይህ መጽሐፍ የተፈጠረበት ዘመን አምልኮተ ማርያም የገነነበት መሆኑ የዚህን መጽሐፍ አገር በቀልነት ግልጽ ያደርገዋል። የአገሪቱ ጳጳሳት እየተሾሙ ይመጡ የነበረው ከግብጽ በመሆኑ ግብጻዊ ተጋቦት እንዳለው አይካድም። ግብጽ እየተወገዘችም የግብጽ አንዳንድ ቦታዎች ተጽፈዋል። ግብጻዊ ተጋቦትና ከውጪ የተጫሩ 'ታሪኮች' ይኑሩበት እንጂ ተተረጎመ የተባለበት [ወይም የተጻፈበት] ዘመንና ሁኔታ ምንጩን አገራዊ ያደርገዋል።

ምንጩን አገራዊ ከሚያደርጉት ነገሮች ሌላው፥ በሌሎች አገሮችና ሃይማኖቶች በአፍቅሮተ ማርያምና በአምልኮተ ማርያም በተጠመዱቱ መካከል እንኳ ይህ መጽሐፍ ያለመገኘቱ ነው። አምልኮተ ማርያም ሲባል፥ መች ማርያም ተመለከች? የሚሉ ይኖራሉ። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ለአምላክ ብቻ የሚቀርብ ለገር ለሌላ ከቀረበ ያ አምልኮ ነው። እርግጥ ነው፤ አምልኮት ሳይሆን አክብሮት ነው የምናቀርበው ሊሰኝ ይቻላል። በካቶሊካውያን ዘንድም ይህንን አምልኮት (latria) ሳይሆን አክብሮት (dulia) ነው ይሉታል። ሁለቱም የግሪክ ቃላት ናቸው። ቃላቱ በእንግሊዝኛ worship እና veneration ናቸው። በካቶሊክ እምነት ማርያምን እግዚአብሔር ከሌሎቹ ቅዱሳን ሁሉ ይልቅ የሆነ አክብሮት (hyper veneration) ይገባታል ይላሉ። በቃላት መጫወት እና በተግባር መገኘት የተለያዩ ናቸውና ተርታው አማኝ ምን እንደሚልና ምን እንደሚያደርግ ማየቱ አፍቅሮትና አክብሮት ከአምልኮት ጋር የተቀየጠ መሆኑን ለማየት አዳጋች አይደለም።

የመጽሐፉ ደራሲዎች ሦስት ሆኑና ከዚህ የተነሣ መጽሐፉ እርስ በርስ የሚጋጩ ብዙ ነገሮች ኖረውበታል። ቅራኔዎቹና ግጭቶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን እርስ በርሱም፥ ከታሪክም ጋር ነው። ምናልባት ሲጠናቀቅ አንድ ሰው ነው የደበለውና ቅራኔዎቹን ሳያስታርቅ፥ ግጭቶቹንም ሳይከረክም በእያንዳንዱ ምዕራፍ ጅማሬና ድምዳሜ ተመሳሳይ አንቀጾችን መለጠፉ መጽሐፉ የአንድ ሰው እጅ እንጂ የማኅበር እንዳይመስል አድርጎታል። ሆኖም እንደ ደራሲዎቹ ቁጥር እምነታቸውና መረዳታቸውም የተዛባ ስለሆነ ሳይሆን አይቀርም ውስጣዊ ግጭቶቹ የበዙት።

የተጻፈበት ዘመን የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሠው በኛ አቆጣጠር ከ፲፬፻፳፯-፲፬፻፷፰ ዓመተ ምሕረት ነው። ተአምረ ማርያም ተተረጎመ የተባለበት የነገሠበት 7ኛ ዓመቱ ፲፬፻፵፬ ዓ. ም. መሆኑ ነው። ይህ ዘርዓ ያዕቆብ የማርያምና የመስቀል ስግደትን ተግባራዊ ያደረገ ሰው ነው። ይህ አዲስና ኋላ መጥ ከመጽሐፍ ቅዱስም ያፈነገጠ ትምህርት መሆኑን የተረዱና እንቢ ያሉ እስጢፋኖስ በሚባል መነኩሴ የተመሩ ሰዎች መኖራቸው አበሳጭቶት ዘለፋ እስጢፋ የሚባል መጽሐፍም የጻፈ ንጉሥ ነው። እነ እስጢፋኖስን በመቃወም ብቻ ሳይሆን ሕዝቡንም በጠንካራ ማስፈራራት ለመጠፈር የማርያም አምልኮ አዋጅ ታወጀ። አዋጁ ደቂቀ እስጢፋን የተቀበለ በቤቱ ያኖረ ርስት ያለው ከርስቱ ሊነቀል፥ ሹሙ ከሹመቱ ሊሻር፥ እነዚህ ደቀ እስጢፋ ለድንግል ማርያምና ለአንድ ልጇ መስቀል እንቢ ያሉ ናቸውና አይሁድ እንደሆኑ ቅጣታቸውም ሞት መሆን እንዳለበት ነው።[25]

እውነትም አዋጁ ገዳይ ብቻ ሳይሆን አሰቃይቶ ገዳይም ሆነ። አፍንጫ እየተፎነነ፥ ምላስ እየተቆረጠ፥ በግርፋት፥ በድንጋይ እየተወገሩ፥ የከብት አጎዳ በላያቸው እየተነዳ፥ ማለትም፥ ጉድጓድ ተቆፍሮ ከፊል ሰውነታቸው ተቀብሮ ባልተቀበረው ላይ ከብቶች እንዲሄዱበት ተደርጎ፥ ብዙዎች በስቃይ ሕይወታቸው አለፈ። ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በቂ እውቀት ከሌለ፥ ቃሉን አንብበው መንፈሳዊ ዓይናቸው በርቶ እውቀቱን ያገኙትም ሲጠይቁ ወይም ሲቃወሙ በንጉሥ ሥልጣንና አቀነባባሪነት ይህ ግድያ ከተፈጸመባቸው ሕዝቡ በመንፈሳዊ ጨለማ እየዳከረ ቢኖር ምን ያስገርማል?

ለእንዲህ ያለው አፍቅሮተ፥ አክብሮተና አምልኮተ ማርያም ቀዳሚው ሁኔታ ምን ነበር? የሚለው ጥያቄ ጥናት የሚፈልግና ከዚህ መጣጥፍ አሳብ ያለፈ ጉዳይ ነው። በአጭር ቃል ግን ስለ ማርያምና ወላጆቿ፥ ስለ ኢየሱስ ሕጻንነትና ከዚያ ጋር ስለተያያዙት ነገሮች የተጻፉት በታሪክ የሚታወቁት መጻሕፍት የተጻፉት ማርያም ካረፈች ከ100 ዓመታት በኋላ ነው። ታሪኩን የሚናገሩ በሌሉበት የተፈጠረ ሥራ ነው ማለት ነው። ተአምረ ማርያምማ ራሱም ስለ ራሱ እንደሚመሰክረው ከዚያ መደብ የሚገባም አይደለም፤ ምክንያቱም ይህኛው መጽሐፍ ከእጅግ ብዙ መቶዎች ዓመታት በኋላ የተፈጠረና ማርያም በሕልምና በራእይም እየተገለጠች ያስጻፈችው ነው።

በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከዚያ ዘመን በፊት ኖሮ ያልታወቀ እንዲህ የመሰለ መጽሐፍ ቢጻፍ ወይም ቢተረጎም ግን አይደንቅም። የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከሚታወቅባቸው መልኮች አንዱ የስነ ጽሑፍ ፍንዳታ ነው። ራሱ ንጉሡም አስቀድሞ በገዳም የኖረ መነኩሴ ሲሆን መንግሥት በአጭር ጊዜ ከአባቱ ሞት በኋላ ወደ ወንድሞቹ እየተላለፈ

[25] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋጽዖ፣ ገጽ 70።

ኋላ ከወንድም ወደ ወንድም ልጅ ሲያልፍ ቆቡን ጥሎ ዘውድ ሊደፋ ከምንኩስና ወደ ንግሥና የመጣ ሰው ነው። እንደ ክርስቲያን የተቀደሰ ኑሮ በመኖር ምሳሌ የሆነ ሰው ሳይሆን ደርቦ እያገባና እንደወደደ የኖረ፥ እንደ ክርስቲያን በእግዚአብሔር በመታመን ሳይሆን ጥንቆላን በመፍራትና በመሳቀቅ የኖረ ሰው ነው።[26]

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደ ገዳም ሰውም፥ እንደ ንጉሥም ራሱም እየጻፈም ሌሎችንም እያስጻፈና ከሌሎች ቋንቋዎች እየተተረጎመም፥ በዘመነ መንግሥቱ ዜጋው በግዴታ የሃይማኖትና የጎሊና ጫና እየተደረገበትም ብዙ ሠርቶአል። ከእርሱ ዘመን ቀደም ሲል መጡ የተባሉ ስዕሎችና ግማደ መስቀልም ገናና ሆነዋል። በዘመኑ ለማርያም ስዕል መስገድ የመንግሥት ግዴታ የሆነው። እነ መጽሐፈ ምዕላድ፥ አርጋኖነ ድንግል፥ ይኸው በዚህ መጣጥፍ የምንመለከተው ተአምረ ማርያም፥ ይህን አዲስ ጫና ላለመቀበል በቆረጡት ላይ የተጻፈ ዘለፋ እስጢፋ፥ መጽሐፈ ብርሃን እና መጽሐፈ ጽልመት የተባሉና ሌሎችም በዚህ ዘመን ተጽፈዋል። ለማርያም የተጋነነ አፍቅሮትና ከሁሉ ያለፈ አክብሮት አለመስጠትና ስግደትን የሚጨምር አምልኮትን አለማቅረብ ሃይማኖታዊ ውግዘትን የሚያስከትል ክሕደት ብቻ ሳይሆን ዜጋዊ ወንጀልም ተደረገ። የሚሰግዱና የማይሰግዱትን ለይቶ ለማወቅ ቃፊሮች የቆሙበትና ስለላ የሚደረግበት ዘመንም ነበረ።

ነገረ ማርያምን በተመለከተ እንዲህ የበዙ መጻሕፍት በተደረሱበት ዘመን ላይ ይህም መጽሐፍ ተተረጎመ ሳይሆን ተደረሰ ቢባል ተገቢ ነው። ሃይማኖቱ የንጉሥ ጫና ያለበት ሲሆንና ንጉሡ ራሱም ደራሲ ሲሆን ይህን መሳይ ጽሑፍ የሚያስሸልምና ባለሟል የሚያስደርግ ከሆነ ለመጽሐፉ ፈጣሪዎችም ይህ ዘመን ምቹ ዘመን ነው። ፈጣሪዎች ያልኩት ግብጽ ተጻፈ ወይም ከግብጽ ተገኘ ተባለ እንጂ የዚያ ዘመን ታሪክ በመሆኑ ነው። አንዱ ምዕራፍ ወይም ተአምር 24 የተባለው የዚህ ምስክር ነው።

የተአምረ ማርያም ምዕ. 24 (ወይም ተአምር 24) የተጻፈው ለማርያም፥ ለመስቀልና ለስዕል የማይሰግዱ የተባሉት የአባ እስጢፋኖስ እና የተማሪዎቹ የደቀ እስጢፋኖስ ታሪክ መጽሐፉ ተተረጎመ በተባለበት ዘመን በ፲፬፻፴፬ ዓ. ም. እንኳ ተፈጽሞ ያላለቀና ገና እየተከሰተ ያለ ነገር በመሆኑ ነው። ይህ ገና ያልተፈጸመው ነገር ከብዙ ዓመታት በፊት ግብጽ አገር ተጽፎ መጣና ተተረጎመ ማለት ጥሬ ውሸት ነው። ዘርዓ ያዕቆብን ንጉሣችን እያለ ከተናገረ ደራሲው የዘርዓ ያዕቆብ ዜጋ ነው ማለት ነው። ግብጻዊ ወይም ሶርያዊ ዜጋ እንዲህ፥ 'ንጉሣችን' ብሎ በኃላፊ ጊዜ አይጽፍም። ተርጓሚው የተጻፈውን የሚተረጉም ተርጓሚ እንጂ ያልተጻፈውን ጨማሪ አለመሆኑ የታወቀ ነው።

[26] Tamrat, p.243.

2. የተቃለለ ኢየሱስ ክርስቶስ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናየው ኢየሱስ ለመሞትና ለኃጢአታችን ስርየት ደሙን ለማፍሰስ ከማርያም ሥጋን ነስቶ ሰው የሆነ አምላክና ፈጣሪ ጌታና እግዚአብሔር ነው። ደሙንም በመስቀል አፍስሶ የኃጢአታችንን ስርየት ያስገኘልን፥ በሞቱ ሕይወትን የሰጠን፥ ከሙታንም ተነሥቶ ወደ ሰማይ ያረገና በአብ ቀኝ የተቀመጠ፥ስለ እኛ የሚማልድ ወይም መካከለኛ ሆኖ የቀረበልን፥ ዳግምም ለፍርድ የሚመጣ የሥላሴ አካል የሆነ አምላክና ጌታ ነው።

በተአምረ ማርያም ውስጥ የምናየው ኢየሱስ ከአምላክና ጌታ ይልቅ የተነገረውን በፍጥነት የሚፈጽም ቀልጣፋ ተላላኪና አገልጋይ ሆኖ ነው የቀረበው። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ክርስቶስ የማርያም ልጅ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ እየተባለ እንኳ አልተገለጠም። ትኩረቱ እንጂ ማርያም እናቱ አይደለችም ማለት አይደለም። ኢየሱስ የማርያም ልጅ መሆኑ ወይም ከድንግል ማርያም ሥጋን መንሳቱ እውነት ሳለ ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ ፈጣሪ ነውና የማርያምም ፈጣሪ ነውና፥ ይህንን መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ እውነት ነው። ሥጋ የለበሰው ኢየሱስ እናትነት አንድ ነገር ነው። የዘመን መጀመሪያ የሌለው አምላክ እናትነት ማርያምን ከፍጥረቷ በላይ ሊያደርጋት የተገባ አለመሆኑን ሲል አውስቼአለሁ።

በተአምረ ማርያም ውስጥ ከማርያም ጋር በተጻፈባቸው ቦታዎች ሁሉ ኢየሱስ የማርያም ልጅ ነው። ስትጠራው፥ 'ልጄ ወዳጄ' ብላ ነው። ሰዎች ደግሞ ወደ ማርያም ሲጸልዩ እርስዋን 'እመቤታችን' (እግዝእትነ) ብለው የመለኮት ሥልጣን ሲያቀዳጇት ኢየሱስን ግን በቀጥታ አያናግሩትም፤ እርሷን ነው፥ 'ከልጅሽ ከወዳጅሽ' እያሉ ሲለምኗትና ሲጠይቋት የሚታየው። ጉዳዩና ትኩረቱ ከልክ በላይ ስለጮኸ በጣም ይሰማል።

ኢየሱስ በብዙ የማርያም ስዕሎች ላይ እንደሚታየው የማርያም አራስ ልጅ፥ ጨቅላ ልጅ፥ ወጣት ልጅ፥ ታዛዥ ልጅ፥ አንድ ጊዜም እርሷ የጠየቀችውን ነገር እንቢ ያላለ፥ የተጠየቀውን ሁሉ በቅልጥፍና የሚፈጽም፥ የተሳሳተ ነገር ጠይቃ እንኳ ቢሆን አሳቡን ስለ ልመናዋ ሲል የሚቀይር ለስላሳ ልጅ ነው። አንዳንዴ ኢየሱስን አፈራርታው አሳቡንና ውሳኔውን፥ ፍርዱንም ታስቀይራዋለች። ለምሳሌ፥ <u>ኢየሱስን ክዶ</u> ማርያምን ያመነን አንድ ሰው (ልብ እንበል ኢየሱስን የካደ ሰው ነው።) ይቅር እንዲለው በለመነችው ጊዜ እንደማይሆን ሲነግራት፥ ልብሷን ቀዳ፥ "እኒህን ጡቶቼን እቆርጣቸዋለሁ" ብላ ፍርዱን አስቀይረዋለች፤ ምዕ. ፲፬ን ተመልከቱ። ኢየሱስም አሳቡን ቀይሮ ይቅር አለው።

በታሪኮቹ ሁሉ፥ ከትንሣኤ በኋላ እንኳ፥ ኢየሱስ በሚታይባቸው ጊዜያት ሁሉ እንደ ባለ ግርማ አምላክ ሳይሆን እንደ ሕጻን ሆኖ ነው የሚታየው። እዚሁ ምዕራፍ 110 ላይ እንኳ ኢየሱስ 'ከዙፋኑ ተነሥቶ በደረቷ ላይ ተቀምጦ' ተብሎ ተጽፎአል። በምዕ. 90 ልጇ የተሰቀለባት አንዲት ሴት ማርያም ልጇን ከተሰቀለበት ካላወረደችው እሷም፥ 'ልጅሽን (ኢየሱስን) ከጭንሽ እወስደዋለሁ' አለች። ኢየሱስ ሁሌ በማርያም ጭን ተቀምጦ የሚኖር ብቻ ሳይሆን ነጥቀው የሚወስዱትም ዓይነት ነው። ምንኛ የተዋረደ ዝቅታ ነው!

በምዕ. 43 ጴጥሮስ ለተባለ ቤተ ክርስቲያንን ላነጸ ሰው መልኩ ያማረ ልጅ ሆኖ ተገለጠለት። 'ቤተ ክርስቲያን ያሠራ ሰው' ስለተባለ ምናልባት ከብዙ መቶ ዓመታት መሆን አለበት። በመጀመሪያዎቹ የስደቱ ዘመናት ቅዱሳን የሚሠራ ቤተ ክርስቲያን ኖሯቸው አያውቅም። ከብዙ ዘመናት በኋላ ነው ቢባል እንኳ በዚያን ጊዜ ጌታ ሕጻን አለመሆኑ ግልጽ ነው። ግን ልጅ (የግዕዙ ሕጻን ነው የሚለው) ሆኖ ነው የተገለጠው። ኅብስቱ ሲቆረስ ደግሞ የዚህ ሕጻን ደም ፈሰሰና ታቦቱንና ልብሱን ሁሉ አራሰ። በምዕ. 82 ኢየሱስ በዓለም ሁሉ ገዢ የነበረ ንጉሥ ሳቤላ የምትባል ሴት አስጠርቶ (ሴቲቱ በስም ስትጠቀስ ንጉሡ አልተጠቀሰም፤ ይህ የመጽሐፉ አንድ ደካማ ገጽታ ነው። ንጉሡ ቢጠቀስ ታሪኩ ይታወቅ ነበር። ምናልባት ዘመኑም።) ምክር ሲጠይቅ ሴቲቱ ራእይ አይታ ለንጉሡ አሳየችው፤ ያም ማርያም ሕጻን አቅፋ ነው። ኢየሱስ ሁሌም ሲታይ፥ ዛሬም ጭምር፥ በእቅፍ ያለ ሕጻን ሆኖ ነው ለማርያም አምላኪዎች የሚታየው።

ኢየሱስ የቀረበበት አቀራረብም ከማንነቱ አውርዶ ያቃልለዋል። በተአምረ ማርያም ሕጻኑ ኢየሱስም ሲራገም አይጣል ነው፤ ማርያምም ስትበቀልና ስትራገም የተለመደ መሆኑ በቀጣዩ ነጥብ ይታያል። በምዕ. 101 ቁ. 108፥ ያፈለቀውን ውኃ ለአገሩ ሰዎች መራራ ይሁንባቸው የጠጣውም አይዳን ብሎ ባረከው ይላል። ረገመው ላለማለት ባረከው አሉት እንጂ ቃሉ ግልጽ እርግማን ነው። በቁ. 125 ግመሎችን ድንጋይ ሁኑ ብሎ አደነገያቸው። 'እስከ ዛሬ ድረስ ደንጊያ ሆኑ' ይላል። ኋላ በስደታቸው ዘመን ኢትዮጵያ ቆይተው ሲመለሱ በድንጋዮቹ ነፍስ ተዘርቶባቸው ተመልሰው ግመል ሆነው ዕቃ ተጭነው እንደሄዱ ተጽፎአል። እስከ ዛሬ የሚለው ውስጣዊ መጣረስ መሆኑ ነው። በቁ. 159 ኢየሱስ የግብጽን አገር ምድሩንም ሕዝቡንም መርገሙ ተጽፎአል። ይህ እዚህ መርገም የሚያፈስሰው ኋላ ላይ፥ 'ገና አፉንም አልፈታም' የተባለው ጨቅላ ኢየሱስ ነው። ግጭቱን ብንተወው እንኳ ይህ የተአምረ ማርያም ፈጣሪዎች የፈጠሩት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ያስተማረውም ያደረገውም ጠላትን መርገም ሳይሆን መውደድ ነው። ይህኛው ደግሞ የመካከለኛውና የጨለማ ዘመን ሕዝባዊ ሃይማኖት ፈጠራ ውጤት ነው።

3. የተጋነነች ማርያም።

ተአምረ ማርያም እንደ ስሙ የማርያም ተአምራት መጽሐፍ ነው። ተአምራቱ ብዙና የተለያዩ ናቸው። ማርያም ብቻ ሳትሆን በስሟ የሚደረጉ ነገሮች ሁሉ ክብራቸውና ክብደታቸው እጅግ ነው። ለምሳሌ፥ በተአምር 12 ውስጥ 78 ሰዎች የበላ ጭራቅ ግን በማርያም ስም ውኃ ያጠጣ፥ ሞቶ ወደ ሲዖል እንዲሄድ ጌታ ፈረደበት። ማርያም ቀርባ 78ቱ ነፍሳትና ውኃው በሚዛን ይደረጉ ብላ ተደርጎ የውኃው ክብደት መዝኖ ጌታ አሳቡን ቀይሮ ወደ መንግሥቱ ያስገባዋል። በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠሩ 78 ሰዎች ነፍሳት በማርያም ስም ከተሰጠ ትንሽ ውኃ መቅለላቸው አሳዛኝ ነው።

በምዕራፎቹ ሁሉ ማለት እስከሚቻል ማርያም ከእግዚአብሔር ጋር ተስተካክላ ነው የምትገለጠው። ለምሳሌ፥ በ41፥13 "በእግዚአብሔር አምነው፥ በወለደችውም በእመቤታችን አምነው ከቤተ ክርስቲያን ወጡ።" ይላል። በማን አምነው? በእግዚአብሔርና በማርያም! እዚሁ ምዕራፍ ቁ. 25፥ "እምነቱን በናቱና በእግዚአብሔር ላይ ያደረገ ሁሉ አያፍርምና።" ይላል። እዚህ እንዲያውም ማርያም ቀድማ እግዚአብሔር ተከተለ! በምዕ. 76 ቁ. 15 መነኮሳቱ ሲጸልዩ እግዚአብሔርንና ማርያምን ነው፤ "እንለምንሃለን . . . እንለምናታለን" ያሉት። አንዱ ቄስ ደግሞ የማርያምን ውዳሴ ብቻ እንጂ ሌላ የማያውቅ ነው፤ ምዕ. 76። ይህንን ቄስ ሌላ ካላወቀ እንዳይቀድስ የከለከለውን ኤጲስ ቆጶስ ወደ አገልግሎቱ ካልመለሰው በ30 ቀን ትሞታለህ አለችው፤ ማርያም። እርሱም ከግዝቱ ፈታውና እርሱም ከሰውየው ጋር ማርያምን እያደነቀ አብረው ኖሩ። እዚህ የምትታየው የተአምረ ማርያሟ ማርያም እርሷ እስከተወደሰች ድረስ እግዚአብሔር ባይመሰገንም ደንታ የሌላት ሴት ናት።

በምዕ. 86 ማርያምን፥ 'በፍጹም አሳቧ፥ በፍጹም ልቧ የምትወድ' የተባለላት ሴት ታሪክ ይገኛል። እንዲህ ባለ መውደድ መወደድ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን። በቃሉ (ዘዳ. 10፥12-13፤ ማቴ. 22፥37፤ ማር. 12፥30-32፤ ሉቃ. 10፥27) እንደተጻፈው ሰው በፍጹም ልቡ መውደድ ያለበት እግዚአብሔርን ነውና ማርያም ይህንን ማሳወቅ ሲኖርባት አለማድረጓ ብቻ ሳይሆን የእርሱን ለራሷ መውሰዷ የመለኮትን ፍቅር ማስቀነሷ ነው። በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው ሰው ጠንቋይን ምክር የጠየቀ ሰው ሆኖ ምንም ወንጌል ሳይሰማ፥ ግን የማርያምን ስም ሲነገረው ብቻ በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ ሆነ። ሲሞትም ማርያም ሬሳውን አንሥተው በገዳም እንዲቀብሩት ተናገረችለት።

ማርያም ሰው የሚሞትበትን ቀን የምታውቅም ናት። ከላይ ለቄሱ በ30 ቀን እንደሚሞት ተናግራው እንደነበር አይተናል። ሌላ ምሳሌ፥ በምዕ. 81 አንድ መነኩሴን

በአንድ ሌሊት ተገልጣ ወደ ኢየሩሳሌም ወስዳ አዙራ አስጎብኝታ፥ በዮርዳኖስም አጥምቃ (አጥማቂም ናት) የሚሞትበትን ጊዜ ነገረችው፤ እንደተናገረችው ጊዜ ዐረፈ ተብሎ ተጽፏል። ከእግዚአብሔር በቀር ሌላው የማያውቃቸውን ነገሮችን ካወቀች ሁሉን አዋቂ ናት ማለት ነው? ሁሉን አዋቂ ከሆነች አምላክ ናት ማለት ነው? ይመስላል።

የተአምረ ማርያሟ ማርያም ስትፈልግ ርኅሩኅ ሳትፈልግ በቀለኛ ናት። ለምሳሌ፥ በምዕ 35 አንድ እስላም ዘራፊ የዘረፈው በገዳም የሚኖር ቄስ ወደ ማርያም ስዕል ሄዶ ተማጸነ፤ ወደ ማርያም ሳይሆን ወደ ማርያም ስዕል ነው የሄደው። ጸልዮ ሲወጣ ዘራፊው ወድቆ እጁ ተሰብሮ አጥንቱ ገጦ ወጥቶ አየው። እስላሙ ይቅርታ ሲጠይቀው ሽማግሌው ማርያም ይቅር ብትልህም ባትልህም እንደወደደች አለው፤ ይህ ሰው ቄስ ሆኖ ስለ ይቅርታ አያውቅም። ቄስ ነው እንጂ ክርስቲያን አይደለም ማለት ነው። ክርስቲያን ቢሆን ክርስቶስን ሊመስል ይሞክር ነበር። ሲጀመርም ወደ ማርያም ስዕል አይሄድም ነበር። ማርያምም በስዕሉ አድርጋ፥ 'በቄሱ ላይ ደፍሯልና ይቅርታ አይገባውም' አለች። ስለዚህ እስላሙ ወንጌልም ሳይሰማ፥ ይቅርታም ሳያገኝ ሞተ። የተአምረ ማርያሟ ማርያም ስለ ይቅርታ የምታውቀው እንደ ስሜቷ ብቻ ነው። በ33፥ 39 ላይ ማርያም፥ 'የይቅርታ ሳጥን' ተብላለች እዚህ ግን ተቃራኒ ናት። እዚህ ግን ሳጥን ሳይሆን ሳጥናኤልን መሳይ ሆና ነው የምትታየው። በቀለኛና ባህርይዋ በሁኔታ ላይ የሚደገፍ ነው።

በምዕ. 39ም በቀለኛ ማርያም ትታያለች። ሌላ እስላም ዘራፊ ገዳም ዘርፎ ሲሄድ ሰዎች አግኝተው ገደሉት፤ ከቤተ ሰቡ 10 ሰዎች ከዘመዶቹ 18 ገደሉና የተዘረፈውን አምጥተው ለገዳሙ ሲመልሱ በቁ. 35፥ "ልቡናችንን እርሱን ለመግደል ያነሳሣችን ማርያም እንደሆነች ፈጥነን አወቅን" አሉ። ቁጥር 26 ላይ ለመግደል ያነሣሳቸውን "በበረሃ ያለው መጣብን" ነው ያሉትና ማርያምና በበረሃ ያለው ያሉት እነዚህ ሁለቱ አንድ ናቸው ማለት ነው። የተአምረ ማርያሟ ማርያም ሰዎችን አስነሥታ ታስፈጀለች። የሚያሳዝነው፥ 'መነኮሳቱም በዚህ ነገር ፍጹም ደስታ ተደሰቱ' የሚለው ነው። ኃጢአተኛ ሲድን ሳይሆን ሲሞት የሚደሰቱ መነኮሳት ወንጌልን ያውቃሉ ይባላል? በምዕ. 98 ከአንድ ሽማግሌ አስተማሪያቸው ጋር ፍልሰቷን ለማክበር ሲሄዱ አስተማሪያቸውን ወደ ገደል የጣሉ 40 ተማሪዎችን በእሳት ጦር እየወጋ የሚገድላቸው መልአከ ሞት አዘዘችና በአንዴ አለቁ። ሽማግሌውን ግን ወደ በዓሏ መከበሪያ ቦታ አደረሰችው። በምዕ. 15 አንድ ግመል ጫኝን ጎድኑን ወግታ ስትገድለው ትታያለች። ደራሲዎቹ ማርያምን በቀለኛ ሲያደርጓት እርሷን ለማግነን ሲሉ አስቀያሚ ቀለም እየቀቧት መሆናቸውን እንኳ አያውቁም። ወይስ አውቀው ነው ያደረጉ ያሉት?

የተአምረ ማርያሟ ማርያም በቀለኛ ብቻ ሳትሆን ቀናተኛም ናት። በምዕ. 92 የአንድ ንጉሥን ወጣት ልጅ እርሱ ከሚወዳት የበለጠ እርሷ እንደምትወደውና እንደምትቀናበት፥ ሚስት ሳያገባ እንዲኖርም እንደመከረችውና በእጇ ስዕሏን እንደሰጠችው ተጽፎአል። ንግግራቸው የሁለት ፍቅረኞች ንግግር ይመስላል። ልጁ ሲሞትም ብዙ መላእክት እና ደም ግባቷ ያማረች ማርያም መጥተው በሰው ሁሉ እየታዩ ይዛው ሄደች። ይዛው ከሄደች ወጣቱም ፈለሰ ማለት ነው? ደግሞስ ደም ግባቷ ያማረች ወጣት ሆና መምጣቷ ምን ምስጢር ይኖረው ይሆን?

በእግዚአብሔር የተደነገገ ጋብቻ የተናቀበትና የተዋረደበት እንደዚህ ያለ መጽሐፍ አላነበብኩም። ያላገቡ እንዳያገቡና ድንግልናቸውን ለማርያም ስዕለት አድርገው እንዲሰጡ የሚበረታቱበት ብቻ ሳይሆን የተጋቡ እንኳ ከተቀደሰ መኝታ የሚከለከሉበት ነው። መመነን፥ መመንኮስ፥ ተሰባስበው በገዳም መኖር በመጽሐፍ ቅዱስ የተደነቀና የተመሰገነ ልምድ አይደለም። ፈጽሞም አይደለም። ምንኩስናና ገዳማዊነት በክርስትና ታሪክ ውስጥ ብቅ ያለው ቤተ ክርስቲያን ከምድራዊ መንግሥት ጋር እንደ ውኃና ወተት በተደባለቀችባቸው ዘመናት ከምድራዊ ርኩሰትና መንግሥታዊ ሃይማኖት ጋር ላለመርከስ የተደረገ ሽሽት ነው። በዚህ መጽሐፍ ግን ነባር ልማድ ብቻ ሳይሆን የተሞገሰ አኗኗር፥ እጅጉን የተጋነነ ሥርዓትም ሆኖ ቀርቧል።

ተአምራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜያት የተደረጉ ሲሆን የተአምራት ዋነኛ ግብ <u>የእግዚአብሔር ክብር</u> ነው። በተአምረ ማርያም በተደረጉት ተአምራት ግን ክብር ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ከቶም አይታይም። እያንዳንዱ ምዕራፍ ሲጀምር የእመቤታችን ተአምር . . . ብሎ ይጀምርና ሲጨርስ በረከቷና . . . ይደርብን ይላል። ሲጀምር ማርያም፥ ሲጨርስ ማርያም። ክብር ለማርያም እንጂ ለእግዚአብሔር የሚባል ቋንቋ በመጽሐፉ ውስጥ የለም።

የኢትዮጵያ ሰዎች ለማርያም የተሰጡ አስራት ሆነው ቀርበዋል። ይህ አጠያያቂ ቃል ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ነው 1/10ኛ የሆኑት? 9ኙ እነማን ናቸው? ሕዝብ አስራት ተደርጎ የተሰጠበት ታሪክ ኖሮ ያውቃል? እንኳን ሕዝብ በሙሉ ይቅርና ከአዳም ጀምሮ ፈቃድ ያለው አንድ ሰውስ ያለ ፈቃዱ በመንፈሱ ላይ ሌላ ሊሰለጥን ይገደዳል? ደግሞስ አስራት ሰጪው ኢየሱስ ተቀባይዋ ማርያም ከሆነች ምን እየተነገረ ነው? አስራትን ማን ለማን ነው የሚሰጠው? አምላክ አስራት ሰጪ ማርያም ደግሞ አስራት ተቀባይ ከሆነች ማርያምን መለኮት ማድረጋቸውም አይደል? ከመለኮትም በላይ እንጂ! በተለይም ሰጪው ከመለኮት ዝቅ ብሎ መዋረዱም አይደል? እግዚአብሔር ነዋ አስራት ሰጪው።

በምዕ. 84 ሰንበትን የሻረ አንድ አገልጋይ ድዳ ሆነ። ጌታው ወደ ማርያም ጸለየና ፈወሰችው። የተሻረው ሰንበት ነው። የምትጠየቀው ደግሞ ማርያም ከሆነች እርሷ

የሰንበት ባለቤት ናት ማለት ይመስላል። በምዕ. 110 ቀደም ሲል የጠቀስኩት እግዚአብሔርን ክዶ ማርያምን ግን አልክድም ያለ ሰው በማርያም ኢየሱስን አስፈራሪነት (እነዚህን ጡቶቼን እቆርጣቸዋለሁ ብላ በማስፈራራቷ) ይቅርታ ሲያገኝ ይታያል። እግዚአብሔርን ክዶ ማርያምን ማምለክ ክቡር ቦታ አግኝቶአል። ጌታን ክዶ ማርያምን አለመካድ ወይም ማምለክ ማንን የማግነን ጉዳይ ነው? በጣም ግልጽ ነው። እንዲህ ያለ እኩይና የክሕደት መጽሐፍ ነው ተአምረ ማርያም።

የተአምረ ማርያሟ ማርያም ማዕረጓ ብዙ ነው። እመቤት ናት፤ የአርያም ንግሥት ናት ወዘተ፤ ችሎታዋ ድንቅ ነው፤ ተፈጥሮ በቁጥጥሯ ስር ነው፤ ተአምራት ታደርጋለች፤ በሰው ልብ የታሰበውን ታውቃለች፤ በሞትም ላይ ሥልጣን አላት፤ ወዘተ፤ ሥልጣኗ የመለኮት ነው፤ መላእክት ይገዙላታል፥ ፍጡራን ሁሉ ያገለግሏታል፤ የመመረቅ፥ የመርገም፥ የመግደል፥ ከሞት የማንሣት፥ ከእግዚአብሔር ጋር በእኩል የምትለመንና የምትመሰገን ናት፤ ወዘተ። ተአምረ ማርያም እንዲህ በመሰሉ ማርያምን በመጽሐፍ ቅዱስ ካላት ትክክለኛ ስፍራ ፈንቅሎ፥ ተገቢ ቦታዋን ነጥቆ፥ ያልሆነችውን አድርጎ፥ ያልተሰጣትን ሰጥቶ፥ ያልለበሰችውን ደርቶ የሚጸለይላት፥ የምትለመን፥ የምትመለክ አድርጎ መለኮታዊ ማዕረግ፥ ችሎታ፥ ሥልጣንና ኀልውና ሰጥቶአታል።

አንዳንድ ሰዎች ማርያምን እንደሚያከብሩ እንጂ እንደማያመልኩ የሚናገሩት የቃል ጨዋታ ነው። ይህንን ቀደም ሲል በመጠኑ ተመልክተነዋል። መጽሐፍ ቅዱስን እየጠሉ ራዕየ ማርያምን በቃል እየሸመደዱ "እንወዳታለን እንጂ፥ እናከብራታለን እንጂ፥ የጸጋ ስግደት እናቀርብላታለን እንጂ . . . አናመልካትም" ማለት የራስ ድለላ ነው። ከላይ እንደጠቀስኳቸው ያሉቱ ምዕራፎች የሚናገሩት እየተከበረች ሳይሆን እግዚአብሔርን ተክታ እየተመለከች መሆኗን ነው። ደግሞ ማክበርስ ከሆነ መከበር የሚገባው ማን ብቻ ነው? ይህ እኮ አንድን ባለሙያ ሰው ለማድነቅና ለማመስገን ከስዕሎቹ ወይም ከቅርጾቹ አንዱ ፊት ሄጄ ለሥራው ውጤት ምስጋናና ውዳሴን ብደረድር እንደማለት ነው። ይህ እንዲህ በሚለው በሮሜ 1፥25 ቃል ፈጽሞ የተወገዘ ነው፤ *ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።*

ማክበር ወይም ማምለክ የቃል ጉዳይ አይደለም። መስተዋል ያለበት ተግባሩና ድርጊቱ ነው። ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለሌላ ለማንም መደረግ የሌለበትን ነገር ለሌላ ማድረግ፤ ለምሳሌ፥ ጸሎትንና ልመናን፥ ውዳሴና ስግደትን ማቅረብ ማምለክ እንጂ ሌላ አይደለም። በአፌ አላመልካትም ብል እና ውዳሴና ልመናን፥ ስዕለትንና ስግደትን ባቀርብላት ራሴን እያሞኘሁ ነኝ። ወይም በእርሷ መጋረጃ ውስጥ እየተደበቅሁና ከእውነት እየሸሸሁ ነኝ። ራእ. 4፥10-11፤ 15፥3-4፤ ነህ. 9፥6 ሁሉ ሊሰግዱለት፥

ሊያከብሩት፥ ሊያመልኩት፥ ሊወድሱት፥ ሊያመሰግኑት የተገባ ብቻውን የሆነ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ከሚነግሩን ጥቅሶች ጥቂቱ ናቸው።

4. የተፈናቀለ ታሪክ። በተአምረ ማርያም ውስጥ ታሪክ የሚያውቃቸው፥ በታሪክ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰና ዘጋቢዎች ያወሷቸው፥ ራሳቸውም ታሪካቸውን የጻፉ በንጽጽር እውነቱን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ሦስት ሰዎች ተጠቅሰዋል። መጽሐፉ እነዚህን የመሰሉ ታሪካዊ ገጸ ባህርያትን የከተተው እና አንድ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ዓመተ ምሕረቶችን ያስገባው ታሪካዊ ስርና መሠረት ያለው ለመምሰል ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ይህ መጽሐፍ እነዚህን ሰዎች ሊጠቅሳቸው ከደፈረ፥ እኔም ከታሪክ አንጻር ልጥቀሳቸው። እነዚህ ሰዎች ንጉሥ ማርቆስ፥ ዮሐንስ አፈወርቅ፥ እና ዮስጢን ሰማዕት ናቸው። ኋላ ላይ ጥጦስም ወንበዴ ሆኖ ተጠቅሶአል። ግን ይህ ጥጦስ ኋላ ኢየሩሳሌምን ያወደመው ይሁን ወይም ሌላ ቀጣይ ታሪኩ በዚህኛው ተአምረ ማርያም ውስጥ አልተነገረም። ሦስቱን ግን እንመልከት።

ሀ. ዮሐንስ አፈወርቅ። ታሪኩን ከእንግሊዝኛ መዛግብት የምታውቁ በተጨማሪ ከሌላ ምንጮች ለመመርመር ለምትሹ ይህ ሰው እንግሊዝኛው አጠራር John Chrysostom የሚባለው ነው። የዮሐንስ አፈወርቅ ተአምረ ማርያምኛ ታሪክ በምዕ. 48 ተጽፎአል። ታሪኩ በአጭሩ ምዕመናንን ሥጋ ወደሙን ሲቀበሉ አንዲት ሴት በመርገመ ደሟ ሳለች መጣች። ሕዝቡም የመንፈስ ቅዱስ ረድዔት እንደራቃት አውቀው ወደ ንስጥሮስ ፊት አመጧት። እርሱም ጠይቆ ከተረዳ በኋላ ራቁቷን ተዘቅዝቃ እንድትሰቀልና ሕዝቡም በኀፍረተ ሥጋዋ ጢቅ እንዲሉ አዘዘ። እንደ ተአምረ ማርያም ጸሐፊ ንስጥሮስ ይህን ያደረገው እግዚአብሔር እንዲህ ከመሰለ ቦታ የሚወለድ እንደሆነ የሚያምን የተረገመ ነው አሰኝቶ ነው። ዮሐንስ የሚባል ቄስ፥ "እኔ እግዚአብሔር በሴት ሥጋ እንደተወለደ አምናለሁ" ብሎ ኃፍረተ ሥጋዋን ባፉ ሳመ። በዚህ ጊዜ የማርያም ስዕል በቤተ መቅደስ ውስጥ ነበረችና፥ "አፈወርቅ" ብላ ጠራችው። ቄሱም ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው እንዲህ ነው።

ይህ ምዕራፍ የንስጥሮስን ክፋት ለመግለጥና ማርያምን ያለ ስፍራ ለማግነን ተብሎ ረጅም ርቀት የተኬደበት ትረካ ነው። መርገም ሴትን አርክሶ ሥጋ ወደሙን ከከለከለ ኀፍረተ ሥጋን ማየትና በላዩ መትፋት ዮሐንስን ከማስመስገን ይልቅ የአድራጊዎችን ሁሉ ኀሊናን አያረክስም? ንስጥሮስ ኋላ በ431 በተደረገው በኤፌሶኑ ጉባኤ እርሱም ትምህርቱም የተወገዙበትን ክርስቶስ ሁለት አካል የሚል ትምህርትን ያስተማረ ሰው ነው። ለዚህ ምላሽ ሆኖ ኋላም በክርክር የቆየ የሁለት ባህርይ (dyophysitism) እና አንድ ባህርይ (monophysitism) ጉዳይ ቀጥሎአል። ሁለት ባህርይ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባህርይ ሲል አንድ ባህርይ ወይም ተዋህዶ የኢየሱስ ስብእና

በመለኮትነቱ ውስጥ ሟሙቶ የተዋሃደ ወይም ተዋህዶ ነው የሚሰኘው ንድፈ አሳብ ነው። የንስጥሮስ ትምህርት ግን ኢየሱስን ሁለት ባህርይ ሳይሆን ሁለት አካል የሚያደርግ ነው።

ንስጥሮስ የማርያምን ወላዲተ አምላክነት (θεοτόκος ቴኦቶኮስ መሆን) የሚቃወም ሰው ነው። ማርያም ቢበዛ ሥጋ የለበሰው ክርስቶስ እናት (ክሪስቶቶኮስ) እንጂ የአምላክ ወይም የእግዚአብሔር እናት መባል የለባትም ያለ ሰው ነው። θεοτόκος ባለፈው መጣጥፍ በመጠኑ የጠቀስኩት ወላዲተ አምላክ ተሰኝቶ በስሱ የተተረጎመ ቃል ይሁን እንጂ ትርጉሙ ከዚህ የጠለቀ ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙ "የአምላክ ተሸካሚ፥ የአምላክ አምጪ፥ አምላክን ያመጣች፥ ወይም እንዲመጣ ያደረገች" (bringer forth of God) ማለት ነው። Theotokosን ያጸደቀው በ431 የተደረገው የኤፌሶኑ ጉባኤ ነው። የጉባኤው ዋና ጉዳይም የማርያም ማንነት ሳይሆን የክርስቶስ ማንነት ነው። ከዚያ በኋላ ነው የማርያም ስዕሎች ስፍራ ሊያገኙ የበቁት። ቀድሞ ስዕሎች የነበሩ ቢሆኑም ከስነ ጥበብ አንጻር የሚታዩ እንጂ ከአምልኮ ጋር የተቆራኙ አልነበሩም። ኋላ ንስጥሮስ በስደት በአንጾኪያ፥ በዐረቢያ እና በግብጽ ኖሮ በ451 ሞቶአል።[27] የንስጥሮስ ትምህርት ዋና ስሕተት በክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ከሁለቱ አካላት አንዱ ሰው የሆነው አካል ብቻ ከሆነ የሞተው ለኃጢአት የተከፈለውን ዋጋ መለኮታዊ ልቀት የሚያሳጣው መሆኑ ነው።

ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ ስንመለስ፥ ይህ ሰው በታሪክ በጣሙን የታወቀ ሰው ነው። ከሰበካቸው ስብከቶች 600 ያህል በጽሑፍ እና ወደ 200 ደብዳቤዎቹ እስከዛሬ ተጠብቀው ይገኛሉ። እንዲህ እንደ ተአምረ ማርያሙ የመሰለ ታሪክ ግን ከቶም የለም። ዮሐንስ ነበልባል የሆነ ሰባኪ ነው። አፈወርቅ የሚል ቅጽል እንዲሰጠው ያደረጉትም እነዚህ ስብከቶቹ ናቸው እንጂ መርገም ያለባትን ሴት ኀፍረተ ሥጋ መሳሙ አይደለም። ዮሐንስ ከንስጥሮስ ጋር በአንድ ዘመን የነበረ ሰው ነው። ዘመናቸው በአጭር ይገናኝ እንጂ የሚተዋወቁና በአንድ ላይ ያመለኩ ሰዎች ግን አልነበሩም። ዮሐንስ ከ347-407 ዓ. ም. [28]ንስጥሮስ ደግሞ ከ386-451 ዓ. ም. የኖሩ ናቸውና ዘመናቸው በ21 ዓመታት ብቻ ይገናኛል። ንስጥሮስ ሲወለድ ዮሐንስ 39 ዓመቱ ሲሆን ዮሐንስ ሲሞት ደግሞ ንስጥሮስ ገና 21 ዓመቱ ነው። ሁለቱም በቁስጥንጥንያ ሊቃነ ጳጳሳት የነበሩ ሲሆኑ ዮሐንስ ጵጵስና የተሾመው በ397 በአምሳ ዓመቱ ነው። ንስጥሮስ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የሆነው ደግሞ በ428 (ከ428-431)

---

[27] ለታሪካዊ ሰዎቹ Schaff, vol. 3, ch. 1-3. History of the Christian Church, እና Schaff, Nicene and Post Nicene Christianity, [electronic version] እንዲሁም ታሪካዊ ክርስትና ላይ ከሚያተኩሩ ድረ ገጾች ያገኘኋቸው ተጨምረውበታል፡

[28] በዚህ መጣጥፍ ዓመተ ምሕረቶቹ በግዕዝ ቁጥሮች ካልተጻፉ በኀርጎራውያን አቆጣጠር ነው።

ነው። ዮሐንስ ከሞተ ከ21 ዓመታት በኋላ ማለት ነው። ዮሐንስ በሚሞትበት ጊዜ ንስጥሮስ ገና 21 ዓመቱ ነበርና በተአምረ ማርያም እንደተጻፈው ጳጳስም በአንብሮተ እድ የሚሾም ሰውም ፈጽሞ አልነበረም።

ኋላ የተጻፉ ምንጭ የሌላቸው ታሪኮች ቢኖሩም ዮሐንስ በቀረቤታ ሲታይ በተአምረ ማርያም የጻፈውን ማድረጉ በታሪኮቹ ሁሉ የማይገኝ ብቻ ሳይሆን እንዲያውም በተቃራኒው ዮሐንስ ሴትን የመናቅና ያለማድነቅ አዝማሚያ የሚታይበት ሰው ነው። የሴትን አብዝቶ ማሸብረቅ ይጠላ ነበርና በጵጵስናው ዘመን ከንጉሡ ሚስት ከአውዶክሲያ ጋር ዓይንና ቁልቋል ሆነው ኖረዋል። ይህችን ሴት ከሄሮድያዳ ጋር እያነጻጸረ ስለተናገረባት ሌሎችን አስተባብራ ለስደት የዳረገችውም እርሷ ናት። "ከዱር አራዊት ሁሉ እንኳ ሴትን የሚያህል ጎጂ ፍጡር አይገኝም" ብሎ ስለ ሴት ጾታ ያተተ አንድ መጽሐፍ ዮሐንስን ተጠቃሽ አድርጎታል።[29] እንዲህ ለእንስት ጾታ ወደ ጥላቻ የተጠጋ ንቀት እንዳለው የሚባልለት ሰው ነው እንግዲህ በተአምረ ማርያም መርገመ ደም ያለባትን ሴት ጎፍረተ ሥጋ የሳመውና ስዕሊቱ አፈወርቅ ብላ የሰየመችው። በተአምረ ማርያም ውስጥ የማርያም ስዕል እስኪሰለች ድረስ ነው ድምጽ እያሰማች የምትናገረው፤ እና፥ ይህ ሲጨመርበት ታሪክ ወደ ተረትነት በቀላሉ ይሻገራል። እነዚህ እርስ በርሳቸው ከተጋጩ እንደ ባለ አእምሮ በመዛግብት የተጻፈውን ተጨባጭ ታሪክ እንቀበል ወይስ በተአምረ ማርያም የተጻፈውን ከታሪክ ጋር የሚጣላ ፈጠራ?

<u>ለ. ንጉሥ ማርቆስ።</u> የንጉሥ ማርቆስ ታሪክ በተአምረ ማርያም በምዕ. 100 የተጻፈው እንደሚተርከው ድንግል ሳለ በሮም መንገሡ ተጽፎአል። 10 ዓመታት ከነገሠ በኋላ ሠራዊቱ ሚስት ማግባት ሞገስ የሚያስገኝ ቁም ነገር ስለሆነ ሚስት እንዲያገባ ማለዱት። እርሱም ማርያምን ልማከር ብሎ በስዕሏ ፊት 7 ቀን ቆሞ ጸለየ። በጸሎቱ መጨረሻ የስዕሊቱ ፊት ቦግ ብላ በራችና በድምጽ እንዳያገባና በድንግልና እንዲኖር፥ እንዲያውም መንግሥቱን ትቶ ደብረ ቶርማቅ ገዳም ሄዶ እንዲኖር ነግራው እዚያ ለመኖር ማንም ሳያየው ጠፍቶ ሄደ። በተአምረ ማርያም ድንግልና እጅጉን የተወደደ ከመሆኑ የተነሣ የተአምረ ማርያሚ ማርያምና የማርያም ስዕል ሰው ሁሉ ሳያገባ እንዲኖር ይፈልጋሉ። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ አሳብ ጋር በትጋት የሚጣላ ነው።

ማርቆስን በተመለከተ በሮም ግዛት ውስጥ በታሪክ የታወቀ በዚህ ስም የተጠራ ንጉሥ ማርቆስ አውራልዮስ (Marcus Aurelius) ነው። ማርቆስ ይህ ሰው ሳይሆን ሌላ ነው ከተባለ ታሪካዊ ማስረጃ ያስፈልገዋል። በተአምረ ማርያም ውስጥ ስም ሳይጠቀስም

[29] http://en.wikipedia.org/wiki/John_Chrysostom

‘በአንድ አገር የነገሠ ንጉሥ’ ይባልና የንጉሡ ስም ሳይነገር መተረክ የተለመደና ቀላል ነገር ነው። ስለ ማርቆስ በታሪክ መዛግብት የተጻፈ ታሪኩ የሚናገረው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ማርቆስ ከ161-180 ለሃያ ዓመታት የነገሠ ንጉሥ ነው። ከ20ው ውስጥ 9ኙን አብሮት የነገሠ ሉቂዮስ ቬሮስ የተባለ ሰው አለ። ንጉሥ ማርቆስ ከታሪኩ እንደምናነብበው ሳያገባ የኖረ እና መንግሥት ትቶ ገዳም የገባ መነኩሴ ሳይሆን 14 ልጆች ከወለደችለት ፋውስቲና ከተባለች ሚስቱ ጋር ለ30 ያህል ዓመታት ተጋብቶ የኖረ ሰው ነው። የቱ ነው ትክክል? በማረጋገጫ የሚፈትሹት እና ማስረጃ የሚያቀርቡለት ታሪክ? ወይስ ከታሪክ ጋር የሚጋጭና ምንጩ የማይታወቅ ተረት?

<u>ሐ. ዮስጢን ሰማዕት።</u> በተአምረ ማርያም ውስጥ የተጻፈው በምዕ. 99 ሲሆን ከዮስጢን ይልቅ ስለሚስቱ ታውክልያ በተጻፈው ውስጥ የተካተተ ነው። የተአምረ ማርያሙ ታሪክ ታውክልያ የዲቅልጥያኖስን ክህደት ለማወቅ በጸሎት ላይ ሳለች ማርያም ከእናቷና ከኤልሳቤጥ ጋር ትገለጥላታለች። (ኤልሳቤጥም ፈልሳለች ማለት ነው? ተአምረ ማርያም በነዚህ ጉዳዮች ላይ ደንታ ቢስ ነው።) ማርያምም የዲዮቅልጥያኖስ ክህደት በልጇ (በኢየሱስ) ዘንድ የታወቀ መሆኑን፥ ኢየሱስ ለዮስጢን በሰማይ ስለሚደረገው ሠርግ (ተዋህዶ) ሊነግረው እንደሄደና እርሷ ደግሞ ወደ እርሷ እንደመጣች፥ ሁለቱም ከልጃቸው ጋር እንደሚሠዉ ነግራት አበረታትታት ተሰወረች።

እዚህ ያለው ትልቅ ታሪካዊ ግጭት ዮስጢን ከ100-165 የኖረ መሆኑ የታወቀ ሆኖ ታውክልያ የምትጸልየው ስለ ዲዮቅልጥያኖስ ክህደት መሆኑ ነው። ሌላ ዮስጢን ካልሆነ በቀር ይህ በታሪክ የታወቀው ዮስጢን ሰማዕት (Justin Martyr) ነው። ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን በእጅጉ ያሳደደ የሮም ንጉሥ ቢሆንም የኖረበት ዘመን ከ244-311 ሆኖ የነገሠው ደግሞ ከ284-305 ድረስ ነው። ታውክልያ ከ120 ዓመታት በኋላ ስለሚመጣው ከሐዲ እያሰበች ነበር ካልተባለ በቀር በዚያን ዘመን ዲዮቅልጥያኖስ፥ ክህደቱና አሳዳጅነቱም አልነበሩም። ዲዮቅልጥያኖስ የተወለደው ዮስጢን ከሞተ ከ80 ዓመታት በኋላ ነውና ዮስጢን የተሰዋው በዲዮቅልጥያኖስ ሳይሆን ከላይ በተጠቀሰው ማርያም ከንጉሥነት ወደ ገዳም አስኮበለለችው በተባለው በማርቆስ አውራልዮስ ዘመነ መንግሥት ነው።

<u>5. የተምታታ ሲዖልና መንግሥተ ሰማያት።</u>

በተአምረ ማርያም ውስጥ የሚታዩት ከሞት በኋላ የሚሆኑት ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነገሩት የተለዩ ናቸው። የተአምረ ማርያሟ ማርያም ሰዎችንና ነፍሳትን ከሲዖል

ታወጣና ወደ መንግሥተ ሰማያት ታስገባቸዋለች። ሥጋዋ ወይም በድኗ በገነት በሕይወት ዛፍ ስር ተደርጎ ነበር። ያደረጉት ደግሞ ሬሳውን ተሸክመው የነበሩት ሰዎች ናቸው። ስለዚህ በአካል ወደ ገነትና ወደ ሕይወት ዛፍ ይደረሳል ማለት ነው። ሰዎች ሲሞቱ ማርያም አንዳንዴ ከመላእክት ጋር፥ አንዳንዴ ደግሞ ከደናግል ጋር እየታጀበች ትመጣና ትወስዳቸዋለች፤ ለሌሎችም ትታያለች። የምትወስደው ምናቸውን መሆኑ፥ ነፍሳቸውን ይሁን በድናቸውን አፍልሳ አይጻፍም፤ ብቻ በአጀብ ትወስዳቸዋለች።

በአጀብ መውሰድ ብቻ አይደለም፤ ሰዎች ከሞቱ በኋላም የተአምረ ማርያሟ ማርያም መልሳ አምጥታ ታሳያለች። በምዕ. 18-19 እነ ጊዮርጊስ፥ ቴዎድሮስ፥ መርቆሬዎስ፥ እና የተመልካቾች ዘመዶቻቸው ሁሉ፥ በሕዝቡ ጥያቄ ደግሞ አዳምና ሔዋን፥ አብርሃም፥ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ እነ ሙሴና ዳዊት፥ ነቢያትና ሐዋርያት፥ ወዘተ፥ እየተሰለፉ መጥተው ከመጋዘን እያመጡ ለሽማች እንደሚያሳዩት ዕቃ ይታያሉ። ከዚያ በኋላ ምን እንደሚሆኑ አልተጻፈም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ከሞት የተነሡባቸው ጊዜያት አሉ። ግን በሰልፍ መጥተው በወረፋ ታይተው ሊሰወሩ ሳይሆን ታይተው ኖረው ሞተዋል። የዓይንዶሯ መናፍስት ጠሪ ለሳኦል ሳሙኤልን አስነሥታለች። በአስማት የምትሠራ ሙታን ሳቢ ናትና እንዳስነሣች መሰለ እንጂ ሳሙኤልን በእርግጥ አላስነሣችም፤ ልታስነሣም አትችልም። ሳሙኤል ተነሥቶ ኖሮ ቢሆን ሳኦልም ያየው ነበር እንጂ ምን እንዳየች አይጠይቃትም ነበር። ይህ በነዚህ ምዕራፎች የሚታየው የመናፍስት ጠሪዎች አሠራር ሆኖ ልዩነቱ የተአምረ ማርያሟ ማርያም እያስነሣች አሰልፋ የምታመጣቸው ለጥቂት ጊዜ መታየታቸው ነው።

በምዕ. 28 ጌታ ለሐዋርያት በገነት ተገለጠላቸው ይላል። በአካል ገነት ገብተው ማለት ነው። በምዕ. 54 የአንድ ደብር አለቃን ወደ ሰማይ አሳረገችው። ሳይሞቱ የሚነጠቁበትም ታሪክ ነው የሚነበበው። በምዕ. 77 ደግሞ የለማኙን ፊት በዳቦ የገመሰው ሰው ሞቶ ሲዖል ሄደ። ማርያም፥ “የለም፤ ይህ የኔ ነው” ብላ ወደ ሲዖል እንዳይወርድ ተከራከረች። ዳቦውን የተቀበለው ፊቱ የተገመሰ ለማኝ ሄዶ መሰከረና ሰውየው ሲዖል መግባት ቀርቶለት ነፍሱ ተመለሰችና ከሞት ዳነ። ጌታ እየተሳሳተ ወይም እየተጸጸተ አሳቡን የሚቀይር ወይም የሰው ምስክርና ምክር የሚያስፈልገው የሰው ዳኛ መምሰሉም መታለፍ የሌለበት ስሕተት ሆኖ ሳለ፥ ለማኙ በምን ወደ ዙፋን ቀርቦ መሰከረ? በአካል ወይስ ያለ አካል?

<u>6. የተጣረሰ ደኅንነትና የተቃወሰ ክርስትና።</u>

በተአምረ ማርያም ውስጥ ተዝካር ያድናል፤ ማርያምን ማመን ያድናል፤ ተዝካሯን መደገስም ያድናል። በምዕ. 67 እረኞች ያጠመቁት አይሁድ ውኃ በቋጫ ስለረጩበት

ብቻ ክርስቲያን ሆነ፤ በምዕ. 94 በንጹህ እጅ መቁረብ መንግሥተ ሰማያት ያስገባል። 78 ሰዎች ቆርጥሞ በልቶ በማርያም ስም ጥርኝ ውኃ ከተሰጠ ያ ሚዛኑን ደፍቶ ከገሃነም ፍርድ ነጻ ያወጣል። ምጽዋት መስጠት መንግሥተ ሰማያት ያስገባል፤ ምዕ. 44፤ ወዘተ። ክርስትና በተአምረ ማርያም መመነን፥ መመንኮስ፥ ያለማግባት ወይም ጋብቻን መጠየፍ፥ ከተጋቡም በኋላ አብሮ ከመተኛት መራቅና ያለመገናኘት፥ ወደ ስዕል መጸለይና መስገድ፥ ወዘተ፥ ናቸው የመዳኛ መንገዶች።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ደህንነትና የክርስትና ኑሮ በቃልና በሥራ ክርስቶስን እየመሰሉ፥ እየተከተሉ የመኖር፥ መስቀሉን የመሸከም የደቀ መዝሙርነት ኑሮ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ መዳን በሌላ በማንም እንደሌለ፥ እንድንበት ዘንድ የተሰጠ የኢየሱስ ስም ብቻ መሆኑ፥ ክርስቶስን የተቀበሉ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸው፥ ለመዳን ማመን ብቻ እንጂ ልፋት እንደማያስፈልግ፥ ያመነ የተጠመቀ እንደሚድን፥ መዳን ደግሞ የሚታወቅና የሚረጋገጥ እንደሆነ በግልጽ ቋንቋ ተጽፎአል። በተአምረ ማርያም ግን ይህ አዳኝ እና የማዳኑ ደስታ ሲሸፈንና እንዳይታይ ሲደበቅ ይስተዋላል።

በምዕ. 41፥13 "በእግዚአብሔር አምነው፥ በወለደችውም በእመቤታችን አምነው ከቤተ ክርስቲያን ወጡ" ይላል። ቁ. 25 'እምነቱን በናቱና በእግዚአብሔር ላይ ያደረገ ሁሉ አያፍርምና' ይላል። 53፥55 ላይ፥ 'እግዚአብሔርን አመሰገኑ እመቤታችንንም አመሰገንዋት' ይላል። እምነት ክርስቶስ ሲደመር ሌላ ነገር ሆነ ማለት ነው! በምዕ. 56 ማርያም አንዱን መነኩሴ፥ "ከሚያልፈው ዓለም እስከወስድህ ድረስ ልጄ ካንተ አይለይም" አለችው። ወሳጁ እርሷ ስትሆን እስክትወስደው ከመነኩሴው የማይለየው ደግሞ ልጁ ነው። ልክ እንደ አገልጋይ ማለት ነው። በመጽሐፉ ማርያም ብቻ "ከልጁ ጎን በፈሰሰው ደሟ" አዳኝ ሆና ቀርባለች። ታዲያ ይህ የሰሚዎችን ጆሮ እያደነቆረ የጠፉቱ የምሥራቹን ወንጌሉን እንዴት ይስሙ? ይህ አሳችና አወናባጅ መጽሐፍ ነው።

## 7. የተላቀቀ መልከዓ ምድር።

በተአምረ ማርያም ውስጥ የተናጋ መልከዓ ምድርም ይታያል። ኢየሱስ በዋሻ ውስጥ ተወለደ ይላል፤ ለምሳሌ፥ ምዕ. 10። ግርግምና ዋሻ እንደምን አንድ ሆኑ? በምዕ. 106 በኢያሪኮ ባህር ዳርቻ ገዳም ያለባት ደሴት መኖሯን ይናገራል። ደሴት በባህር ውስጥ እንጂ በባህር ዳርቻ አይኖርም። ይሁን እዳሩጋ ጠጋ ብሎ ነው ይባል። ግን ኢያሪኮ እኮ ከተማ እንጂ ባህር አይደለችም። ኢያሪኮ የሚባል ባህር ኖሮም አያውቅም። በኢያሪኮ አቅራቢያ የዮርዳኖስ ወንዝ ነው ያለው፤ ያም ቢሆን ገዳም የተገደመበት ደሴት የለበትም።

ምዕ. 9 እና ምዕ. 118 ከእስራኤል ወደ ግብጽ ወይም ከግብጽ እስራኤል ሲሄዱ ባህር ሲሻገሩ ይታያሉ። በሁለቱ አገሮች መካከል የየብስ መንገድ ሳለ በባህር የሚያስዞር ምክንያት የለም። ምናልባት ከእስራኤል ባህረ ኤርትራን መሻገር ጋር ለማቆራኘት ይሆናል። ወይም ምናልባት ከክብረ ነገሥት ታሪክ ጋር ለማመሳሰል የተደረገ ሙከራ ነው። በጉዞውም ተጋንነው የተጻፉት ነገሮች ከክብረ ነገሥት ጋር መመሳሰል ስላላቸው ከዚያ የተኮረጀ ይመስላል።

በምዕ. 72 ከሄሮድስ ሸሽታ ወደ ዮሳፍጥ ሸለቆ ሄዳ መሸሸጓ ተጽፏል። ሊያያት የመጣው ገዢ ከሄሮድስ ሌላ ሲሆን ይህ ሰው ከሄሮድስ ጋር ሊዋጋ ዘምቶ በማርያም አማላጅነት ተመለሰ። እንደ ፀሐይ የሚያበራ ግርማ ኖሯት መሸሿ ወደ ጎን ይቅርና፥ ጫካውም ጫካ ሆኖ ገዳም መሆኑ ወይም መባሉም ይቅርና በዮሳፍጥ ሸለቆ መደበቋና ሁለቱ ኃያላን ሊዋጉ መሰላለፋቸው ሁለት አገሮች ብቻ ሳይሆኑ የሩቅ አገሮችም ያስመስላቸዋል። ግን የዮሳፍጥ ሸለቆ ከኢየሩሳሌም በ20 ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኝ ስፍራ ነው። በዚህ አጭር ርቀት በሄሮድስ ግዛት ውስጥ ሌላ ገዥ ያውም ከሄሮድስ ጋር ሊዋጋ የቃጣ አልኖረም።

## 8. የተዋረደ ጋብቻ።

መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻ ክቡር መኝታውም በሁሉ ቅዱስ መሆኑን ያስተምራል። ጋብቻ በማኅበራዊ ረገድ፥ ለቤተ ሰብ ጤናማነት፥ በቅድስና ለመኖር፥ ዘርን ለመጠበቅ በሙሉ መልኩ፥ የተከበረ ተቋም ነው። በተአምረ ማርያም ውስጥ የሚታየው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ጋብቻ የተናቀ ነው። ያላገቡ ሰዎች በተአምረ ማርያሟ ማርያም እንዳያገቡ ይመከራሉ። የተጋቡም ሳይቀሩ ትዳራቸው ፈርሶ እንዲመንኑ ይደፋፈራሉ። በምዕ. 65፥ 66፥ 68፥ 75፥ 86፥ 92፥ 100 እንዳያገቡ የተከለከሉ ሰዎች ታሪኮች ይነበባሉ።

በምዕ. 30 ካህን ዘራፊዎችን ግደሉ አባለ ዘራቸውንም ስለቧቸው ብሎ ሲያዝ ይታያል። ለነገሩ ከተገደሉ በኋላ የአባለ ዘር ብልት ዋጋ የለውም፤ ግን የተደረገው ሁሉ ተደርጎ ይህ ሁሉ በማርያም አማላጅነት ተደረገ ብሎ ይደመድማል። የተአምረ ማርያሟ ማርያም አባለ ዘርም እንዲሰለብ ታደርጋለች።

በምዕ. 85 ከገዛ ሚስቱ ጋር መተኛቱ እንደ ኃጢአት ሆኖበት አባለ ዘሩን የቆረጠ ሰው ይገኛል። ይህ ሰው ከደም ፍሰት የተነሣ ሞቶ መንግሥተ ሰማያት ሄዶ በማርያም ትእዛዝ ነፍሱ ወደ ሥጋዋ ተመለሰችና በሕይወት ኖረ። መንግሥተ ሰማያት ከገባ በኋላ ነፍሱን ብትመልስም ቅሉ ብልቱን ግን አልቀጠለችለትም። የሽንት መሽኛ ቀዳዳ ብቻ ተደርጎለት መንኩሶ ኖረ። በተአምረ ማርያም ትዳር የቀለለ ብቻ ሳይሆን የረከሰ ነገር

ነው። ከመነኮሰች በኋላ በፈቃደ ሥጋ ተሸንፋ ከገዳም የወጣችና ያገባች ሴት በመካንነት ተቀጥታ ወደ ገዳሟ ተመለሰች። ሌሎችም ይህም የመሰሉ ታሪኮች ታጭቀውበታል።

## 9. ያፈነገጠ ተፈጥሮ።

በተአምረ ማርያም ውስጥ የበዙ ከተፈጥሮ ሥርዓት ጋር የማይስማሙና የሚቃረኑ ነገሮች ይነበባሉ። በምዕ. 70 አንድ ሰው ሥጋ ወደሙን ከወሰደ በኋላ አውጥቶ በንብ ቀፎው ውስጥ አደረገው። በኋላ ሥጋ ወደሙ ወደ ብርሃንና የማርያም ስዕልነት ተለወጠ።

በእጅግ ብዙ ቦታዎች የማርያም ስዕል ከስዕል ተፈጥሮ ውጪ ድምጽ ሲወጣው፥ ሲደማ፥ ወዝ ሲወጣውና ሰዎች ያንን እየተቀቡ ሲፈወሱ ይታያል። እጅ ዘርግቶ ከተንቀሳቀሰ ወይም ስዕሉ ለሌላ ሰው ስዕል ከሰጠ፥ የቆሰለበት ስፍራ ጠባሳ ከኖረው፥ ሲወጉት ከደማ (ለምሳሌ፥ ምዕ. 31) ስዕሉ ሕይወት አለው ማለት ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሕይወት በደም ውስጥ መኖሩን ይመሰክራል። ከላይ እንደተጠቀሰው ስዕል በራሱ የተፈጠረ ካልሆነ ስዕል እየሠሩ፥ እየሸጡ የሚተዳደሩ ሰዎች አሉና ስዕሎቹ በሰው የተሠሩ ለመሆናቸው ጥርጥር የለበትም። የስዕል አምልኮ በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፥ ስዕሎቹ ተአምራት ካደረጉ፥ ሲወጉአቸው ከደሙ ሕይወት አላቸውና ሠሪዎቹ ምን ሊባሉ ነው? ፈጣሪ? አምላክ? ፍጡር ከፈጠሩ ሰዓሊዎቹም ፈጣሪ አምላክ ናቸው ሊባል ነው! በተአምረ ማርያም ስዕል ብቻ ሳይሆን ዳቦም ሲቆርሱት ደምቷል።

በተአምረ ማርያም ወደ ዓሳነት ሳይለወጡ በባህር ውስጥ ሆኖ መተንፈስም፥ መጸለይም፥ እንዲያውም መውለድም ይቻላል። በተአምር 97 አንድ መነኩሴ የውኃ ሙላት አማታውና ሰይጣን ወስዶ እባህር ከተተው። እዚያ ሳለ ማርያምን ጠርቶ ሲጸልይ ማርያም መጥታ ሰይጣንን ገሰጸችለት። እሱም ውዳሴውን ቀጠለ፤ የሚጸልይበትን ቦታ አሳየችውና በዚያ ሲጸልይ አደረ። ዋናተኞች ለፍለጋ ሲጠልቁ ውዳሴዋን ሲደግም አግኝተው አወጡት። እዚያ ለመቆየት ሲል፥ 'ባትመጡብኝ ይሻለኝ ነበር' አላቸው። በተአምር 88 ደግሞ አንዲት ነፍሰ ጡር ከመስጠም መዳኗ ብቻ ሳይሆን በባሕር ውስጥ ሳለች በቤት ውስጥ እንዳለች ሆና በማርያም ተሸፍና ወልዳለች። ያውም ያለምጥ ነው የወለደችው። ከተአምረ ማርያሟ ማርያም ሌላ ያለምጥ የወለደች ሴት ይህች ሴት ናት። ይህ የውኃ ውስጥ ኑሮ በ375 ዓመቷ

የሞተችው ክርስቶስ ሠምራ በጣና ባህር ውስጥ ሰውነቷ ተበጣጥሶ ዓሳዎች በውስጧ እየሾለኩ 12 ዓመት ጸልያ ወጣች እንደሚባለው የመሰለ ታሪክ ነው።[30]

በምዕ. 59 አንድ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ አንድ ቀን ከራት በኋላ የሥጋ ድቀት አግኝቶት ዝሙት ፈጸመ። በመልአክ ተነክቶ የሴት መርገም ደረሰበትና ከዚያ በኋላ ማርያም ያደረገችበትን ይህን ነገር አገር ላገር እየተናገረ በመዞር ኖረ። መልአክ ቢነካውም ይህን ያደረገችው ማርያም ናት። ይህች የዚህ መጽሐፍ ማርያም ምንም ነገር ማድረግ ትችላለች። ሰብዓዊ ተፈጥሮንም ትቀይራለች። የወር አበባ ካየ ማኅጸን ተሠራለት ማለት ነው። ማመንዘሩ ኃጢአት ሳለ ቅጣቱ ሴት መደረግ ወይም እንደ ሴት መደረግ ከሆነ ይህች ማርያም ሴትነቷንም ትጠላዋለች ማለት ይሆን? የተፈጥሮ ሕግን አፋልሳ ውንዱን ሴት ካደረገች በዚህ ዘመን ጾታቸውን ቀይረው ሌላ ሆነው ሌላ የሚያገቡት ሰዶማውያን ልክ ናቸውና መከልከል የለበትም ማለት ነው?

በምዕ. 107 ብዙ ኃጢአት ፈጽማ ተስፋ የቆረጠች ተቅበዝባዥ የሆነች ሴት ታሪክ ይገኛል። ይህች ሴት ወደ በረሃ ሂዳ ጊንጥ አገኘችና ዋጠችው። መርዙ በሰውነቷ ተሰራጭቶ ስትሰቃይ የማርያም ስዕል መጥቶላት በዚያ ሆዷን እያሸች ማርያምን ለመነች። ማርያም ወደ ቄስ ልካት ለዚያ ቄስ ተናዝዛ አምጣ ወለደች። የወለደችው ሕጻንን ሳይሆን 40 ትልልቅና ትንንሽ ጊንጦችን ነው። ወደ አፍ የገባ ወደ እዳሪ እንደሚወጣ ጌታ የተናገረው ስሕተት ተደርጎ ወደ ማሕጸን ገብቶ በ40 ተባዝቶ ወጣ! እንደዚህ ትምህርት ከሆነ ሴቶች ላም እንወልዳለን ብለው በመፍራት ወተት መጠጣት ማቆም አለባቸው። ወይም አስር ዶሮ እንወልዳለን ብለው እንቁላል መብላት መተው ይኖርባቸዋል። ደግሞ ሁሉም እንደየወገኑ እንዲዋለድ በፍጥረት መጀመሪያ የተነገረውም ተሰረዘና ሴት ሰውን ሳይሆን ጊንጥ ወለደች። ለተአምሩ ትክክልነት ሲባል መጽሐፍ ቅዱስ መስተካከል አለበት።

ጊንጥ ብቻ ሳይሆን ሌላም የከፋ የወሊድ ታሪክ አለ። በምዕ. 55 የሌላ ሴት ባል የቀማች አንዲት ሴትና ሌላኛዋ ሴት በማርያም ታቦት ፊት እውነተኞች መሆናቸውን ይማማላሉ። የቀማችው ሴት ኃጢአተኛ ኖራለችና እርጉዝም ነበረችና ቆይታ ወለደች። የወለደችው ሕጻን ሳይሆን በትል የተሞሉ ሁለት የላም፥ ሁለት የበግ ቀንዶችን ነው። ይህች ሴት እብድ ሆና እየዞረች ይህንኑም ያደረገችው ማርያም መሆኗን እየተናገረች ቆይታ ሞተች። ቀንዶቹ ደግሞ ከማኅጸን እንደወጡ እንኳ አልተቀበሩም። በማርያም ቤተ ክርስቲያን መስኮቶች ተሰክተው ይኖራሉ። የትኛዋ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ቢናገሩ ጉዱ ይታይ ነበር። አገሩ ብሔረ አግዓዚ ከመባሉ ሌላ አይታወቅም። በቀጣዩ ምዕራፍ (ምዕ. 56) የያሬድ ቅኔ ማኅሌት እውስጡ ስለተጠቀሰ ብሔረ አግዓዚ የኛው

[30] ገድለ ክርስቶስ ሠምራ (ዘጥቅምት እና ዘነሐሴ)።

አገር መሆኑን እንረዳለን። ቀድሞውኑም የሌለ ነገር ስለሆነና እንዲጠየቅና እንዲመረመርም ስለማይፈለግ ስፍራው አይገለጥም። ወይስ ዛሬም ቀንዶቹ ከአገራችን ቤተ ክርስቲያኖች ባንዷ መስኮቶች እንደተሰኩ ይሆኑ?

የተአምረ ማርያም ጸሐፊዎች የሻፉት መጽሐፍ ሰዎችን በማስፈራራትና በማስደንገጥ የማይመረምሩትና ከባለ ሥልጣኑ ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማያስተያዩት፥ የሃይማኖት ግዞተኛ አድርገው ለማኖር የፈጠሩት ፈጠራ ከተፈጥሮና ከስነ ፍጥረትም፥ ከአእምሮም ጋር የሚጋጭ መጽሐፍ ነው። እነዚህ ከስነ ፍጥረት ሕግ ጋር የሚጋጩ ያፈነገጡ ከብዙ ጥቂት ታሪኮች ናቸው።

ጥቂት ተጨማሪ ናሙና ግጭቶች

መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው መደመጥና መከበር እንዳለበት ሁሉ ዝም ባለበት ጉዳይ ሁሉ ዝምታውም መከበር አለበት እንጂ በራሳችን ምናብ የተፈተሉ ነገሮችን እየፈጠርን ያላለውን ማስባል የለብንም። የኢየሱስ የልጅነቱ ዘመናት ታሪኮች በወንጌላት ውስጥ አልተጻፉም። ያልተጻፉት አስፈላጊ ስላልሆኑ ነው። ቢሆኑ ኖሮ፥ *እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ* ያለውና ከወንጌላቱ ሁሉ በዝርዝር የዘገበው ሉቃስ ይህን አይጽፍም ኖሮአል?

ስሚስ? የማርያምን የስሟን ትርጉም በመቅድሙ ላይ 'መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታገባ' ማለት ነው ሲል ይተረጉማል። በሌሎችም ቦታዎች፥ ለምሳሌ፥ ምዕ. 12፥ 74፥ 98 ወዘተ፥ በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባለች እያለ ተመሳሳይ ስምና ትርጉም ያቀርባል። እንዴት ፈጥረው ቢተረጉሙት ነው ባለ አራት ፊደል ስም ይህ ሁሉ ቃል ያለበት ትርጉም (መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታገባ) የሚሰጠው? መምራት፥ ማስገባት፥ እና መንግሥተ ሰማያት የሚባሉት ቃላት ማርያም ወይም ሚርያም በሚባለው ስም ውስጥ ከቶም የሉም። በመጀመሪያ ማርያም በዕብራይስጥ ማሪሃም አትባልም፤ ሚርያም ናት። ማርያም በምንም ቋንቋ፥ ማሪሃም አልተባለችም። ደግሞም የስሟ ትርጉም የተለያዩ አገባብ ትርጉሞችም እንኳ ተጨምረው ዓመጽ፥ እንቢተኝነት፥ መራራ፥ መራራ ባሕር ማለት ነው እንጂ፥ መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታገባ ማለት አይደለም። ይህ አልዋጥ ካለንም በግድ እንዋጠው፤ ዕብራይስጥ ብለን ከጠቀስን ትርጉሙ ይኸው ነው።

በተአምር 21 ኢየሱስና ማርያም ለሐዋርያት ተገልጠው ጌታ ለሐዋርያት በእርሱና በእናቱ ስም በ4ቱ ማዕዘናት አብያተ ክርስቲያናት ይሠሩ ብሎ አዘዘ። በስሟ ቤተ ክርስቲያን ማነጽ ቀርቶ ሐዋርያት ስሟን ጠርተው ሰብከው ያውቃሉ? በምዕ. 7 ደግሞ

ዕርገቷን በ4ቱ ማዕዘን እንዲያውጁ አዘዛቸው ይላል። ሐዋርያት እንዲህ ተብለው ይህን አለመጻፋቸው ይደንቃል! የታዘዙትን ቤተ ክርስቲያን አለመሥራታቸውም ዕርገቷን አለማወጃቸውም ያስጠይቃቸዋል። አንዱን ቤተ ክርስቲያን ጴጥሮስ እዚያው ማነጹ ተጽፎአል። በአዲስ ኪዳንና በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመናት ውስጥ ክርስቲያኖች ምእመናንን ሲያንጹ እንጂ ሕንጻ ሲያንጹና ሲሠሩ አይታወቅም። ያመልኩ የነበረውም በምኩራቦችና በቤት ውስጥ እንጂ ሕንጻስ አላነጹም። ጊዜያቸው እኮ የስደት ዘመን ነበረ።

ማርያም ለመጨረሻ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀችውም ይኖሩበት በነበረው በተባለው ሰገነት ውስጥ ከጌታ ሐዋርያት፥ ከደቀ መዛሙርትና ከወንድሞቹ ጋር በጸሎት ስትተጋ ነው የታየችው እንጂ ሰዎች ወደ እርሷና ወደ ስዕሏ ሲጸልዩ አትታይም፤ ሐዋ. 1፥14። *በገቡም ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስም፥ ያዕቆብም፥ እንድርያስም፥ ፊልጶስም፥ ቶማስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፥ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም። እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።* ይላልና።

ይኼ ሁሉ የተደረተባት ድሪቶ ማርያምን እንደሚያሳዝናት የታወቀ ነው። በእውነቱ የተአምረ ማርያሟ ማርያም ደራሲዎቹ በመልካቸው እንደምሳሌያቸው የፈጠሯት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሷ ማርያም ከቶም አይደለችም። የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን (ዕብ. 12፥1-2) ከተባለለት ከኢየሱስ ሰዎች ዓይናቸውን እንዲያነሡ፥ እንዲያውም ከቶውኑ እንዳያዩት ተብሎ የተፈጠረችና 'ማርያም' ተብላ የተሰየመች ሴት ናት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሷ ማርያም ዛሬም ብትጠየቅ ያኔ እንዳለችው፥ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ የምትልና ወደ ኢየሱስ የምታመለክት ሴት ናት። እርሷን እንወድዳታለን፥ እናከብራታለን የሚሉ ሁሉ ሊያደርጉ የተገባቸው በሕይወተ ሥጋ በነበረች ጊዜ አድርጉ ያለችውን ማድረግ ነው። እርሱን ክርስቶስን መስማት፥ እርሱን መታዘዝ።

በተአምር 4 ላይ ማርያምን ለመገነዝ ሲሄዱ ታውፋንያ የተባለ አይሁድ አልጋዋን ስለያዘ እጁ በመልአክ ተቆርጦ አልጋው ላይ ቀረ። ይህ ሰው ሐዋርያትን ይቅርታ ጠየቀ፤ <u>ክርስቶስንም ይቅር እንዲለው ለመነ። ሐዋርያት ግን ወደ እመቤታችን ለምን አሉት።</u> ማርያም ቀድሞውኑ ከሞት ተነሥታ ነበርና ለመናት። ማርያምም ጴጥሮስን እንዲቀጥልለት ነገረችው። ጴጥሮስም <u>በክርስቶስ ስምና በማርያም ስም</u> እጁን መለሰለት። ይህ ጴጥሮስ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከሆነ መቸም ይደንቃል! ይህ ጴጥሮስ በሐዋ. 3፥6 *ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ* አለው ያለውና በኋላ በዚህ ስም ላይ ሌላ የለጠፈበት

ጴጥሮስ ነው? ይህ ጴጥሮስ በሐዋ. 4፥12 *መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና* ያለው ነው? እንዴት ያለ ቁልጭ ያለ ግጭት ነው? ይህ የተከሰተው ከሐዋ. 3 እና 4 በኋላ ነው ቢባል ጴጥሮስ ብዙ ቆይቶ በጻፈው በመልእክቱ ምነው የማርያምን ስም እንዲያው አንዴ እንኳ ያላስገባው? ይህ በኢየሱስና በማርያም ስም ብሎ እንደተናገረ የተጻፈለት ጴጥሮስ በመልእክቱ ውስጥ በ1ጴጥ. 4፥14 *ስለ ክርስቶስ ስም ብትነቀፉ የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን ናችሁ* ያለውና የክርስቶስን ስም ብቻ ያጎላውና የእርሱን ብቻ ማንነት አጉልቶ የገለጠው ነው? ነው ቢባል እንኳ የቱን እንቀበል? መጽሐፍ ቅዱስን ወይስ መጽሐፍ ቅዱስን የሚጻረረውን ተአምረ ማርያም የተባለ ሌላ መጽሐፍ?

በተአምር 3 ማርያምን ለመቅበር ሲሄዱ ሐዋርያት ሁሉ ጥለዋት ተበተኑ ከዮሐንስ በቀር ይላል። ልክ ጌታን ሲይዙት እርቃኑን በነጠላ ከሸፈነው ከአንዱ በቀር ሁሉ እንደሸሹ ይህንንም የጻፈው ይህ ደቀ መዝሙር መሆኑ እንደተጻፈ እዚህም የፍልሰቱን መጽሐፍ የጻፈ እርሱ መሆኑ ተጽፎአል። የዚህ ምዕራፍ ግጭት ከምዕ. 6 ጋር ነው። በተአምር 3 ጥለዋት ተበተኑ ሲል በተአምር 6 ፈጽሞ እንዳልጣሏት፥ ግን ገንዘው፥ ታቅፈው፥ ተሸክመው እጅ ነስተው በጌቴሴማኒ ቀበሯት እንጂ አልጣሏትም ይላል። የቱ ነው ትክክል? ምዕ. 3 ወይስ ምዕ. 6? ለነገሩ የተለያዩ ሰዎች ያዋጡት መጽሐፍ ስለሆነ እንዲህ እርስ በርሱ ቢጋጭ አያስገርምም።

በምዕ. 10 ኢየሱስ በዋሻ ውስጥ መወለዱና በጨርቅ መጠቅለሉ ሳይሆን የበለስ ቅጠል መልበሱ፥ በምዕ. 11 ደግሞ በጨርቅ መጠቅለሉ ተጽፎአል። በመንገድ መካከል ተወለደም ይላል። ይህ ሌላ የራስ ከራስ ግጭት ነው። መልአክ ሄዶ ለሰብዓ ሰገል እንደነገራቸው፥ ሰብዓ ሰገል ደግሞ ሽቱም አምጥተውለት እንደነበር ተጽፎአል። ሽቱው ተጨማሪ ስጦታ መሆኑ ይመስላል። እነዚህ ሁሉ የተጻፈ ታሪክን የሚያፋልሱ ናቸው።

ከንጉሥ ልጇ ደም በፈሰሰ ደሟ እኛን ንጹሐን አድርጋ . . . ይላል ምዕ. 12፥54። የማን ደም ነው የፈሰሰ? የማን ደም ነው ያዳነ? የማርያም ደም ያዳነ ኖሮ ቢሆንማ ክርስቶስ ምነው በመስቀል መዋሉ? ቃሉ በኤፌ. 2፥13 የሚለው አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ <u>በክርስቶስ ደም</u> ቀርባችኋል ነው፤ እንጂ ከልጇ በፈሰሰው በማርያም ደም ቀርባችኋል አይልም። ጳውሎስ ኤፌሶንን ሲጽፍ ማርያም ሞታ ወይም ተአምረ ማርያም እንደሚለው አርጋ ስለነበረ ጳውሎስ ይህንን የማርያም ደም ጉዳይ ማወቅ ነበረበት። እርሱ ግን በቆላ. 1፥19 <u>በመስቀሉ ደም</u> ሰላም ማድረጉን ይናገራል፤ ሌላ ደም አይናገርም። ዕብ. 9 በሙሉው ይህንን ደም

ይናገራል እንጂ የማርያም ደም አይልም። 1ጴጥ. 1 የተዋጀንበትን ክቡር ደም <u>የክርስቶስ ደም</u> ይለዋል እንጂ የማርያም አይለውም።

በምዕ. 7 በፍልሰቷ ቀን (ለነገሩ ቀኖቹ ሁሉ በኛ አቆጣጠር ነው የተጻፉትና በግብጽ ወይም በአይሁድ ቆጠራ ተጽፈው መመንዘራቸው አልተነገረም) በነሐሴ 16 ተዝካሯን ለዘከረ ኃጢአቱ እንደሚሰረይ ጌታ እንደሰጠ ይናገራል። በጣም ትልቅ ግጭት! ኃጢአት የሚደመሰሰው በነሐሴ 16 ተዝካር ማድረግ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር ፈጽሞ ይቃረናል። በክርስቶስ በማመን በጸጋ ድኖ በመስቀል ላይ በፈሰሰ ደሙ የኃጢአት ስርየት ማግኘት ወይስ ደግሶ አብልቶ መዳን? ወይስ ከሁለቱ ደስ ያለንን መርጠን መውሰድ?

በተአምር 32 ስለ አንዲት ዘማዊት ሴት ይናገራል። እንደ ሙሴ ሕግ እንድትወገር እንደተፈረደ ይናገርና.. ደግሞ ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብታ ይላል። በአዲስ ኪዳን ኃጢአተኛን በድንጋይ መውገር የለምና ይህ የብሉይ ኪዳን ዘመን ይመስላል። እንዳይባል ደግሞ ዘማዊቷ የማርያምን ስዕል አግኝታ ለመነች ይላል። መቸም በብሉይ ኪዳን የማርያም ምስል አለነበረም። አይሁድም ከምስል ጋር ፍቅር የላቸውም። መልእክቱ ወደ ስዕል ለምኖ መፍትሔ ማግኘት ቢሆንም በመቅደስ ውስጥ የማርያም ስዕል ሊኖር አይችልም። የቤተ ክርስቲያን መቅደስ ነው ከተባለ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስትና ዘመን ኃጢአተኛን መውገር ከየት የመጣ ፍርድ ነው? ሌላ እርስ በራሱ የተማታ ታሪክ ነው።

ሰይጣን መንፈስ ነው እንጂ ስጋዊ አካል አይደለም። በተአምረ ማርያም ምዕራፍ 34 ማርያም ሰይጣንን በጥፊ አጩላው ልቡናውን ሲስት ይታያል። በምዕራፍ 51 ደግሞ የመነኮሳትን ምድጃ ያፈረሰ አንድ ሰይጣን ታሪክ ተጽፎአል። መነኮሳቱ ወደ ማርያም ጮኹና ማርያምም ለ12 ዓመታት ባሪያ ሆኖ እንዲያገለግላቸው፥ ምድጃቸውን ያፈረሰውን ያንኑ ሰይጣን መልሳ ሸለመቻቸው። እነዚህ መነኮሳት ሰይጣንን ተቃወሙት የሚለውን ቃል አይታዘዙም ማለት ነው። ወይም ቃሉን ጨርሶውኑ አያውቁትም ማለት ነው። ሳያውቁ ግን መነኩሴዎች ናቸው። ማዕድ ቤት አስገብተው እየፈጨ፥ እያቦካ፥ እየጋገረ ዓሳ ነባሪ እያጠመደ፥ ዓሳ ነባሪውን ከመርከብ ጋር እየተሸከመ አምጥቶ መርከቡ ውስጥ የነበሩትን ሰዎች የሚያስመነኩስ ሰይጣን ነው ይህ ሰይጣን። ይህ 'አገልግሎት' ከፈጭታነትና ከጋጋሪነት የማዕድ ቤት ሥራም ያለፈ ነው!

በምዕራፍ 37 ማርያም ቴክላ ወደተባለች ሴት ሄዳ ስታስተዛዝናት፥ ልጇን 30 ዓመት በሆነው ጊዜ ከእርሷ ቀምተው በእንጨት ላይ ሰቅለው እንደ ገደሉት ነገረቻት። ጌታ ከማርያም ተቀምቶ ተገደለ? ወይስ ቀድሞም ሊሞት ነው የመጣው? ደግሞስ በ30 ዓመቱ ነው የተገደለው? በሉቃ. 3፥23 በሠላሳ ዓመቱ አገልግሎቱን መጀመሩ ነው

የጻፈው። በወንጌላት ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች ሁሉ ሳያደርግና ሳያገለግል ነው የተሰቀለው ማለት ነው? ሌላ ግጭት።

በምዕ. 98 ስለ ይሁዳ እግረ መንገድም ቢሆን የተነገረው፥ ጌታን ሸጦ፥ እናቱን አግብቶ፥ አባቱን መግደሉ ተጽፎአል። ቅደም ተከተሉ እንደዚያ ከሆነ እናቱን አግብቶ አባቱን የገደለው ጌታን ከሸጠ በኋላ ነው ማለት ነው። በትክክል የሞተው መቼ እንደሆነ ባይታወቅም ጌታን አሳልፎ በመስጠቱ ተጸጽቶ ወዲያው ሄዶ ነው ታንቆ የሞተውና (ማቴ. 27፥1-10) ኃብቻውም ግድያውም በሰዓቶች ውስጥ ምናልባት በደቂቃዎች መሆን አለበት። ያለዚያ እናቱን አግብቶ አባቱን የገደለውንና የአይሁድ ሕግ ዝም ያለውን ሰው ነው ጌታ ከሐዋርያቱ ቁጥር ውስጥ ያስገባው ማለት ነው።

በምዕ. 121 ኢየሱስን በ8 ዓመቱ በጎች እንዲጠብቅ ላከችው ይልና ወደ ደብረ ዘይት መጥቶ በጎቹን አሰማራ ይላል። ለማያውቅ ሰው ልክ እሰፈር ዳርቻ በጎቹን ወስዶ የመሰገ ይመስላል። የሚኖሩት ናዝሬት በጎች የሚጠብቀው ደግሞ ደብረ ዘይት መሆኑን እንደገና እናስተውል። ደብረ ዘይት ከናዝሬት የ105 ኪሎ ሜትር ሩቅ አገር ነው። በኛ አገር ከአዲስ አበባ አምቦ እንደ ማለት ነው። መልከዓ ምድሩን ምንም ለማያውቁና ለማይጠይቁ፥ ወይም የተባለውን ሁሉ እውነት ነው ብለው ለሚቀበሉ አድማጮች የተጻፈ በመሆኑ ደራሲዎቹ ይህን እና ይህን የመሰሉትን ግጭቶች ለመመርመር ሙከራ አላደረጉም።

በምዕ. 120 ኢየሱስን በ5 ዓመቱ የሚያስተምረው አስተማሪ፥ “ይህ የመበለት ልጅ” ይለዋል። ማርያም መበለት ሆነችሳ! ዮሴፍ ሞተ ይሆን? መቼም የኢየሱስ አስተማሪ ተአምረ ማርያም እንደሚለው ዮሴፍ “ጠባቂዋ” መሆኑን አያውቅም። በምዕ. 121 ደግሞ በ8 ዓመቱ አሳዳጊው ዮሴፍ ተጠቅሶአል። በወንጌሉ ውስጥ ደግሞ በ12 ዓመቱም በሕይወት መኖሩ ተዘግቦአል። በተአምረ ማርያም ዮሴፍ የማርያም እጮኛ እንኳ ሆኖ አልቀረበም። እንደ አገልጋይ ሆኖ ነው የቀረበው። ማርያምም አባታችን እያለች ትጠራዋለች። ዮሴፍ እጮኛዋ ሳይሆን አገልጋይዋና ጠባቂዋ ቢሆን ኖሮ በቃሉ ውስጥ እንደተጻፈው ቀደም ሲል እንዳየነው በስውር ሊተዋት ለምን አሰበ?

ተአምረ ማርያም ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ገድሎች ጋርም ይጋጫል፤ ይጣላል። አንድ ብቻ ምሳሌ ለመውሰድ፥ በገድለ ተክለ ሃይማኖት በመግቢያው ምዕራፍ ቁ. 40-46 እና 80-81 “. . . አባቴ የሚለው ግን ዝክሩን የሚዘክር ስሙን የሚጠራ ከሱ ጋራ የዘላለም ሕይወት ያገኛል ዝክሩን ያልዘከረ ቃሉን ያልጠበቀ ከርስቱ ከመንግሥተ ሰማያት የተለየ ይሆናል የሞቱ ሰዎችን ነፍስ ሁሉ ክርስቲያን የሚባሉ ጻድቅም ኃጥእም ቢሆን የሞቱትን ከክቡር አባታችን ከተክለ ሃይማኖት ዘንድ ሳያደርሱ አይወስዳቸውምና . . . ለሥጋችሁ መጠበቂያ ለነፍሳችሁ መዳኛ ነውና፤ ኃጢአታችሁን የሚያነጻ . . .” ይላል። እዚህ ተክለ ሃይማኖት የመንግሥተ ሰማያት መንገድ፥ የነፍስ

መዳኛና የኃጢአት ስርየት ሆኖ ተገልጦአል።[31] እዚያ ደግሞ ማርያም ወደ መንግሥተ ሰማይ መርታ የምታስገባ ተብላለች። ተክለ ሃይማኖትም በሩ ከሆነ የመዳን መንገዱ ብዙ ነው ማለት ነዋ! የማርያም ዝክር ነው መዳኛው ወይስ የተክለ ሃይማኖት? ወይስ ማንም በመረጠው?

## መደምደሚያ

ሲደመደም፥ ተአምረ ማርያም ለሥጋዊ አኗኗርና ለኃጢአተኛ ተፈጥሮ የሚስማማ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቅድስና አመላለስ፥ ክርስቶስን መምሰል፥ ዋጋ መክፈል፥ ለእውነት መሰደድ በውስጡ የሉበትም። ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ መቀበልና የሕይወት ጌታ አድርጎ እርሱን መከተል የሉበትም። በምንም ኃጢአት ውስጥ ተኑሮ ለስዕል አቤት ከተባለ፥ ዝክር ከተዘከረ፥ በማርያም ስም አንዳች ከተደረገ መንግሥተ ሰማያት የመግባት ተስፋ አለ። ስለዚህ እንደፈለጉ ኖሮ ማርያምን ጠርቶ መናገርና እርሷ ደግሞ ለልጇ ተናግራ የሚሹትን ሁሉ ማድረግ ስለምትችል መልካሙን ገድል መጋደል አይታወቅም።

ተአምረ ማርያምን ማሔስን ካላቆሙት በቀር መቆም አይችልም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ምዕራፍ ከራሱ ከመጽሐፉ ሌላ ምዕራፍ፥ ከታሪክና ከእውነት፥ ከአእምሮና ከተፈጥሮ፥ በተለይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በምሬት የሚጣላ መጽሐፍ ነው። በአጭር ቃል ተአምረ ማርያም ጠላት ከዘራቸው ብዙ እንክርዳዶች አንዱ ነው። ከዚህ እና ይህን ከመሰለ የክርስቶስን ማዳን ከሚሸፍንና ብርሃኑን ከሚያጨልም የሰውና የሰይጣን ሥራ እንራቅ።

ጌታ እውነትን ከሐሰት መለየት የሚችል ብሩህ አእምሮ በማደል ይባርካችሁ።

ዘላለም መንግሥቱ

[31] ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገጽ 10 እና 12።

## ዋቤ መጻሕፍት


መሠረት ስብሐት ለአብ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአስተዋጽዖ፥ አሳታሚ ፍኖተ ሕይወት ማኅበረ መነኮሳት፥ የኅትመት ዘመን አይታወቅም፥ አዲስ አበባ።

ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል፥ ቀ ዶ/ር ፥ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 2000 ዓ.ም.

ስሜ ታደሰ፥ ለእውነት እንቁም፥ SIM Publishing፥ አዲስ አበባ፥ ፪ሺህ ፬ ዓ. ም.።

ባዩ ታደሰ እርዳቸው (መምህር)፥ በአባቶቻችን አፈርን፥ [ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም] አዲስ አበባ፥ ፪ሺህ፫ ዓ. ም.።

ውዳሴ ማርያም፤ ዓምደ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት፤ ቪክቶሪያ መንበረ ብርሃን ዳግማዊ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ።

ደስታ ተክለ ወልድ፤ ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ ፲፱፻፷፪ ዓ. ም.

ገድለ ተክለ ሃይማኖት፥ [አሳታሚና ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም] አዲስ አበባ፥ ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. ።

ገድለ ክርስቶስ ሠምራ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ፥ ፲፱፻፺፪ ዓ. ም. ።

ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፥ ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. አሳታሚ፥ መምህር ወማኅበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ በ18 ሊቃውንት የተዘጋጀ። ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፤ 1988 ዓመተ ምሕረት (1996)።

ጽጌ ስጦታው (ዲያቆን)፥ ይነጋል፥ አፍሪካ ማተሚያ፥ አዲስ አበባ፥ ፲፱፻፺፯ ዓመተ ምሕረት።

Aren, Gustav; Evangelical Pioneers in Ethiopia, Origins of the Evangelical Church Mekane Yesus; Offsetcenter, ab, Stockholm, 1978.

Bagster, Samuel; The Bible of Every Land, History of the Sacred Scripturein Every Language and Dialect into which Translations have been made; London, 1848.

Proceedings of the Church Mission Society for Africa and the East, Twentieth Year (1819-1820), L. B. Seeley, Printer R. Watt, Crown Court, Temple Bar, London, 1820.

Schaff, Philip, History of the Christian Church, Nicene and Post Nicene Christianity, T & T Clark, Edinburgh, 1884.

Tamrat, Tadesse, Church and State in Ethiopia 1270-1527, Oxford University Press, London, 1972.

The Church of England Magazine, Vol. 45 July-December 1858. William Hughes Stationer's Hall Court, Rogerson and Tuxford Printers, London, 1958.

The Eightieth Report of the British and Foreign Bible Society, Spottiswood and Co., London, 1884.

The Thirty-Ninth Report of the British and Foreign Bible Society, Printed by Richard Clay, London, 1843.

Ullendorf, Edward Ethiopia in the Bible, Oxford, University Press Inc. New York, 1968.